# እውነተኛ ሁን

## 1ኛ ዮሐንስ መልእክት

ፍቅርና ትክክለኛ አኗኗር በማይታወቁበት ዘመን፥ ጭንብልህን
አውልቀህ ጣልና በእነዚሁ ነገሮች ላይ እውነተኛ አመለካከት ያዝ!

ጸሐፍ፡- በዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

ትርጉም፡- በግርማዊ

እርማት፡- በዓለማየሁ ማሞ

Copyright © 1996 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia. Orginally published in English under the title of BE REAL. Copyright © 1988 by SP Publications, Inc., Wheaton, Illinois USA. All rights reserved.

# ማውጫ

መግቢያ

1. እውነት ነው!..........1

1ኛ ዮሐንስ 1፡1-4

2. ቃላችንና አካሄዳችን..........16

1ኛ ዮሐንስ 1፡5-2፡6

3. አዲስና አሮጌ..........31

1ኛ ዮሐንስ 2፡7-11

4. እግዚአብሔር የሚጠላው ፍቅር ..........46

1ኛ ዮሐንስ 2፡12-17

5. እውነት ወይም ከእውነት የመራቅ ውጤቶች..........61

1ኛ ዮሐንስ 2፡18-19

6. ግብዞች ..........76

1ኛ ዮሐንስ 3፡1-10

7. ማፍቀር ወይስ መሞት..........91

1ኛ ዮሐንስ 3፡11-24

8. የጠለቀ ፍቅር ..........106

1ኛ ዮሐንስ 4፡7-16

9. ውደድ፥ አክብር፥ ታዘዝ ..........121

1ኛ ዮሐንስ 4፡17-5፡5

10. በእርግጠኛነት የምታውቀው ነገር ምንድን ነው? ..........137

1ኛ ዮሐንስ 5፡6-21

# መግቢያ

ዋረን ዌርዝቢ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያካተቱአቸው ቁም ነገሮች ሁሉ ወዳጆቻቸው የሚያስታውሱአቸውና የሚያደንቁላቸው ናቸው። ዌርዝቢ በቃላት አመራረጥ የታወቁ በመሆናቸው፥ በዚህ መጽሐፋቸው ቅር እንደማያሰኙህ እርግጠኛ ነኝ። በመሆኑም፥ የአገላለጽ አድማሱን ለማስፋት ለሚሻ ሰው ሁሉ የልብ እርካታ የሚሰጡትን መንገዶች ይጠቀማሉ።

ዌርዝቢ ምሳሌያዊ አነጋገሮችንና አንዳንድ ጊዜም ቀልዶችን መጠቀም ይወዳሉ። ይህም ራሱን ጨምሮ በሰው ላይ ፈገግ ለማለት የሚችል ሰው እንደማይከፋ የሚገልጸውን አባባል በማመናቸውም ሳይሆን አይቀርም።

ዌርዝቢን የሚያውቁአቸው ሰዎች አድማጮቻቸውንና አንባቢዎቻቸውን በቀጥታ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ከማገናኘም እንደማይመለሱ ይረዳሉ። ይህ የመጀመሪያና የመጨረሻ ነጥባቸው ሲሆን፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የተሰጡ መሆናቸውን እንገነዘባለን። ከቶውንም ይህንን እንድትረሳ አይፈልጉም።

የዌርዝቢ ጽሑፎች ሐዋርያው ጳውሎስ ለዝማሬና ለምስጋና እንዲውል ያሰበውን ቁም-ነገር ያጠናክራሉ፤ «በመንፈስ እጸልያለሁ በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በመንፈስ እዘምራለሁ በአእምሮም ደግሞ እዘምራለሁ» (1ኛ ቆሮ. 14፡15)።

በመሆኑም፥ የእኚህ ሰው ጽሑፎች ይባርኩሃል። ከገጽ ወደ ገጽ እየተሻገርህ ስታነብ በልብህና በሕሊናህ የእግዚአብሔርን መንፈስ ዳሰሳ ትለማመዳለህ፤ እንዲሁም ደግሞ ታሰላስላለህ! ይህ እሽግና ቀድሞውኑ የተብላላ ሃይማኖታዊ ምግብ አይደለም፤ ይልቁንም በግልጽ የተብራራና በታማኝነት ከሕይወት ጋር የተዛመደ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው። እናም አንብበው...ራስህን ወደ በረከት ምራ፤ በዚህም እውነተኛነትን አትርፍ!

ሮበርት ኤ. ኩክ

የቀድሞው የኪንግስ ኮሌጅ ፕሬዚዳንት፥

ኒውዮርክ።

## - 1 -

# እውነት ነው!

## 1ኛ ዮሐንስ 1፡1-4

«ከዕለታት አንድ ቀን…»

እነዚህ ቃላት ምን ያህል አስደሳች እንደነበሩ ታስታውሳለህ? እነርሱ የልጅነትን ችግሮች ሁሉ እንድትዘነጋ ወደ ረዳህ የህልም ዓለም የመሩህ ክፍት በሮች ነበሩ።

ከዚያም ሁኔታው ከመቅጽበት ተለውጦ፥ «ከዕለታት አንድ ቀን…» የሕፃናት ጨዋታ ሆነ። እናም ሕይወት የጦር ዐውድማ እንጂ የኳስ ሜዳ እንዳልሆነችና የተረት አባት ታሪኮች ከእንግዲህ ጣዕም እንደማይሰጡ ተረዳህ።

ለእውነተኛ ነገር የሚደረገው ፍለጋ አዲስ አይደለም። ከታሪክ ጅማሬ አንሥቶ እንደ ቀጠለ ነው። ሰዎች ከሀብት፥ ከምቾት፥ ከወረራ፥ ከሥልጣን፥ ከትምህርትና ከሃይማኖትም ሳይቀር እውነታንና እርካታን ሲሹ ቆይተዋል።

እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ከቶውንም ሊያረኩ አይችሉም እንጂ ክፋት የለባቸውም። አንድን እውነተኛ ነገር *መፈለግና* አንድን እውነተኛ ነገር *ማግኘት* ሁለት በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። በትርዒት ማሳያ ስፍራ ከረሜላ እንደሚያላምጥ ልጅ አንድን እውነተኛ ነገር የሚፈልጉ አያሌ ሰዎች ባዶአቸውን ይቀራሉ። ውድ ዘመናቸውን በከንቱ የእውነታ መተኪያዎች ላይ ያሳልፋሉ።

የሐዋርያው ዮሐንስ የመጀመሪያው መልእክት የሚገጥመው ከዚህ አሳብ ጋር ነው። ከብዙ ምእተ ዓመታት በፊት የተጻፈው ይኸው መጽሐፍ ለሁልጊዜም ከሚዛመደው ጭብጥ ላይ ተንተርሶአል፤ ይኸውም *«እውነተኛ የሆነ ሕይወት»* የሚል ነው።

ሐዋርያው ዮሐንስ እርኪው እውነታ የሚገኘው በነገሮች ወይም በምቾት ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አካላዊ ህልውና እንደሆነ ተረድቶ ነበር። ምንም ጊዜ ሳያባክን በመጽሐፉ የመጀመሪያ አንቀጽ ስለዚሁ «ሕያው እውነታ» ይነግረናል።

1ኛ ዮሐንስ 1፡1-4ን ስታነብብ ሦስት ከባድ አሳቦችን ስለ እውነተኛ ሕይወት ትማራለህ።

## 1. ይህ ሕይወት ተገልጦአል

የዮሐንስን መልእክት በምታነብበት ጊዜ፥ አንዳንድ ቃላትን ለመጠቀም እንደሚመርጥ ትረዳለህ፤ ከነዚህም ተወዳጅ ቃላቱ አንዱ «መገለጥ» የሚለው ነው «ሕይወትም ተገለጠ» (ቁጥር 2)። ፈልገን እናገኘው ዘንድ ይህ ሕይወት አልተሰወረም። ይልቁንም፥ በይፋ የተገለጠ ነው።

አንተ አምላክ ብትሆን ራስህን ለሰዎች የምትገልጸው እንዴት ነበር? ይደሰቱበት ዘንድ ስለምትፈልገው ሕይወት የምትነግራቸውና ይህንንም ሕይወት የምትሰጣቸው እንዴት ይሆን ነበር?

እግዚአብሔር ራሱን በፍጥረት ውስጥ ገልጦአል (ሮሜ. 1፡20)፤ ይሁንና፥ ፍጥረት ብቻውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ታሪክ አይነግረንም። እንዲሁም እግዚአብሔር ራሱን በቃሉ ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት ይበልጥ በሙላት ገልጦአል። ይህም ሆኖ፥ የእግዚአብሔር የመጨረሻውና የተሟላው መገለጥ የተሰጠው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ነው። ኢየሱስ፥ «እኔን ያየ አብን አይቶአል» ብሏል (ዮሐ. 14፡9)።

ኢየሱስ የእግዚአብሔር የራሱ መገለጥ ስለሆነ፥ «የሕይወት ቃል» የሚል በጣም የተለየ ስም አለው (1ኛ ዮሐ. 1፡1)።

የዮሐንስም ወንጌል የሚጀምረው በዚሁ ቃል ነው፤ «በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» (ዮሐ. 1፡1)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ስም የተቀበለው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ክርስቶስ ለእኛ ቃላችን ለሌሎች ሰዎች እንደሆነው ያህል ነው። ቃላችን ስለምናስበው ነገርና ስለሚሰማን ስሜት ለሌሎች ይገልጣል። ክርስቶስም የእግዚአብሔርን ልብና አሳብ ይገልጥልናል። እርሱ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሕያው የመገናኛ መንገድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው።

ዮሐንስ ኢየሱስን ሲገልጽ ምንም ትክክል ያልሆነ ማስረጃ አላቀረበም። ኢየሱስ የአብ ማለትም የእግዚአብሔር ልጅ ነው (1ኛ ዮሐ. 1፡3)። ዮሐንስ በመልእክቱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ውሸተኛ ወሬ የሚያቀብሉትን የሐሰት አስተማሪዎች እንዳንሰማ በአያሌው ያስጠነቅቀናል። «ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማንነው?» (2፡22)። «ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር

አይደለም» (4፡2፥3)። አንድ ሰው ስለ ኢየሱስ የተሳሳተ አሳብ ካለው፥ ስለ እግዚአብሔም የተሳሳተ አሳብ ይኖረዋል፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው የመጨረሻውና የተሟላው መገለጥ ነው።

ለምሳሌ ኢየሱስ ሰው እንጂ አምላክ አይደለም የሚሉን አሉ። ዮሐንስ ለእንዲህ ዓይነቶቹ መምህራን ስፍራ የለውም። በዚህ መልእክቱ ውስጥ ከሚያካትታቸው የመጨረሻ ነገሮች አንዱ፥ «እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ *እውነተኛ አምላክና* የዘላለም ሕይወት ነው» የሚል ነው (5፡20)።

የሐሰት ትምህርት አደገኛ እንደመሆኑ፥ ዮሐንስ በሁለተኛው መልእክቱም አማኞች ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ወደ ቤታቸው እንዳያስገቡ በማስጠንቀቅ ጽፎአል (2ኛ ዮሐ. ቁጥር 9-10)። የኢየሱስን አምላክነት መካድ ማለት የሐሳዊ-መሢሑን ውሸቶች መከተል እንደሆነም በግልጽ አብራርቶአል (1ኛ ዮሐ. 2፡22-23)።

ይህም ብዙዎችን ወዳደናገረው መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጥ ማለትም ወደ ሥላሴ ዶክትሪን ይመራናል።

ዮሐንስ በመልእክቱ አብን፥ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ይጠቅሳል። ለምሳሌ፥ «የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው» (4፡2) ይላል። እዚህ በአንድ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተገልጸዋል። በ4፡13-15 ላይም ሦስቱን የሥላሴ አካላት የሚጠቅስ ክፍል ይገኛል።

*ሥላሴ* በእንግሊዝኛ «ትሪኒቲ» የሚባል ሲሆን፥ ይህም «ትራይ» ሦስት እና «ዩኒቲ» አንድ ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገነባ ነው። በመሆኑም ሥላሴ የሦስቱ አንድነት ወይም የአንዱ ሦስትነት ነው ማለት ነው። ምንም እንኳ ይኸው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጾ ባይገኝም፥ እውነታው ግን እዚያው አለ (ማቴ. 28፡19፥ 20፤ ዮሐ. 14፡16፥ 17፥ 26፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡14፤ ኤፌ. 4፡4-6)።

ክርስቲያኖች *ሦስት አማልክት* እንዳሉ አያምኑም። ይልቁንም አንዱ አምላክ በሦስት አካላት ማለትም በአብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንደሚኖር ያምናሉ። እንዲሁም ደግሞ አንዱ አምላክ ራሱን በሦስት የተለያዩ መንገዶች ይገልጻል ብለን አናምንም፤ ይህም እንደ አባት፥ ባል እና ልጅ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን እግዚአብሔር *አንድ* እንደሆነና *በሦስት* አካላት እንደሚኖር ነው።

አንድ የዶክትሪን መምህር፥ «የሥላሴን ጽንሰ-አሳብ ለማብራራት ብትሞክር አእምሮህን ታጣ ይሆናል። ሥላሴን ለመካድ ብትሞክር ግን ነፍስህን ልታጣ ትችላለህ» ሲል ገልጾአል። ሐዋርያው ዮሐንስም፥ «ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም» ብሏል (1ኛ ዮሐ. 2፡23)። ከሥላሴ አካላት አስፈላጊ አይደለም ተብሎ የሚጣል የለም።

ስለ ኢየሱስ ሕይወት ወንጌላት የጻፉአቸውን ዘገባዎች ስታነብ፥ እግዚአብሔር እንድንደሰትበት የሚፈልገውን ግሩም ሕይወት ትመለከታለህ። ይህም ሆኖ፥ ምሳሌአችን የሆነውን ኢየሱስን *በመምሰል* አይደለም የዚህ ሕይወት ተካፋይ የምንሆነው። ዳሩ ግን ከዚህ የላቀ መንገድ አለ፡-

## 2. ይህ ሕይወት በተግባር የታየ ነው

የዮሐንስን መልእክት አራት የመጀመሪያ ቁጥሮች ደግመህ ብታነብ፥ ሐዋርያው *ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ግላዊ ግንኙነት* እንደነበረው ትገነዘባለህ። ይህ ከሌላ ሰው የተላለፈ ወይም ከመጽሐፍ የተገኘ ትውፊታዊ «ሃይማኖታዊ ልምምድ» አልነበረም! ዮሐንስ ኢየሱስ ክርስቶስን በደንብ በአካል *ያውቀው* ነበር። እርሱና ሌሎቹ ሐዋርያት ኢየሱስ ሲናገር ሰምተዋል። አብሮአቸው ሲኖር አይተውታል። በጥንቃቄ የመረመሩት ሲሆን፥ ሰውነቱንም ዳስሰው አይተዋል። ኢየሱስ ራእይ ወይም መንፈስ ሳይሆን፥ በሰብአዊ አካል የተገለጸ *እውነተኛ* አምላክ እንደሆነ *ያውቁ* ነበር።

አንድ የ20ኛው ክፍለ-ዘመን ተማሪ እንዲህ ይል ይሆናል፤ «ይህ ማለት እንግዲህ ዮሐንስ *ዕድለኛ* ነበር ማለት ነው። እርሱ የኖረው ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ነው። ኢየሱስን በግል *ያውቀው* ነበር። እኔ ግን ጊዜው ካለፈ 2000 *ዓመታት* በኋላ ተወለድሁ።»

*ተማሪው* የተሳሳተው እዚህ *ጋ* ነው። ሐዋርያት የሆኑትን እንዲሆኑ ያደርጋቸው ለኢየሱስ ክርስቶስ *በሥጋዊ ሁኔታዎች* መቅረባቸው አልነበረም። ይልቁንም *መንፈሳዊ* ቅርበታቸው ነበር። እንደ ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው እየተመለከቱት ራሳቸውን ለእርሱ ሰጥተው ነበር። ኢየሱስ ለዮሐንስና ለሥራ ጓደኞቹ እውነተኛና አስደሳች የነበረው እርሱን ስላመኑት ነው። በክርስቶስ በማመን *የዘላለምን ሕይወት አገኙ!*

ዮሐንስ በዚህ መልእክቱ ስድስት ጊዜ «ከእግዚአብሔር የተወለዱ» የሚለውን ሐረግ ይጠቀማል። ይህ ዮሐንስ የፈጠረው ሳይሆን ከኢየሱስ የሰማው *ቃል* ነው። ኢየሱስ፥ «ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን *መንግሥት* ሊያይ አይችልም...ከሥጋ የተወለደ

ሥጋ ነው ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁ አታድንቅ» ብሏል (ዮሐ. 3፡3፥ 6፥ 7)። ይህንኑ «እውነተኛ ሕይወት» ልናገኝ የምንችለው ወንጌሉን ከተቀበልን፥ በክርስቶስ ካመንንና በዚህም «ከእግዚአብሔር ከተወለድን» በኋላ ብቻ ነው።

«ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል» (1ኛ ዮሐ. 5፡1)። የዘላለም ሕይወት በሰናይ ምግባራችን የምናገኘው ወይም ከመልካም ባሕርያችን የተነሣ በይገባኛል መብት የምንቀበለው አይደለም። እውነተኛ የሆነው ሕይወት ማለትም የዘላለም ሕይወት ልጁን እንደ አዳኛቸው አድርገው ለሚቀበሉ ሰዎች የተዘጋጀ ነፃ ስጦታ ነው።

ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ሰዎች ይህንን ድንቅ ሕይወት እንዴት እንደሚቀበሉ ለመንገር ነው (ዮሐ. 20፡31)። የመጀመሪያ መልእክቱን የጻፈው ደግሞ እውን ከእግዚአብሔር መወለዳቸውን እንዴት እንደሚያረጋግጡ ለማስረዳት ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡9–13)።

አንድ የኮሌጅ ተማሪ ለቤተሰብ ልቅሶ ወደ ሠፈሩ ደርሶ ከተመለሰ በኋላ፥ በአንድ ጊዜ ውጤቱ ሁሉ ያሽቆለቁል ጀመር። አማካሪው የሴት አያቱ ሞት ልጁን እንደጎዳውና በጊዜ ርዝመት ችግሩ እንደሚቃለል ቢያስቡም፥ ውጤቱ ይበልጥ እየከፋ ሄደ። በመጨረሻም፥ ልጁ እውነተኛው ችግር ምን እንደሆነ ገለጠ። በቤት ሳለ የሴት አያቱን አሮጌ መጽሐፍ ቅዱስ አይቶ ነበርና በዚያ ውስጥ በሚገኘው የቤተሰብ ዘገባ ማደጎ ልጅ መሆኑን ተገነዘበ።

«የማን እንደሆንሁ አላውቅም። ከየት እንደመጣሁ አላውቅም!» ሲል ለአማካሪው ገለጸ።

በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የመሆናችን ዋስትና «ከእግዚአብሔር መወለዳችን» ለሁላችንም እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። የተወሰኑ ባሕርያት ለሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች የሚሠሩ ናቸው። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰው የጽድቅ ሕይወት ይኖራል (2፡29)። የእግዚአብሔር ልጅ ኃጢአትን አይለማመድም። አንድ አማኝ በአጋጣሚ ኃጢአት ሊሠራ ቢችልም (1፡8–2፡2)፥ ልማድ አድርጎ አይኖርበትም።

በተጨማሪም፥ የእግዚአብሔር ልጆች እርስ በርሳቸውና ከሰማያዊ አባታቸው ጋር ፍቅር ይኖራቸዋል (4፡7፤ 5፡1)። ዙሪያቸውን ለከበበው የዓለም ዘይቤ ልባቸውን በፍቅር አይሰጡም (2፡15–17)፤ ይህም በመሆኑ ዓለም ይጠላቸዋል (3፡13)። በዚህ ዓለም ውጥረቶች

ከመረታትና ሚዛን ከማጣት ይልቅ፥ የእግዚአብሔር ልጆች ዓለምን ያሸንፋሉ (5፡4)። ይህም ሌላው እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ምልክት ነው።

ከእግዚአብሔር መወለዳችንን ማወቃችን አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ዮሐንስ መልሱን ይሰጠናል። በዚህ ዓለም የእግዚአብሔር ልጆችና የሰይጣን ልጆች የሚባሉ ሁለት ዓይነት ልጆች አሉ (3፡10)። «የሰይጣን ልጅ» ማለት በብዙ ኃጢአት እንደሚኖር አድርገህ ልትገምት ትችላለህ፤ ይህ ግን ሁልጊዜም እውነት ላይሆን ይችላል። የማያምን ሰው «የዲያብሎስ ልጅ» ነው። ይህም ሆኖ ጥሩ ግብር የሞላበት ሕይወት ሊኖረውና ሃይማኖተኛ ሰው ሊሆን ይችላል። ዳሩ ግን «ከእግዚአብሔር ስላልተወለደ» እና በግሉ መንፈሳዊ ሕይወትን ስላልተለማመደ፥ «የሰይጣን ልጅ» ነው።

በዓለማችን ላይ በብዛት የሚገኙ የአስመሳይ ክርስቲያኖች ሁኔታ የውሸት ገንዘብ ዓይነት ነው።

ለምሳሌ በማስመሰል የተሠራ የውሸት ገንዘብ በኪስህ ይዘሃል እንበል። አንተም ገንዘቡ እውነተኛ ገንዘብ መስሎሃል። አንድ ጀሪካን ጋዝ ገዛህበት። የጋዙ ሽያጭ አስተዳዳሪም አንተ የሰጠኸውን ገንዘብ የፍጆታ ዕቃዎችን ለመግዛት ተጠቀመበት። የፍጆታ ዕቃዎች ሻጭ ደግሞ ገንዘቡን ለግሮሰሪ ክፍያ አዋለው። የግሮሰሪው ባለቤት ያንተን ገንዘብ ከሌሎቹ ጋር አንድ ላይ በማድረግ ወደ ባንክ ቤት ለማስገባት ፈለገ። ገንዘብ ተቀባዩ ግን ገንዘቡ የውሸት እንደሆነ ይነግርዋል።

በማስመሰል የተሠራው ገንዘብ በገበያ ልውውጡ ወቅት አያሌ ጠቀሜታዎችን ሊሰጥ ቢችልም፥ ወደ ባንክ በደረሰ ጊዜ እውነተኛ ማንነቱ ታውቆ ከጥቅም ውጭ ሆኗል።

የአስመሳይ ክርስቲያንም ጉዳይ ይኸው ነው። በዚህ ሕይወት አያሌ ሰናይ ምግባራትን ሊከውን ቢችልም፥ የመጨረሻውን ፍርድ በሚጋፈጥበት ጊዜ መጣሉ የማይቀር ነው። «በዚያን ቀን ብዙዎች፡- ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም፡- ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ» (ማቴ. 7፡22-23)።

እያንዳንዳችን «እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ወይስ አስመሳይ ክርስቲያን? በእውነት ከእግዚአብሔር ተወልጄአለሁ?» በማለት ራሳችንን ከእውነተኛ ልብ ልንጠይቅ ይገባል።

እስካሁን ይህንን እውነተኛ ሕይወት ማለትም የዘላለም ሕይወት ካላገኘህ አሁኑኑ ልታገኘው ትችላለህ። 1ኛ ዮሐንስ 5:9–15ን በጥንቃቄ አንብብ። እግዚአብሔር በቃሉ ገልጾልሃል። እርሱ የዘላለምን ሕይወት ይሰጥሃል። የተስፋ ቃሉን አምነህ ስጦታውን ተቀበል። «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» (ሮሜ 10:13)።

«እውነተኛ ስለ ሆነው ሕይወት» ሁለት ነገሮችን አይተናል፦ ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተገለጠና አዳኛችን አድርገን እርሱን ስናምን እንደምናገኘው ነው። ይህም ሆኖ፥ ዮሐንስ ገለጻውን ይቀጥላል።

## 3. ይህ ሕይወት ለሌሎች ተዳርሶአል

«ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን» (1ኛ ዮሐ. 1:3)። ዮሐንስ በአንደኛው ምእተ ዓመት ለነበሩ አንባቢዎች «ለማውራት» እንደፈለገ ሁሉ፥ አንተም ይህንን እውነተኛና አስደሳች ሕይወት ከተቀበልህ በኋላ ለሌሎች ለማካፈል ትሻለህ።

አንድ መጋቢ ከተበሳጨች ሴት የስልክ ጥሪ ገጠመው፥ «ከቤተ ክርስቲያናችሁ የተሰራጨ አንድ ጽሑፍ አገኘሁ፤ እንደዚህ ሰውን የሚያበሳጭ ጽሑፍ በመላካችሁ ተናድጄአለሁ» ስትል ጮኸችበት።

መጋቢውም፥ «ከቤተ ክርስቲያን የተሰራጨው ጽሑፍ እንዲህ ያበሳጨሽ ለምንድን ነው?» ሲል ረጋ ብሎ ጠየቃት።

«እናንተ የእኔን ሃይማኖት ለመለወጥ የምትሞክሩበት መብት የላችሁም!» ስትል ነጎድጓድማ ድምፅዋን አስተጋባች። «አንተ ያንተ ሃይማኖት አለህ እኔም የራሴ ሃይማኖት አለኝ፥ እኔ ሃይማኖትህን ለማስለወጥ እየሞከርሁ አይደለም!»

መጋቢውም፥ «ዓላማችን ያንቺን ወይም የማንንም እምነት መለወጥ አይደለም። ዳሩ ግን በክርስቶስ በማመን አዲስና ልዩ ሕይወት ስላገኘን ይህንኑ ለሌሎች ለማካፈል የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን» ሲል አብራራላት።

አንዳንድ ክርስቲያኖችን ጨምሮ ብዙዎች እንደሚያስቡት፥ ምስክርነት መስጠት ማለት በሃይማኖታዊ አመለካከቶችና ልዩነቶች ላይ መሟገት ወይም ቁጭ ብሎ አብያተ ክርስቲያንን ማወዳደር ነው።

ዮሐንስ ያሰበው ይህንን አልነበረም። ዮሐንስ መመስከር ማለት በምንኖረው ሕይወትና በምንናገረው ቃል መንፈሳዊ ገጠመኞቻችንን ለሌሎች ማካፈል እንደሆነ ይነግረናል።

ዮሐንስ ይህንን መልእክት የጻፈው ክርስቶስን ለእኛ ለማስተዋወቅ ነበር። መልእክቱን በምታነብበት ጊዜ፥ ዮሐንስ ይህንን ያደረገባቸው አምስት ዓላማዎች እንደነበሩት ትገነዘባለህ:—

1. *ኅብረት እንዲኖረን (1ኛ ዮሐ. 1:3)*

በክርስቲያን አነጋገር ይህ «ኅብረት» የሚለው ቃል በጣም አስፈላጊ ነው። ፍችውም «መጋራት» ማለት ነው። ኃጢአተኞች እንደመሆናቸው ሰዎች ከእግዚአብሔር የሚጋሩት ምንም ነገር የላቸውም። እግዚአብሔር ግን ከሰዎች ጋር የሚጋራውን ነገር ለማዘጋጀት በጸጋው ክርስቶስን ላከው። ክርስቶስ የሰውን ሥጋ ለብሶ ሰው ሆነ። ከዚያም ወደ መስቀሉ በመሄድ በዚያው ሰውነት የዓለምን ኃጢአት ተቀበለ (1ኛ ጴጥ. 2:24)። ለኃጢአታችን ዋጋ ስለከፈለ፥ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለንና ወደ ቤተሰቡ እንዲቀላቅለን መንገድ ተከፈተ። ስለዚህም በክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ የመለኮታዊ ባሕርዩ ተካፋዮች እንሆናለን (2ኛ ጴጥ. 1:4)። በጴጥሮስ መልእክት «ተካፋይ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል በዮሐንስ 1:3 «ኅብረት» ከተባለው ጋር በግሪኩ ቅጂ አንድ ዓይነት ነው።

ይህ ምንኛ የሚያስደስት ተአምር ነው! በእምነት የእግዚአብሔርን ዓይነተኛ ባሕርይ እንለብስ ዘንድ ክርስቶስ የሰውን ባሕርይ ወሰደ።

አንድ ዝነኛ የብሪታኒያ ደራሲ ከሊቨርፑል በመርከብ ተሳፍሮ ይሄድ ነበር። ይህ ሰው ሌሎች መንገደኞች በመርከቡ መቆሚያ አካባቢ ለሚገኙ ወዳጆቻቸው እጃቸውን በማወዛወዝ የስንብት ሰላምታ ሲሰጡ ተመለከተ። እርሱም ወደ መርከቡ መሳፈሪያ ወርዶ አንድ ትንሽ ልጅ አገኘና፥ «ገንዘብ ብሰጥህ እኔ ወደ መርከቡ ስወጣ እጅህን አወዛውዘህ ሰላምታ ትሰጠኛለህ?» ሲል ጠየቀው። ልጁም በአሳቡ ተስማማ። ደራሲው እጁን የሚያውለበልብለት ሰው በማግኘቱ ደስ ብሎት ወደ መርከቡ ፈጥኖ ወጣና ለልጁ እጅ የማውለብለብ አጸፋ መለሰለት።

ይህ ሞኝነት ይሆንን? ሊሆን ይችላል—ዳሩ ግን *ሰው ብቸኝነትን እንደሚጠላ ያስታውሰናል*። ሁላችንም ተፈላጊ መሆንን እንሻለን። ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር እና ከወገኖቻቸው ጋር እውነተኛ ኅብረት አላቸው! እውነተኛ ኅብረት ስላላቸው የብቸኝነትን መሠረታዊ ችግር ለመቅረፍ ይረዳል። ኢየሱስ፥ «እነሆ፥ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ሲል የተስፋ ቃሉን ሰጥቶናል (ማቴ. 28:20)። ዮሐንስ በመልእክቱ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት የማድረጉን ምሥጢር ይገልጽልናል። ዮሐንስ ለመልእክቱ መጻፍ የጠቀሰው የመጀመሪያ ዓላማ ይህ ነው – ያገኘውን የዘላለም ሕይወት ለሌሎች ለማካፈል።

*2. ደስታችን እንዲፈጸም (1ኛ ዮሐ. 1፡4)።*

ኅብረት ክርስቶስ ለብቸኝነት ሕይወት የሚሰጠው ምላሽ ነው። ደስታ ደግሞ ለሕይወት ባዶነት የሚሰጠው ምላሽ ነው።

ዮሐንስ በመልእክቱ «ደስታ» የሚለውን ቃል የተጠቀመው አንድ ጊዜ ብቻ ቢሆንም፥ አሳቡ ግን በመልእክቱ ውስጥ ሁሉ ይገኛል። ደስታ ራሳችን የምንፈበርከው ነገር ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ግንኙነት መልካም ውጤት ነው። ዳዊት፥ «ከፊትህ ደስታን አጠገብኸኝ» [መዝ. (16)፡11] ሲል፥ ዮሐንስ የሚናገረውን ዓይነት ደስታ እንደቀመሰ ያሳያል።

በመሠረታዊነቱ ኃጢአት ዛሬ ዓለማችንን የሚያሸንፍ የደስተኛነት ጉድለት መንሥኤ ነው። ምንም እንኳ ኃጢአት ደስታን እንደሚሰጥ ቢነገርም፥ ሁልጊዜም ውጤቱ ኃዘን ነው። የኃጢአት ደስታዎች ለጊዜው ብቻ የሚቆዩ ወቅታዊ ነገሮች ናቸው (ዕብ. 11፡25)። የእግዚአብሔር ምቾቶች ግን ለዘላለም ይዘልቃሉ [መዝ. (16)፡11]።

እውነተኛ ሕይወት የሚያስከትለው ጊዜያዊውን ሳይሆን፥ እውነተኛ የሆነውን ደስታ ነው። ኢየሱስ ከመስቀሉ ቀደም ብላ በነበረችው ሌሊት፥ «ደስታችሁን የሚወስድባችሁ የለም» ብሏል (ዮሐ. 16፡22)። «ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ» (15፡11)።

ካርል ማርክስ፥ «ሰው ደስታን እንዲያገኝ የመጀመሪያው ቀዳሚ ጉዳይ ሃይማኖትን ማጥፋት ነው» ሲል ጽፎአል። ሐዋርያው ዮሐንስ ግን፥ «በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ዓለም ሊሰጥ የማይችለውን ደስታ ይሰጣችኋል። እኔም ራሴ ይህንን ደስታ ስለተለማመድሁት ለእናንተ ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ» ሲል ጽፎአል።

*3. ኃጢአት እንዳናደርግ (1ኛ ዮሐ. 2፡1)*

ዮሐንስ የኃጢአትን ችግር በቀጥታ ያቀርብና (ከ3፡4-9 ጋር አመሳክር) ለዚህ አደናጋሪ ጉዳይ ብቸኛ መፍትሔ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስን አካልና ተግባር ያውጃል። ክርስቶስ የኃጢአታችንን ቅጣት ለመሸከም መሞት ብቻ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ሊያማልድልን ከሞት ተነሥቷል፤ «ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (2፡1)።

ክርስቶስ ወኪላችን ነው። በመሆኑም፥ በአብ ዙፋን ፊት ጥብቅና ይቆምልናል። ሰይጣን እንደ ወንድሞች ከሳሽ በዚያ ሊገኝ ቢችልም

(ራእይ 12፡10፤ ዘካ. 3)፥ ክርስቶስ ግን የሚቆመው እንደ ጠበቃችን ነው። ለእኛ ይማልዳል። ለጸሎት ምላሽ በመስጠት ይቅርታ ማድርግ መቀጠሉ፥ ለኃጢአተኛነታችን የእግዚአብሔር መፍትሔ ነው።

አንዲት የክርስትና ጥማት ያደረባት ሴት በጉብኝት ላይ ለነበረው መጋቢ፥ «ክርስቲያን ብሆን እወድ ነበር፤ ዳሩ ግን የመጽናቱ ጉዳይ ያስፈራኛል። ተመልሼ ኃጢአት እንደምሠራ እርግጠኛ ነኝ» አለች።

መጋቢውም ወደ 1ኛ ዮሐንስ በመመለስ፥ የእግዚአብሔር ቃል «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» ስለሚል፥ ተመልሰሽ ኃጢአት እንደምትሠሪ ጥርጥር የለውም። ይሁንና፥ ኃጢአት ብትሠሪ እንኳ ለእርሱ ከተናዘዝሽ ይቅር ይልሻል። ነገር ግን ለክርስቲያን ኃጢአት መሥራት አስፈላጊ አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግና ለቃሉ በመታዘዝ በምንመላለስበት ጊዜ ፈተናን የምንቋቋምበትንና ድል የምናገኝበትን ችሎታ ይሰጠናል» ሲል መለሰላት።

ከዚያም መጋቢው ሴቲቱ ከጥቂት ወራት በፊት የቀዶ–ሕክምና ማድረጓን አስታወሰ።

«የቀዶ–ሕክምና ከተደረገልሽ በኋላ ችግሮች ነበሩብሽ?» ሲል ጠየቃት።

«አዎን...ዳሩ ግን ችግር በሚያጋጥመኝ ጊዜ ሁሉ ወደ ዶክተሩ ሄጄ እታከማለሁ!» ስትል መለሰች።

ከቆይታ በኋላ፥ «አሁን ገባኝ! ሁልጊዜም እኔን ከኃጢአት ለመጠበቅ ወይም ይቅር ለማለት ክርስቶስ ዝግጁ ነው ማለት ነው!» ስትል በአጽንኦት ተናገረች።

እውነተኛ የሆነ ሕይወት የድል ሕይወት ነው። ዮሐንስ በዚህ መልእክቱ በፈተናና በኃጢአት ላይ ድልን ለመቀዳጀት እንዴት መንፈሳዊ ሀብቶቻችንን መጠቀም እንዳለብን ይነግረናል።

*4. እንዳንታለል (1ኛ ዮሐ. 2፡26)*

ክርስቲያኖች ዛሬ በትክክለኛና በተሳሳተ፥ በእውነተኛና ሐሰት በሆነ ነገር መካከል የሚገኘውን ልዩነት ከቀድሞ በበለጠ ማወቅ ይኖርባቸዋል። በትውልዳችን «ቁርጠኝነት» (ይህም ሁልጊዜ ስሕተት ወይም ሁልጊዜ ትክክል የሚሆን ነገር የለም ማለት ነው) የሚባል ነገር የለም የሚለው አሳብ በስፋት ተሰራጭቷል። ስለሆነም የሐሰት ትምህርቶች በታሪክ ከማንኛውም ጊዜ በላይ ዛሬ ተስፋፍተው

ይታያሉ፤ ሰዎችም ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች በቀር የትኛውንም ትምህርት ለመቀበል ፈቃደኞች ይመስላሉ።

በዮሐንስ መልእክት ውስጥ ሌሎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ያልተጠቀሙበት ቃል አለ፤ «የክርስቶስ ተቃዋሚ» ወይም «ሐሳዊ–መሢሕ» የሚል (2፥18፥ 22፥ 4፥3፤ 2ኛ ዮሐ.7)። «ተቃዋሚ» የሚለው ባዕድ መነሻ በግሪኩ ቋንቋ *ተፃራሪ* እና *«በእርሱ ምትክ»* የሚሉ ሁለት ፍችዎች አሉት። በዚህ ዓለም ከክርስቶስ ጋር የሚቃረኑ የሐሰት አስተማሪዎች ሲኖሩ፥ ሰዎችን የሚስቡባቸው ዘዴዎቻቸው *ውሸት* እንዲናገሩ ያደርጋል። እነዚህ ሐሰተኞች ተተኪ ክርስቶስን፥ ተተኪ ደኅንነትንና ተተኪ መጽሐፍ ቅዱስን ያቀርባሉ። *ከእውነተኛው* የእግዚአብሔር ቃልና ከእውነተኛው የዘላለም ሕይወት ይልቅ ሌላ ነገር ሊሰጡህ ይፈልጋሉ።

ክርስቶስ እውነት ሲሆን (ዮሐ. 14፥6) ሰይጣን ግን ውሸተኛ ነው (8፥44)። ስለሆነም፥ ሰይጣን ሰዎችን ወደ ጥፋት ይነዳል፤ ይህንንም የሚያደርገው የግድ አጠቃላይ ስሜታዊ ኃጢአቶችን እንዲፈጽሙ በማድረግ ብቻ ሳይሆን፥ ግማሽ እውነትና ቀጥተኛ ውሸትን በመጠቀም ነው። ይህንኑ ሰዎችን የመሳብ *ሥራውን* የጀመረው በዔድን ገነት ነበር። «እግዚአብሔር ብሎአችኋል?» ሲል ነበር ሔዋንን የጠየቃት። ከዚያ በኋላ እንኳ ወደ እርሷ የቀረበው እውነተኛ ባሕርዩን ይዞ ሳይሆን፥ እንደ ውብ ፍጡር ጭንብል አጥልቆ ነበር (ከ2ኛ ቆሮ. 11፥13–15 ጋር አመሳክር)።

ሰይጣን ዛሬም በሃይማኖታዊ ቡድኖች በኩል ሳይቀር ውሸቶቹን ያሰራጫል። በመድረክ ላይ የሚቆም ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት የሚናገር አይደለም። ሐሰተኛ የሃይማኖት መምህራንና ሐሰተኛ ሰባኪያን ሁልጊዜም ሰይጣን ከሚወዳቸው ስኬታማ መሣሪያዎቹ መሐል የሚመደቡ ናቸው።

ክርስቲያኖች ዛሬ የሰይጣንን ውሸቶች ሊለዩ የሚችሉት እንዴት ነው? ሐሰተኛ አስተማሪዎችን እንዴት ያውቁአቸዋል? በሐሰተኛ ትምህርቶች የተጎዱ እንዳይሆኑ በራሳቸው የእውነት ግንዛቤ ሊያድጉ የሚችሉት እንዴት ነው?

ዮሐንስ እነዚህን ጥያቄዎች መልሶአቸዋል። እንደ እርሱ መረዳት እውነተኛ ሕይወት የመለየትን ባሕርይ በመጠቀም ይታወቃል።

ዮሐንስ፥ «ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት» የሚለው መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ ለመለየትና ያሉብንን ችግር ለማቃለል የሰጠን ምላሽ ነው (1ኛ ዮሐ 2፥27)። መንፈስ ቅዱስ አስተማሪያችን ነው፤ እውነቱን

ከስሕተት እንድንለይና በክርስቶስ እንድንኖር የሚያስችለን እርሱ ነው። ካለማወቅ፥ ከመታለልና እውነተኛ ካልሆነ አካሄድ የሚጠብቀን እርሱ ነው።

ሐሰተኛ አስተማሪዎችንና ሐሰተኛ ትምህርቶችን መለየት በዚሁ መጽሐፍ ምዕራፍ 5 እና 6 ውስጥ ደግመን የምንመለከተው ይሆናል።

*5. እንደዳንን እንድናውቅ (1ኛ ዮሐ. 5፡13)።*

ከዚህ ቀደም ይህንኑ እውነት የነካካን ሲሆን፥ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ እንደገና ቀርቦአል። እውነተኛ የሆነ ሕይወት በባዶ ተስፋዎች ወይም በሰው ግምቶች ላይ በተንተራሱ ምኞቶች ድጋፍ አይመሠረትም፥ ይልቁንም በዋስትና ላይ የተመረኮዘ ነው። እንዲያውም የዮሐንስን መልእክት በምታነብበት ጊዜ «*ማወቅ*» የሚለውን ቃል ከ30 ጊዜያት በላይ ተደጋግሞ ታገኘዋለህ። አንድ ክርስቲያን ሲሞት ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚሄድ ወይም እንደማይሄድ ሲጠየቅ፥ «*ተስፋ አደርጋለሁ*» ወይም «*ይመስለኛል*» ብሎ እንዲመልስ አይጠበቅም። ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚሄድ ሊጠራጠር አይገባምና።

እውነተኛ ሕይወት በማይነቃነቁ ሐቆች ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነፃና አስደሳች ነው። «እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» (ዮሐ. 8፡32) ሲል ነበር ኢየሱስ የተናገረው። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርትም፥ «በብልሃት የተፈጠረውን ተረት አልተከተልንም» ሲሉ መስክረዋል (2ኛ ጴጥ. 1፡16)። እነዚህ ለእምነታቸው ሲሉ ራሳቸውን እስከ ሞት ያቀረቡ ሰዎች ነበሩ። እነርሱ አንዳንድ የክርስትና ተቺዎች በሞኝነት እንደሚሉት፥ ራሳቸው ለፈጠሩት የውሸት መታለያ አንገታቸውን አልሰጡም ነበር። የተመለከቱትን ያውቁት ነበርና!

ከዓመታት በፊት አንድ ተጓዥ የመዝናኛ ትርዒት ባለሙያ ራሱን «የሰው ዝንብ» ሲል አቅርቦ ነበር። የገመድ እገዛ ወይም የመረብ ጥበቃ ሳያስፈልገው ሕንፃዎችና ሐውልቶች ላይ ይወጣ ነበር። በአብዛኛው በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ብቅ እያሉ ይመለከቱት ነበር።

በአንድ የትርዒት ወቅት፥ ይኸው ሰው ከአንዱ ሕንፃ ላይ ደረሰና ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለበት እንደማያውቅ ሁሉ ተገትሮ ቀረ። ከዚያም ትንሽ ከፍ ለማለት በቀኝ እጁ የሕንፃውን ብሎኬት ያዘ። ይሁንና፥ ወደ ላይ ከፍ እንደማለት ወደ ኋላ ወደቀና ከሥሩ ባለው የስሚንቶ ንጣፍ ላይ ተፈጥፍጦ ሞተ።

ፖሊሱ ቀኝ እጁን በተመለከተ ጊዜ የሸረሪት ድርን እንጂ የሕንፃውን ድንጋይ እንዳልያዘ ተረዳ። «የሰው ዝንብ» የሸረሪት ድር ጨብጦ ለመሄድ ቢሞክር አልሆነለትም።

ቀደም ብለን በተመለከትነው ምንባብ ውስጥ ኢየሱስ እንዲህ ባለ ሐሰተኛ ዋስትና እንዳንደገፍ አስጠንቅቆናል። በእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ብዙ ሰዎች ወደ ውጭ ይጣላሉ።

ዮሐንስ በመልእክቱ፥ «የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ አርግጠኞች እንድትሆኑ እፈልጋለሁ» እያለ ነበር።

ይህንን አስደሳች ደብዳቤ በምታነብበት ጊዜ ዮሐንስ በአብዛኛው አሳቦችን እንደሚደጋግም ትመለከታለህ። የሚያጠነጥነውም *«ታዛዥነት»*፥ *«ፍቅር»* እና *«እውነት»* በሚሉ ሦስት ጭብጦች ላይ ነው። በምዕራፍ 1 እና 2 ሐዋርያው በኅብረት ላይ አጽንኦት በመስጠት፥ ለዚሁ የሚያስፈልጉ ቅደመ–ሁኔታዎች *ታዛዥነት* (1፡5–2፡6)፥ ፍቅር (2፡7–17) እና እውነት (2፡18–29) እንደሆኑ ይናገራል።

በሁለተኛው የመልእክቱ ክፍል ዮሐንስ በቀዳሚነት ስለ *«ልጅነት»* ይናገራል፤ ይህም ከእግዚአብሔር ስለ መወለዳችን ነው። አንድ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንዴት ያውቃል? ዮሐንስ ልጅነት በታዛዥነት (ምዕ. 3)፥ በፍቅር (ምዕ. 4) እና በእውነት (ምዕ. 5) ራሱን እንደሚገልጽ ይናገራል።

ታዛዥነት – ፍቅር – እውነት። ዮሐንስ እነዚህን ዓይነተኛ መመዘኛዎች ለኅብረትና ለልጅነት የተጠቀመው ለምንድን ነው? አንድ በጣም ተጨባጭ የሆነ ምክንያት አለው።

እግዚአብሔር ሲፈጥረን የፈጠረን በራሱ አምሳል ነው (ዘፍ. 1፡26–27)። ይህም በእግዚአብሔር መልክ የተቀረጸ ባሕርይ እንዳለን ያሳያል። የምናስብበት *አእምሮ*፥ የምንወስንበት *ፈቃድና* ስሜትን የምናስተናግድበት *ልብ* አለን። አንዳንዴ እነዚህን የባሕርያችንን ገጽታዎች *አውቀት*፥ *ፈቃድና ስሜት* እንላለን።

እውነተኛ የሆነ ሕይወት *የባሕርይን አካላት ሁሉ ማካተት አለበት።*

ዛሬ የብዙ ሰዎች ባሕርይ እውነተኛና ትርጉም ባለው ነገር ቁጥጥር ሥር ባለመዋሉ እርካታን አጥተው ይመላለሳሉ። አንድ ሰው በክርስቶስ በማመን ከእግዚአብሔር በሚወለድበት ጊዜ፥ መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም ይኖር ዘንድ ወደ ሰውዬው ሕይወት ይመጣል። መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናትና በመጸለይ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በሚያደርግበት ጊዜ፥ መንፈስ ቅዱስ አእምሮውን፥ ልቡንና ፈቃዱን ለመቆጣጠር ይችላል። ከዚያስ ምን ይሆናል?

በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር የዋለ አእምሮ እውነትን ይረዳል፤ ያውቃልም።

በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር የዋለ ልብ የፍቅርን ስሜት ያስተናግዳል።

በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር የዋለ ፈቃድ ወደ መታዘዝ ይመራናል።

ዮሐንስ እነዚህን እውነታዎች ሊያስተላልፍልን ስለሚፈልግ በመልእክቱ ተከታታይ ማነጻጸሪያዎችን ይጠቀማል፤ በመሆኑም፥ እውነትን ከሐሰት፥ ፍቅርን ከጥላቻ፥ ታዛዥነትን ከእንቢተኝነት ጋር ያወዳድራል።

እውነተኛ በሆነ ሕይወት ውስጥ መሀል ሰፋሪነት የለም። በአንድ ወይም በሌላ ወገን መሆን አለብን።

እንግዲህ እውነተኛ የሆነ ሕይወት ይህ ነው። ይህም በክርስቶስ የተገለጠና ክርስቶስን ላመኑት የተሰጠ ሲሆን፥ ዛሬም ለሌሎች ሊተላለፍ ይችላል።

አዲሱ ሕይወት በልጅነት ይጀመርና በኅብረት ይቀጥላል። በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር የተወለድን ከሆነ ከዚያ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር እንመላለሳለን።

በመሆኑም፥ እኛ ወደምናስበው ደስታና ድል የማይገቡ ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ ማለት ነው፤ እነዚህም ዳግም ያልተወለዱና ከዳኑ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሌላቸው ናቸው።

ስለሆነም፥ የራሳችንን መንፈሳዊ ሕይወት በመገምገም (2ኛ ቆሮ. 13፡5ን ተመልከት)፥ የዮሐንስ መልእክት ለሚናገረው ፍሬ ነገር ብቁዎች መሆን አለመሆናችንን መመልከቱ አዋቂነት ነው።

ከእግዚአብሔር የመወለድን አስፈላጊነት ቀደም ብለን በአጽንኦት ተመልክተናል፤ ይህም ሆኖ፥ ማንኛውም ጥያቄ ወይም ጥርጥር ቢኖርብህ፥ እውነታ ሁለትን መከለሱ መልካም ነው።

እውነተኛ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የማያደርግ ከሆነ፥ ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ይኸውም፡-

1. የእግዚአብሔርን ምኞትና ፈቃድ ተላልፎአል።

2. ከሌሎች አማኞች ጋር ተገቢውን ኅብረት አያደርግም።

3. ውሸትን በመጠመድ የውሸት ሕይወት በመኖር ላይ ነው።

ክርስቲያንም እንኳ ስለ እውነት የተሳሳተ ግንዛቤ ሊኖረው ይችላል። ለዚህ ነው ዮሐንስ፥ «ልጆች ሆይ፥ ማንም አያስታችሁ» የሚለን (1ኛ ዮሐ. 3፡7)።

እነዚህ ሦስቱ ምክንያቶች ከዮሐንስ ሦስቱ አስፈላጊ ጭብጦች ማለትም ከታዛዥነት፥ ፍቅርና እውነት ጋር ይዛመዳሉ። ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ኅብረት ውጭ የሆነበትን ምክንያት ካወቀ በኋላ፥ ያንኑ ኃጢአት (ወይም እነዚያኑ ኃጢአቶች) ለጌታ በመናዘዝ ሙሉ ይቅርታውን መቀበል አለበት (1፡9–2፡2)። ኃጢአት በመካከል ግድግዳ ሆኖ ከቆመ፥ አማኝ ከጌታ ጋር አስደሳች ኅብረት ሊኖረው አይችልም።

ዛሬ እግዚአብሔር የሚያቀርብልን ጥሪ «ኑና ከእኔ ጋር ኅብረት በማድረግ ደስ ተሰኙ! እርስ በርሳችሁም በዚሁ ኅብረት ተደሰቱ! ኑና እውነተኛ የሆነውን ሕይወት ተቀበሉ!» የሚል ነው።

# – 2 –

# ቃላችንና አካሄዳችን

## 1ኛ ዮሐንስ 1፡5–2፡6

ማንኛውም ዓይነት ሕይወት የራሱ ተፃራሪዎች አሉት። ትናንሽ ነፍሳት ከተራቡ ወፎች መሸሸግ ሲኖርባቸው፥ ወፎችም በበኩላቸው ከተራቡ ድመቶችና ውሾች መጠንቀቅ አለባቸው። እኛ ሰዎችም ከመኪና አደጋና ከበሽታ አምጪ ተሃዋስያን መጠንቀቅ አለብን።

እውነተኛ የሆነ ሕይወትም የራሱ ጠላቶች እንዳሉት ከዚህ ክፍል እናነባለን። ይህም ጠላት ኃጢአት ነው። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ዮሐንስ ኃጢአትን ዘጠኝ ጊዜያት ስለሚጠቅስ፥ የጉዳዩን አሳሳቢነት ልብ ልንል እንችላለን። ዮሐንስ በብርሃንና ጨለማ መካከል ያለውን ንጽጽር በማቅረብ ጭብጡን ያብራራዋል፤ በማብራሪያው መሠረት እግዚአብሔር ብርሃን ሲሆን፥ ኃጢአት ግን ጨለማ ነው።

በተጨማሪም፥ *የቃላትና የድርጊት ንጽጽር* ቀርቧል። ዮሐንስ አራት ጊዜ «ብንል» ወይም «የሚል» ሲል ጠቅሶአል (1፡6፥ 8፥ 10፤ 2፡4)። የክርስትና ሕይወታችን በቃላችን ብቻ እንደማይገታ ግልጽ ነው፤ የምናምነውን መኖር አለብን። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ካለን (በብርሃኑ የምንመላለስ ከሆነ)፥ ሕይወታችን የከንፈራችንን ቃል ይደግፈዋል። በኃጢአት የምንኖር ከሆነ ግን (በጨለማ ብንመላለስ)፥ ሕይወታችን የከንፈራችንን ቃል በመጻረር ግብዞች ያደርገናል።

አዲስ ኪዳን የክርስትናን ሕይወት «መመላለስ» ሲል ይጠራዋል። ይህ ረዥም *ጉዞ* ክርስቶስን አዳኛችን አድርገን ከተቀበልንበት የእምነት እርምጃ ይጀምራል። በዚህ ላይ ደኅንነት የመንፈሳዊ ሕይወት ጅማሬ እንጂ ፍጻሜ አይደለም። በ«መመላለስ» ውስጥ ዕድገት አለ፤ ክርስቲያኖችም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ተጠይቀዋል። አንድ ሕፃን ለመራመድ መማርና በዚህም ውስጥ ብዙ ችግሮችን ማሸነፍ እንዳለበት ሁሉ፥ ክርስቲያንም በብርሃን ለመመላለስ መማር አለበት። በዚህም ውስጥ የሚገጥመው መሠረታዊ ችግር ኃጢአት ነው።

በመሠረቱ ኃጢአት ውጫዊ አለመታዘዝ ብቻ ሳይሆን፥ ውጫዊ ዓመፅ እና የውስጥ መሻትም ነው። ለምሳሌ ከሥጋ ምኞትና ከዓይን አምሮት ብሎም ከትምክህት እንድንጠነቀቅ ተነግሮናል (2፡16)፤ እነዚህም ሁሉ የኃጢአት ተግባራት ናቸው። ኃጢአት ሕግን መተላለፍ (3፡4) ወይም በቀጥታ «ዓመፀኝነት» ነው። ኃጢአት ለእግዚአብሔር

ሕግ ለመገዛት አለመፍቀድ ነው። የኃጢአት ዓይነተኛው ባሕርይ ዓመፀኛነት ወይም ከሕግ ነፃ መሆን ነው። አንድ አማኝ ነፃ የሆነ ሕይወት ለመኖር ከወሰነ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እያደረገ ሊመላለስ የሚችለው እንዴት ነው? «በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን?» (አሞ. 3:3)።

በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሳንን ኃጢአት አይሸፍንም። አብርሃም ረሃብን በመሸሽ በእምነቱ ደከመና ወደ ግብፅ በመሄድ ለፈርዖን ውሸትን ተናገረ (ዘፍ. 12)። በኋላም፥ የእምነት አባት (ፓትርያርክ) የተባለው አብርሃም አጋርን በማግባትና ከእርሷ ልጅ በመውለድ እግዚአብሔርን ሊረዳ ሞከረ (ዘፍ. 16)። በሁለቱም አጋጣሚዎች እግዚአብሔር የአብርሃምን ኃጢአት ይቅር ብሎአል፤ አብርሃም ግን የዘራውን ከማጨድ አላመለጠም። እግዚአብሔር የኃጢአትን መዝገብ ሊፍቅ ይችላል፤ ኃጢአት የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ግን አይለውጣቸውም።

ጴጥሮስ ሦስት ጊዜ ጌታን የካደ ሲሆን፥ ኢየሱስ በታሰረ ጊዜ በአትክልት ስፍራው አንድ ሰው ሊገድል ሞክሯል። ሰይጣን ውሸተኛና ነፍሰ-ገዳይ መሆኑ ግልጽ ነው (ዮሐ. 8:44)፤ ጴጥሮስም በእጁ ውስጥ እየገባ ነበር። ይህም ሆኖ፥ ክርስቶስ ጴጥሮስን ይቅር ብሎታል (ዮሐ. 21)፤ ይሁንና፥ ጴጥሮስ ያደረገው ነገር ምስክርነቱን በከፍተኛ ደረጃ በመጉዳት የጌታን ሥራ አደናቅፎአል።

የክርስቲያኖች ኃጢአት መሥራት አንዳንድ ሰዎችን-በተለይም አዳዲስ አማኞችን ያሳስባል። አዲሱን ባሕርይ መቀበላቸው አብረው የተወለዱበትን አሮጌውን ባሕርይ እንደማያስወግድ ይዘነጋሉ። በሥጋ ከተወለድንበት ጊዜ አንሥቶ ከእኛ ጋር የነበረው አሮጌው ባሕርይ ዳግም ስንወለድ ካገኘነው ከአዲሱ ባሕርይ ጋር ይዋጋል (ገላ. 5:16-26)። ምንም ያህል ራስን ፈር ማስያዝ፥ ምንም ያህል ሰው ሠራሽ ደንብና ሥርዓት ይህንኑ አሮጌ ተፈጥሮ ሊቆጣጠር አይችልም። አሮጌውን ባሕርይ «እንድንገድል» ኃይል ሊሰጠን (ሮሜ 8:12፥ 13) እና በአዲሱ ባሕርይ አማካኝነት የመንፈስ ፍሬ ሊያፈራልን የሚችለው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው (ገላ. 5:22-23)።

ኃጢአት የሠሩ ቅዱሳን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ሊያስጠነቅቁን እንጂ ተስፋ ሊያስቆርጡን አይደለም።

አንዲት በንዴት የጦፈች ክርስቲያን ለመጋቢዋ፥ «ለእኛ ለክርስቲያኖች ሁልጊዜም ስለ ኃጢአት የምትሰብከው ለምንድን ነው? የክርስቲያን ኃጢአት ካልዳነው ሰው ኃጢአት የተለየ አይደለምን?» ስትል ጮኸችበት።

*መጋቢዋም፥ «ልክ ነሽ። የክርስቲያኑ ኃጢአት የተለየ ነው። ይህም እጅግ የከፋ በመሆኑ ነው።» ሲል መለሰላት።*

እውነተኛ በሆነው ሕይወት ልንደሰት ከፈለግን ሁላችንም ኃጢአታችንን ማስወገድ አለብን። በዚህ ክፍል ዮሐንስ ለዚህ የሚረዱን ሦስት መንገዶች ይገልጻል፡-

## 1. ኃጢአታችንን ለመሸፈን ልንሞክር እንችላለን።

«እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም» (1ኛ ዮሐ. 1:5)። በዳንን ጊዜ እግዚአብሔር ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ጠርቶናል (1ኛ ጴጥ. 2:9)። እኛ የብርሃን ልጆች ነን (1ኛ ተሰ. 5:5)። ክፉ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ብርሃንን ይጠላሉ (ዮሐ. 3:19-21)። ብርሃን በእኛ ላይ ሲንጸባረቅ እውነተኛ ባሕርያችንን ይገልጻል (ኤፌ. 5:8-13)።

ብርሃን ሕይወትን፥ ዕድገትንና ውበትን ሲያፈራ፥ ኃጢአት ግን ጨለማን ነው፤ በመሆኑም፥ ጨለማና ብርሃን በአንድ ስፍራ አብረው ሊኖሩ አይችሉም። በብርሃን የምንመላለስ ከሆነ፥ ጨለማው ስፍራ መልቀቅ አለበት። ኃጢአት በመሥራት የምንቀጥል ከሆነ ግን ብርሃኑ ስፍራ ይለቃል። ኃጢአት የሚቀመጥበት መሀል ቤት የለም።

ክርስቲያኖች ኃጢአታቸውን ለመሸፈን የሚሞክሩት እንዴት ነው? *ውሸትን በመናገር ነው!* በመጀመሪያ፥ ውሸትን ለሌሎች ሰዎች እንናገራለን (1ኛ ዮሐ. 1:6)። ክርስቲያን ወዳጆቻችን «መንፈሳውያን» እንደሆንን እንዲያስቡ ለማድረግ ስንል ስለ ሕይወታችን በመዋሸት ምቹ ድባብ ለመፍጠር እንጥራለን። እውነቱ በጨለማ መመላለሳችን ሆኖ ሳለ፥ በብርሃን እንደምንመላለስ አድርገው እንዲያስቡ እንሻለን።

አንድ ሰው ለሌሎች መዋሸት ከጀመረ፥ ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ ለራሱ መዋሸቱን ይቀጥላል፤ የምንባብ ክፍላችንም የሚናገረው ስለዚሁ ለራስ ስለመዋሸት ነው (ቁጥር 8)። ችግሩ ሌሎችን ማታለሉ ሳይሆን ራሳችንን ማታለሉ ነው። ለአንድ አማኝ በኃጢአት ውስጥ ተዘፍዝፎ ሳለ ከጌታ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ሁሉም ነገር ደህና እንደሆነ ለራሱ ማሳመን የማይሞከር አይደለም።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ንጉሥ ዳዊት ነው (2ኛ ሳሙ. 11 እና ምዕራፍ 12)። መጀመሪያ ዳዊት ቤርሳቤህን ተመኛት። ከዚያም ዝሙት ፈጸመ። ቀጥሎም ያደረገውን ነገር በግልጽ እንደመቀበል ሊሸፋፍን ሞከረ። የቤርሳቤህን ባለቤት ሊያታልል ሞክሮ መጠጥ አጠጣውና ከዚያም ገደለው። ለራሱ በመዋሸት የንጉሥነት ግዴታዎቹን በተለመደው መንገድ ለማካሄድ ጣረ። የችሎቱ መንፈሳዊ ጉዳዮች

ኃላፊ የሆነው ነቢዩ ናታን ተመሳሳይ የግብዝነት ገጠመኝ በመተረክ ሊያወጣጣው ሲሞክር፥ ዳዊት ለራሱ የኩነኔ ስሜት ሳያድርበት ናታን ያቀረበውን ባለታሪክ ኮነነው። ለሌሎች መዋሸት ከጀመርን ውሸታችንን ለራሳችን ለማመን ብዙ ጊዜ አይወስድብንም።

ይሁንና፥ መንፈሳዊ ውድቀት አሁንም እየከፋ ይሄዳል፤ በመሆኑም ቀጣዩ እርምጃችን እግዚአብሔርን ለመዋሸት መጣር ይሆናል (1ኛ ዮሐ. 1፡10)። ራሳችንን ዋሾዎች ስላደረግን እግዚአብሔርን ዋሾ ለማድረግ እንጥራለን። «ሁሉም ኃጢአት ሠርቶአል» የሚለውን የእርሱን ቃል በመቃወም፥ እኛ ከዚህ አባባል ውጭ እንደሆንን እንናገራለን። የእግዚአብሔርን ቃል ከሌሎች እንጂ ከራሳችን ሕይወት ጋር አናዛምድም። የአምልኮ ፕሮግራሞችን ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ስናደርግ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ልባችንን አይነካንም፥ በዚህ የዝቅጠት ደረጃ ላይ የደረሱት አማኞች በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ ከፍተኛ የትችት ቃላት ቢሰነዝሩም፥ ቃሉን ከራሳቸው ሕይወት ጋር የማዛመዱን ነገር አጥብቀው ይቃወማሉ።

መንፈስ ቅዱስ በእስትንፋሰ-መለኮቱ ስለ ሰው ልብ የሚሰጠው መግለጫ እጅግ አስፈሪ ነው! አማኝ ስለ *ኅብረቱ* ይዋሻል (ቁጥር 6)፤ ስለ *ባሕርዩ* ይዋሻል፤ ስለ ባሕርዩ የሚዋሸው «እንዲህ ዓይነት ነገር ላደርግ አልችልም!» (ቁጥር 8) በማለት ነው፤ እንዲሁም፥ ደግሞ ስለ *ተግባራቱ* ይዋሻል (ቁጥር 10)።

ኃጢአት አደገኛ የመስፋፋት መንገድ አለው፥ አይደለም እንዴ?

በዚህ ነጥብ ላይ እውነተኛ ስለሆነው ሕይወት በአንድ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ላይ እንነጋገራለን። ይኸውም *እውነተኛነት* ነው። ለራሳችን፥ ለሌሎችና ለእግዚአብሔር እውነተኞች መሆን አለብን። የምንባብ ክፍላችን እውነተኛ ያልሆነ ሕይወት የሚመራውን አማኝ ውሸተኛ ይለዋል። ይህ ሰው በአንድ ተውኔት ውስጥ የተወሰነ ሚና እየተጫወተ እንጂ እውነተኛ ሕይወት እየኖረ አይደለም። ይህ ሰው ታማኝ አይደለም።

የዚህ ዓይነቱ ሰው ምን ዓይነቱ ኪሳራ ይገጥመዋል?

አንደኛ፥ *ቃሉን* ማጣቱ ነው። እውነትን ከማድረግ ስለሚታቀብ (ቁጥር 6) እውነት በእርሱ ውስጥ አይኖርም (ቁጥር 8)፤ ከዚያም እውነትን ወደ ውሸት ይለውጣል (ቁጥር 10)! ኢየሱስ «ቃልህ እውነት ነው» ብሏል (ዮሐ. 17፡17)። ውሸትን የሚኖር ሰው ግን ቃሉን ያጣል። አንድ ሰው በጨለማ እንደሚመላለስ ከሚያሳዩን የመጀመሪያ ምልክቶች አንዱ ከመጽሐፍ ቅዱስ በረከትን ማጣት ነው። በጨለማ

ውስጥ እየተመላለስህ ሳለ ቃሉን በትርፋማ መንገድ ልታነብ አትችልም።

ሁለተኛ፥ እውነተኛ ያልሆነ ሰው ሌላም ነገር ያጣል፤ ይኸውም ከእግዚአብሔር እና ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር የነበረው ኅብረት ይጠፋል (1ኛ ዮሐ. 1፥6፥ 7)። ከዚህም የተነሣ ጸሎት ባዶ የቃላት ጨዋታ፥ አምልኮ ደግሞ ስልቹ ድግግሞሽ ይሆንበታል። በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ የትችት አመለካከት በማዳበር ከቤተ ክርስቲያን መቅረትን ይመርጣል፤ «ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?» (2ኛ ቆሮ. 6፥14)።

ለምሳሌ ከእግዚአብሔር ኅብረት ተለይቶ በመንፈሳዊ ጽልመት ውስጥ የሚዳክር ኮብላይ ባል፥ በብርሃን ከምትመላለስ ክርስቲያን ሚስቱ ጋር ኅብረት እያደረገ ደስ ሊሰኝ አይችልም። ባለትዳሮች ከልብ ያልሆነ ጓደኝነት ሊኖራቸው ቢችልም፥ እውነተኛ መንፈሳዊ ኅብረት ሊያደርጉ አይችሉም። ይህ መንፈሳዊ ጉዳዮችን ያለመጋራቱ ችግር በቤት ውስጥና በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል አያሌ ግላዊ እክሎችን ይፈጥራል።

አንድ ጊዜ የተወሰኑ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስለ መጋቢያቸው እየተነጋገሩ ነበር።

ከመካከላቸው አንዱ፥ «ለምን እንደሆነ እንጃ፥ ይህ ሰው ብዙም አይመቸኝም። ደህና ሰው እንደሆነ ባምንም፥ አንድ ነገር በመካከላችን የቆመ ይመስለኛል» አለ።

ሌላው መልሶ፥ «ልክ ነህ፤ አንተ የምትለውን የማውቅ ይመስለኛል። እኔም ከእርሱ ጋር እንደዚያው ዓይነት ችግር ነበረብኝ፤ አሁን ግን ችግር የለብኝም። መጋቢውና እኔ ግሩም ኅብረት አለን» አለው።

«ነገሮችን ለማስተካከል ምን እርምጃ ወሰደ?»

«እርሱ ምንም አላደረገም፤ ለውጡን ያመጣሁት እኔው ነኝ!»

«አንተው ለውጡን አመጣኸው?»

«አዎን። እንደመጋቢያችን እኔም ግልጽና እውነተኛ ልሆን ወሰንሁ። አየህ፥ በእርሱ ሕይወት ውስጥ አንድም ግብዝነት የለም፤ በእኔ ሕይወት እጅግ ብዙ ግብዝነት ነበርና አንድነት ልንፈጥር አልቻልንም። እርሱም ሆነ እኔ ውሸታምነቴን እናውቅ ነበር። እውነተኛ የክርስትና ሕይወት መኖር ከጀመርሁበት ጊዜ አንሥቶ ሁሉም ነገር ተሻሽሎአል።»

የውሸተኛነት አንዱ ችግር የውሸቶቻችንን መዝገብና እውነት የማስመሰያ ዘዴዎችን ማቀናበሩ የሙሉ ጊዜ ተግባር ሆኖ መቅረቱ ነው። አብርሃም ሊንከን «አንድ ሰው ውሸተኛ ከሆነ ጥሩ የማኅደረ ትውስታ ችሎታ ሊኖረው ይገባል» ይሉ ነበር። አንድ ሰው ጉልበቱን ሁሉ *በማስመሰል* ላይ ሲያሳርፍ ለኑሮ የሚተርፈው አይኖረውም። ከዚህም የተነሣ ሕይወት ባዶና ጣዕም–አልባ ትሆናለች። አስመሳይነትን የሚያበዛ ግብዝ ሰው ራሱን ከእውነታ ማራቅ ብቻ ሳይሆን፥ ከዕድገትም ይታቀባል፤ ይህም እውነተኛ ማንነቱ በውሸት ስለ ተሸፈነ ነው።

ሦስተኛው እጦት የመጀመሪያ ሁለቱ ውጤት ይሆናል። ይኸውም አማኙ ባሕርዩን እንደሚያጣ ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡4)። ሂደቱ ውሸትን *በመናገር ይጀምርና ሰውዬውን ውሸተኛ* በማድረግ ያከትማል! ታማኝ ወይም እውነተኛ አለመሆኑ በመጀመሪያ እርሱ የሚጫወተው ሚና ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ሚናነቱ ቀርቶ «ልማድ ሲሠለጥን ተፈጥሮ ይሆናል።» የሕይወቱ ዓይነተኛ ባሕርይ ይሆናል። ባሕርዩ ተሸራርፎአል። እናም ውሸተኛ የሆነው ውሸትን ስለሚናገር አይደለም፤ ይልቁንም አሁን በውሸተኛነቱ ስላመነ ውሸትን ይናገራል።

እንግዲህ እግዚአብሔር፥ «ኃጢአቱን የሚደብቅ አይለማም» ሲል ማስጠንቀቁ ያስደንቅ ይሆን? (ምሳሌ 28፡13)። ዳዊት ኃጢአቶቹን ሊሰውር ሞክሮ ጤንነቱን [መዝ. (32)፡3–4]፥ ደስታውን [መዝ. (51)] ፥ ቤተሰቡን አጥቷል፤ መንግሥቱንም ሊያጣ ተቃርቦ ነበር። እውነተኛ በሆነው ሕይወት ልንደሰት ከፈለግን ኃጢአታችንን *መሸፈን* የለብንም።

*ምን እናድርግ?*

## 2. *ኃጢአታችንን* ልንናዘዝ እንችላለን።

ዮሐንስ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት አስገራሚ ስሞችን ይሰጣል– *ጠበቃ* እና *ማስተሰሪያ* (1ኛ ዮሐ. 2፡1–2)። እነዚህ ሁለት ስሞች ጌታ ራሱ የሚፈጽማቸውን ሁለት አገልግሎቶች ስለሚወክሉ በሚገባ ልናጤናቸው ይገባል።

*ከማስተሰሪያ* እንጀምር፤ የዚህን ቃል ፍች ከመዝገበ ቃላት ብትፈልግ ምናልባትም የተሳሳተ አሳብ ሊያጋጥምህ ይችላል። በአንዳንድ የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት «ማስተሰሪያ» ማለት «የተቆጣን ሰው ቁጣ ማብረድ ነው» ተብሎ ተቀምጦአል። ይህንን ከክርስቶስ ጋር ብታዛምድ፥ በቁጣ ጦፎ ዓለምን ሊያጠፋ የደረሰውን አምላክ አስፈሪ ምስልና አፍቃሪው አዳኝ የአምላክን ቁጣ ለማብረድ ራሱን የሚሰጥበትን ሁኔታ ትመለከታለህ፤ ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ደኅንነትን የሚያቀርብበት መንገድ *አይደለም*። በመሠረቱ

እግዚአብሔር ይህ ነው በማይባል ቅድስና የተላበሰ አምላክ በመሆኑ፥ በኃጢአት ላይ እንደሚቆጣ እሙን ነው። ይህም ሆኖ፥ መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር ዓለምን [*ስለ ጠላ* ሳይሆን] ስለ *ወደደ*» ሲል *ያረጋግጥልናል* (ዮሐ. 3፡16)።

ስለሆነም፥ ማስተሰረይ የተቆጣን አምላክ ቁጣ ማብረድ አይደለም። ይልቁንም፥ *የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሕግ ማርካት ነው*። «እግዚአብሔር ብርሃን» ስለሆነ (1ኛ ዮሐ. 1፡5)፥ ኃጢአትን ሊያስተናግድ አይችልም። ይሁንና፥ «እግዚአብሔር ፍቅር» በመሆኑ (1ኛ ዮሐ. 4፡8)፥ ኃጢአተኞችን ሊያድን ይፈልጋል።

እንግዲህ፥ ቅዱስ አምላክ የራሱን ጽድቅ ሳያጣ ኃጢአተኞችን ሊያድን የሚችለው እንዴት ነው? መልሱ ከክርስቶስ መሥዋዕት ይመጣል። በመስቀሉ ላይ እግዚአብሔር በቅድስናው በኃጢአት ላይ ፈርዶአል። እግዚአብሔር በፍቅሩ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝ ለዓለም ሰጥቷል። እግዚአብሔር *ጻድቅ* (ቅን ፈራጅ) በመሆኑ ኃጢአትን ቀጥቷል፤ በተጨማሪም፥ *አፍቃሪ* በመሆኑ ኢየሱስ በጎልጎታ በፈጸመው ተግባር ነፃ ይቅርታ ሰጥቷል። (1ኛ ዮሐንስ 4፡10 ንና ሮሜ 3፡23–26ን አንብብ።)

ክርስቶስ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት መሥዋዕት ሲሆን፥ ጥብቅናው ግን ለአማኞች ብቻ ነው። እኛ (ክርስቲያኖች) ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን። ጠበቃ የሕግ ቃል ነው። ይህም ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት በተናገረ ጊዜ ከተጠቀመው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው (ዮሐ. 14፡16፥ 26፤ 15፡26)። ፍችውም ከአንድ ሰው ጎን ተጠርቶ የቆመ ማለት ነው። አንድ ሰው ተከስሶ ችሎት ፊት ሲቀርብ ከጎኑ ቆሞ ይሟገትለት ዘንድ ጠበቃ ይቀጥራል።

ኢየሱስ በምድር ላይ *ሥራውን* ፈጽሞአል (ዮሐ. 17፡4)፤ ይህም ሕይወቱን ለኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ የመስጠት *ሥራ* ነበር። ዛሬ በሰማይ «*ያልተጠናቀቀ ሥራ*» አለው። *ይህም በእግዚአብሔር ፊት እኛን ወክሎ መቅረብ ነው*። ሊቀ ካህናችን እንደመሆኑ፥ ለድካማችንና ለሚያጋጥሙን ፈተናዎች በመራራት የሚያስፈልገንን ጸጋ ይሰጠናል (ዕብ. 4፡15፥ 16፤ 7፡23–28)። ጠበቃችን እንደ መሆኑ፥ *ኃጢአትን በምንሠራበት ጊዜ* ይረዳናል። ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር በምንናዘዝበት ጊዜ፥ ከክርስቶስ የጠበቃነት ተግባር የተነሣ እግዚአብሔር ይቅር ይለናል።

ብሉይ ኪዳን ለዚህ ውብ ምሳሌ አለው። አይሁዳውያን ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ወደ ምድራቸው ሲመለሱ ኢያሱ በሊቀ ካህንነት ያገለግላቸው ነበር (ዘካ. 3፡1–7)። (ይኸኛው ኢያሱ ወደ ተስፋዪቱ

ምድር ያስገባቸው ኢያሱ እንዳልሆነ ልብ በል።) ሕዝቡ ኃጢአት ሠርቶ ነበር፤ ይህንኑ በተምሳሌት ለማመልከት፥ ኢያሱ አዳፋ ልብስ ለብሶ በእግዚአብሔር ፊት ሲቆም፥ ሰይጣን ደግሞ ይከስሰው ዘንድ ከኢያሱ በስተቀኝ ቆመ (ከራእይ 12፡10 ጋር አመሳክር።) እግዚአብሔር አብ ዳኛ ሲሆን፥ የተከሰሰው ደግሞ ሕዝቡን የሚወክለው ኢያሱ ነበር። ተሟጋች ዓቃቤ ሕጉም ሰይጣን ነበር። (መጽሐፍ ቅዱስ የወንድሞች ከሳሽ ሲል ይጠራዋል።) ሰይጣን በጉዳዩ አሸናፊ ይመስል ነበር። ይሁንና፥ ኢያሱ በእግዚአብሔር ቀኝ የሚቆም ጠበቃ ነበረው፤ ይህም ሁኔታውን ለወጠው። ክርስቶስ ለኢያሱ የልብስ ልዋጭ በማቅረብ የሰይጣንን ክስ ዝም አሰኘ።

ኢየሱስ ክርስቶስ «ጠበቃችን» ሲባል አሳቡ ይኼ ነው። እርሱ አማኞችን በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ይወክላል፤ *መሥዋዕቱ* ደግሞ የአማኙን ኃጢአት ያስተሰርያል። ክርስቶስ ለሕዝቡ *ስለሞተ*፥ የእግዚአብሔርን የጽድቅ *ሥራ* ፈጽሟል። («የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው።») በእግዚአብሔር ቀኝ ስለ እኛ *ስለሚቆም*፥ ዕለት በዕለት *መሥዋዕትነቱን* ለጉድለታችን ሊያቀርበው ይችላል።

ከእኛ የሚፈለገው ነገር ቢኖር በምንወድቅበት ጊዜ ኃጢአታችንን እንድንናዘዝ ብቻ ነው።

«መናዘዝ» ማለት ምን ማለት ነው? ኃጢአትን *መናዘዝ* ማለት ኃጢአታችንን «ከመቀበል» የላቀ ነው። *ኑዛዜ* ማለት «[ስለ አንድ ነገር] ተመሳሳይ ነገር መናገር» ማለት ነው። ስለሆነም፥ ኃጢአትን መናዘዝ ማለት እግዚአብሔር ስለዚያ ኃጢአት የሚለውን ተመሳሳይ ነገር መድገም ማለት ነው።

አንድ አማካሪ በወንጌል ስብሰባ ወቅት ወደፊት የመጣውን ሰው ለመርዳት እየሞከረ ነበር። ሰውዬው «እኔ ክርስቲያን ነኝ፤ ዳሩ ግን በሕይወቴ ውስጥ ኃጢአት ስላለ እርዳታ እፈልጋለሁ» አለ። አማካሪው 1ኛ ዮሐንስ 1፡9ን አሳየውና ሰውዬው ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር እንዲናዘዝ ነገረው።

ሰውዬውም፥ «አባት ሆይ፥ አንድ ነገር አጥፍቼ እንደሆነ...»ብሎ ጀመረ። በዚህ ጊዜ አማካሪው አቋርጦት፥ «ቆይ አንድ ጊዜ፥ እኔንም ወደ ኃጢአትህ አትጨምረኝ። ወንድሜ፥ ‹እንደሆነ› ወይም ‹እኛ› ብሎ ነገር አይሠራም፤ ጉዳይህን ከእግዚአብሔር ጋር መጨረስ አለብህ!» አለው።

አማካሪው አልተሳሳተም።

ኑዛዜው ግሩም ጸሎት ማድረግ፥ ወይም ሃይማኖታዊ ማመኻኛ ማቅረብ፥ ወይም እግዚአብሔርንና ሌሎች ክርስቲያኖችን ለማስደነቅ መሞከር አይደለም። ኑዛዜ ኃጢአትን እግዚአብሔር በሚጠራው ስም መጥራት ነው– ቅንዓት፥ ጥላቻ፥ ምኞት፥ ማታለል፥ ወይም ሌላ። መናዘዝ ማለት ለራሳችንና ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን ማለት ነው፤ ሌሎችም ከተካተቱበት ከእነርሱም ጋር ታማኝ መሆን። ይህም ኃጢአትን ከመቀበል የላቀ ነው። በኃጢአት ላይ መፍረድና ፊት ለፊት መጋፈጥ ማለት ነው።

ኃጢአታችንን ስንናዘዝ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚለን ቃል ገብቶልናል (ቁጥር 9)። ይሁንና፥ የተስፋ ቃል የእግዚአብሔርን ቃል እንድንተላለፍ በር አይከፍትልንም!

አንድ ተማሪ በትምህርት ቤቱ የመንፈሳዊ ጉዳዮች ኃላፊ ለሆነው ወንድም «ተመልሼ ከእግዚአብሔር ይቅርታ ልጠይቅ እንደምችል ስለማውቅ፥ ኃጢአት ሠርቼ መጣሁ» አለው።

ኃላፊውም ወደ 1ኛ ዮሐንስ 1፡9 እያመለከተ፥ «እግዚአብሔር ይቅር ሊልህ የሚችለው ምን ላይ ተመሥርቶ ነው?» ሲል ጠየቀው።

ልጁም፥ «እግዚአብሔር የታመነና ጻድቅ ነው» አለው።

ኃላፊውም፥ «እነዚያ ሁለቱ ቃላት ከኃጢአት ሊጠብቁህ ይገባ ነበር። ኃጢአትህን ይቅር ለማለት ከእግዚአብሔር ምን እንደሚጠበቅበት ታውቃለህ?» ሲል ጠየቀው።

ልጁ አንገቱን አቀረቀረና፥ «ኢየሱስ የግድ ሊሞትልኝ ያስፈልግ ነበር» አለ።

ከዚያም ኃላፊው ወደ ነጥቡ አመራ። «ልክ ነህ። ይቅርታ እግዚአብሔር የሚፈጽመው ቀላል ተግባር አይደለም። እግዚአብሔር ለተስፋ ቃሉ የታመነና ጻድቅ የሆነው ክርስቶስ ለኃጢአቶችህ ስለሞተና የቅጣትህን ዋጋ ስለ ከፈለ ነው። እንግዲህ፥ በሚቀጥለው ጊዜ ኃጢአት ለመሥራት ስታቅድ ታማኝና አፍቃሪ በሆነ አምላክ ላይ ኃጢአት እንደምትሠራ አስታውስ!» አለው።

በመሠረቱ፥ ማንጻት ሁለት ጎኖች አሉት፤ እነዚህም የሕግን ችሎት ፊትና ግላዊ ማንጻትን የሚያመለክቱ ናቸው። በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ከኃጢአት በደል ነፃ በማውጣት፥ በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ አቋም (ጽድቅ) ይሰጠናል። የኢየሱስ ሞት ቅዱስ ሕጉን ስለፈጸመው እግዚአብሔር ይቅር ይለናል።

በተጨማሪ፥ እግዚአብሔር የኃጢአተኛውን ውስጣዊ ሕይወት ለማንጻት ይፈልጋል። ዳዊት፥ «አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ» ሲል ጸልዮአል [መዝ. (51)፥10]። ኑዛዜአችን እውነተኛ ሲሆን፥ እግዚአብሔር በመንፈስና በቃሉ አማካኝነት ተግባሩን ያከናውናል (ዮሐ. 15፡3)። በልባችን የማንጻትን ተግባር ይፈጽማል (1ኛ ዮሐ. 1፡9)።

ንጉሥ ዳዊት የፈጸመው ትልቅ ጥፋት ኃጢአቶቹን ከመናዘዝ ይልቅ ለመሸፋፈን መሞከሩ ነበር። ምናልባትም ለአንድ ዓመት ያህል በማታለልና በሽንፈት ኖሮአል። ስለሆነም፥ ሰው በምቹ ጊዜ መጸለይ እንዳለበት መግለጹ አስገራሚ አይደለም [መዝ. (32)፥6]።

ኃጢአታችንን መናዘዝ የሚኖርብን መቼ ነው? *ወዲያውኑ ኃጢአት ውስጥ እንደወደቅን ስናውቅ!* «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል» (ምሳ. 28፡13)። በብርሃኑ በመመላለስ በሕይወታችን ውስጥ ያለውን «ቆሻሻ» ልንመለከትና ወዲያውኑ ልናስወግደው እንችላለን።

ይህም ኃጢአትን ለማስወገድ ወደሚረዳን ሦስተኛ መንገድ ይመራናል፤ ለመሸፋፈን ልንጥርም ሆነ ልንናዘዝ እንችላለን፤ ወይም ደግሞ

3. *ኃጢአታችንን ልናሸንፍ እንችላለን።*

ዮሐንስ ክርስቲያኖች ኃጢአት መሥራት እንደሌለባቸው በግልጽ ይናገራል። «*ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ*» (1ኛ ዮሐ. 2፡1)።

በኃጢአት ላይ ድልን የመቀዳጀቱ ምሥጢር የሚገኘው «በብርሃን ተመላለሱ» በሚለው ሐረግ ውስጥ ነው (1፡7)።

በብርሃን መመላለስ ማለት ግልጽ፥ እውነተኛና ታማኝ መሆን ማለት ነው። ጳውሎስ ወዳጆቹ፥ «ቅኖችና ያለ ነውር» እንዲሆኑ ጸልዮአል (ፊልጵ. 1፡10)። ታማኝነት (በእንግሊዝኛው ‹ስንሲር›) «ሳይን» እና «ሲራ» ከሚባሉ ሁለት የላቲን ቃላት የተገነባ ሲሆን ፍችውም «ያለሰም» ማለት ነው። በሮም መንግሥታት፥ አንዳንድ ሐውልት ሠሪዎች የተበላሹባቸውን የተቀረጸ ድንጋይ ማጣበቂያዎች በሰም ሸፍነው ያልፉ ነበር፤ ይህም ወደ በኋላ ሐውልቱ ለፀሐይ ሙቀት እስኪገለጥ ለጊዜው አያስታውቅም ነበር። ይሁንና፥ በጣም አስተማማኝ የሐውልት ሠሪዎች የሚሠሩአቸው ሐውልቶች «ሳይን

ሲራ» ማለትም ያለ ስም መሆናቸውን ደንበኞቻቸው እንዲያውቁላቸው ያደርጉ ነበር።

አብያተ ክርስቲያናትና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች በእግዚአብሔር ብርሃን ተፈትኖ የማለፍ ሕይወት በሌላቸው ታማኝ ባልሆኑ ሰዎች መሞላታቸው አሳዛኝ ነገር ነው። «እግዚአብሔር ብርሃን» በመሆኑ፥ በብርሃኑ ስንመላለስ ልንደብቅ የምንችለው ምንም ነገር የለም። ግልጽና ታማኝ ሆኖ ለማስመሰል የማይሞክር ክርስቲያን ማግኘቱ የሚያጽናና ነገር ነው።

በብርሃን መመላለስ ማለት ለእግዚአብሔር፥ ለራሳችንና ለሌሎች ታማኝ መሆን ነው። ብርሃኑ ኃጢአታችንን በሚገልጽልን ጊዜ ወዲያውኑ ለእግዚአብሔር ተናዝዞ ይቅርታውን መቀበል ማለት ነው። ኃጢአታችን ሌላውን ሰው ሲጎዳው እርሱን ደግሞ ይቅርታ እንዲያደርግልን እንጠይቃለን።

በብርሃኑ መመላለስ ሌላም አሳብ ይጨምራል። ይኸውም የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ ነው (1ኛ ዮሐ. 2:3፥4)። «ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው» [መዝ. (119)፡105]። በብርሃን መመላለስ በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ጊዜ በማሳለፍ ፈቃዱን ማወቅና ከዚያም የነገረንን ሁሉ መታዘዝ ነው።

ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዛችን እርሱን መውደዳችንን ያረጋግጣል። ለመታዘዝ የሚያነሣሱ ሦስት ዓላማዎች አሉ። *ግዴታችን ስለሆነ፥ አስፈላጊያችን ስለሆነ፥ ወይም እኛው በፍላጎታችን ልንታዘዝ* እንችላለን።

*አንድ ባሪያ የሚታዘዘው ግዴታው ስለሆነ ነው።* ካልታዘዘ መቀጣቱ የማይቀር ነው። አንድ በደመወዝ የተቀጠረ ሠራተኛ የሚታዘዘው *መታዘዝ ስለሚያስፈልገው* ነው። በሥራው ላይደሰት ቢችልም፥ ደመወዙን ለመቀበል ደስ ይሰኛል! ሠርቶ በሚያገኘው ገንዘብ ቤተሰቡን መመገብና ማልበስ ስለሚኖርበት መታዘዝ ያሻዋል። ክርስቲያን ግን ሰማያዊ አባቱን የሚታዘዘው ስለሚፈልግ ነው፤ ይህም የሆነው በእርሱና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት የፍቅር ስለሆነ ነው። «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» (ዮሐ. 14፡15)።

ልጆች ሳለን መታዘዝን የተማርነው በዚህ መንገድ ነበር። በመጀመሪያ፥ *ግዴታችን በመሆኑ* ታዘዝን። ባንታዘዝ እንገረፋለን! እያደግን ስንመጣ ግን መታዘዝ ደስታና ሽልማት መሆኑን ተረዳን፤ ስለሆነም በሕይወታችን የተወሰኑ ጉድለቶችን ስለሚሞላልን መታዘዝ

ጀመርን። ከፍቅር የተነሣ መታዘዝ መጀመራችን ደግሞ የእውነተኛ ብስለት ምልክት ነበር።

«አዲስ ክርስቲያኖች» ይታዘዙ ዘንድ ባለማቋረጥ ማስጠንቀቅ ወይም መሸለም ያሻል። በሳል ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው እርሱን ስለሚወዱት ብቻ ይታዘዛሉ።

በብርሃን መመላለስ እውነተኛነትን፥ ታዛዥነትንና ፍቅርን ያካትታል፤ እንዲሁም የክርስቶስን ምሳሌ ይዞ የእርሱን ፈለግ መከተልን ያካትታል (1ኛ ዮሐ. 2፡6)። በመሠረቱ፥ ማንም ሰው የክርስቶስን ምሳሌ በመከተል ክርስቲያን አይሆንም፤ ይሁንና፥ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ከመጣን በኋላ ስለምንኖርበት ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አንድ ታላቅ ምሳሌ አድርገን ልንከተለው ይገባል።

ይህም «በክርስቶስ መኖር» ማለት ነው። ክርስቶስ የኃጢአታችን ማስተሰሪያ (ወይም መሥዋዕት) (ቁጥር 2) እና በእግዚአብሔር ፊት የሚወክለን ጠበቃችን (ቁጥር 1) ብቻ ሳይሆን፥ ለዕለታዊ ሕይወታችንም ፍጹም የሆነ ምሳሌአችን ነው (እርሱ «ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ» ነው።)

በዚህ ስፍራ ቁልፍ ቃል «በእርሱ እንዳለ» የሚለው ነው (ቁጥር 6)። «እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ በዚህ ዓለም ነንና» (4፡17)። «እርሱ በብርሃን እንዳለ» በብርሃን ልንመላለስ ይገባል (1፡7)። «እርሱ ንጹሕ እንደሆነ» ራሳችንን ልናነጻ ይገባል (3፡3)። «እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው» (3፡7)። በብርሃን መመላለስ ማለት በዚህ ምድር ላይ ኢየሱስ በኖረበትና አሁንም በሰማይ ባለበት መንገድ መኖር ማለት ነው።

ይህ በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ ተግባራዊ ተዛምዶ አለው። ለምሳሌ፥ የሌላው ኃጢአት ሲበድለው የአማኝ ምላሽ ምን ሊሆን ይገባል? መልሱ እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ይቅር እንዳላቸው አማኞች ይቅር ሊባባሉ ይገባል ነው (ኤፌ. 4፡32ን ከቆላስይስ 3፡13 ጋር አመሳክር)።

በብርሃን መመላለስ ማለትም የክርስቶስን ምሳሌ መከተል በቤተሰብ ውስጥም ለውጥ ያስከትላል። ባሎች «ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት» ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ ተነግሮአቸዋል (ኤፌ. 5፡25)። «ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት» ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲንከባከቡ ተነግሮአቸዋል (5፡29)። ሚስቶች ደግሞ ባሎቻቸውን እንዲያከብሩና እንዲታዘዙ ተነግሮአቸዋል (5፡22-24)።

በየትኛውም የሕይወት ክፍል ኃላፊነታችን የኢየሱስ ምሳሌነት መከተል ነው። «እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና።» እርሱ እንደተመላለሰ ልንመላለስ ይገባል።

እንደ ሰብአዊ ፍጥረት ባለችን ደካማ ማንነት የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት በምሳሌነት ልንከተል አንችልም። ጥረታችንም በእግር ኳስ ሜዳ ውስጥ እንደ ዝነኛ ተጨዋች ሊታይ ከሚፈልግ የአካል ጉዳተኛ ተነጥሎ አይታይም፤ የአካል ጉዳተኛው ላደረገው ጥረት «ድንቅ ነው» የሚል ማበረታቻ እንሰጠው ይሆናል። እርሱ ግን ከጥረቱ ወደኋላ ይቀራል። ለዚህ ነው ዮሐንስ «ኑሩ» የሚል ቃል የሚጠቀመው (1ኛ ዮሐ. 2:6)። ክርስቶስ እንደተመላለሰ የምንመላለስበት ብቸኛው መንገድ በእርሱ መኖር ነው።

ይህ በኃጢአት ድል የማግኛ ምሥጢር ነው።

ኢየሱስ ራሱ በእርሱ መኖር ምን እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ተናግሮአል። በወይኑና በወይን ቅርንጫፎቹ ምሳሌነት ነበር አሳቡን ያብራራላቸው (ዮሐ. 15)። ቅርንጫፍ ከወይኑ ግንድ ጋር አብሮ በመኖር ሕይወትን እንደሚያገኝ ሁሉ፥ አማኞችም ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ኅብረት በመጠበቅ ጥንካሬ ያገኛሉ።

በክርስቶስ መኖር ማለት ለእርሱ ለመኖርና እርሱን ለማገልገል በሚያስፈልገን ሁሉ ሙሉ ለሙሉ በእርሱ ላይ መደገፍ ማለት ነው። ይህ ሕያው ግንኙነት ነው። እርሱ በእኛ በኩል ሕይወቱን ሲኖር፥ እኛም ምሳሌነቱን መከተልና እርሱ እንደተመላለሰ ልንመላለስ እንችላለን። ጳውሎስ፥ «ክርስቶስ... በእኔ ይኖራል» ሲል ይህንኑ ሁኔታ በፍጹምነት ይገልጸዋል (ገላ. 2:20)።

ይህ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ያመለክታል። ክርስቶስ ኃጢአት በምንሠራበት ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ይወክለን ዘንድ በሰማይ ጠበቃችን ነው (1ኛ ዮሐ. 2:1)። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እዚህ በምድር ላይ ለእኛ የእግዚአብሔር ጠበቃ ነው። ክርስቶስ ስለ እኛ ሲማልድ (ሮሜ 8:34)፥ መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ ስለ እኛ ይማልዳል (8:26-27)። እኛ ግሩም «ሰማያዊ ስልክ አለን» ይኸውም፥ እግዚአብሔር ወልድ ስለ እኛ በሰማይ ሲማልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ሆኖ ስለ እኛ ስለሚቃትት ነው። እኛ በወልድ አማካኝነት ከአብ ጋር ግንኙነት አለን፤ አብም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከእኛ ጋር ግንኙነት አለው።

ክርስቶስ በእኛ ውስጥ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት በእኛ ሕይወቱን ይገልጻል። በክርስቶስ ውስጥ

የምንኖረውና እንደ እርሱ የምንመላለሰው በኩረጃ ሳይሆን፥ በተሠግዎ ነው፤ በመንፈሱ አማካኝነት ክርስቶስ በእኛ ይኖራል። በብርሃን መመላለስ በመንፈስ ቅዱስ እንጂ የሥጋን ምኞት በመፈጸም አይደለም (ከገላትያ 5፡16 ጋር አመሳክር)።

እግዚአብሔር ኃጢአትን ልናሸንፍ የምንችልባቸውን መንገዶች አዘጋጅቶልናል። አብሮን የተወለደውን የኃጢአት ተፈጥሮ ልንለውጥ ወይም ልናጠፋው አንችልም (1ኛ ዮሐ. 1፡8)፤ ዳሩ ግን ምኞቶቹን መፈጸም የለብንም። በብርሃን ስንመላለስና የኃጢአትን ትክክለኛ ምንነት ስንመለከት፥ እንጠላውና ከዚያ ዘወር እንላለን። ኃጢአት ብናደርግ ግን ወዲያውኑ ለእግዚአብሔር ተናዝዘን ማንጻቱን እንቀበላለን። በውስጣችን በሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመደገፍ በክርስቶስ እየኖርን እርሱ እንደተመላለሰ እንመላለሳለን።

ይሁንና፥ ይህ ሁሉ የሚጀምረው በሰዎችና በእግዚአብሔር ፊት ግልጽና እውነተኛ ከመሆን ነው። ልናስመስልና ሌሎችን ለማስደነቅ ትወና በምንጀምርበት ጊዜ ከብርሃኑ ወደ ጨለማ እንሻገራለን። ሰር ዎልተር ስኮት ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላሉ፡–

«ማታለል የጀመርን ዕለት
አቤት፥ የድሩ ውስብስብነት!»

እውነተኛ ሕይወት በማታለያ ነገሮች ላይ ሊመሠረት አይችልም። በብርሃኑ ከመመላለሳችን በፊት፥ ራሳችንን ልናውቅ፥ ራሳችንን ልንቀበልና ራሳችንን ለእግዚአብሔር ልናስረክብ ይገባል። እግዚአብሔር ማንነታችንን ቀደም ብሎ ስለሚያውቅ ሌሎችን ለማታለል መጣሩ ሞኝነት ነው።

ይህ ሁሉ በብርሃን መመላለስ ለምን ሕይወትን ቀላልና አስደሳች እንደሚያደርግ ለማብራራት ያግዛል። በብርሃን ስትመላለስ የምትኖረው አንዱን አካል ብቻ ለማስደሰት ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔርን ነው። ይህም ነገርን ሁሉ ያቃልላል። ኢየሱስ፥ «እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና» ብሏል (ዮሐ. 8፡29)። በብርሃን ልንመላለስና እግዚአብሔርን ደስ ልናሰኝ ይገባል (1ኛ ተሰ. 4፡1)። ራሳችንንና እግዚአብሔርን ለማስደሰት ብንኖር፥ ይህ ሁለት ጌቶችን ለማገልገል መሞከር ስለሆነ ከዳር ሊደርስ አይችልም። ሰዎችን ለማስደሰት ብንኖር ደግሞ፥ ሁለት ሰዎች በሁሉም ነገር ስለማይስማሙ ከመሀል ስንጎሰም እንኖራለን። በብርሃን መመላለስና እግዚአብሔርን ለማስደሰት መኖር–ዓላማዎቻችንን በማቃለልና ሕይወታችንን ፈር በማስያዝ ሰላምንና የተረጋጋ አኗኗርን ያለማምደናል።

ዮሐንስ እውነተኛ የሆነ ሕይወት ኃጢአትን እንደማይወድ ይገልጻል። እውነተኛ አማኝ በመሸፈን ፈንታ ኃጢአቱን በመናዘዝና

በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን በመመላለስ ለማሸነፍ ይሞክራል። ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚሄድ በማወቁ ብቻ አይረካም። ይልቁንም፥ ሰማያዊውን ሕይወት አሁኑኑ በዚህ ምድር ላይ ለመኖር ይፈልጋል። «እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ በዚህ ዓለም እንዲሁ ነንና።» እርሱ ቃሉንና አካሄዱን ላለመነጣጠል ይጠነቀቃል። እርሱ በብዙ «አፋዊ» ውትወታ ራሱን ለማስደነቅ አይሞክርም።

ጉባኤው በስብሰባው መዝጊያ ላይ «ላንተ እጸልያለሁ» እያለ ይዘምራል። ሰባኪው ከመድረኩ አካባቢ ወደ ነበረው ሰውዬ ዘወር አለና «ለማን ነው የምትጸልየው?» ሲል ጠየቀው።

ሰውዬው ግራ ተጋብቶ ዝም አለ። ከዚያም፥ «እንጃ፥ እኔ ለማንም እየጸለይሁ አይመስለኝም» በማለት መለሰ።

ሰባኪውም፥ «ላንተ እጸልያለሁ» ስትል ስለሰማሁ እውነትህን መስሎኝ ነው» አለው።

«የለ የለም...ዝም ብዬ እየዘመርሁ ነኝ» አለ። የተደናገረው ሰውዬ።

የማይጠቅም ሃይማኖታዊ ንግግር! የቃላት ሃይማኖት ብቻ! ያዕቆብ 1:23ን በነፃ ትርጉም ስናስቀምጠው፥ «ቃሉን የምንፈጽምና ስለ ቃሉ የምንናገር እንሁን» የሚል ይሆናል። የምንናገረውን ቃል መኖር አለብን። ቃላቱን ማወቅ ብቻውን በቂ አይደለም፤ ሕይወቱንም መኖር አለብን። ከተናገርን በዚያው መሠረት ልንኖር ይገባል።

# አዲስና አሮጌ

## 1ኛ ዮሐንስ 2፡7-11

ዮሐንስ እውነተኛ የሆነውን ሕይወት ሲገልጽ፥ በተደጋጋሚ ሦስት ቃላት ይጠቀማል፤ እነዚህም፥ *ሕይወት፥ፍቅርና ብርሃን* ናቸው። እንዲያውም፥ ለክርስቲያን ፍቅር ርእሰ-ጉዳይ የደብዳቤውን ሦስት ክፍሎች ተጠቅሟል። ዮሐንስ ፍቅር፥ ሕይወትና ብርሃን ጎን ለጎን እንደሚሄድ ይገልጻል። እነዚህን ሦስት ክፍሎች (2፡7-11፤ 3፡10-24 እና 4፡7-21) ለብቻቸው አንብብና ፍቅር፥ ሕይወትና ብርሃን ሊነጣጠሉ እንደማይገባ ትረዳለህ።

በአሁኑ ጊዜ ጥናታችን (2፡7-14)፥ የክርስቲያን ፍቅር *በብርሃንና በጨለማ* ተጽዕኖ እንደሚደርስበት እንማራለን። በብርሃን የሚመላለስ (ማለትም እግዚአብሔርን የሚታዘዝ) ክርስቲያን ወንድሙን ይወዳል። በ1ኛ ዮሐንስ 3፡10-24፥ የክርስቲያን ፍቅር *የሕይወት ወይም የሞት* ጉዳይ እንደሆነ ተነግሮናል፤ ይህም በጥላቻ መኖር ማለት በመንፈሳዊ ሞት መኖር በመሆኑ ነው። በ1ኛ ዮሐንስ 4፡7-21፥ የክርስቲያን ፍቅር *የእውነትና የስሕተት* ጉዳይ እንደሆነ እንመለከታለን (ከ4፡6 ጋር አወዳድር)፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር *በማወቅ* የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች *ስለምናሳይ* ነው።

በእነዚህ ሦስት ክፍሎች ክርስቲያኖች ለምን እርስ በርሳቸው ሊዋደዱ እንደሚገባ ሦስት ምክንያቶችን እናገኛለን።

1. እግዚአብሔር እንድንዋደድ አዝዞናል (2፡7-11)

2. ከእግዚአብሔር ስለ ተወለድን የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ውስጥ አለ (3፡10-24)።

3. እግዚአብሔር *መጀመሪያ* ፍቅሩን ገልጾልናል (4፡7-21)። «እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን!»

ዮሐንስ ስለ ፍቅር መጻፍ ብቻ ሳይሆን በሕይወቱም ይለማመደዋል። ለተደራስያኑ ከሚሰጣቸው ውድ ስሞች አንዱ «ወንድሞች» የሚለው ነው። ለአንባቢዎቹ የፍቅር ስሜት ነበረው። ዮሐንስ በወንጌሉና በመልእክቶቹ ለፍቅር ርእሰ-ጉዳይ እንዲህ የላቀ ስፍራ ስለሚሰጥ «የፍቅር ሐዋርያ» ተብሎ ይታወቃል። ይህም ሆኖ፥ ዮሐንስ ሁልጊዜም «የፍቅር ሐዋርያ» አልነበረም። በአንድ ወቅት ኢየሱስ ለዮሐንስና እንደ እርሱው ሁሉ ተናዳጅ ለነበረው ወንድሙ

ለያዕቆብ «ቦአኔርጌስ» የሚል የቅጽል ስም ሰጥቶአቸው ነበር– «የነጎድጓድ ልጆች» ለማለት ነበር (ማር. 3፡17)። በሌላ አጋጣሚ እነዚህ ሁለቱ ወንድማማቾች አንዲት መንደር ለማጥፋት እሳት ከሰማይ ሊያወርዱ ፈልገው ነበር (ሉቃስ 9፡51–56)።

አዲስ ኪዳን የተጻፈው በግሪክ ስለነበር፥ ጸሐፊዎቹ ብዙውን ጊዜ ይበልጥ አሳቡን በውስንነት የሚገልጽ ቃል ለመጠቀም ይችሉ ነበር። የአማርኛው ቃል አንዳንዴ ፍቅር፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ መውደድ በሚል ተተርጉሞአል። በ1ኛ ዮሐንስ ስለ «ፍቅር» የተጻፈውን ስናነብ የግሪኩ ቃል «አጋፔ» የሚል ነው፤ ይህም እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅር፥ ክርስቲያን ለሌሎች ክርስቲያኖች ያለውን ፍቅርና እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ያለውን ፍቅር የሚያሳይ ቃል ነው (ኤፌ. 5፡22–33)።

በሌላ ስፍራ ለፍቅር የተሰጠው የግሪክ ቃል «ፊሊያ» «የጓደኝነት መዋደድ» የሚል አሳብ አለው፤ ይህም የአጋፔን ፍቅር ያህል የጠለቀ ወይም መለኮታዊ አይደለም። (ለጾታዊ ፍቅር የሚያገለግለው የግሪኩ «ኢሮስ» በአዲስ ኪዳናችን ውስጥ አልተጻፈም።)

የሚያስደንቀው የክርስቲያን ፍቅር አሮጌም አዲስም መሆኑ ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡7፥8)። ይህ እርስ በርሱ የሚቃረን አሳብ ይመስላል። በመሠረቱ፥ ፍቅር ራሱ አዲስ ወይም ትእዛዝ አይደለም፤ ሰዎች እግዚአብሔርን መውደዳቸው አዲስ ነገር አይደለም። ኢየሱስ ራሱ ሁለት የብሉይ ኪዳን ትእዛዛትን ዘዳግም 6፡5ን እና ዘሌዋውያን 19፡18ን– አንድ ላይ አዋህዶ፥ እነዚህ ሁለቱ ትእዛዛት ሕግንና ነቢያትን ሁሉ እንደሚያጠቃልሉ ተናግሯል (ማር. 12፡28–34)። እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራን መውደድ ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት የሚታወቁ ጥንታዊ አባባሎች ነበሩ።

እንግዲህ፥ «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» (1ኛ ዮሐ. 2፡8) የምትለው ትእዛዝ «አዲስ» የምትሆነው በምን መልኩ ነው? አሁንም የግሪኩን ቃል ማየቱ መልስ ለመስጠት ይረዳናል።

ግሪኮች «አዲስ» ለሚለው ሁለት የተለያዩ ቃላት ነበሩአቸው። አንደኛው «በጊዜ አዲስ» ሲሆን፥ ሁለተኛው «በጥራት አዲስ ነው»። ለምሳሌ፥ የመጀመሪያው ዘመናዊ ሆኖ፥ የተሠራውን አዲስ የተለመደ ቶዮታ መኪና ለመግለጽ ሊያገለግል ይችላል፤ ዳሩ ግን በፊት ያልታወቀና በብዙ መንገድ የተሻሻለ መርቼዲስ መኪና ብትገዛ ሁለተኛውን ቃል ልትጠቀም ትችላለህ– በጥራት አዲስ ለማለት።

እርስ በርስ ስለ መዋደድ የተሰጠው ትእዛዝ አዲስ የሆነው በጊዜ ሳይሆን በባሕርዩ ጥራት ነው። ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ፥ እርስ በርስ ስለመዋደድ የሚናገረው አሮጌ ትእዛዝ አዲስ ትርጉም ይዞአል። በነዚህ አምስት አጫጭር ቁጥሮች (ቁጥር 7–11) ውስጥ ትእዛዙ በሦስት አስፈላጊ መንገዶች አዲስ እንደሆነ እንመለከታለን።

## 1. በአጽንኦት አዲስ ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡7)።

በቀደመው አንቀጽ (ቁጥር 3–6) ዮሐንስ ስለ «ትእዛዛት» በአጠቃላይ መልኩ ሲናገር የነበረ ሲሆን፥ አሁን ግን ትኩረቱን *በአንድ ተነጣይ ትእዛዝ* ላይ ያሳርፋል። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝቦች እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ የሚናገረው ትእዛዝ *ከብዙዎቹ* ትእዛዛት አንድ ብቻ ነበር፤ አሁን ግን ይህ የድሮ ትእዛዝ ተመርጦ የበላይነት ስፍራ ተሰጠው።

አንድ ትእዛዝ ከሌሎች ሁሉ በላይ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? ይህ ፍቅር የእግዚአብሔር ሕግ ፍጻሜ ከመሆኑ እውነታ አንጻር ተብራርቷል (ሮሜ 13፡8–10)።

ከሕግ አኳያ ወላጆች ለልጆቻቸው እንክብካቤ ማድረግ አለባቸው። ልጅን ችላ ማለት የከፋ ወንጀል ነው። ይሁንና፥ ጠዋት ጊዜው እየረፈደ ሳለ የሚከተለውን ዓይነት ውይይት የሚያደርጉ ስንት ወላጆች ይኖራሉ?

ሚስት፡– «የእኔ ውድ፥ ብትነሣና ወደ ሥራ ብትሄድ ይሻላል። መታሰር አላማረንም።»

ባል፡– «ልክነሽ፤ አንቺም ብድግ ብለሽ ለልጆቹ ቁርሳቸውን ስጪአቸው፤ ልብሳቸውንም አልብሺአቸው። ምናልባት ፖሊሶች መጥተው እስር ቤት እንዳይከቱን...»

ሚስት፡– «ልክ ብለሃል። ልጆች፥ የሕጉ መኖር መልካም ነው፤ አለበለዚያ ግን ተኝተን ልንውል እንችል ነበር።»

ብዙውን ጊዜ ሠርቶ ለማደር ወይም ለልጆች እንክብካቤ ለማድረግ ሕግ አነሣሽ ምክንያት መሆኑ አጠራጣሪ ነው። ወላጆቹ እርስ በርሳቸው ስለሚዋደዱና ልጆቻቸውን ስለሚወዱ (አንዳንዶ ሊያማርሩ ቢችሉም)፥ ኃላፊነቶቻቸውን ይወጣሉ። ለእነርሱ ትክክለኛውን ነገር ማድረግ የሕግ ጉዳይ ሳይሆን፥ *የፍቅር ጉዳይ* ነው።

«እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው ትእዛዝ የእግዚአብሔር ሕግ ፍጻሜ የሚሆነው በዚህ መልኩ ነው። ሰዎችን ስትወድ ስለ እነርሱ

ልትዋሽም ሆነ ከእነርሱ ልትሰርቅ አትችልም። ልትገድላቸውም አትሻም። እግዚአብሔርንና ሌሎችን መውደድ አንድ ሰው *ሳያስብ እንኳ* የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲፈጽም ያደርጋል! አንድ ሰው በክርስቲያን ፍቅር ተነሣሥቶ አንድ ተግባር ሲያከናውን በፍርሃት ሳይሆን በፍቅር እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሌሎችን ያገለግላል።

ለዚህ ነው ዮሐንስ «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው አዲስ ትእዛዝ እንደሆነ የተናገረው፤ *አዲስ የሆነውም በአጽንኦት ነው።* በመሆኑም ይህ ከዝርዝሩ ላይ የመጀመሪያውን ስፍራ የሚይዝ የትእዛዛት ቁንጮ እንጂ፥ ተራ ትእዛዝ አይደለም።

ይህም ሆኖ፥ ይህ ትእዛዝ በሌላም አቅጣጫ በአጽንኦት አዲስ ነው። ይህም በክርስትና ሕይወት የቀዳሚነቱን ስፍራ ስለሚይዝ ነው። «ከመጀመሪያ የነበረቻችሁ አሮጌ ትእዛዝ እንጂ የምጽፍላችሁ አዲስ ትእዛዝ አይደለችም» (1ኛ ዮሐ. 2፡7)። ይህ «ከመጀመሪያ» የሚለው ቃል በዮሐንስ መልእክት ውስጥ በሁለት የተለያዩ መንገዶች የተጠቀሰ ሲሆን፥ ሁለቱንም መለየቱ ጠቃሚ ነው። በ 1ኛ ዮሐንስ 1፡1፥ የክርስቶስን ዘላለማዊነት በመግለጽ «ከመጀመሪያው» እንደነበረ ያስረዳናል። ከዚህ አሳብ ጋር በሚዛመደው በዮሐንስ ወንጌል 1፡1፥ «በመጀመሪያ ቃል ነበር» የሚል እናነባለን።

ይሁንና፥ በ 1ኛ ዮሐንስ 2፡7 ርእሰ-ጉዳዩ *የክርስትና ሕይወት ጅማሬ* ነው። እርስ በርሳችን እንድንዋደድ የተሰጠን ትእዛዝ እግዚአብሔር በኋላ አስታውሶ ያከለልን የክርስትና ሕይወታችን ተጨማሪ ልምምድ አይደለም። ይልቁንም፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንን ጊዜ አንሥቶ በልባችን የኖረ ነው። ይህማ ባይሆን፥ ዮሐንስ «እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እናውቃለን» ብሎ ሊጽፍ አይችልም ነበር (3፡14)። ኢየሱስም፥ «እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ» ብሏል (ዮሐ. 13፡35)።

ያልዳነ ሰው በተፈጥሮው ራስ-ወዳድና በጥላቻ የተሞላ ሊሆን ይችላል፥ አዲስ የተወለደ ሕፃን በጣም የምንወደውን ያህል፥ እርሱ በበኩሉ ራስ-ወዳድና ጠቅላላው ዓለም ከትንሽዬ አልጋው ዙሪያ እንደሚሽከረከር አድርጎ እንደሚያስብ ማስታወስ አለብን። ሕፃኑ ደኅንነት ካላገኘው ሰው ጋር ይመስላል። «እኛ ደግሞ አስቀድመን የማናስተውል ነበርንና፥ የማንታዘዝ፥ የምንስት፥ ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ እንደ ባሪያዎች የምንገዛ፥ በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር፥ የምንጣላ፥ እርስ በርሳችን የምንጠላላ ነበርን» (ቲቶ 3፡3)። ይህ ግልጽ የዓለማውያን ባሕርይ ውብ ነው ባይባልም፥ በትክክል ያለ ነገር ነው።

አንዳንድ ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ላያደርጉ ቢችሉም፥ የሥጋ ፍሬዎች ሁልጊዜም በባሕርያቸው ውስጥ አሉ (ገላ. 5:19–21)።

አንድ ሰው በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ አዲስ ሕይወትና አዲስ ባሕርይ ይቀበላል። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ዘንድ ለመኖር ይመጣል፤ የእግዚአብሔርም ፍቅር በመንፈሱ አማካኝነት በልቡ ውስጥ ይፈስሳል (ሮሜ 5:5)። እግዚአብሔር ለአዲስ አማኝ ስለ ፍቅር ረዥም ገለጻ ማድረግ አያስፈልገውም! «እናንተ ራሳችሁ (በውስጣችሁ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት) እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና» (1ኛ ተሰ. 4:9)። አንድ አዲስ አማኝ ሲወደው የነበረውን ነገር ሲጠላና ሲጠላው የነበረውን ነገር ሲወድ ራሱን ያገኛል!

ስለሆነም እርስ በርሳችን እንድንዋደድ የሚናገረው ትእዛዝ ከአጽንኦት አንጻር አዲስ ነው፤ ይህም ክርስቶስ ከሰጠን እጅግ ጠቃሚ ትእዛዛት አንዱ ነው (ዮሐ. 13:34)። «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው ቃል ቢያንስ አሥራ ሁለት ጊዜያት ያህል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሶአል (ዮሐ. 13:34፤ 15:9፥ 12፥ 17፤ ሮሜ 13:8፤ 1ኛ ተሰ. 4:9፤ 1ኛ ጴጥ. 1:22፤ 1ኛ ዮሐ. 3:11፥ 23፤ 4:7፥ 11፥ 12፤ 2ኛ ዮሐ. 5)። እንዲሁም፥ ስለ ወንድማማች መዋደድ የሚናገሩ ሌሎች በርካታ ጥቅሶች አሉ።

የክርስትናን ፍቅር ፍች መረዳቱ አስፈላጊ ነገር ነው። ይህ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ለመስማማት ይችሉ ዘንድ ለማጎልበት የሚጥሩት ባዶ ስሜታዊ ክንውን አይደለም። ይህ ለአንዳንድ ሰዎች የሚኖረን ስሜታዊ ስበት ሳይሆን፥ የፈቃድ ጉዳይ ነው። ውሳኔም ነው፤ በመሆኑም፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በአንተ በኩል ለሌሎች እንዲዳረስ አእምሮህን አንቅተህ በፈቃደኛነት የምትወስንበትና እነርሱንም በፍቅር የምትመለከትበት መንገድ ነው። የምትወዳቸው ይመስል የትወና ተግባር የምታከናውንበት ሳይሆን፥ በትክክል ፍቅርህን የምትገልጽበት ነው። ይህ ግብዝነት አይደለም፤ እግዚአብሔርን መታዘዝ እንጂ።

ምናልባትም ለክርስትና ፍቅር ከሁሉ የሚሻለው ምሳሌ 1ኛ ቆሮንቶስ 13 ይሆናል። የመልእክቱን ሙሉ ጉልበት ለማግኘት ከአዲሱ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ ሞክር፤ ይህም ፍቅር የሌለው የክርስትና ሕይወት «ባዶ» እንደሆነ ይገልጻል!

ይሁንና፥ «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው ትእዛዝ አዲስ የሆነው በአጽንኦት ብቻ አይደለም፦

## 2. በምሳሌነት አዲስ ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡8)።

ዮሐንስ፥ «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው በመጀመሪያ በክርስቶስ ሕይወት እንደሠራና አሁን ደግሞ በክርስቶስ በሚያምኑ ሰዎች ሕይወት እንደሚሠራ ይገልጻል። ኢየሱስ ራሱ ለዚህ ትእዛዝ ዋና ምሳሌ ነው።

ወደ በኋላ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» በሚለው ታላቅ አባባል ላይ የምናተኩር ቢሆንም (4፡8)፥ በዚህ ስፍራ በጥቆማ መልክ ተቀምጦልናል። አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን ሲመለከት፥ ፍቅር በእርሱ ውስጥ ሞልቶና በምሳሌነት ተቀምጦ ያያል። ኢየሱስ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ በማዘዙ፥ እርሱ ራሱ ያደረገውን እንድናደርግ ጠይቆናል። አራቱ የወንጌል ዘገባዎች የሚያሳዩት በፍቅር መንፈስ ያሳለፈውን ሕይወት ነው፤ ያንንም ሕይወት የኖረው ከአሳብ ደረጃ እጅግ በራቀ ሁኔታዎች ነበር። ኢየሱስ፥ «እኔ ሕይወቴን የመራሁት በዚህ ታላቅ ትእዛዝ መሠረት ነውና፥ ምሳሌነቴን እንድትከተሉ ላስችላችሁ እችላለሁ» ማለቱ ነበር።

ኢየሱስ ፍቅርን ያብራራው እርሱ ራሱ በኖረበት ሕይወት ነበር። እርሱ *ከቶውንም* ጥላቻን ወይም ክፋትን አላሳየም። ምንም እንኳ ጻድቅ ነፍሱ *ኃጢአትንና* አለመታዘዝን ብትጠላም፥ *እንዲህ ያሉ ኃጢአቶች የፈጸሙትን ሰዎች ጠልቶ አያውቅም*። ፍርድን በሚያውጁባቸው የጽድቅ ብያኔዎቹ ውስጥ እንኳ ሁልጊዜም በቃላት የማይገልጸው ስውር የፍቅር ስሜት ነበር።

ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ የነበረውን ፍቅር ማሰብ የሚያጽናና እውነት ነው። ከመካከላቸው ማን ታላቅ እንደሆነ ሲሟገቱ፥ ወይም ሰዎች ወደ ጌታቸው እንዳይቀርቡ ሲከለክሉ ምንኛ ልቡን አቁስለውት ይሆን? እያንዳንዱ ከሌሎቹ የተለየ ነበርና የክርስቶስ ፍቅር ግን እያንዳንዱን በሚረዳ ግላዊ መንገድ ለማካተት ሲል ነበር። እርሱ የጴጥሮስን ችኩልነት፥ የቶማስን አለማመንና የይሁዳን ክህደት ሳይቀር ይታገሥ ነበር። ስለሆነም፥ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ ሲናገር፥ እርሱ እንዳደረገው እንዲያደርጉ ብቻ ነበር ያዘዛቸው።

ጌታችን ለሁሉም ዓይነት ሰዎች ፍቅር እንደነበረውም ተመልከት። ኃጢአተኞችና ቀራጮች በፍቅሩ ሲሳቡ (ሉቃስ 15፡1)፥ የዝቅተኞች ዝቅተኛም ከእግሩ ሥር ሊያነባ ይችል ነበር (ሉቃስ 7፡36–39)። መንፈሳዊ ረሃብ የተጠናወተው ረቡኒ ኒቆዲሞስ ሌሊት በስውር ሊያገኘው ቻለ (ዮሐ. 3፡1–21)፤ አራት ሺህ «ተራ ሰዎች» ለሦስት ቀናት ትምህርቱን ሊከታተሉና (ማርቆስ 8፡1–9) ከዚያም ተአምራዊ ምግብ ሊመገቡ ችለው ነበር። እርሱ ሕፃናትን በእቅፉ አኑሮአቸዋል። ወታደሮች ወደ ጎልጎታ ሲወስዱት ሳለ የሚያለቅሱለትን ሴቶች ሳይቀር አጽናንቶአል።

ምናልባትም ስለ ኢየሱስ ፍቅር የሚበልጠው ነገር የጠላቶቹን ሕይወት ሳይቀር የነካበት መንገድ ነበር። በመንፈሳዊ ዕውርነታቸው የሰይጣን ማኅበርተኛ እንደሆነ አድርገው የከሰሱትን ሃይማኖታዊ መሪዎች በፍቅር ርኅራኄ ተመልክቶአቸዋል (ማቴ. 12፡24)። ሕዝቡ ሊያስሩት በመጡ ጊዜ የሰማይ ሠራዊትን ሊጠራ ሲችል፥ ለጠላቶቹ እጁን ሰጥቷል። ከዚያም ለእነዚያው ጠላቶቹ ሞቶላቸዋል! «ነፍሱን ስለ *ወዳጆቹ* ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» (ዮሐ. 15፡13)። ይሁንና፥ ኢየሱስ የሞተው ለወዳጆቹ ብቻ ሳይሆን ለጠላቶቹም ጭምር ነበር። ሲሰቅሉት ሳለ እንኳ ጸልዮላቸዋል፤ «አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ብሎአል።

ኢየሱስ በሕይወቱ፥ በትምህርቶቹና በሞቱ ሳይቀር «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» ለሚለው ለዚህ አዲስ ትእዛዝ ፍጹም ምሳሌ ነው። ትእዛዙን «አዲስ» ለማድረግ የሚረዳውም ይኸው ነው። ምክንያቱም፥ በክርስቶስ እግዚአብሔር ፍቅር ነው ለሚለው አሮጌ እውነታ አዲስ ማብራሪያ ማግኘታችንና የፍቅር ሕይወት የደስታና የድል ሕይወት እንደሆነ መረዳታችን ነው።

በክርስቶስ ሕይወት የነበረው ነገር በእያንዳንዱ አማኝም ሕይወት ሊኖር ይገባል። «እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና» (1ኛ ዮሐ. 4፡17)። አማኝ የክርስትናን የፍቅር ሕይወት መኖር አለበት፤ ምክንያቱም «ጨለማው ያልፋልና እውነተኛውም ብርሃን አሁን ይበራል» (2፡8)። ይህ በብርሃን ስለ መመላለስ የተሰጠውን አጽንኦት (ምዕ. 1) ያስታውሰናል። ሁለት የሕይወት መንገዶች በተነጻጻሪነት ቀርበዋል፤ ይኸውም በብርሃን የሚመላለሱ ፍቅርን ሲያደርጉ፥ በጨለማ የሚመላለሱ ጥላቻን እንደሚለማመዱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እውነት በተደጋጋሚ ያቀርበዋል።

«ጨለማው ያልፋል!» ብርሃኑ ግን ገና በዓለም ሁሉ አላበራም፤ ይህም ቀርቶ የአማኝን የሕይወት ክፍሎች ሁሉ እንኳ ገና ሙሉ

ለሙሉ አልተቆጣጠረም። ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ «ከላይ የመጣ ብርሃን» ዓለምን ጎብኝቷል (ሉቃስ 1፡78)። ይህም «የማለዳ ፀሐይ ጮራ» እንደ ማለት ነው። የክርስቶስ ልደት ለሰው ልጅ የአዲስ ቀን ጅማሬ ነበር! በሰዎች ፊት ሲኖር፥ ሲያስተምራቸውና ሲያገለግላቸው የሕይወትንና የፍቅርን ብርሃን አንጸባርቋል። «በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፥ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው» (ማቴ. 4፡16)።

ስለሆነም፥ በዚህ ዓለም በጨለማና በብርሃን ኃይላት መካከል ግጭት አለ። «ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥ ጨለማም አላሸነፈውም» (ዮሐ. 1፡5)። ሰይጣን የጨለማ ገዥ በመሆኑ፥ ውሸትንና ጥላቻን በመመሪያነት በመጠቀም የክፋት መንግሥቱን ያስፋፋል። ክርስቶስ ግን የጽድቅ ፀሐይ ነውና (ሚልክ. 4፡2)፥ እውነትንና ፍቅርን በመሣሪያነት በመጠቀም መንግሥቱን ይዘረጋል።

ዛሬ የክርስቶስና የሰይጣን መንግሥታት በግጭት ላይ ናቸው፤ «የጻድቃን መንገድ ግን እንደ ንጋት ብርሃን ነው፥ ሙሉ ቀን እስኪሆንም ድረስ እየተጨመረ ይበራል» (ምሳ. 4፡18)። ጨለማው ቀስ በቀስ እያለፈ ሲሄድ፥ እውነተኛው ብርሃን ግን በልባችን ውስጥ ይበልጥ እያበራ ይመጣል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለክርስቲያኖች የፍቅር መመዘኛ ነው። «እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ» ብሎናል (ዮሐ. 13፡34)። ይህንኑም፥ *«እኔ እንደወደድኋችሁ* እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት» ሲል ይደግመዋል (15፡12)። የክርስትና ፍቅራችንን በሌላ ክርስቲያን ፍቅር ልንለካ አይገባም (ይህንን ስናደርግ ብዙውን ጊዜ ከምሳሌነት ይልቅ ማመኻኘት የሚጎላበት ሕይወት ያለውን ሰው እንመርጣለን)፤ ፍቅራችንን ልንለካ የሚገባን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር አኳያ ነው። በክርስቶስ ተፈጽሞ ስናየው አሮጌው ትእዛዝ «አዲስ» ይሆናል።

ስለሆነም፥ «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው ትእዛዝ በአጽንኦትም ሆነ በምሳሌነት አዲስ ነው። ሌላም አዲስ የሚሆንበት ሦስተኛ መንገድ አለው፡-

### 3. በተሞክሮ አዲስ ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡9-11)።

ምንባባችን የብርሃንንና የጨለማን ማብራሪያ መስጠቱን ይቀጥላል። አንድ ክርስቲያን በብርሃን የሚመላለስና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሚያደርግ ከሆነ፥ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ከሌሎችም ወገኖች

ጋር ኅብረት ይኖረዋል። ፍቅር ከብርሃን ጋር ዝምድና እንዳለው እንዲሁም ጥላቻ ከጨለማ ጋር ይዛመዳል።

በክርስትና ፍቅር መመላለሱ ስለ ክርስትና ፍቅር የመነጋገርን ያህል ቀላል አይደለም። የዚህ ዓይነቱ ፍቅር የቃላት ልውውጥ ጉዳይ ብቻ አይደለም (ቁጥር 9)። ለአንድ ክርስቲያን ሌላውን አማኝ እየጠላ ሳለ ወንድሞችን እንደሚወድ መናገር (ወይም መዘመር) ውሸተኛ ያደርገዋል። በሌላ አባባል፥ *ከአባት ጋር ኅብረት እያደረጉ በተመሳሳይ ጊዜ ከሌላ ክርስቲያን ጋር ኅብረት አለማድረግ የማይቻል ነገር ነው፤* ይህም የማይታበል እውነት ነው።

እግዚአብሔር የአማኞች ኅብረት የሆነችውን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከመሠረተባቸው ምክንያቶች አንዱ ይኼ ነው። «ብቸኛ ክርስቲያን ልትሆን አትችልም»። ከእግዚአብሔር ሕዝቦች ጋር ኅብረት የማያደርግ ክርስቲያን ሙሉና አዳጊ የክርስትና ሕይወት ሊኖር አይችልም። የክርስትና ሕይወት ሁለት ግንኙነቶች አሉት፤ እነዚህም ወደ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ግንኙነትና ወደ ጎን ከሰዎች ጋር የሚደረግ ግንኙነት ናቸው። በመሆኑም፥ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው ሊለየው አይገባም! እነዚህ ሁለቱም ግንኙነቶች እያንዳንዳቸው ፍቅርን የሚያጎሉ መሆን አለባቸው።

ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ ስለዚህ ጉዳይ ይናገራል (ከማቴ. 5፡21–26 ጋር አወዳድር)። ከወንድሙ ጋር ሊያስተካክል የሚገባው ሙግት እስካለው ድረስ ማንኛውም አማኝ በመሠዊያው ላይ የሚያቀርበው ስጦታ ዋጋ አልነበረውም። ኢየሱስ አምላኪው በወንድሙ ላይ የያዘው ነገር ካለው እንደማይልና ዳሩ ግን ወንድሙ ከአምላኪው ላይ የያዘው ነገር ካለው እንደሚል ልብ በል። በአጭሩ አንድ ሰው ቢያስቀይመን እንኳ ያስቀየመን ሰው ወደ እኛ እስኪመጣ ድረስ መጠበቅ የለብንም ማለት ነው። *ይልቁንም ወደ ሰውዬው መሄድ አለብን።* ይህንን ካላደረግን፥ ኢየሱስ የመጨረሻዋን ሣንቲም ለመክፈል ወደምንገደድበት የመንፈሳዊ ፍርድ ወህኒ ቤት እንደምንገባ ያስጠነቅቀናል (ማቴ. 18፡21–35)። በሌላ አባባል፥ ይቅር የማይልና የማያፈቅር መንፈስ ካለን ይበልጥ የምንጎዳው ራሳችንን ነው ማለት ነው።

«በመናገር» እና «በማድረግ» መካከል ያለውን ንጽጽር ከዚህ በፊት ተመልክተነዋል (1ኛ ዮሐ. 1፡6፥ 8፥10፤ 2፡4 እና 6)። በ«ቃላት» ክርስትና መኖሩ ቀላል ነው፤ ይኸውም ትክክለኛ መዝሙሮችን መዘመር፥ ትክክለኛ ቃላት መጠቀም፥ ትክክለኛ ጸሎት ማድረስና በዚህ ሁሉ «መንፈሳውያን ነን» ብሎ ራስን ማታለል ነው።

በተጨማሪም፥ ይህ ስሕተት ኢየሱስ በተራራ ላይ ስብከቱ ካስተማረው ነገር ጋር ይዛመዳል (ማቴ. 5፡33–37)። የምንናገረው የባሕርያችን እውነተኛ መገለጫ ሊሆን ይገባል። የምንናገረውን ለማጽናት ተጨማሪ ቃላትን («መሀላ») መጠቀም የለብንም፥ «አዎን» ከሆነ «አዎን» «አይደለም»ም ከሆነ «አይደለም» ልንል ይገባል። ስለሆነም፥ በብርሃን እንደምንመላለስ የምንናገር ከሆነ ወንድሞችን በመውደድ እናረጋግጣለን። ብዙ ክርስቲያኖች ተቀባይነት ለማግኘትና ለመፈቀር ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው።

በስፋት ከሚሰነዘረው አሳብ ባሻገር የክርስትና ፍቅር «ዕውር» አይደለም። በእውነተኛ የክርስትና ፍቅር መኖር ስንጀምር ሕይወት ይበልጥ እየፈካ ሲሄድ እናያለን። ጥላቻ ሕይወታችንን ያጨልማል! እውነተኛ የክርስትና ፍቅር ከልባችን ሲፈልቅ፥ ለመንፈሳዊ ነገሮች የበለጠ ግንዛቤ ይኖረናል። ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «የሚሻለውን ነገር ፈትናችሁ ትወዱ ዘንድ፥ ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ» እያለ የሚጸልየው ለዚህ ነው (ፊልጵ. 1፡9–10)። ወንድሙን የሚወድ ክርስቲያን ይበልጥ አጥርቶ የሚያይ ክርስቲያን ነው።

እንደ መጽሐፈ አስቴር የጭፍን ጥላቻን ኃይል የሚያብራራ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የለም። በዚያ ውስጥ የተመዘገቡ ክስተቶች የተፈጸሙት ከምርኮ በኋላ ብዙ አይሁዶች ይኖሩበት በነበረው በፋርስ ነው። ከንጉሡ ቀልፍ ሰዎች አንዱ የነበረው ሐማ ለአይሁዶች ከፍተኛ ጥላቻ ነበረው። ይህንን ቁጣውን የሚያበርድበት ብቸኛ መንገድ አይሁዶች በሙሉ ሲደመሰሱ በማየት ነበር። በክፉ ጨለማ ሙሉ ለሙሉ ስለ ታወረ፥ አይሁዶች እንደሚያሸንፉትና እርሱ ራሱ እንደሚጠፋ ለማየት አልቻለም ነበር።

ዛሬም ጥላቻ ሰዎችን እያሳወረ ነው።

የክርስትና ፍቅር በቤተ ክርስቲያን አምልኮ ጊዜ ብቻ የምንገልጸው አላፊ ስሜታዊ ነጸብራቅ አይደለም። የክርስትና ፍቅር *ተግባራዊ* ነገር ነው፤ በዕለታዊ የሕይወት ጉዳዮች ላይ ይገለጻል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ «እርስ በርስ» የሚሉትን ዓረፍተ ነገሮች ተመልከትና እርስ በርስ መዋደድ ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆነ ተረዳ። ከዚህ በታች ጥቂቶቹ የቀረቡ ሲሆን፥ ከ20 የሚበልጡ እንደዚህ ዓይነት ዓረፍተ ነገሮች አሉ፡–

እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ... (ዮሐ. 13፡14)።

እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ (ሮሜ 12፡10)።

እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስማሙ (ሮሜ 12:16)።

እርስ በርሳችን አንፈራረድ (ሮሜ 14:13)

እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ (ሮሜ 15:7)

እርስ በርሳችሁ... ልትገሠጹ... (ሮሜ 15:14)

አንዱ ሌላውን ያንጸው (1ኛ ተሰ. 5:11)።

እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም (ገላ. 6:2)።

እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ (ያዕ. 5:16)።

እርስ በርሳችሁ እንግድነትን ተቀባበሉ (1ኛ ጴጥ. 4:9)።

በአጭሩ፥ ሌሎች ክርስቲያኖችን መውደድ ማለት *እግዚአብሔር* በሚያስተናግዳቸው መንገድ ማስተናገድ ማለት ነው፤ እኛንም እግዚአብሔር በሚያስተናግደን መንገድ ማስተናገድ ነው። ራሱን በተግባርና በአመለካከት የማይገልጽ የክርስትና ፍቅር የውሸት ማታለያ ነው (1ኛ ቆሮ. 13:4-7ን ተመልከት)።

ወንድሞችን የማይወድ አማኝ ምን ይገጥመዋል? ቀደም ብለን የመጀመሪያው አሳዛኝ ውጤት ምን እንደሆነ ተመልክተናል፤ ይኸውም፥ ምንም እንኳ ምናልባትም በብርሃን እንዳለ *ሊያስብ* ቢችልም በጨለማ ውስጥ እንደሚኖር ነው (1ኛ ዮሐ. 2:9)። አያለሁ ብሎ *ሊያስብ* ቢችልም፥ በጥላቻ ጽልመት ውስጥ ይዳክራል። በክርስቲያን ቡድኖች ውስጥ ችግር የሚፈጥረው የዚህ ዓይነቱ ሰው ነው። በጣም አነስተኛ መንፈሳዊ ግንዛቤ ያለው ሕፃን ሆኖ ሳለ፥ ራሱን ከፍተኛ መረዳት እንዳለው «መንፈሳዊ ጀግና» አድርጎ ይቆጥረዋል። ምንም በታማኝነት መጽሐፍ ቅዱስ ሊያነብና በትጋት ሊጸልይ ቢችልም፥ በልቡ ውስጥ ጥላቻ ካለ ኑሮውም የውሸት ነው።

ሁለተኛው አሳዛኝ ውጤት ደግሞ እንዲህ ዓይነት አማኝ የማሰናከያ ምክንያት መሆኑ ነው (ቁጥር 10)። ፍቅር የሌለው አማኝ ራሱን መጉዳቱ ክፉ ሆኖ ሳለ (ቁጥር 9)፥ *ሌሎችን* መጉዳት ሲጀምር ደግሞ ጉዳዩ እጅግ አሳሳቢ ይሆናል። በጨለማ ውስጥ መመላለሱ *አደገኛ* ነው። እንዲሁም በመንገዱ ላይ የሚያሰናክሉ እንቅፋቶች እያሉ በጨለማ ውስጥ መመላለሱ *የከፋ* ነው። ፍቅር የሌለው አማኝ ራሱን ከማሰናከሉም በላይ ሌሎችም እንዲሰናከሉ ምክንያት ይሆናል።

በአንድ ምሽት ጨለማ ያጠላበትን ቁልቁለት የሚወርድ ሰውዬ ብልጭ ድርግም የሚል ብርሃን ወደ እርሱ ሲመጣ ተመለከተ። በዚህም ጊዜ ባትሪውን የያዘው ሰው በሽተኛ ወይም የሰከረ ሰው ይሆናል ሲል

አሰበ፤ እየቀረበ ሲመጣ ግን አንድ ዕውር ሰው ነጭ ባትሪ ይዞ ሲመጣ ተመለከተ።

«ላያይ ነገር ዓይነ-ስውር ሰው ለምን ባትሪውን ይይዛል?» ሲል ተደነቀና ሊጠይቀው ወሰነ።

ዓይነ-ስውሩም ፈገግ ብሎ፥ «ባትሪውን የምይዘው ለማየት ብዬ ሳይሆን ሌሎች እንዲያዩኝ ብዬ ነው። ዓይነ-ስውርነቴን ላስወግድ ባልችልም ማሰናከያ ከመሆን ልቆጠብ እችላለሁ» ሲል መለሰ።

ሌሎች ክርስቲያኖች እንዳይሰናከሉ ለመርዳት ከሁሉም የሚሻለው መንገድ እነርሱን መውደድ ነው። ፍቅር የመሸጋገሪያ ድልድዮች ሲያደርገን፥ ጥላቻ (ወይም እንደ ቅንዓትና ክፋት ያለው ዝሪያ ሁሉ) የማሰናከያ ዓለቶች ያደርጉናል። ክርስቲያኖች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ፍቅርን ቢለማመዱ መልካም ነው፤ አለዚያ ግን ሁልጊዜም ችግሮችና መከፋፈል ይኖራሉ። አንዳችን ሌላውን ወደ ላይ ከፍ እንደማድረግ ታች የምንጥል ከሆነ፥ ከቶውንም ደስተኛ መንፈሳዊ ቤተሰብ ልንሆን አንችልም።

ለምሳሌ፥ ይህንን መመሪያ ብዙ ጊዜ በማያግባቡት «አከራካሪ ነገሮች» ላይ ልትጠቀም ትችላለህ (ሮሜ 14፡15)። መቼም አማኞች የተሰባሰቡት ከተለያዩ ዳራዎች ነውና ሁልጊዜም ሊስማሙ አይችሉም። በጳውሎስ ዘመን፥ እንደ አመጋገብና የበዓል ቀናት ባሉት ጉዳዮች ላይ በአሳብ ተለያይተዋል። አንደኛው ቡድን ለጣዖት የተሠዋን ምግብ መብላት መንፈሳዊ አለመሆን ነው ሲል፥ ሌላው ቡድን በሰንበት ቀን ምንም ነገር ሳይሠሩ ማክበርን ፈልጓል። ለችግሩ የተለያዩ ገጽታዎች ቢኖሩም፥ ለመፍትሔው መሠረታዊ ቁም ነገር፥ «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው ነው። ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡- «እርስ በርሳችን አንፈራረድ፤ ይልቁን ግን ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖርበት ይህን ቁረጡ... ወንድምህንም በመብል ምክንያት የምታሳዝን ከሆንህ እንግዲህ በፍቅር አልተመላለስህም» (ሮሜ 14፡13፥ 15)።

ሦስተኛው የጥላቻ አሳዛኝ ውጤት የአማኙን መንፈሳዊ ዕድገት መግታቱ ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡11)። በጨለማ ውስጥ የሚመላለስ ዓይነ-ስውር ከቶውንም መንገዱን ሊያውቅ አይችልም። ለመንፈሳዊ ዕድገት የሚመች ብቸኛው ድባብ የፍቅር መንፈሳዊ ብርሃን ነው። የፀሐይ ብርሃን ለፍራፍሬና ለአበቦች እንደሚያስፈልግ ሁሉ፥ የእግዚአብሔርም ሕዝብ እንዲያድጉ ከተፈለገ ፍቅር ያስፈልጋቸዋል።

«እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው ትእዛዝ በዕለት ተዕለት ልምምዳችን አዲስ ይሆንልናል። በአጽንኦት አዲስ መሆኑን ተረድቶ፥ «አዎን፥ ፍቅር አስፈላጊ ነው!» ማለቱ ብቻ አይበቃንም። እንዲሁም፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት ሲቀርብ መመልከቱ ብቻ አይበቃንም። *በራሳችን የሕይወት ልምምድ ይህንኑ* ፍቅር ማወቅ አለብን። የእግዚአብሔርን ፍቅር በዕለታዊ ሕይወታችን ስንለማመድ «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው ጥንታዊ ትእዛዝ *አዲስ* ይሆናል።

እስካሁን ከቁጥር 9–11 ያለውን ክፍል *አሉታዊ* ጎኖች አይተናል። አሁን እስኪ *አዎንታዊ* ገጽታውን እንመልከት። በክርስትና ፍቅር ስንመላለስ የሚከሰቱ ወርቃማ ውጤቶች ምን ይሆኑ?

ከሁሉም በፊት፥ በብርሃኑ እንመላለሳለን፤ ከእግዚአብሔርና ከክርስቲያን ወንድሞቻችን ጋር በኅብረት እንኖራለን።

ሁለተኛ፥ ከመሰናከልም ሆነ ለሌሎች የማሰናከያ ዓለት ከመሆን እንተርፋለን።

ሦስተኛ፥ መንፈሳዊ ሕይወታችን ሲጎለብት፥ ክርስቶስን ወደ መምሰል እናድጋለን።

በዚህ ነጥብ ላይ በአስጸያፊዎቹ «የሥጋ ሥራዎች» (ገላ. 5፡19–21) እና በውቡ የመንፈስ ፍሬ ማለትም ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ገርነት፥ በጎነት፥ ታማኝነት፥ የውሃትና ራስን መግዛት መካከል ስላለው ንጽጽር ማሰብ አለብን (ቁጥር 22–23)።

በብርሃን በምንመላለስበት ጊዜ፥ «የቃሉ ዘር» (ሉቃስ 8፡11) ሥር በመስደድ ፍሬ ሊያፈራ ይችላል። መንፈስ ቅዱስ የሚያፈራው የመጀመሪያው እንቡጥ *ፍቅር* ነው!

ይሁንና፥ ፍቅር ለብቻው አይኖርም እናም ፍቅር *ደስታን ያፈራል!* ጥላቻ አንድን ሰው ሲያሠቃይ ፍቅር ግን በደስታ እንዲጥለቀለቅ ያደርገዋል።

ጋብቻቸው ባፍጢሙ ሊደፋ የተቃረበባቸው ባለትዳሮች መጋቢውን ሊያማክሩ መጡ። አቶ ባል ተስፋ መቁረጥን በሚያስተጋባ ድምፁ፥ «ሁለታችንም የዳንን ክርስቲያኖች ነን፤ ግን ሁለታችንም ደስተኞች አይደለንም። በቤታችን ውስጥ ደስታ የሚባል ነገር የለም» አለ። መጋቢው ሲያነጋግራቸውና እነርሱም መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን አሳብ ሲፈልጉ ሳለ አንድ ሐቅ ብቅ አለ፤ ባልና ሚስት ሁለቱም ጥቃቅን

በደሎችን ይቆጥሩ ነበር። እያንዳንዳቸው ሌላው ያደረጋትን ቅንጣት ነገር በማስታወስ ሲጣሉ ቆይተዋል!

መጋቢው «ሁለታችሁ በርግጥ ከልብ የምትዋደዱ ከሆናችሁ እነዚህን ጉዳቶች በልባችሁ አትይዙም ነበር። ጥላቻ በልባችን ውስጥ እንደተመረዘ ቁስል ይሆንና ሁለመናችንን ይበክላል» ሲል ተናገረ።

ከዚያም፥ «ፍቅር በደልን አይቆጥርም» (1ኛ ቆሮ. 13:5) የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አነበበና ገለጻውን ቀጠለ። «ይህም ማለት ፍቅር ሌሎች በእኛ ላይ ያደረሱትን በደል አይቆጥርም ማለት ነው። አንድን ሰው በእውነተኛ ልብ በምንወድበት ጊዜ ፍቅራችን ኃጢአታቸውን በመሸፈን የሚያስከትሉብንን ቁስል ለመፈወስ ይረዳናል። በማያያዝም «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ» የሚለውን ክፍል አነበበ (1ኛ ጴጥ. 4:8)።

ከመሄዳቸውም በፊት እንዲህ ሲል መከራቸው፤ «ካሁን በኋላ የሚያቆስሉአችሁን ነገሮች ከማስታወስ ይልቅ የሚያስደስቱአችሁን ነገሮች አስታውሱ። ይቅር የማይል መንፈስ ሁልጊዜም መርዝን ያረባል፤ ዳሩ ግን ከሁሉም የሚሻለውን የሚመለከትና የሚያስታውስ አፍቃሪ መንፈስ ሁልጊዜም ጤንነትን ያስከትላል።»

«የመንፈስ ፍሬ» ፍቅርና ደስታ በመሆኑ፥ በፍቅር የሚመላለስ ክርስቲያን ሁልጊዜም አንድን አዲስ ደስታ ይለማመዳል። «ፍቅር» እና «ደስታ»ን ስናቀላቅል «ሰላም»ን እናገኛለን፤ ሰላምም በበኩሉ «ትዕግሥት»ን ለማግኘት ያግዛል። በሌላ አባባል፥ በብርሃን መመላለስ ማለትም በፍቅር መመላለስ የክርስትና ዕድገት ምሥጢር ነው፤ ይህም ሁልጊዜም ለማለት ይቻላል የሚጀምረው በፍቅር ነው።

በራሳችን ጥረት የክርስትና ፍቅር ልናመነጭ እንደማንችል ልንረዳ ይገባል። በተፈጥሮአችን ራስ ወዳዶችና በጥላቻ የተያዝን ነን። የእግዚአብሔር መንፈስ ልባችንን በፍቅር ሲሞላው ብቻ ነው እኛም በምላሹ እርስ በርሳችን ልንዋደድ የምንችለው። «በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም» (ሮሜ 5:5)። «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለውን ትእዛዝ ወደ አዲስና አስደሳች ዕለታዊ ልምምድ የሚቀይረው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። በብርሃን ብንመላለስ የእግዚአብሔር መንፈስ ፍቅርን ያፈራልናል። በጨለማ ብንመላለስ የነበረው የራስ–ወዳድነት መንፈስ ጥላቻን ያፈራብናል።

የክርስትና ሕይወት ማለትም እውነተኛው ሕይወት «የጥንታዊና የአዲስ ነገር» ውብ ጥምረት ነው። መንፈስ ቅዱስ «የጥንት ነገሮች»ን ወስዶ በልምምዳችን ውስጥ «አዳዲስ ነገሮች» ያደርጋቸዋል። አንተ ማሰብህን ብታቆምም መንፈስ ቅዱስ አያረጅም! እርሱ ሁልጊዜም ወጣት ነው! ከምእተ-ዓመታት በፊት ኢየሱስ በዚህች ምድር በነበረ፥ ባስተማረ፥ በሞተና በተነሣ ጊዜ የነበረውና *አሁንም* ያለው እርሱ ብቻ ነው። «የጥንቱን እውነት» ወስዶ በአሁኑ ጊዜ በዕለታዊ ገጠመኞችን አዲስ ሊያደርግ የሚችለው እርሱ ነው።

በተቀረው የዮሐንስ መልእክት ውስጥ ሌሎችም አስደሳች እውነቶች አሉ፤ ይሁንና፥ በዚህ የፍቅር ጉዳይ ላይ ሳንታዘዝ ብንቀር የተቀረው ደብዳቤ «ጨለማ» ሊሆንብን ይችላል። *በዚህ ጊዜ* ልናደርግ የምንችለው ከሁሉም የተሻለ ነገር በወንድማችን ላይ የያዝነው ቂም እንዳለ፥ ወይም ሌላ ሰው በእኛ ላይ ቂም እንዳለው መመርመር ነው። እውነተኛ የሆነ ሕይወት የታማኝነት ሕይወት ነው፤ ይህም *የተግባር* እንጂ *የባዶ ቃላት* ጥርቅም አይደለም። ይህ በክርስቶስ የሆነ የንቁ ፍቅር ሕይወት ነው ማለትም ይቅርታ፥ ቸርነት፥ ትዕግሥት የሚገኙበት። እንዲሁም ደግሞ ደስታ፥ ሰላምና ድል ማለት ነው።

የፍቅር ሕይወት እውነተኛ ሕይወት በመሆኑ ብቸኛው ሕይወት ነው!

# እግዚአብሔር የሚጠላው ፍቅር

## 1ኛ ዮሐንስ 2:12–17

የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች የሆስፒታል ውስጥ ጉብኝታቸውን እንደፈጸሙ፥ በጉብኝቱ ወቅት የመረቻቸው ነርስ ጥያቄዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ዕድል ሰጠቻቸው። ወዲያው አንድ እጅ ከባቢውን አየር እየሰነጣጠቀ ወደ ላይ ብቅ አለ።

«እዚህ የሚሠሩ ሰዎች ደጋግመው እጃቸውን የሚታጠቡት ለምንድን ነው?» ሲል አንድ ትንሽ ልጅ ጠየቀ።

ነርሷም፥ «ሁልጊዜም እጆቻቸውን የሚታጠቡት ለሁለት ምክንያቶች ነው። በመጀመሪያ፥ ጤንነትን ስለሚወዱ፥ ሁለተኛ፥ *ተሐዋስያንን ስለሚጠሉ»* ስትል ጥሩ ምላሽ ሰጠች።

በአያሌ የሕይወት ክፍሎች ፍቅርና ጥላቻ ጎን ለጎን ይሄዳሉ። ሚስቱን የሚወድ ባል እርሷን የሚጎዳትን ነገር ይጠላል። «እግዚአብሔርን የምትወዱ ክፋትን ጥሉ» [መዝ. (97):10]። «ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ክፉውን ነገር *ተጸየፉት!* ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ» (ሮሜ 12:9)።

የዮሐንስ መልእክት ትክክለኛውን ዓይነት ፍቅር እንድናደርግ አስታውሶናል (1ኛ ዮሐ. 2:7–11)። አሁን ደግሞ እግዚአብሔር የሚጠላው የተሳሳተ ፍቅር እንዳለ በመግለጽ ያስጠነቅቀናል። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ «ዓለም» ብሎ ለሚጠራው ነገር የሚኖረን ፍቅር ነው።

ክርስቲያኖች ዓለምን መውደድ የለባቸውም። ለዚህም አራት ምክንያቶች አሉ።

### 1. ከዓለም ምንነት የተነሣ

በአዲስ ኪዳን *«ዓለም»* ተብሎ የተጠቀሰው ቃል ቢያንስ ሦስት ፍችዎች አሉት። አንዳንድ ጊዜ *ቁሳዊውን* ዓለም ማለትም *ምድረ–ዓለምን* ያመለክታል፤ ዓለሙን [የእኛዋ ምድረ–ዓለም] እና በእርሷ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ» (የሐዋ. 17:24)። እንዲሁም *ሰብአዊ ዓለም* ማለትም *የሰው* ልጅ ማለት ነው፤ «እግዚአብሔር ዓለምን ስለወደደ» (ዮሐ. 3:16)። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ሁለት አሳቦች በአንድ

ላይ ይገኛሉ፤ «[ኢየሱስ] በዓለም በዚህ ምድር ነበረ፥ ዓለምም [የሰው ልጅ] አላወቀውም» (ዮሐ. 1፡10)።

«ዓለምን አትውደዱ!» የሚለው ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ግን ስለ ተፈጥሮአዊ ዓለም ወይም ስለ ሰዎች ዓለም አይደለም። እግዚአብሔር እንደሰትበት ዘንድ ሁሉንም ነገር አትረፍርፎ ስለሚሰጠን (1ኛ ጢሞ. 6፡17)፥ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሠራትን ምድር ውበትና ጠቃሚነት ማድነቅ አለባቸው። እንዲሁም፥ በትክክል ሰዎችን መውደድ አለባቸው–ወዳጆቻቸውን ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻቸውንም ጭምር።

በዚህ ስፍራ ጠላታችን እንደሆነ የተጠቀሰው «ዓለም» ከእግዚአብሔርና ከክርስቶስ ጋር የሚያቃርን እና የማይታይ መንፈሳዊ ሥርዓት ነው።

በዕለታዊ ውይይታችን «ዓለም» የሚለውን ቃል «ሥርዓት» በሚል መልኩ እንጠቀማለን። የቴሌቪዥን ጋዜጠኛ፥ «የስፖርት ዓለም ዜናዎች እናቀርብላችኋለን» ሲል፥ «የስፖርት ዓለም» የተለየ ፕላኔት ወይም ከፍለ–ዓለም እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይልቁንም፥ ይህ ከተለያዩ አሳቦች፥ ሰዎች፥ እንቅስቃሴዎች፥ ወዘተ... የተዋቀረ ሥርዓት (ዘይቤ) ነው። «የመዋዕለ–ንዋይ ዓለም» እና «የፖለቲካ ዓለም»ም እንዲሁ ራሳቸውን የቻሉ ሥርዓቶች ናቸው። በስፖርት ወይም በመዋዕለ–ንዋይ ከምንመለከታቸው ባሻገር ልንመለከት የምንችለው የማይታይ ሥርዓት አለ፤ ይህም «ነገሮች የተወሰነ ሂደታቸውን እንዲቀጥሉ የሚያደርግ» ሥርዓት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ «ዓለም» የሚለው በምድር ላይ የክርስቶስን ሥራ ለመቃወም ሰይጣን ያዋቀረውን ሥርዓት ነው። ይህም መንፈሳዊ ለሆነ (1ኛ ዮሐ. 2፡16)፥ ቅዱስና ተቃራኒ ነው። «ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን ዓለም በሞላው በክፉው እንደተያዘ እናውቃለን» (5፡19)። ኢየሱስ ሰይጣንን «የዚህ ዓለም አለቃ» ሲል ጠርቶታል (ዮሐ. 12፡31)። ዲያብሎስ ከእርሱ ጋር የሚሠራና «የዚህን ዓለም» ጉዳዮች የሚጸናወት የክፉ መናፍስት ድርጅት አለው (ኤፌ. 6፡11–12)።

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ላይ ለመፈጸም ሰዎችን እንደሚጠቀም ሁሉ፥ ሰይጣንም ክፉ ዓላማዎቹን ለማሳካት ሰዎችን ይጠቀማል። ያልዳኑት ሰዎች አወቁትም አላወቁት፥ «በማይታዘዙት ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ» ኃይል ይመላለሳሉ (ኤፌ. 2፡1–2)።

ያልዳኑ ሰዎች «ከዚህ ዓለም» ናቸው። ኢየሱስ «የዚህ ዓለም ልጆች» ሲል ይጠራቸዋል (ሉቃስ 16፡8)። ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ «የዚህ ዓለም» ሰዎች አልተረዱትም ነበር፤ ዛሬም እርሱን የምናምነውን እኛን አይረዱንም (1ኛ ዮሐ. 3፡1)። ክርስቲያን *የሰብአዊ* ዓለም አባልና *የቁሳዊ* ዓለም ነዋሪ ቢሆንም፥ እግዚአብሔርን ለመቃወም የተዋቀረው የሰይጣን *ሥርዓት መንፈሳዊ* ዓለም አካል ግን አይደለም። «ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል» (ዮሐ. 15፡19)።

ስለሆነም፥ «ዓለም» ለአማኝ ተፈጥሮአዊ የመኖሪያ ስፍራ አይደለም። የአማኙ ዜግነት ሰማያዊ ሲሆን (ፊልጵ. 3፡20)፥ በምድር ላይ ለመኖር የሚያስፈልገው ኃይል የሚመጡት በሰማይ ካለው ከአባቱ ነው።

አማኝ በውኃ የውስጠኛው ክፍል ውስጥ እንደሚጓዝ ዋናተኛ ነው። ውኃ ለሰው ተፈጥሮአዊ የመኖሪያ ስፍራ አይደለም፤ ሰው በውኃ ውስጥም ሆነ ከውኃ ሥር እንዲኖር የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሉትምና፥ በውኃ ውስጥ ለመቆየት የሚፈልግ ሰው ለመተንፈስ የሚያስችለውን መሣሪያ ከአፉ ላይ ገጥሞ መግባት አለበት።

በውስጣችን ከሚኖረው መንፈስ ቅዱስ፥ በጸሎት ከምንቀበለው መንፈሳዊ በረከት፥ ከክርስቲያናዊ ኅብረትና ከቃሉ በምናገኘው ኃይል ባይሆን ኖሮ፥ በምድር ላይ ልንኖር አንችልም ነበር። በምድር ከባቢ አየር መበከል ምክንያት እናጉረመርማለን፤ «የዓለምም» አየር በመንፈሳዊ ሁኔታ የተበከለ በመሆኑ ክርስቲያኖች በአግባቡ ወደ ውስጥ ሊስቡትና ወደ ውጭ ሊያስወጡት አይችሉም!

ይህም ሆኖ፥ ክርስቲያኖች ዓለምን ሊወድዱ የማይገባበት ክበድ ያለ ሁለተኛው ምክንያት የሚከተለው ነው።

## 2. ዓለም በእኛ ላይ ከምታደርገው ነገር የተነሣ

«ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም» (1ኛ ዮሐ. 2፡15)።

ዓለማዊነት በአብዛኛው *የአመለካከት* እንጂ *የተግባር* ጉዳይ አይደለም። ዓለማዊነት የልብ ዝንባሌ ጉዳይ በመሆኑ፥ አንድ ክርስቲያን ከአጠያያቂ ነገሮችና አጠራጣሪ ስፍራዎች ርቆ እያለ ግን ዓለምን ሊወድ ይችላል። ይህም ክርስቲያን የዓለምን ሥርዓትና በውስጧ የሚገኙትን ነገሮች በሚወድበት ልክ አብን አይወደውም ማለት ነው።

ዓለማዊነት የሚጻናወተው ለእግዚአብሔር ፍቅር የምትሰጠውን አፀፋ ብቻ ሳይሆን፥ *ለእግዚአብሔር ፈቃድ* ያለህን ምላሽ ጭምር ነው። «ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል» (1ኛ ዮሐ. 2፡17)።

በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ደስታ ነው። «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ።» ዳሩ ግን አንድ አማኝ ከአብ ፍቅር የሚያገኘውን ደስታ ሲያጣ፥ የአብን ፈቃድ መፈጸም ይከብደዋል።

እነዚህን ሁለት ነገሮች አንድ ላይ ስታጣምር የዓለማዊነትን ተግባራዊ ድንጋጌ ታገኛለህ፤ ይኸውም፥ በክርስቲያን ሕይወት የአብን ፍቅር ደስታ ወይም የአብን ፈቃድ ለመፈጸም የሚኖረውን መሻት እንዲያጣ ምክንያት የሚሆን ነገር ሁሉ ዓለማዊነት ስለሆነ ሊወገድ ይገባል። የዓለማዊነት ሁለቱ መፈተኛዎች ለአብ ፍቅር የምትሰጠው ምላሽ (የጽሞና ሕይወትህ) እና የአብን ፈቃድ ማድረግህ (ዕለታዊ ጠባይህ) ናቸው።

በዚህ ዓለም ውስጥ ብዙ የተሳሳቱ ነገሮች የሚገኙ ሲሆን፥ የእግዚአብሔርም ቃል ኃጢአት በማለት ይለያቸዋል። መስረቅና መዋሸት ስሕተት ነው (ኤፌ. 4፡25፥ 28)። ወሲባዊ ኃጢአት ስሕተት ነው (ኤፌ. 5፡1–3)። ስለ እነዚህና ሌሎችም አያሌ ነገሮች ክርስቲያኖች ብዙም በአሳብ ላይለያዩ ይችላሉ። ዳሩ ግን በግልጽ ያልተቀመጡ የክርስቲያን ባሕርይ ጉዳዮች አሉ፤ በእነዚህም ላይ በጣም መንፈሳውያን የተባሉ ክርስቲያኖችም እንኳ በአሳብ አይጣጣሙም። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም፥ እያንዳንዱ አማኝ የራሱን ሕይወት መፈተኛ በመጠቀም ከፍተኛ ጥንቃቄ የታከለበትን የታማኝነት ግምገማ ሊያደርግ ይገባል፤ በዚህም ጊዜ *«መልካም»* የተባለው ነገር እንኳ ሳይቀር ከአማኙ የእግዚአብሔርን ፍቅር ደስታና የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማድረግ መሻት ሊነጥቅበት እንደሚችል መገንዘብ አለበት።

በአንድ የክርስቲያን ኮሌጅ ውስጥ የሚማር ተማሪ ግሩም ውጤቶችን በማስመዝገብና ስኬታማ አገልግሎት በመስጠት ይታወቅ ነበር። እሑድ እሑድ የስብከት አገልግሎት ሲሰጥ፥ እግዚአብሔር ነፍሳትን ለመማረክና ክርስቲያኖችን ለማበረታታት ይጠቀምበት ነበር።

ከዚያም አንድ ነገር ተከሰተ፤ ውጤቱ አሽቆለቆለ፤ ምስክርነቱ ከመበላሸቱም በላይ ባሕርዩም የተለወጠ መሰለ። የኮሌጁም ፕሬዚዳንት ወደ ቢሮው ጠራው።

«ሕይወትህና ሥራህ ተለውጧል፤ ምን ችግር እንዳጋጠመህ ብትነግረኝ ደስ ይለኛል» ሲል ጠየቀው።

ተማሪው ለጊዜው ስለ ጉዳዩ ላለማንሣት ቢሞክርም፥ በኋላ ግን ታሪኩን ግልጽ አደረገው። ከአንዲት ቆንጆ ክርስቲያን ልጃገረድ ጋር የተጫጨ ሲሆን፥ ከምረቃው በኋላ ለመጋባት ዐቅዶ ነበር። በዚህ መሀል በአንድ የተንቆጠቆጠ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግል በመጠራቱ፥ ከጋብቻ በኋላ እጮኛውን ይዞ ለአገልጋዮች ወደ ተዘጋጀው መኖሪያ ቤት ለመግባትና የመጋቢነቱን ተግባር ለመጀመር ተጣደፈ።

«በሁኔታው በጣም ከመርካቴ ጌታ በቶሎ ተመልሶ እንዲመጣ ወደማልፈልግበት ደረጃ ደረስሁ። ከዚያ በኋላ ኃይል ከሕይወቴ ጠፋ» ሲል ተናዘዘ።

መልካምና ውብ ዕቅዶቹ በእርሱና በአባቱ መካከል ግርዶሽ ፈጠሩ። በዚህም የአብን ፍቅር ደስታ አጥቶ ዓለማዊ ሆነ!

ሐዋርያው ዮሐንስ የዓለም ሥርዓት ክርስቲያኖችን ለማጥመድ ሦስት መሣሪያዎችን እንደሚጠቀም አመልክቷል፤ እነዚህም የሥጋ ምኞት፥ የዓይን አምሮትና ስለ ገንዘብ መመካት ወይም የሕይወት ትምክህት ናቸው (1ኛ ዮሐ. 2፡16)። ከብዙ ዘመናት በፊት ሔዋንን ያጠመዱአት እነዚሁ ሦስቱ መሣሪያዎች ነበሩ፤ «ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ *(የሥጋ ምኞት)*፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ *(የዓይን አምሮት)*፥ ለጥበብም መልካም እንደሆነ *(የሕይወት ትምክህት)* አየች» (ዘፍ. 3፡6)።

የሥጋ ምኞት ለሰው የወደቀ ባሕርይ የሚጥመውን ማንኛውንም ነገር ያካትታል። «ሥጋ» «ሰውነት» አይደለም። ይልቁንም፥ ለመንፈሳዊ እውነት ዓይነ-ስውር የሚያደርገውን ዳግም ያልተወለደን ሰው መሠረታዊ ባሕርይ ያመለክታል (1ኛ ቆሮ. 2፡14)። ሥጋ ከሥጋዊ ልደት የምናገኘው ባሕርይ ሲሆን፥ መንፈስ ከሁለተኛው ልደት የምናገኘው ባሕርይ ነው (ዮሐ. 3፡5፥6)፥ በክርስቶስ ስናምን የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንሆናለን (2ኛ ጴጥ. 1፡4)። ክርስቲያን በሕይወቱ ውስጥ አሮጌ (የሥጋ) ባሕርይና አዲስ (የመንፈስ) ባሕርይ አሉት። እነዚህ ሁለቱ ባሕርያት የሚያካሂዱት ጦርነት ምንኛ የጠፈ ነው! (ገላ. 5፡17-23)።

እግዚአብሔር ለሰው የተወሰኑ ፍላጎቶችን ሰጥቷል፤ እነዚህም ፍላጎቶች መልካም ናቸው። ረሃብ፥ ጥማት፥ ድካም፥ ወሲብ በራሳቸው ክፉዎች አይደሉም። መብላት፥ መጠጣት፥ መተኛት፥ ወይም ልጅ

መውለድ ስሕተት አይደለም። ዳሩ ግን የሥጋ ባሕርይ በሚቆጣጠራቸው ጊዜ እነዚህ መልካም ነገሮች ኃጢአታዊ «ምኞቶች» ይሆናሉ። ረሃብ ክፉ ባይሆንም፥ ሆዳምነት ኃጢአት ነው። ጥማት ክፉ ባይሆንም፥ ስካር ኃጢአት ነው። እንቅልፍ የእግዚአብሔር ስጦታ ቢሆንም፥ ስንፍና አሳፋሪ ነገር ነው። በትክክል ሲጠቀሙበት ወሲብ የእግዚአብሔር መልካም ስጦታ ነው፤ በተሳሳተ መንገድ አገልግሎት ላይ ሲውል ግን ዝሙት ይሆናል።

እንግዲህ ዓለም ተግባሯን እንዴት እንደምታከናውን ታያለህ። ለተገቢ ፍላጎቶች ምክንያት በመስጠት ባልተገባ መንገድ እንድናረካቸው ትፈትነናለች። በዛሬው ዓለም ፍጥረታዊ ባሕርያችንን «የሥጋን ደካማነት» የሚፈታተኑ ሁሉም ዓይነት መስህቦች ከብበውናል። (ማቴ. 26፡41)። ክርስቲያን ለዚህ ነገር እጁን ቢሰጥ፥ «በሥጋ ሥራዎች» ውስጥ ይሳተፋል (ገላ. 5፡19–21 አስቀያሚውን ዝርዝር ይሰጠናል)።

አማኝ ስለ አሮጌ ተፈጥሮው ማለትም ስለ ሥጋ እግዚአብሔር የሚናገረውን ቢያስታውስ መልካም ነው። እግዚአብሔር ስለ ሥጋ የሚናገረው ሁሉ *አሉታዊ ነው። በሥጋ ውስጥ ምንም መልካም ነገር* የለም (ሮሜ 7፡18)። *ሥጋ ምንም* አይጠቅምም (ዮሐ. 6፡63)። ክርስቲያን *በሥጋ ሊታመን አይገባም* (ፊልጵ. 3፡3)። *ለሥጋ ማሰብ አይገባም* (ሮሜ 13፡14)። ስለሆነም ለሥጋ የሚኖር ሰው አሉታዊ ሕይወት ይመራል።

ዓለም ክርስቲያኖችን ለማጥመድ የምትጠቀምበት ሁለተኛው መሣሪያ «የዓይን አምሮት» ይባላል። አንዳንዴ ዓይኖች ፍላጎት እንደሚኖሩአቸው እንዘነጋለን። የሥጋ ምኞት በኃጢአት መንገድ እናገኛቸው ዘንድ እየፈተነን ለአሮጌ ባሕርይ ዝቅተኛ ፍላጎቶች እርካታን ይሰጣል። የዓይን አምሮት ግን ከዚህ በላቀ መንገድ ይሠራል። በዚህ ስፍራ የተመለከቱት እይታንና አእምሮን የሚያረኩ ምኞቶች ናቸው– ውስብስብና ምሁራዊ ምኞቶች።

በሐዋርያው ዮሐንስ ዘመን ግሪኮችና ሮማውያን ዓይንን ለሚማርኩ እንቅስቃሴዎችና መዝናኛዎች ራሳቸውን ሰጥተው ይኖሩ ነበር። የዛሬም ጊዜ ብዙ አልተለወጠም! ከቴሌቪዥን አንጻር፥ ምናልባትም ሁሉም ክርስቲያን፥ «ከንቱ ነገርን እንዳያዩ ዓይኖቼን መልስ» ብሎ ሊጸልይ ይገባል [መዝ. (119)፡37]።

ወታደሩ አካን (ኢያሱ 7) በኢያሱ ሠራዊት ላይ ሽንፈትን ያስከተለው ከዓይኖቹ አምሮት የተነሣ ነበር። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከተከለከላቸው የኢያሪኮ ከተማ ምንም ዓይነት ምርኮ

እንዳይወስዱ ቢያዛቸውም አካን ሊሰማ አልፈለገም። ሁኔታውንም ሲያስረዳ፥ «በዘረፋ መካከል አንድ ያማረ የሰናዖር ካባ፥ ሁለት መቶም ሰቅል ብር፥ ሚዛኑም አምሳ ሰቅል የሆነ ወርቅ አይቼ ተመኘኋቸው፥ ወሰድኋቸውም» ብሏል (ቁጥር 21)። የዓይን አምሮት ይህንን ሰው ወደ ኃጢአት መራው፤ ኃጢአትም በበኩሉ ሠራዊቱን ለሽንፈት ዳረገ።

እንደ ሌሎቹ የስሜት ሕዋሳት ሁሉ፥ ዓይኖች አሳብን ወደ አእምሮ የሚያስገቡ በሮች ናቸው። ስለሆነም፥ የዓይን አምሮት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረኑትን ምሁራዊ አሳቦች ሊያጠቃልል ይችላል። ክርስቲያኖች ዓለም በሚያስብበት መንገድ እንዲያስቡ የሚዳርግ ከፍተኛ ውጥረት አለ። አምላካችን ፈሪሃ-እግዚአብሔር ከሌለበት ምክር እንድንጠበቅ ያስጠነቅቀናል። ይህም ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ያልሆነውን ትምህርት ያገልላሉ ማለት ሳይሆን፥ ምሁራዊነት የእግዚአብሔርን ስፍራ እንዳይተካባቸው ይጠንቀቃሉ ማለት ነው።

ሦስተኛው መማሪያ የሕይወት ትምክህት ወይም ስለ ገንዘብ መመካት ነው። የእግዚአብሔር ክብር የተትረፈረፈና ሙሉ ሲሆን፥ የሰው ክብር ከንቱ ነው። እንዲያውም፥ ለ«መመካት» የተሰጠው የግሪኩ ቃል ታላቅነቱን በማሳየት ሰዎችን ለማስደነቅ የሚጥረውን ጉረኛ ሰው ለመግለጽ ያገለገለ ነው። ሁልጊዜም ሰዎች ከሌሎች በልጠው ለመታየት ሲጥሩ ኖረዋል። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ከሚያደርጓቸው ነገሮች ብዙዎቹን የሚያንግግሠው ትምክህተኛ የሕይወት ነጸብራቅ ነው።

አያሌ ሰዎች ከዓቅማቸው የላቀውን ቤት፥ መኪና፥ የቤት ውስጥ መገልገያ የሚገዙት ለምንድን ነው? ለነጋዴዎች ቅስቀሳ ራሳቸውን ሰጥተው ከገቢያቸው በላቀ ዕዳ ውስጥ የሚዘፈቁት ለምንድን ነው? በአብዛኛው ሌሎችን ለማስደነቅ ካላቸው የሕይወት ትምክህት የተነሣ ነው። ምንኛ ሀብታሞች ወይም ስኬታማ እንደሆኑ ሌሎች እንዲረዱላቸው ይፈልጋሉ።

ብዙዎቻችን ያንን ያህል ባንደፍርም፥ ሌሎችን ለማስደነቅ ሲሉ ሰዎች ምን ያህል የጅልነት ተግባር እንደሚፈጽሙ ማየት አስገራሚ ነው። ተፈላጊነትና ዝናን ለማግኘት ሲሉ ታማኝነትና እውነተኛነትን የሚሠዉም አሉ።

አዎን፥ ዓለም በሥጋ ምኞት፥ በዓይን አምሮትና በሕይወት ትምክህት አማካኝነት ክርስቲያኖችን ለመሳብ ይጥራል። ዓለም ከእነዚህ በአንዱ ዘልቆ ከገባና ስፍራም ከያዘ ክርስቲያን ወዲያውኑ ያውቀዋል። የአብን ፍቅር ደስታና የአብን ፈቃድ ለማድረግ የሚኖረውን መሻት ያጣል። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና መጸለይ አሰልቺ ሥራ

ይሆንበታል። ክርስቲያናዊ ኅብረትም እንኳ ባዶና ዋጋ የሌለው ሊመስለው ይችላል። ይህም የሚሆነው ሌሎች ሰዎች አንድን ነገር ስላጠፉ ሳይሆን፥ የክርስቲያኑ ልብ ዓለማዊነትን ስላዘለ ነው።

እዚህ ላይ ማንኛውም ክርስቲያን ከመቅጽበት ዓለማዊ እንደማይሆን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህም በዝግታ የሚከናወን ሂደት ነው። ቀዳሚው *ከዓለም ጋር መወዳጀቱ* ይሆናል (ያዕ. 4፡4)። ክርስቲያንና ዓለም በተፈጥሮ ጠላቶች ናቸው። «ወንድሞች ሆይ፥ ዓለም ቢጠላችሁ አትደነቁ» (1ኛ ዮሐ. 3፡13)። የዓለም ወዳጅ የሆነ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ጠላት ነው።

ቀጥሎ፥ ክርስቲያኑ *በዓለም እድፍ ይበከላል* (ያዕ. 1፡27)። ዓለም በአንድ ወይም ሁለት የሕይወት ክፍሎች ውስጥ አስቀያሚ ምልክቷን ትጥላለች፤ ይህም አማኙ ቀስ በቀስ የዓለምን መንገዶች ይቀበላል ማለት ነው።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ ዓለም ክርስቲያኑን መጥላት ታቆምና ልትወደው ትጀምራለች። ስለዚህ ሐዋርያው ዮሐንስ «ዓለምን አትውደዱ!» ሲል ያስጠነቅቀናል፤ ብዙውን ጊዜ ግን ከዓለም ጋር የሚኖረን ጓደኝነት ወደ ወዳጅነት ያመራል። በውጤቱም ክርስቲያኑ *ዓለምን ይመስላል* (ሮሜ 12፡2)፤ በዚህም ጊዜ አንዱን ከሌላው ነጥሎ ማየቱ አስቸጋሪ ይሆናል።

በክርስቲያኖች መካከል ዓለማዊነት ሰርጎ የሚገባው በብዙ ስውርና የማይታወቁ መልኮች ነው። አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ታላላቅ ስፖርተኞች፥ የፊልም ኮከቦች፥ ወይም የፖለቲካ መሪዎች ሁሉን ለሚችል አምላክ አንዳች እገዛ የሚያደርጉ ይመስል እንደ ጣዖታት ልናመልካቸው እንከጅላለን። ወይም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች፥ ያለ ሀብታሞችና ዝነኞች መልካም ፈቃድና የገንዘብ ድጋፍ የእግዚአብሔር *ሥራ* የሚታቀብ ይመስል ቅድሚያ ለእነርሱ እንሰጣለን። ብዙ የዓለማዊነት መልኮች ጥሩ ያልሆነ መጽሐፍ ማንበብና «በ*ሥጋዊ*» መዝናኛዎች መሳተፍን አያካትቱም።

የሚያሳዝነው ዓለምን *መምሰል ከዓለም ጋር የሚያስኮንን* መሆኑ ነው (1ኛ ቆሮ. 11፡32)። አንድ አማኝ ይህንን ኃጢአት ተናዝዞ ከፈረደበት እግዚአብሔር ይቅር ይለዋል፤ አለበለዚያ ግን እግዚአብሔር በፍቅር ይቀጣዋል። ክርስቲያን ከዓለም ጋር ሲኮነን ልጅነቱ አይወሰድበትም። ይልቁንም፥ ምስክርነቱንና መንፈሳዊ ጠቃሚነቱን ያጣል። ይሁንና፥ እጅግ በከፉ ሁኔታዎች ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን ሳይቀር አጥተዋል። (1ኛ ቆሮ. 11፡29-30ን አንብብ።)

የማሽቆልቆል ደረጃዎችና ውጤቶቻቸው በሎጥ ታሪክ ተብራርተዋል (ዘፍ. 13፡5-13፤ 14፡8-14፤ ምዕ. 19)። በመጀመሪያ ዓይኑን ወደ ሰዶም አነሣ። ከዚያም በኋላ እጅግ በለመለመው ውኃማ የዮርዳኖስ አካባቢ ድንኳኑን ለመዘርጋት አማተረ። ከዚያ በኋላ ወደ ሰዶም ተጓዘ። ይሁንና፥ ሰዶም በጠላት ስትወረር ሎጥም ተማረከ። አማኝ ቢሆንም እንኳ (2ኛ ጴጥ. 2፡6-8) ከማያምኑት የዚያች የኃጢአት ከተማ ነዋሪዎች ጋር ለመሠቃየት ተገደደ። እግዚአብሔር ሰዶምን በደመሰሰም ጊዜ ሎጥ ሕይወቱን የሰጠበት ነገር ሁሉ ተቃጠለ። ሎጥ ዘላለማዊ ሽልማቱን አጥቶ ከእሳት ተረፈ (1ኛ ቆሮ. 3፡12-15)።

ከዚህ አንጻር፥ ዮሐንስ ዓለምን እንዳንወድ ማስጠንቀቁ አስገራሚ አይደለም።

## 3. ከክርስቲያኑ ማንነት የተነሣ

ይህ አሳብ ስለ ክርስቲያን ባሕርይና ዓለማዊ ከመሆን ስለሚድንበት መንገድ ተግባራዊና አስፈላጊ ጥያቄ ያነሣል።

መልሱም የሚገኘው በ1ኛ ዮሐንስ 2፡12-14 ከተጠቀሱት ያልተለመዱ የስም መጥሪያዎች ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ ለክርስቲያን አንባቢዎቹ ሲጽፍ የተጠቀመባቸውን ስሞች ልብ በል፤ «ልጆች ሆይ... አባቶች ሆይ... ጎበዞች ሆይ... ልጆች ሆይ...»

ይኼ ሁሉ የሚያመለክተው ምንድን ነው?

በመጀመሪያ ደረጃ፥ «ልጆች» (ቁጥር 12) የሚለው *አማኞችን ሁሉ* ያመለክታል። የዚህ ቃል ቀጥተኛ ፍች «ዳግም የተወለዳችሁ» የሚል ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የተወለዱ ሲሆን፥ ኃጢአታቸውም ይቅር ተብሎላቸዋል። አንድ ሰው በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ሆኖ ባሕርዩን የመጋራት እውነታ ከዓለም ጋር ከመወዳጀት ሊጠብቀው ይገባ ነበር። ከዓለም ጋር መወዳጀት ክህደት ነው! «ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል» (ያዕ. 4፡4)።

ሌላም እውነት የሆነ ነገር አለ፤ የምንጀምረው በዳግም ልደት እንደ ትናንሽ ልጆች ቢሆንም፥ *በዚያው ማቆም የለብንም*። ክርስቲያን ዓለምን የሚያሸንፈው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሲያድግ ብቻ ነው።

ሐዋርያው ዮሐንስ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ሦስት ዓይነት ክርስቲያኖች እንዳሉ ይጠቅሳል፤ እነዚህም፥ አባቶች፥ ወጣቶችና፥ ልጆች ናቸው (1ኛ ዮሐ. 2፡12-14)። «አባቶች» የተባሉት

እግዚአብሔርን በቅርብ በግላቸው የሚያውቁ በሳል አማኞች ናቸው። እግዚአብሔርን ስለሚያውቁ የዓለምን አደጋዎች ያውቃሉ። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የማድረግንና የማገልገልን ድንቅ ልምምድና ደስታ የተመለከተ ማንኛውም አማኝ ይህች ዓለም የምትሰጠውን ተተኪ ምቾቶች አይፈልግም።

«ጎበዞች» የተባሉት ድል-ነሺዎች ናቸው። እነዚህ የዚህ ዓለም ሥርዓት አለቃ የሆነውን ክፉውን ሰይጣንን አሸንፈዋል። እንዴት አሸነፉት? በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት! «ጎበዞች ሆይ፥ ብርቱዎች ስለሆናችሁ የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር ክፉውንም ስለ አሸነፋችሁ እጽፍላችኋለሁ» (ቁጥር 14)። «ጎበዞች» ግን ሙሉ ለሙሉ ወደ መብሰሉ ደረጃ አልደረሱም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ስለሚጠቀሙ እየበሰሉ በመሄድ ላይ ናቸው። ሰይጣንን የሚያሸንፈው ብቸኛው መሣሪያ ቃሉ ነው (ኤፌ. 6፡17)።

በ1ኛ ዮሐንስ 2፡13 «ልጆች» የሚለው ቃል በቁጥር 12 ከተጠቀሰው የተለየ ነው፤ በዚህ ስፍራ ሁለት የተለያዩ የግሪክ ቃላት አገልግለዋል። በቁጥር 13 የተጠቀሰው ገና በአስተማሪዎች እንክብካቤ ሥር የሚገኙትን «ያልበሰሉ» ትናንሽ ልጆች ያመለክታል። እነዚህ ገና በክርስቶስ ያላደጉ «ወጣት ክርስቲያኖች» ናቸው። እንደ ትናንሽ ልጆች፥ እነዚህ መንፈሳዊ ልጆች አባታቸውን ቢያውቁም፥ ገና ማደግ ይጠበቅባቸዋል።

በዚህ ስፍራ ክርስቲያን ቤተሰብን እንመለከታለን! ሁሉም «ዳግም ተወልደዋል!» ዳሩ ግን አንዳንዶቹ ከሕፃንነት ወደ መንፈሳዊ ጉርምስናና አዋቂነት አድገዋል። *ዓለምን የማይወደው በብስለት እያደገ ያለ ክርስቲያን ነው።* አባቱን ለማፍቀርና ፈቃዱን ለመፈጸም እጅግ ደስ ይለዋል። የዓለም መስህብ አይማርከውም። የዓለም ነገሮች የሕፃናት አሻንጉሊቶች መሆናቸውን ስለሚያውቅ፥ እንደ ጳውሎስ፥ «ጎልማሳ ሆኜ የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ» ሊል ይችላል (1ኛ ቆሮ. 13፡11)።

ክርስቲያን ከዓለም የሚርቀው (ክርስቶስን የሚጠላና የሚቃወም ሰይጣናዊ ሥርዓት ካለው) (በኃጢአታዊ መተኪያዎች ላይ ተንተርሰን እንድንኖር በመማረክ) በእኛ ላይ ከምትፈጽመው ተግባርና የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆኑ (ክርስቲያኑ) ከተላበሰው ማንነት የተነሣ ነው።

## 4. ከዓለም የጉዞ አቅጣጫ የተነሣ

«ዓለምም ምኞቱም ያልፋሉ» (1ኛ ዮሐ. 2፡17)።

ይህንን ዓረፍተ ነገር ዓለም ማለትም የምንኖርበት ሥርዓት እንደማንኛውም ነገር ሁሉ ቋሚ ነው የሚሉ ብዙ ሰዎች ይፈታተኑታል። ይሁንና፥ ዓለም ቋሚ አይደለችም። ስለዚህች ዓለም የምናውቀው ብቸኛና እርግጠኛ ነገር ቢኖር ለዘላለሙ እንደማትኖር ነው። አንድ ቀን ሥርዓቱ ያልፍና ከውስጧ የተከማቹት ጣፋጭ መስህቦችም ይወገዳሉ፤ ሁሉም አላፊ ነው። ዘላቂው እንግዲህ ምንድን ነው?

*የእግዚአብሔር ፈቃድ አካል የሆነው ብቻ ለዘላለም ይኖራል!*

መንፈሳውያን ክርስቲያኖች የሚኖሩት ከዚህ እጅግ ለተሻለ ነገር በመሆኑ፥ ከዚህ ዓለም ጋር እስከዚህም የጠበቀ ግንኙነት አይመሠርቱም። «በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ» (ዕብ. 11፡13)። «በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና፥ ነገር ግን ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን» (ዕብ. 13፡14)። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን፥ ብዙ አማኞች በድንኳን ውስጥ ይኖሩ ነበር፤ ይህም እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ሳሉ በቤታቸው ተመቻችተው እንዲቀመጡ ስላልፈለገ ነው።

ዮሐንስ ሁለት የሕይወት ዘይቤዎችን ያነጻጽራል፤ እነዚህም ለዘላለምና ለጊዜው መኖር ናቸው። ዓለማዊ ሰው ለሥጋ ምኞት ሲኖር፥ ራሱን የሰጠ ክርስቲያን ግን ለመንፈስ ደስታ ይኖራል። ዓለማዊ አማኝ ሊያየው ለሚችለው ነገር በመኖር የዓይን አምሮቱን ለመወጣት ይፈልጋል፤ መንፈሳዊ አማኝ ግን ለማይታዩ የእግዚአብሔር ስውር እውነታዎች ይኖራል (2ኛ ቆሮ. 4፡8–18)። ዓለማዊ አስተሳሰብ ያለው ሰው ሰዎችን ለሚስብ ከንቱ ጉራ ማለትም ለሕይወት ትምክህት ይኖራል፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ክርስቲያን ግን የእግዚአብሔርን ተቀባይነትና ድጋፍ ለማግኘት ይኖራል። እርሱም «ለዘላለም ይኖራል።»

በታሪክ ሁሉም ታላላቅ አገሮች እያዘቀዘቁ መጥተው በመጨረሻ በሌሎች አገሮች ተሸንፈዋል። ስለሆነም፥ የራሳችን አገር ሁኔታ የተለየ እንደሚሆን የምናስብበት ምክንያት የለም። ከዚህ ቀደም የነበሩ ወደ 19 የሚሆኑ የዓለም ሥልጣኔዎች ዛሬ ተዘንግተዋል። ስለሆነም፥ የዛሬው ሥልጣኔ ለዘላለም እንደሚቆይ የምናስብበት ምክንያት የለም። ሄንሪ ኤፍ. ላይት (1793–1847)፥ «በዙሪያዬ ሁሉ ለውጥና ብስባሽ ይታየኛል»። ሲሉ ጽፈው ነበር። ሥልጣኔአችን በለውጥና ብስባሽ

ይቀየርና ክርስቶስ ሲመጣ በአዲስ የነገሮች ሥርዓት ይተካል፤ ይህም የክርስቶስ ምጽአት በማንኛውም ጊዜ ሊፈጸም የሚችል ነው።

ቀስ በቀስና ዳሩ ግን በማይቀር ሁኔታ ዓለም እያለፈች ነች፤ ይህም ምናልባት ክርስቲያኖች ከሚያስቡት በተፋጠነ መንገድ ነው፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሰው ግን ለዘላለም ይኖራል።

ይህ ማለት ግን የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁሉ በቀጣዩ ትውልድ ይታወሳሉ ማለት አይደለም። በምድር ላይ ከሚኖሩት እጅግ በርካታ ዝነኞች መካከል ለአንድ ምእተ ዓመት ያህል የሚታወሱት ከ2,000 ያነሱ ናቸው።

ወይም ደግሞ የእግዚአብሔር ባሪያዎች በጽሑፎቻቸው ወይም በለወጡአቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ ሲታወሱ ይኖራሉ ማለት አይደለም። የዚህ ዓይነቱ «ሕያውነት» እውነት ሊሆን ቢችልም፥ እንደ ካርል ማርክስ፥ ቮልቴር ወይም አዶልፍ ሒትለር ያሉትም በተግባራቸው ይታወሳሉ።

በዚህ ስፍራ የተገለጸው (1ኛ ዮሐ. 2:17) የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም፥ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ራሳቸውን የሰጡ ክርስቲያኖች «ለዘላለም እንደሚኖሩ» ነው። የዚህ ዓለም ሥርዓት ከትምክህተኛ ባህሉ፥ ከትዕቢተኛ ፍልስፍናው፥ ከራስ ወዳድ ምሁራዊነቱ፥ ብሎም ከአምላክ የለሽ ቁሳዊነቱ ጋር ከተዘነጋና ይህችም ምድር በአዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ከተተካች በኋላ፥ የእግዚአብሔር ታማኝ ባሪያዎች ለዘላለሙ የእግዚአብሔርን ክብር እየፈነጠቁ ይኖራሉ።

ይህም ዕድል ለሙዲ፥ ለስፐርጀን፥ ለሉተር ወይም ለዌስሊና ለመሳሰሉት ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ ይልቁንም ለሁሉም ያልታወቀ አማኝ ክፍት ነው። አንተም በክርስቶስ የምታምን ከሆንህ *ያንተው* ነው።

ይህ የአሁኑ ዓለም ሥርዓት ዘላቂ አይደለም። «የዚህች ዓለም መልክ አላፊ ነውና» (1ኛ ቆሮ. 7:31)። በዙሪያችን ያለው ነገር ሁሉ ይለወጣል፤ ዘላለማዊ የሆኑ ነገሮች ግን ከቶውንም አይለወጡም። ይሁንና፥ ዓለምን የሚወድ ክርስቲያን በለውጥ ሂደት ውስጥ ከሚገኝ ነገር ጋር ሕይወቱን አጠላልፎአልና ከቶውንም ሰላም ወይም ፀጥታ ሊኖረው አይችልም። ሚሲዮናዊው ሰማዕት ጂም ኤሊዬት፥ «ሊያጣ የማይችለውን ለማግኘት በእጁ ሊያቆይ የማይችለውን የሚሰጥ ሞኝ አይደለም» ሲሉ ጽፈዋል።

አዲስ ኪዳን ስለ «እግዚአብሔር ፈቃድ» ብዙ የሚለው አለው። ከደኅንነት «ትርፍ ጠቀሜታዎች» አንዱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ

ማወቅ ነው (የሐዋ. 22:14)። እንዲያውም፥ እግዚአብሔር የሚፈልገው በፈቃዱ እውቀት እንሞላ ዘንድ ነው (ቆላ. 1:9)። የእግዚአብሔር ፈቃድ የጠቃሚ ጉዳዮችን ምሥጢር እንደ ያዘው ስንክሣር ወይም «ኢንሳይክሎፒድያ» መጽሐፍ አንዳንዴ የምንጠቀምበት አይደለም። ይህ ሕይወታችንን ሙሉ ለሙሉ የሚቆጣጠር ነገር ነው። ራሱን ለሰጠ ክርስቲያን ዋንኛው ጉዳይ የአንድ ነገር «ትክክለኛነት ወይም ስሕተተኛነት» ወይም «መልካምነት ወይም ክፋነት» ብቻ አይደለም። ዋንኛው ጉዳይ፥ «ይህ ለእኔ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ወይ?» የሚለው ነው።

እግዚአብሔር በአእምሮአችን እንድናውቀው ብቻ ሳይሆን የፈቃዱን ምንነት እንድንረዳም ይፈልጋል (ኤፌ. 5:17)። «ለሙሴ መንገዱን አስታወቀ፥ ለእስራኤል ልጆችም አደራረጉን» [መዝ. (103):7]። እስራኤላውያን እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን ሲያውቁ፥ ሙሴ ግን ለምን የሚያደርገውን እንደሚያደርግም ያውቅ ነበር! እኛም እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን ፈቃዱን ብንረዳና የሚፈጽማቸውን ዓላማዎች ብናውቅ መልካም ነው።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካወቅን በኋላ ከልባችን ልንፈጽመው ይገባል (ኤፌ. 6:6)። እግዚአብሔርን የምናስደስተው ስለፈቃዱ በመነጋገር ብቻ ሳይሆን፥ የሚነግረንን በመፈጸም ነው (ማቴ. 7:21)። እንዲሁም እግዚአብሔርን ይበልጥ በታዘዝን መጠን ፈቃዱን የማወቅና የመፈጸም ብቃታችንም ይጨምራል (ሮሜ 12:2)። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና ማድረግ ከውኃ ዋና ልምምድ ጋር ይመሳሰላል፤ ይኸውም ዋናው በሕይወትህ እውነተኛ ክንዋኔ ከመሆኑ በፊት ወደ ውኃ ውስጥ ጠልቆ መግባት ስለሚኖርብህ ነው። እንደዚሁም እግዚአብሔርን ይበልጥ በታዘዝን መጠን እናደርግ ዘንድ የሚፈልገውን በማወቁ ረገድ ይበልጥ ብቁዎች እየሆንን እንመጣለን።

የእግዚአብሔር ዓላማ ለእኛ በእርሱ ፈቃድ ሁሉ ምሉዓን ሆነን እንድንቆም ነው (ቆላ. 4:12)። ይህም በእግዚአብሔር ፈቃድ «መብሰል» አለብን ማለት ነው።

ትንሽ ልጅ ትክክል ስለሆነውና ስላልሆነው፥ ብሎም ወላጆቹ እንዲያደርግ ስለሚፈልጉትና ስለማይፈልጉት ነገር በተደጋጋሚ ይጠይቃቸዋል። ዳሩ ግን ከወላጆቹ ጋር ሲኖር ሥልጣናቸውንና ትምህርታቸውንም ሲቀበል፥ ቀስ በቀስ ለእርሱ ያላቸውን ፈቃድ ይረዳል። እንዲያውም፥ የተማረ ልጅ የወላጆቹን ፊትና ዓይኖች ብቻ በማየት «የአባቱን አሳብ ሊያነብብ» ይችላል። ያልበሰለ ክርስቲያን ሁልጊዜም ለእርሱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ለማወቅ

ወዳጆቹን ይጠይቃል። በሳል ክርስቲያን ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ተደላድሎ ይቆማል። ጌታ ምን እንዲያደርግ እንደሚፈልግ ያውቃል።

አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊያውቅ የሚችለው እንዴት ነው? ሂደቱ የሚጀምረው ራስን «በመስጠት» ነው፤ «ሰውነታችሁን...ሕያው... መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ...እለምናችኋለሁ... የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ [በልምምድ] ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ» (ሮሜ 12፡1-2)። ዓለምን የሚወድ ክርስቲያን በምንም ዓይነት በዚህ መልኩ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊያውቅ አይችልም። አብ ምሥጢራቱን የሚያጋራው ለሚታዘዙት ነው። «ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል» (ዮሐ. 7፡17)። በተጨማሪም፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ክርስቲያን የሚፈልገውን ወስዶ ሌላውን የሚተውበት «መንፈሳዊ ምግብ ቤት» አይደለም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሙሉ ለሙሉ መቀበል የግድ ነው። ይህም የራስን ሕይወት ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር መስጠትን ያካትታል።

እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚገልጽልን በቃሉ አማካኝነት ነው። «ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው» [መዝ. (119)፡105]። ዓለማዊነት የሚያጠቃው አማኝ ለመጽሐፍ ቅዱስ ፍላጎት የለውም። ሲያነብበውም የሚያገኘው ጥቅም ኢምንት ወይም ምንም ነው። ዳሩ ግን በየዕለቱ ቃሉን በማንበብና በዚያውም ላይ በማሰላሰል በቂ ጊዜ የሚያሳልፈው መንፈሳዊ አማኝ፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከዚያው አግኝቶ ከዕለታዊ ሕይወቱ ጋር ያዛምደዋል።

ምናልባት ከሁኔታዎችም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልንማር እንችላለን። እግዚአብሔር በሮችን ለመክፈትና ለመዝጋት በሚያስደንቁ መንገዶች ይንቀሳቀሳል። ስለሆነም የዚህ ዓይነቱን ምሪት በእግዚአብሔር ቃል ልንፈትን ይገባል፤ ዳሩ ግን የመጽሐፍ ቅዱስን ግልጽ አስተምህሮ በሁኔታዎች ልንፈትን አይገባም!

በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር ወደ ፈቃዱ የሚመራን በጸሎትና በልባችን ውስጥ ባለው የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ነው። ስለ አንድ ውሳኔ ስንጸልይ መንፈስ ቅዱስ ይናገረናል። በዚህም ጊዜ «ውስጣዊው ድምፅ» ከሁኔታዎች ምሪት ጋር ሊስማማ ይችላል። ዳሩ ግን ይህንን «ውስጣዊ ድምፅ» ብቻ ልንከተል አይገባም፤ ሁልጊዜም በመጽሐፍ ቅዱስ መፈተን አለብን፤ ይህም ሥጋ ወይም ሰይጣን ሁኔታዎችን

ወይም የራሳችንን ስሜቶች በመጠቀም ወደማንመለስበት መቀመቅ ሊከተን ስለሚችል ነው።

ለማጠቃለል፥ ክርስቲያን በሥጋው በዓለም ውስጥ ቢሆንም (ዮሐ. 17፡11)፥ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ከዓለም አይደለም (ቁጥር 14)። ክርስቶስ ወደ ዓለም የላከን ለስሙ እንድንመሰክርለት ነው (ቁጥር 18)። በጥልቁ የውኃ ክፍል ውስጥ እንደሚዋኝ ሰው በተገጠመልን መሣሪያ መጠቀም አለብን፤ ካልተጠነቀቅን ደግሞ ውኃው ሊያጠፋን ይችላል። ክርስቲያን በዓለም ውስጥ ከመኖር ራሱን ሊያቅብ አይችልም፤ ዳሩ ግን ዓለም በክርስቲያን ውስጥ መኖር ስትጀምር ችግር ይፈጠራል!

ዓለም ወደ ክርስቲያን የምትገባው በልቡ ነው፤ «ዓለምን አትውደዱ!» ክርስቲያን በአባቱ ፍቅር እንዳይደሰት ወይም የአባቱን ፈቃድ እንዳይፈጽም የሚያደናቅፍ ነገር ሁሉ ዓለማዊ ስለሆነ ሊወገድ ይገባል። በእግዚአብሔር ቃል በመመሥረት ሁሉም አማኝ እነዚያን ነገሮች ለራሱ ሊለያቸው ያሻል።

ክርስቲያን፥ «የምኖረው ለአሁኑ ዓለም ነው ወይስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ ለዘላለም እዘልቃለሁ?» ብሎ ሊጠይቅና ለራሱ ሊወስን ይገባል። ኢየሱስ ስለ ሁለት ሰዎች በመናገር ስለዚሁ ምርጫ አብራርቷል (ማቴ. 7፡24–27)። ጳውሎስም ስለ ሁለት ዓይነት የግንባታ መሣሪያዎች ማለትም ጊዜያዊና ዘለቄታዊ በመናገር ይህንኑ ተመሳሳይ አሳብ ገልጾአል (1ኛ ቆሮ. 3፡11–15)።

እግዚአብሔር የሚጠላው ፍቅር ዓለምን መውደድ ነው። ስለሆነም ይህ ክርስቲያን ሙሉ ለሙሉ ሊያስወግደው የሚገባው ዓይነት ፍቅር ነው!

# — 5 —

# እውነት ወይም ከእውነት የመራቅ ውጤቶች

## 1ኛ ዮሐንስ 2፡18–29

«እውነተኛ እስከሆንህ ድረስ የምታምነው ነገር ለውጥ አያመጣም!»

ይህ ዓረፍተ ነገር ዛሬ የብዙ ሰዎችን ግላዊ ፍልስፍና ያንጸባርቃል፤ ይሁንና፥ ይህንን የሚሉ ሰዎች በደንብ አስበውበት መናገራቸው አጠራጣሪ ነው። «እውነተኛነት» አንድን ነገር እውነት የሚያደርግ ምትሐታዊ አካል ይሆን? ይህ ከሆነ ደግሞ ለሃይማኖት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የሕይወት ክፍሎች ማዛመድ ያሻል።

አንዲት የሆስፒታል ነርስ ለህመምተኛዋ የሆነ መድኃኒት ሰጠችው። ግን ሰውዬው ከበፊቱ ይበልጥ ታመመ። ምንም እንኳ ሐኪሟ እውነተኛ ብትሆንም መድኃኒቱ ግን የተሳሳተ በመሆኑ፥ በሽተኛው ወደ ሞት አፋፍ ተቃረበ።

አንድ ሌሊት ሰውዬው በቤት ውስጥ የሆነ ድምፅ ሰማና ሌባ እንደገባ በርግጠኛነት አሰበ። ሽጉጡንም አቀባብሎ «በሌባው» ላይ ተኮሰ፤ ለካስ ልጁ ኖራለች! በረሃብ ሳቢያ እንቅልፍ ስላልወሰዳት የሆነ ነገር ልትበላ ተነሥታ ነበር። ሆኖም የአባቷ «እውነተኛ» ግምት ሰለባ ሆነች።

አንድን ነገር እውነት ለማድረግ ከእውነተኛነት የበለጠ እርምጃ ይጠይቃል። ሐሰተኛ ነገር ማመን ሁልጊዜም አደገኛ ውጤቶችን ያስከትላል፤ በእውነት ማመን ግን ከቶውንም የሚያሳፍር አይሆንም። *ስለሆነም አንድ ሰው የሚያምነው ነገር ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል!* አንድ ሰው ከአዲስ አበባ ተነሥቶ ወደ ጅማ በመኪናው ለመሄድ ቢፈልግ፥ መንገዱ ወደ ጎንደር የሚመራ ከሆነ ምንም ዓይነት እውነተኛነት እዚያ ሊያደርሰው አይችልም። *እውነተኛ* የሆነ ሰው ሕይወቱን የሚመሠርተው በእውነት ላይ እንጂ በአጉል እምነት ወይም በውሸት ላይ አይደለም። ስለሆነም ውሸትን በማመን እውነተኛ ሕይወት መኖር አይቻልም።

እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንን ቤተሰብ (ልጆች) በብርሃንና በጨለማ (1፡1–2፡6)፥ በፍቅርና በጥላቻ (2፡7–17) መካከል ስላለው ግጭት በመግለጽ አስጠንቅቋል። አሁን ደግሞ ስለ ሦስተኛው ማለትም በእውነትና በስሕተት መካከል ስላለው ግጭት ያስጠነቅቃቸዋል። ለአማኝ በብርሃንና በፍቅር መመላለሱ ብቻ

አይበቃም፤ በእውነትም መመላለስ አለበት። ዋናው፥ እውነት ወይም ውጤቱ ነው!

ዮሐንስ ከእውነት የመመለስን አሳዛኝ ውጤቶች ከማብራራቱ በፊት፥ በጉዳዩ ክብደት ላይ ያተኩራል። ይህንንም የሚያደርገው ሁለት ልዩ ቃላት በመጠቀም ነው፤ እነዚህም «የመጨረሻው ዘመን» እና «የክርስቶስ ተቃዋሚ» (ሐሳዊ መሲሕ) የሚሉ ናቸው። ሁለቱም ቃላት ክርስቲያኖች በተቃወሰ ዘመን እንደሚኖሩና ከጠላት ስሕተቶች መጠበቅ እንዳለባቸው በግልጽ ያስቀምጣሉ።

«የመጨረሻው ዘመን» ወይም «የመጨረሻው ሰዓት» በዓለም ላይ የአዲስ ዘመን ጮራ እንደፈነጠቀ የሚያስታውሰን ነው። «ጨለማው ያልፋልና እውነተኛውም ብርሃን አሁን ይበራል» (2፡8)። ከኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ፥ እግዚአብሔር በዚህች ዓለም «አዲስ ነገር» እያደረገ ነው»። የብሉይ ኪዳን ታሪክ ሁሉ በመስቀል ላይ ለሚፈጸመው የክርስቶስ ሥራ ጥርጊያ መንገድ አዘጋጅቷል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያለው ታሪክ ኢየሱስ ተመልሶ መንግሥቱን ለሚመሠርትበት «ፍጻሜ ዘመን» መዘጋጃ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለማዳን ከዚህ የበለጠ ሊያደርግ የሚገባው ነገር የለም።

ይህም ሆኖ፥ «የዮሐንስ ዘመን ‹የመጨረሻው ዘመን› ከተባለ ኢየሱስ ለምን እስካሁን አልተመለሰም?» ብለህ ትጠይቅ ይሆናል።

ይህ ውብ ጥያቄ ስለሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠንን መልስ እንመለከታለን። እግዚአብሔር እንደ ፍጥረቱ በጊዜ የተገደበ አይደለም። እግዚአብሔር በሰዎች ጊዜ ውስጥ ይሠራል እንጂ ከጊዜ *በላይ* ነው (2ኛ ጴጥ. 3፡8)።

«የመጨረሻው ሰዓት» የተጀመረው በሐዋርያው ዮሐንስ ዘመን ሲሆን፥ *ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጥልቀት እያደገ ነው።* በዮሐንስ ዘመን እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሐሰተኛ መምህራን ነበሩ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በቁጥርም በተጽዕኖም ጨምረዋል። «የመጨረሻው ሰዓት» ወይም «የመጨረሻው ዘመን» የሚሉ ሐረጎች የጊዜውን *ዓይነት* እንጂ የጊዜውን *ገደብ* አይገልጹም፤ «የኋለኞቹ ዘመናት» በ1ኛ ጢሞቴዎስ 4 ውስጥ ተገልጾአል። ጳውሎስም እንደ ዮሐንስ ሁሉ የዘመኑን ባሕርያት የተመለከተ ሲሆን፥ እኛም ዛሬ በበለጠ ጥልቀት ተመሳሳይ ባሕርያት እንመለከታለን።

በሌላ አባባል፥ ክርስቲያኖች *ሁልጊዜም* የኖሩት «በመጨረሻው ዘመን» ማለትም በስንክሳር ቀናት ውስጥ ነው። ስለሆነም፥ የምታምነውንና የምታምንበትን ምክንያት ማወቁ አስፈላጊ ነው።

(የክርስቶስ ተቃዋሚ) «ሐሳዊ መሢሕ» የሚለውን ሁለተኛ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጠቀሰው ዮሐንስ ብቻ ነው (1ኛ ዮሐ. 2:18፥ 22፤ 4:3፤ 2ኛ ዮሐ. 7)። ይህም ሦስት ነገሮችን ይገልጻል፤ 1) በዓለም ውስጥ ክርስቶስን የሚቃወም ወይም የሚክድ መንፈስ፥ 2) ይህንኑ መንፈስ የሚቀበሉ ሐሰተኛ አስተማሪዎች እና 3) በክርስቶስ ላይ የሚነሣውን የመጨረሻ የዓለም ዓመፅ የሚመራ ሰው።

ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት ካወጀበት ጊዜ አንሥቶ «የሐሰተኛው ክርስቶስ መንፈስ» (1ኛ ዮሐ. 4:3) በዓለም ነበረ (ዘፍ. 3)። ከሁሉም የሐሰት ትምህርትና ክርስቲያኖች በክርስቶስ ላገኙአቸው እውነታዎች መተኪያ ለሚቀርቡ «ሃይማኖታዊ አሳቦች» ሁሉ የኋላ ደጀን ሆኖ የሚሠራው «የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ» ነው። *«ተቃዋሚ» ወይም «ሐሳዊ»* የሚለው ቃል በግሪኩ ሁለት ትርጉሞች ነበሩት። እነዚህም በክርስቶስ «ምትክ» እና ክርስቶስን «በመቃወም» የሚሉ ናቸው። ሰይጣን በክፋቱ ከክርስቶስና ከዘላለማዊ እውነቱ ጋር *በመዋጋት* ላይ ይገኛል፤ በተጨማሪም፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ለሚገኙ እውነታዎች *መተኪያ* እያቀረበልን ነው።

«የሐሳዊ መሢሑ መንፈስ» ዛሬ በዓለም ውስጥ አለ። ይህም በመጨረሻው መጽሐፍ ቅዱስ «ሐሳዊ-መሢሕ» ብሎ ወደሚጠራው «ሰይጣናዊ የላቀ ሰው» መገለጽ ይመራል። ይህም «የዓመፅ ሰው» ተብሏል (2ኛ ተሰ. 2:1-12)።

ይህ ክፍለ ንባብ ዛሬ በዓለም ውስጥ ሁለት ኃይሎች በመሥራት ላይ እንደሚገኙ ይገልጻል፤ እነዚህም፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት የሚሠራው እውነታና በሰይጣን ጉልበት የሚሠራው ክፋት ናቸው። ዛሬ በክርስቲያኖች ውስጥ የሚገኘው መንፈስ ቅዱስ ዓመፀኛነትን በመከላከል ላይ ይገኛል፤ ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን በመነጠቅ ስትወሰድ (1ኛ ተሰ. 4:13-18) ሰይጣን ጊዜያዊ ድሉን ለመቀዳጀትና ዓለምን ለመግዛት ዕድሉን ያገኛል። (በዮሐንስ ራእይ ስለዚህ የዓለም ገዥና ክፉ ሥርዓቱ በስፋት የሚለው አለው፥ በተለይም በ13:1-18፤ 16:13 እና 19:20።)

የምታምነው ነገር የሚያስከትለው ለውጥ አለ? አዎን፥ ከፍተኛውን ለውጥ ያስከትላል። የምትኖረው በቀውጢ ጊዜ ማለትም በመጨረሻው ሰዓት ነው፤ እናም የሐሳዊ-መሢሕ መንፈስ በዓለም ውስጥ እየሠራ ነው። እውነትን አውቆ ማመኑና ውሸት ሲያጋጥምህ ለይቶ መረዳቱ እጅግ አስፈላጊ ነው።

የዮሐንስ መልእክት «በሐሳዊ–መሢሕ መንፈስ» ቁጥጥር የሚሠራውን የሐሰተኛ አስተማሪ ሦስት ዓይነተኛ ምልክቶች ይገልጻል።

## 1. ከኅብረቱ ይለያል (1ኛ ዮሐ. 2፡18–19)

«ከእኛ ዘንድ ወጡ፥ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም። ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር» (ቁጥር 19)።

«እኛ» የሚለው ቃል መቼም የአማኞችን ኅብረት ማለትም ቤተ ክርስቲያንን የሚገልጽ ነው። የአማኞች ጉባኤ አካል የሆነው ሁሉ የግድ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ላይሆን ይችላል።

አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያንን እንደ አንዲት ዓለም–አቀፍ ቤተሰብና እንደ አጥቢያ አካላት ወይም የአማኞች ጉባኤዎች ለይቶ በሁለት ገጽታ ያቀርባታል። ጠቅላላው ዓለም–አቀፍ የአማኞች አንድነት *ከሰውነት* (1ኛ ቆሮ. 12) እና *ከሕንፃ* (ኤፌ. 2፡19–22) ጋር ተወዳድሮአል። አንድ ኃጢአተኛ ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ በሚያምንበት ጊዜ የዘላለምን ሕይወት ይቀበልና ወዲያውኑ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባልና የክርስቶስ መንፈሳዊ አካል ክፍል ይሆናል። ከዚያ በኋላ ከአጥቢያ የክርስቲያኖች ቡድን (ቤተ ክርስቲያን) ጋር በመተባበር ክርስቶስን ማገልገል ሊጀምር ይገባል (የሐዋ. 2፡41፥ 42)። ይሁንና፥ በዚህ ስፍራ ላይ አጽንኦት የተሰጠው አንድ ሰው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሊሆንና የክርስቶስ እውነተኛ መንፈሳዊ አካል ክፍል ላይሆን እንደሚችል ነው።

የእውነተኛ ክርስትና ሕይወት አንዱ መረጃ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ለመተባበር መሻት ነው። «እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እናውቃለን» (1ኛ ዮሐ. 3፡14)። ሰዎች አንዱን መለኮታዊ ባሕርይ ሲጋሩና (2ኛ ጴጥ. 1፡4) የአንዱ መንፈስ ማደሪያ ሲሆኑ (ሮሜ 8፡14–16)፥ በኅብረት ደስ ሊሰኙና እርስ በርሳቸው አሳቦችን ሊካፈሉ ይፈልጋሉ። አስቀድመን እንደተመለከትነው፥ *ኅብረት* ማለት *«መጋራት»* ማለት ነው። ስለሆነም፥ ሰዎች የጋራ መንፈሳዊ እውነታዎች ሲኖሩአቸው በአንድነት ሊሆኑ ይፈልጋሉ።

ይሁንና፥ በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ ሁለት የተጠቀሱት «አስመሳይ ክርስቲያኖች» በኅብረቱ ውስጥ *አልጸኑም።* ወጥተው ሄዱ። ይህ ማለት ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖር አንድን ሰው እንደሚያድን አያመለክትም፤ ይልቁንም በኅብረቱ ውስጥ መቆየት ሰውዬው እውነተኛ ክርስቲያን እንደሆነ ያመለክታል። ኢየሱስ ስለ ዘሪው

በተናገረው ምሳሌ (ማቴ. 13፡1-9፥ 18-23) እውነተኛ ዳግም ልደት ያገኙት ፍሬ የሚያፈሩት ብቻ እንደሆኑ ገልጾአል። ወደ ደኅንነት ገጠመኝ ከቀረቡና እንዲያውም አንዳንድ «የክርስቲያኖች» ጠባያት ከያዙ በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ አለመሆን ይቻላል። በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ ሁለት የተጠቀሱት ሰዎች ኅብረቱን የለቀቁት እውነተኛውን ሕይወት ስላላገኙና በልባቸውም የክርስቶስ ፍቅር ስላልነበረ ነው።

ዛሬ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል አያሌ አሳዛኝ ክፍፍሎች ይታያሉ፤ ይህም ሆኖ፥ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት ባሻገር የሚጋሩአቸው ነገሮች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነና ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያምናሉ። እንዲሁም ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች እንደሆኑና ብቸኛው የመዳኛ መንገድ በክርስቶስ ማመን እንደሆነ ያምናሉ። ክርስቶስ ለሰው ምትክ ሆኖ በመስቀል ላይ እንደሞተና ከሞትም እንደተነሣ ያምናሉ። መንፈስ ቅዱስ በእውነተኛ አማኞች ልብ ውስጥ እንደሚያድር ያምናሉ። በመጨረሻም፥ ወደፊት አንድ ቀን ኢየሱስ እንደሚመለስ ያምናሉ። ክርስቲያኖች እንደ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ወይም የጥምቀት አሠራር በመሳሰሉ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ላይስማሙ ቢችሉም፥ በመሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች ላይ ይስማማሉ።

በዛሬው ዓለም ሐሰተኞች ትምህርቶችንና ክርስቶስን የሚቃወሙ የሃይማኖት ዘይቤዎች ብትመረምር፥ በአብዛኛው የእነዚህ ሃይማኖቶች መሪዎች *ከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት* እንደወጡ ትረዳለህ። «ከእኛ ጋር» ቢኖሩም፥ «ከእኛ ወገን አልነበሩም»ና የራሳቸውን ቡድኖች አፈሩ።

ምንም ያህል «ሃይማኖታዊ» ቢሆንም፥ ከእምነት ትምህርቶች የተነሣ ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ከተገነጠለ ቡድን ሁሉ ሊጠረጠር ይገባል። በአብዛኛው እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስንና የእግዚአብሔርን ቃል መከተልን ትተው ሰብአዊ መሪዎችንና ሰዎች የጻፉአቸውን መጻሕፍት ይከተላሉ። አዲስ ኪዳን ከኅብረት መገንጠሉ አደገኛ እንደሆነ ያስተምራል (ለምሳሌ 2ኛ ጢሞ. 3 እና 4፤ 2ኛ ጴጥ. 2)።

## 2. እምነትን ይከዳል (1ኛ ዮሐ. 2፡20-25፤ 4፡1-6)።

ለክርስቲያን ዋንኛው ጥያቄ፥ ክርስቶስ ኢየሱስ ማን ነው? ክርስቶስ «ምሳሌ» ብቻ ነውን? «ደግ ሰው» ነው? «ግሩም መምህር» ነው? ወይስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ? የሚለው ነው።

የዮሐንስ መልእክት አንባቢዎች ስለ ክርስቶስ እውነቱን ያውቁ ነበር፤ አሊያማ ባልዳኑ ነበር። «እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፥... የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ... በእርሱ ኑሩ» (ቁጥር 20 እና 27ን ተመልከት)። «የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም» (ሮሜ 8:9)።

በዮሐንስ ዘመን የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች ልምምዳቸውን ለመግለጽ ሁለት ልዩ ቃላት ማለትም «እውቀት»ን እና «ቅባት»ን ይጠቀሙ ነበር። እነዚህ ሰዎች ልዩ እውቀት ያስገኘላቸውን ቅባት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደተቀበሉ ይናገሩ ነበር። «አብርሆት»ን ያገኙ በመሆናቸው ከማንም በላይ ከፍ ብለው እንደተሰየሙ ይገልጹ ነበር። ዮሐንስ ግን እውነተኛ ክርስቲያኖች *«ሁሉ»* እግዚአብሔርን እንደሚያውቁና የእርሱንም መንፈስ እንደተቀበሉ አስረድቶአል። እንዲሁም እውነትን ስላመኑ ውሸት ሲያጋጥማቸው ለይተው ያውቁታል።

ክርስቲያኖችን ከሌሎች የሚለየው ትልቁ ማረጋገጫ *ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋው የተገለጠ አምላክ መሆኑ ነው* (1ኛ ዮሐ. 4:2)።

ክርስቲያን ነኝ የሚሉ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ሁሉ በእምነታቸው እውነተኛ ክርስቲያኖች አይደሉም (4:1–6)። ኢየሱስ በሥጋ የመጣ አምላክ እንደሆነ ቢመሰክሩ ግን የእውነተኛው እምነት አባላት መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። ክርስቶስን ቢክዱ ግን የሐሳዊ መሲሑ ወገኖች ናቸው ማለት ነው። በዓለም «ውስጥ» የሚገኙ «የዓለም ንብረቶች» እንጂ ከዓለም ተጠርተው «እንደወጡ» እውነተኛ አማኞች አይደሉም። ሲናገሩም ዓለሙ (ያልዳኑ ሰዎች) ያምናቸዋል። ነገር ግን ያልዳነው ዓለም ከቶውንም እውነተኛውን አማኝ ሊረዳ አይችልም። ክርስቲያን የሚናገረው በእውነት መንፈስ ምሪት ነው፤ ሐሰተኛ አስተማሪ የሚናገረው ግን በስሕተት መንፈስ ማለትም በክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ተጽዕኖ ነው።

«ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ» መመስከር ክርስቶስን ከማወቅ የጠለቀ አሳብ ይዞአል። አጋንንት አውቀውታል (ማር. 1:24)፤ ይህ ግን አላዳናቸውም። እውነተኛ ምስክርነት በክርስቶስ ማንነትና ተግባር በግል ማመንን ያካትታል። ይህ ምሁራዊ «ሥነ–መለኮታዊ መግለጫ» ብቻ ሳይሆን፥ ክርስቶስ ስላደረገልህ ነገር ከልብህ የሚመነጭ ግላዊ ምስክርነት ነው። ስለሆነም፥ በክርስቶስ ካመንህና እምነትህን በምስክርነት ከገለጥህ የዘላለም ሕይወት አለህ (1ኛ ዮሐ. 2:25)። ይህንኑ ምስክርነት (የእምነት መግለጫ) በእውነተኛነት

የማይገልጹ ሰዎች የዘላለም ሕይወት የላቸውም። ይህም እጅግ አደገኛ ነገር ነው።

ታላቁ የብሪታኒያ ወንጌላዊ ጆርጅ ኋይት ፊልድ ለአንድ ሰውዬ ስለ ነፍሱ እየተናገረ ነበር። ከዚያም፥ «ጌታዬ፥ እርስዎ ምን ያምናሉ?» ሲል ሰውዬውን ጠየቀው።

ሰውዬውም፥ «ቤተ ክርስቲያኔ የምታምነውን አምናለሁ» ሲል መለሰለት።

«ቤተ ክርስቲያንዎ ምን ታምናለች?»

«እኔ የማምነውን።»

«ሁለታችሁም የምታምኑት ምንድን ነው?»

«ሁለታችንም በአንድ ነገር እናምናለን!» ነበር የመጨረሻ ቃሉ።

ሰው ከቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫ ጋር በመስማማቱ አይድንም። ሰው የሚድነው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንና ለእምነቱም ምስክርነት በመስጠት ነው (ሮሜ 10፡9–10)።

የሐሰት አስተማሪዎች ብዙ ጊዜ፥ «እኛ አብን እናመልካለን። ምንም እንኳ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለን አመለካከት ከእናንተ ቢለይም፥ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን» ይላሉ።

ይሁንና፥ ወልድን መካድ ማለት አብንም መካድ ነው። ሁለቱም አንድ አምላክ በመሆናቸው፥ አብንና ወልድን ልንለያይ አንችልም። ኢየሱስ፥ «እኔና አብ አንድ ነን» ብሏል (ዮሐ. 10፡30)። እንዲሁም፥ እውነተኛ አማኞች ሁለቱንም አብንና ወልድን እንደሚያከብሩ ተናግሯል፤ «ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው...ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም» (ዮሐ. 5፡23)። ስለሆነም፥ «አንዱን አምላክ አምልኩ» ብትል ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ከአምልኮ ውጭ ብታደርግ፥ እንደ እውነተኛ ክርስቲያን እያመለክህ አይደለህም።

ከእግዚአብሔር ቃል እውነት ጋር መኖሩ አስፈላጊ ነው። ክርስቲያኖች ከመጀመሪያው የሰጡት ቃል (ወይም መልእክት) ለእምነቱ እውነተኛ ሆነህ እንድትኖር የሚረዳህ ነው። የክርስትና ሕይወት ሂደቱን የሚቀጥለው በጀመረበት መልኩ ነው። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት በማመን ነው። ክርስቲያኖች ከመጀመሪያ ከሰሙት አሳብ ጋር የሚቃረን አንድ «አዲስ ነገር» ይዞ የመጣ የሃይማኖት መሪ ሊታመን አይገባም። «መናፍስት ከእግዚአብሔር

ሆነው እንደሆነ መርምሩ» (1ኛ ዮሐ. 4፡1)። ቃሉ በአንተ ይኑር (2፡24)፤ አንተም በክርስቶስ ኑር (ቁጥር 28)፤ ይህ ካልሆነ በሐሳዊ-መሢሕ መንፈስ ወደ ጥፋት ትወሰዳለህ። የሐሰት አስተማሪዎች ምንም ዓይነት የተስፋ ቃል ቢገቡልህ አንተ የተረጋገጠ የዘላለም ሕይወት የተስፋ ቃል አለህ (ቁጥር 25)። ከዚህ በላይ የምትፈልገውም የለም!

የሐሰት አስተማሪዎች በራሳቸው ስብሰባዎች ለራሳቸው ብቻ በመደሰት ቢረኩ እንኳ መቼም ምን ይደረግ በተባለ። የሚያሳዝነው ሌሎችን ክርስቶስን ወደሚፃረረው ትምህርታቸው ለመመለስ ሆን ብለው መነሣታቸው ነው። ከእግዚአብሔር እውነት የተመለሰው ሰው ሦስተኛው ምልክት ይህ ነው:-

## 3. የታመኑትን ለማታለል ይሞክራል (1ኛ ዮሐ. 2፡26-29)

ሐሳዊ-መሢሓውያን ቡድኖች ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን ሰዎች ወደ ተሳሳተ እምነታቸው ለማስገባት እምብዛም እንደማይጥሩ ማስተዋል አስገራሚ ነገር ነው። ይልቁንም የቤተ ክርስቲያን አባሎች የሆኑትን አማኞች ወደ ራሳቸው ትምህርት ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። በዚህም ታማኝ የሆነውን «ለማሳት» ይፈልጋሉ።

«ማሳት» የሚለው ቃል «ወደ ጥፋት መመራት» የሚል አሳብ አለው። ጳውሎስ ይህ ነገር እንደሚከሰት ገልጾ አስጠንቅቆናል፤ «መንፈስ ግን በግልጥ:- በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል» (1ኛ ጢሞ. 4፡1)።

ኢየሱስ ሰይጣንን «የውሸት አባት» በማለት ይጠራዋል (ዮሐ. 8፡44)። የሰይጣን ዓላማ የሐሰት ትምህርቶችን በማስተማር ክርስቲያኖችን ወደ ጥፋት መምራት ነው (2ኛ ቆሮ. 11፡1-4 እና 13-15)። አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አምናለሁ ስላለ ብቻ የሚነግረንን ሁሉ መቀበል የለብንም፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የትኛውንም አሳብ እንዲናገር «መጠምዘዝ» ስለሚቻል ነው (2ኛ ቆሮ. 4፡1-2)።

ሰይጣን አስመሳይ እንጂ ፈጣሪ አይደለም። በመሆኑም፥ የእግዚአብሔርን ሥራ ይኮርጃል። ለምሳሌ ሰይጣን የማስመሰያ ወንጌል የሚሰብኩለት (ገላ. 1፡6-11) አስመሳይ «አገልጋዮች» አሉት (2ኛ ቆሮ. 11፡13-15)። እነዚህም በማስመሰያ ጽድቅ የሚደገፉትን (ሮሜ 10፡1-10) አስመሳይ ክርስቲያኖች ያፈራሉ (ዮሐ. 8፡43-44)። በእንክርዳዱ ምሳሌ ውስጥ (ማቴ. 13፡24-30፤ 36-43) ኢየሱስና ሰይጣን እንደ ዘሪዎች ተሥለዋል። ኢየሱስ እውነተኛውን ዘር ማለትም የእግዚአብሔርን ልጆች ሲዘራ፥ ሰይጣን ግን «የክፉውን ልጆች» ይዘራል። ሁለቱ ዓይነት

ተክሎች በሚያድጉበት ጊዜ በጣም ስለሚመሳሰሉ፥ ፍሬአቸው እስኪታይ ድረስ ሠራተኞቹ ልዩነታቸውን አይገነዘቡም። በዚህ ዘመን የሰይጣን ዋንኛ ዘዴ ክርስቶስ እውነተኛውን በሚዘራበት ስፍራ ሁሉ አስመሳዩን ዘር መዝራት ነው። ስለሆነም፥ ማስመሰያውን በማወቅ የክርስቶስን ትምህርቶች ከሐሳዊ-መሢሑ ሐሰተኛ ትምህርቶች መለየቱ አስፈላጊ ነው።

አማኝ ይህንን ሊያደርግ የሚችለው እንዴት ነው? በመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ ላይ በመደገፍ ነው። እያንዳንዱ አማኝ የመንፈስ ቅዱስን *ቅባት* ስለ ተቀበለ (1ኛ ዮሐ. 2:20)፥ መንፈስ ቅዱስ እውነቱን ያስተምረዋል (ዮሐ. 14:17፤ 15:26)። ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሚመሩት በእውነት መንፈስ ሳይሆን በስሕተት መንፈስ ነው (1ኛ ዮሐ. 4:3፥ 6)።

*«ቅባት»* የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ለልዩ አገልግሎት በተለየ ሰው ራስ ላይ ዘይት የሚፈስስበትን ልማድ ያስታውሰናል። ንጉሥ (1ኛ ሳሙ. 15:1)፥ ካህን (ዘጸ. 28:41)፥ እና ነቢይ (1ኛ ነገ. 19:16) ይቀቡ ነበር። የአዲስ ኪዳኑ ክርስቲያን የተቀባው በተራው ዘይት ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ይህም ከእግዚአብሔር ካህናት እንደ አንዱ ሆኖ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚለየው ቅባት ነው (1ኛ ጴጥ. 2:5፥ 9)። የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ለመቀበል መጸለይ አስፈላጊ አይደለም፤ ክርስቲያን ከሆንህ ቀድሞውኑ ይህንኑ የተለየ ቅባት *ተቀብለሃል።* ይህ ቅባት በእኛ ዘንድ «ስለሚኖር» ዳግም መቀበሉ አስፈላጊ አይሆንም።

ሐሰተኛ አስተማሪዎች አብንና ወልድን እንደሚክዱ ተመልክተናል፤ መንፈስ ቅዱስንም እንዲሁ ይክዱታል። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር የሰጠን አስተማሪያችን ነው (ዮሐ. 14:26)፤ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ግን ለራሳቸው አስተማሪዎች ሊሆኑ ስለሚፈልጉ ሌሎችን ወደ ጥፋት ይነዳሉ። *በዚህ ድርጊታቸውም የመንፈስ ቅዱስን ስፍራ ለመውሰድ ይጥራሉ!*

እግዚአብሔር እውነቱን ያስተምረን ዘንድ ቅዱሱን መንፈስ ስለሰጠን፥ ማንም አስተማሪያችን እንዳይሆን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል። ይህ በቤተ ክርስቲያን የሚያስተምሩንን አገልጋዮች ሥልጣን አይሽርም (ኤፌ. 4:11-12)፤ ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስን ለራሳችን በምናነብበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሰዎችን ትምህርት መፈተን እንዳለብን ነው (ከየሐዋ. 17:11 ጋር አወዳድር)።

ለአሜሪካውያን ሕንዶች አገልግሎት የሚሰጠው ሚሲዮናዊ በሎስ አንጀለስ አዲስ ክርስቲያን ከሆነ ሕንዳዊ ሰው ጋር ነበረ። በመንገዱም

ላይ ሲያልፍ ሳለ ከወደ ጥግ መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ የሚሰብክ ሰው ተመለከቱ። ሚሲዮናዊው ሰውዬው የሐሰት አስተማሪ መሆኑን ሲረዳ፥ ሕንዳዊው ግን መጽሐፍ ቅዱስ መያዙን ብቻ ነበር ያስተዋለው። እናም ስብከቱን ሊሰማ ቆመ።

ሚሲዮናዊው፥ «ወዳጄ ግራ እንደማይጋባ ተስፋ አደርጋለሁ» ሲል እያሰበ መጸለይ ጀመረ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሕንዳዊው ከስብከቱ ተመለሰና ከሚሲዮናዊ ወዳጁ ጋር ተገናኘ።

«ስለ ሰባኪው ምን ታስባለህ? ሲል ጠየቀው ሚሲዮናዊው።

ሕንዳዊው ጠንከር ባለ አነጋገር እንዲህ ሲል መለሰለት፡- «በሚናገርበት ጊዜ ሁሉ ከውስጤ አንድ ነገር ‹ውሸታም! ውሸታም!› ሲል ያቃጭላል።»

ያ በልቡ ውስጥ የነበረው «አንድ ነገር» የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት በመምራት ስሕተትን እንድንለይ ይረዳናል። «መንፈስ ቅዱስ እውነት» ስለሆነ (1ኛ ዮሐ. 5፡6)፥ ይህ የእግዚአብሔር ቅባት «ውሸት» አይደለም።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ሐሰተኛ ትምህርት በማመን ወደ ጥፋት የሚሄዱት ለምንድን ነው? ምክንያቱ በመንፈስ ውስጥ *ባለመኖራቸው* ነው። «መኖር» የሚለው ቃል በዚሁ የ1ኛ ዮሐንስ መልእክት ክፍል አያሌ ጊዜያት ስለ ተጠቀሰ መከለሱ አስፈላጊ ይሆናል፡-

- ሐሰተኛ አስተማሪዎች በኅብረቱ ውስጥ አይኖሩም ወይም በኅብረት ኑሮአችሁ አይቀጥሉም (2፡19)።

- ማነው ቃል (መልእክት) በእኛ ሊኖር ይገባል (ቁጥር 24)

- ቅባቱ (መንፈስ ቅዱስ) በእኛ ይኖራል፤ እኛም በመንፈስ ልንኖር ይገባል (ቁጥር 27)።

- በቃሉና በመንፈስ ስንኖር፥ በክርስቶስም እንኖራለን (ቁጥር 28)።

ቀደም ብሎም በዮሐንስ መልእክት ውስጥ ይህንኑ *«መኖር»* የተባለ ቃል ተመልክተናል፡-

- በክርስቶስ እንኖራለን የምንል ከሆነ፥ እርሱ እንደተመላለሰ ልንመላለስ ይገባል (2፡6)።

- ወንድማችንን የምንወድ ከሆነ፥ በብርሃን እንኖራለን (ቁጥር 10)።

• ቃሉ በእኛ ቢኖር፥ መንፈሳዊ ጥንካሬ ይኖረናል (ቁጥር 14)።

• የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናደርግ ከሆነ፥ ለዘላለም እንኖራለን (ቁጥር 17)።

«መኖር» ማለት *በኅብረት ውስጥ መቆየት* ማለት ነው፤ «ኅብረት» ደግሞ በዚህ መልእክት የመጀመሪያ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ ቁልፍ አሳብ ነው። ከምዕራፍ 3 እስከ 5 አጽንኦት የተሰጠው *በልጅነት* ማለትም «ከእግዚአብሔር በመወለድ» ላይ ነው።

የአንድ ቤተሰብ ልጅ ሆኖ ከአባትና ከእናት፥ ብሎም ከሌሎችም የቤተሰብ አባላት ጋር ኅብረት አለማድረግ ይቻላል። ሰማያዊ አባታችን ከእርሱ ጋር ኅብረት እንደማናደርግ ሲረዳ፥ በእርሱ እንድንኖር ሊመልሰን ይፈልጋል። ይህም ሂደት «ቅጣት» ማለትም የልጅ ሥልጠና ተብሎ ይታወቃል (ዕብ. 12፡5—11)።

አማኝ የእግዚአብሔርን መንፈስ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዲያስተምረው መፍቀድ አለበት። ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዓበይት አገልግሎቶች አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡2፤ 4፡1—5)። መንፈስ ቅዱስ በኅብረቱ ውስጥ ለተወሰኑ ግለሰቦች የማስተማርን ስጦታ ስለሚሰጥ (ሮሜ 12፡6—7)፥ ሌሎችን ያስተምራሉ፤ የሚያስተምሩት ነገር ግን መፈተን አለበት (1ኛ ዮሐ. 4፡1—3)።

ሆን ብሎ ማታለልና በመንፈሳዊ መሃይምነት መካከል ልዩነት አለ። አጵሎስ በኤፌሶን ምኩራብ በሰበከ ጊዜ መልእክቱ ትክክል ቢሆንም ሙሉ አልነበረም። ስለሆነም በማኅበረ ምእመኑ ውስጥ የነበሩ በሳል አማኞች ጵርስቅላና አቂላ በግል ወስደው የክርስቶስን መልእክት አስተማሩት (የሐዋ. 18፡24—28)። በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብና በመጸለይ ጊዜ የሚያሳልፍ ክርስቲያን በመንፈስ በመመላለስ የሚያስፈልገውን የመለየት ብቃት ያገኛል።

መንፈስ ቅዱስ ስለ *«ሁሉም»* ነገር ያስተምረናል (1ኛ ዮሐ. 2፡27)። ሐሰተኛ አስተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስን *ሙሉ* መልእክት በማግለል በትንቢት ወይም በቅድስና ወይም በምግብ ላይ ብቻ የማተኮር ባሕል አላቸው። ኢየሱስ «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል *ሁሉ»* እንደሚኖር ገልጾአል (ማቴ. 4፡4)። ጳውሎስም «የእግዚአብሔር ምክር *ሁሉ»* ለማስተማር ይጠነቀቅ ነበር (የሐዋ. 20፡27)። «የእግዚአብሔርን መንፈስ ያለበት መጽሐፍ *ሁሉ»* ጠቃሚያችን ነው (2ኛ ጢሞ. 3፡16)።

የመጽሐፍ ቅዱስን *ማንኛውንም* ክፍል ቸል ብትል ወይም ብታስወግድ ችግር መጥራትህ ነው። *ጠቅላላውን* መጽሐፍ ልታነብና

«በቅንነት ልትናገር» ይገባል (2ኛ ጢሞ. 2፡15)፤ ይህም በአግባቡ መጠቀም እንዳለብህ ያስገነዝብሃል። እግዚአብሔር ለተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት የሚናገረውን ማስታወስ አለብህ፤ ለአይሁዶች ወይም ለአሕዛብ ወይም ለቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚዛመዱ ምንባቦች አሉ (1ኛ ቆሮ. 10፡23)። እነዚህን መለየት አለብህ። ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ለአንተ እንድታነብ የተጻፈ ቢሆንም፥ ሁሉም ለአንተ ለግልህ አልተጻፈም። የሐሰት አስተማሪዎች ግን የሚፈልጉትን ብቻ ከዓውደ-ንባብ ውጭ ፈንቅለው በማውጣት፥ ለጥንቶቹ እስራኤላውያን የተሰጠውን ምንባብ ለዛሬዎቹ አማኞች ያዛምዳሉ።

የዮሐንስ ሁለተኛው መልእክት ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል (2ኛ ዮሐ. 7–11) ከእነዚህ አታላዮች ጋር የሚወግን አማኝ ሙሉ ሽልማቱን የማጣት አደጋ ያንዣብብበታል (ቁጥር 8)። እንዲያውም «ደህና ሁኑ» (በቀጥታ ሲተረጎም) «እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን» እንዳንልም ተነግሮናል። ክርስቲያናዊ ባሕርይህን መጠበቅ ስለሚኖርብህ ጨካኝ ወይም ክፉ ልትሆንባቸው አይገባም፤ ዳሩ ግን ትምህርታቸውን ይዘረዝሩ ዘንድ ወደ ቤትህ ማስገባት የለብህም። ለምን? ወደ ቤትህ ካስገባሃቸው ሁለት ውጤቶች ሊከተሉ ስለሚችሉ ነው፤ መጀመሪያው፥ በአእምሮህ የሐሰተኛ ትምህርትን ዘሮች ሊዘሩብህ ይችላሉ፤ ይህም ሲሆን ሰይጣን እነዚህ ዘሮች መራራ ፍሬ እንዲያፈሩ ውኃ ሊያጠጣቸውና ሊንከባከባቸው ይችላል። ሁለተኛው፥ ይህ ባይሆን እንኳ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በቤትህ በማስተናገድህ ወደ ሌሎች ቤቶች እንዲገቡ በር ትከፍትላቸዋለህ። ሐሰተኛው ከቤትህ ጎን ለሚገኙ ጎረቤቶችህ፥ «አቶ እገሌና ወይዘሮ እገሊት በቤታቸው ተቀብለውኝ...እንዴት ያሉ ጥሩ ክርስቲያኖች መሰሉአችሁ!» ሊል ይችላል።

ዮሐንስ አሁን በኅብረት ርእሰ-ጉዳይ ላይ የሚሰጠውን ትምህርት ጨርሶ ወደ ልጅነት ትምህርት ይሻገራል። በብርሃንና በጨለማ (1፡1–2፡6)፥ በፍቅርና በጥላቻ (2፡7–17)፥ ብሎም በእውነትና በስሕተት (2፡18–22) መካከል የሚገኙትን ንጽጽሮች ገልጾአል። እውነተኛ የክርስትና ኑሮ *የታዛዥነት* (በጨለማ ሳይሆን በብርሃን መመላለስ)፥ *የፍቅርና የእውነት* ሕይወት እንደሆነ አስረድቶአል። የማትታዘዝ ወይም የማታፈቅር ወይም እውነተኛ ያልሆንህ እንደሆንህ ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት መኖሩ የማይቻል ነው። ከእነዚህ ኃጢአቶች ማናቸውም ከእውነታ ወደ ግብዝነት ሊመሩህ ይችላሉ፤ በመሆኑም፥ ከእውነተኛ ሕይወት ይልቅ «ሰው ሠራሽና ብልጭልጭ» ሕይወት ይኖርሃል።

ቁጥር 28 እና 29 ስለ *ኅብረት* ከሚናገረው ስለ *ልጅነት* ወደሚያብራራው ክፍል የሚያሸጋግሩ «ድልድዮች» ናቸው። («ከእግዚአብሔር ተወለዱ»)፤ በእነዚህ ጥቅሶች ዮሐንስ ከአብ፥ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንድንኖር ሊያበረታቱን የሚገቡትን ሦስት ቃላት ይጠቀማል።

1. *ኑሩ።* ይህ ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ ያጋጠመን ቃል ነው። በክርስቶስ የመኖርን አስፈላጊነት መገንዘብ ይኖርብሃል። እንዲያውም ይህ ቃል የመልእክቱ የመጀመሪያ ሁለት ምዕራፎች ዋና ጭብጥ ነበር። በክርስቶስ የምትኖረው እውነትን በማመን፥ እውነትን በመታዘዝና ሌሎች ክርስቲያኖችን ማለትም ወንድሞችን በመውደድ፡- ማለትም በታዛዥነት፥ በፍቅር እና በእውነት ነው። ስለሆነም አማኝ ሆነህ ከእግዚአብሔር ኅብረት ውጭ ብትገኝ፥ ምክንያቱ ቃሉን ስላልታዘዝህ፥ ለወንድምህ ፍቅር ስላጣህ ወይም ውሸትን ስላመንህ ነው። ለዚህም መፍትሔው ወዲያውኑ ኃጢአትህን መናዘዝና የእግዚአብሔርን ይቅርታ መቀበል ይሆናል (1:9)።

2. *መገለጥ።* በዚህ መልእክት ይህ ተስፋ ስለተገባው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የመጀመሪያው ማጣቀሻ ነው። የዮሐንስ ራእይ ወደፊት ስለሚከሰቱ ጉዳዮች በስፋት ይዘግባል። የዮሐንስ መልእክት የሚጠቅሰው የክርስቶስ መመለስና መጪውን የፍርድ ቀን ብቻ ነበር (1ኛ ዮሐ. 2:28–3:3፤ 4:17)።

በወደፊቱ ክስተቶች ዝርዝር ላይ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ባይስማሙም፥ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ እንደሚመለስ ያምናሉ (1ኛ ተሰ. 4:13–18)። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖች ምንም እንኳ ለኃጢአታቸው ፍርድን ባይቀበሉም፥ ክርስቶስን ሲያገለግሉ ባሳዩት ታማኝነት መሠረት ይዳኛሉ (1ኛ ቆሮ. 3:10–15)። በታማኝነት ያገለገሉ ሽልማታቸውን ሲቀበሉ (1ኛ ቆሮ. 4:5)፥ ታማኞች ያልነበሩ ሽልማታቸውን ያጣሉ። ይህ ክስተት «የክርስቶስ የፍርድ ወንበር» በመባል ይታወቃል (ሮሜ 14:10፤ 2ኛ ቆሮ. 5:10)፤ ይህ በዘመኑ መጨረሻ ያልዳኑ ሰዎች ከሚዳኙበት ከ«ታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ» ጋር ሊምታታብህ አይገባም (ራእይ 20:11–15)።

ኢየሱስ ክርስቶስ በማንኛውም ሰዓት ሊመለስ የመቻሉ እውነታ ከእርሱ ጋር በኅብረት እንድትኖርና ለቃሉም እንድትታዘዝ ሊያነቃቃህ ይገባል። ለዚህም ዮሐንስ ሦስተኛውን ቃል ይጠቀማል፡-

3. *ኃፍረት።* አንዳንድ ክርስቲያኖች ሲመጣ በፊቱ ያፍራሉ (1ኛ ዮሐ. 2:28)። ሁሉም አማኞች «ተቀባይነት ያገኙ» ቢሆንም፥

*«ተቀባይነት* በማግኘቱ እና *«ተቀባይነት ማግኘት በመቻሉ»* ላይ ግን ልዩነት አለ። «ስለዚህ...እርሱን ደስ የምናሰኝ ልንሆን እንቀናለን» (2ኛ ቆሮ. 5፡9)። ከክርስቶስ ጋር በታዛዥነት፥ በፍቅርና በእውነት ያልተመላለሰ ክርስቲያን ሽልማቶቹን ያጣል፤ ይህም ለኃፍረት ያጋልጣል።

ክርስቲያን በየትኛውም አቅጣጫ ቢመለከትም፥ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በቂ ምክንያት ያገኛል። ወደ ኋላ ቢመለከት ክርስቶስ ስለ እርሱ የሞተበትን ጎልጎታ ያስባል። ወደ ውስጡ ቢመለከት፥ ከልቡ ውስጥ አድሮ እውነትን የሚያስተምረውን መንፈስ ቅዱስ ያገኛል። ዙሪያውን ሲመለከት የሚወዳቸውን ክርስቲያን ወንድሞቹን ያያል፤ እንዲሁም፥ በኃጢአት ውስጥ ሰጥማ መንፈሳዊ ምስክርነቱን በከፍተኛ ሁኔታ የምትሻውን ዓለምን ያስተውላል። ወደፊት ቢመለከት የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ያያል። «በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደሆነ ራሱን ያነጻል» (1ኛ ዮሐ. 3፡3)። የክርስቶስ ምጽአት ፈሪሃ–እግዚአብሔር ላለበት ሕይወት ታላቁ ማነቃቂያ ነው።

ዮሐንስ ስለ ብርሃንና ጨለማ፥ ፍቅርና ጥላቻ፥ ብሎም እውነትና ስሕተት ጽፎአል፤ በ2፡29 ደግሞ የክርስትና አኗኗርን ጠቅላላ ሁኔታ «ጽድቅን የሚያደርግ» በምትል በአንዲት ሐረግ ያጠቃልላል።

*እውነተኛ* የሆነ *ሕይወት የተግባር* እንጂ *የቃላት* (1፡8–2፡9) ወይም ለትምህርቱ እውነትን በአእምሮ መስማማት ብቻ አይደለም። «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ *የሚለኝ* ሁሉ *መንግሥተ* ሰማያት የሚገባ አይደለም» (ማቴ. 7፡21)። ክርስቲያኖች እውነትን *ማመን* ብቻ ሳይሆን *በተግባርም ይፈጽሙታል* (1ኛ ዮሐ. 1፡6)።

ክርስቲያን ነኝ *እያለ* በታዛዥነት፥ በፍቅርና በእውነት የማይኖር ሰው አንድም አታላይ አሊያም የተታለለ ነው። ልጅ የአባቱን ባሕርይ ስለሚይዝ፥ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰው የሰማያዊ አባቱን ባሕርይ ያንጸባርቃል። «እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ (የምትመስሉ) ሁኑ» (ኤፌ. 5፡1)። «እንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ። ዳሩ ግን እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ» (1ኛ ጴጥ. 1፡14–15)።

በአንድ የሰንበት ትምህርት የማያቋርጥ ችግር የሚታይበት የመማርያ ክፍል ነበር። ስለሆነም መጋቢውና የሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፊው

ከመምህርቷና ከሌሎች ባለ ሥልጣናት ጋር ተገናኝተው መከሩ፤ አሁንም ለውጥ አልታየም። ከዚያም አንድ እሑድ ጠዋት የቤተ ክርስቲያኒቱ የአምልኮ ማጠቃለያ መዝሙር ሲዘመር ሳለ የሰንበት ትምህርት ቤቱ መምህርት ወደፊት መጣች። መጋቢው «ሕይወቷን ለጌታ ለመስጠት ፈልጋ ይሆናል» ሲል አሰበ።

እርሷም፥ «ውድ መጋቢ፥ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ እንደ ተቀበልሁ ልመሰክር እፈልጋለሁ። በእነዚህ ሁሉ ዓመታት የዳንሁ መስሎኝ ነበር፤ ዳሩ ግን አልዳንሁም ነበር። ሁልጊዜም በሕይወቴ ውስጥ አንድ ነገር እንደ ጎደለ ሆኖ ሲሰማኝ ቆይቷል። የሰንበት ትምህርት ቤቱ ችግር የመነጨው ከእኔ ነበር፤ አሁን ግን ተቃልሏል። የዳንኩ መሆኔንም አውቃለሁ» አለች።

«በእምነት መሆናችሁን ለማረጋገጥ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ» (2ኛ ቆሮ. 13፡5–ከ1980 ዓ.ም. እትም)። ሕይወትህ የመታዘዝን፥ የፍቅርንና የእውነትን ምልክቶች ይፈነጥቃል? የክርስትና ሕይወትህ *እውነተኛ ፍቱንና አንጡራ ነው? ወይስ የማስመሰል?*

ይህ የእውነት ወይም የውጤቶች ጥያቄ ነው። ስለሆነም፥ እውነቱን ካልተጋፈጥህ ውጤቶቹ የሚጠይቁህን ዋጋ መክፈል ይኖርብሃል!

# ግብዞች

## 1ኛ ዮሐንስ 3፡1–10

የአሜሪካ የመዋዕለ ንዋይ ዘርፍ በማስመሰል የተሠሩትን ገንዘቦች ለማሰስ የተመደበ የባለሙያዎች ቡድን አለው። እነዚህ ሰዎች በማጭበርበር የተሠራውን ገንዘብ አይቶ መለየት ያስፈልጋቸዋል።

የውሸት ብሮችን ለመለየት የሚማሩት እንዴት ነው?

ይህንን የሚያደርጉት በማጭበርበር የተሠራውን የሐሰት ብር በመመርመር ረዥም ጊዜ በማሳለፍ አይደለም። ይልቁንም *እውነተኛውን ገንዘብ* ያጠናሉ። እውነተኛውን ገንዘብ በደንብ ስለሚያውቁት በማየት ወይም በመዳሰስ ብቻ የተጭበረበረውን ገንዘብ ይለዩታል።

በዛሬው ዓለም «የዲያብሎስ ልጆች» ከሆኑ (ቁጥር 10) አስመሳይ ክርስቲያኖች የሚያስጠነቅቀን የ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ ሦስት አቀራረብም እንዲሁ ነው። በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ የሰይጣንን ልጆች ክፉ ባሕርያት ከመዘርዘር ይልቅ *የእግዚአብሔርን* ልጆች ግልጽ ዝርዝር ይሰጠናል። በሁለቱ መካከል የሚገኘው ልዩነት ግልጽ ነው።

የዚህ ምዕራፍ ቁልፍ ጥቅስ ቁጥር 10 ነው፤ ይህም ጥቅስ እውነተኛ ክርስቲያን ጽድቅን እንደሚያደርግና ከልዩነቶች ባሻገር ሌሎች ክርስቲያኖችን እንደሚወድ የሚናገር ነው። ከቁጥር 1–10 ያለው ስለ መጀመሪያው ርእሰ–ጉዳይ (ጽድቅ) ሲገልጽ፥ ከቁጥር 11–24 ያለው ስለ ሁለተኛው ርእሰ–ጉዳይ (የወንድማማች ፍቅር) ይናገራል።

በመሠረቱ ጽድቅን ማድረግና የወንድማማች መዋደድ አዳዲስ ጭብጦች አይደሉም። እነዚህ ሁለት አስፈላጊ ርእሰ–ጉዳዮች በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ የተገለጹ ሲሆኑ፥ በምዕራፍ ሦስት ግን አቀራረባቸው ለየት ይላል። በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች አጽንኦት የተሰጠው *በኅብረት* ላይ ነበር፤ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያለው አማኝ ጽድቅን ከማድረጉም በላይ ወንድሞችንም ይወድዳል። ከምዕራፍ 3–5 ግን አጽንኦት የተሰጠው *ለልጅነት* ነው፤ ክርስቲያን «ከእግዚአብሔር ስለተወለደ» ጽድቅ ከማድረጉም በላይ ወንድሞችንም ይወድዳል።

«ከእግዚአብሔር የተወለደ» የሚለው በነዚህ ምዕራፎች ውስጥ መሠረታዊ አሳብ ነው (2፡29፤ 3፡9፤ 4፡7፤ 5፡1፥ 4፥ 18)።

የግሪክ ምንባብ የሚለው ልክ በ1962 (እ. ኤ. አ) የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለው ነው፤ «ኃጢአትን *የሚያደርግም፤* ሁሉ አላየውም አላወቀውምም» (ቁጥር 6)። «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን *አያደርግም*... ከእግዚአብሔር ተወልዶአልና ኃጢአትን *ሊያደርግ* አይችልም» (ቁ.9)። ኃጢአት «ማድረግ» ማለት እንደ ሕይወት ዘይቤ ሳያቋርጡ ኃጢአት መሥራት ማለት ነው። ይህም *በ«አጋጣሚ»* በኃጢአት መውደቅን አያመለክትም። መቼም ኃጢአትን ያልሠራ ክርስቲያን እንደሌለ ግልጽ ነው (1፡8–10)፤ ይሁንና፥ እግዚአብሔር እውነተኛ አማኝ ኃጢአትን ልማድ እንዲያደርግ ሳይሆን ከኃጢአቱ እየተመለሰ በቅድስና እንዲኖር ይፈልጋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ታላላቅ ሰዎች ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ ጊዜ ኃጢአትን ሠርተዋል። አብርሃም ስለ ሚስቱ ውሸት ሲናገር (ዘፍ. 12፡10–20)፥ ሙሴ በብስጭት የእግዚአብሕርን ትእዛዝ ተላልፎአል (ዘኍል. 20፡7–13)። ጴጥሮስም ሦስት ጊዜ ጌታን ክዶአል (ማቴ. 26፡69–75)። ይሁንና፥ ኃጢአት የእነዚህ ሰዎች ውጥን ተግባር አልነበረም። ይልቁንም፥ ከተለመደው ተግባራቸው ውጭ *በድንገት* የደረሰባቸው የሕይወት ገጠመኝ ነበር። ኃጢአት ሲያደርጉ ደግሞ ውድቀታቸውን በማመን እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸው ጠይቀውታል።

ያልዳነው ሰው (ምንም እንኳ ክርስቲያን ነኝ እያለ ቢያስመስልም) በልማድ ኃጢአቱ ይኖራል። ኃጢአት፥ በተለይም ያለማመን ኃጢአት በሕይወቱ *የተለመደ ነገር* ነው (ኤፌ. 2፡1–3)። የሚጠቀምበት መለኮታዊ መሠረት የለውም። አለኝ የሚለው እምነቱም እውነተኛ አይደለም። በ1ኛ ዮሐንስ 3፡1–10 የቀረበው መለያ ይህ ነው– አማኝ በልማድ ኃጢአት አይኖርም። በአጋጣሚ *በኃጢአት ሊወድቅ* ቢችልም፥ ኃጢአትን የሕይወት ዘይቤ አድርጎ *አይለማመድም።*

ልዩነቱ እንግዲህ እውነተኛ ክርስቲያን እግዚአብሔርን የሚያውቅ መሆኑ ነው። አስመሳይ ክርስቲያን ስለ እግዚአብሔር ሊናገርና በ«ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች» ውስጥ ሊሳተፍ ቢችልም፥ እግዚአብሔርን በትክክል *አያውቀውም።* በክርስቶስ በማመን «ከእግዚአብሔር የተወለደ» ሰው እግዚአብሔር አብን፥ እግዚአብሔር ወልድንና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን *ያውቃል።* እግዚአብሔርን *ስለሚያውቅም* የታዛዥነትን ሕይወት ይኖራል እንጂ ኃጢአትን አያደርግም።

ዮሐንስ ለምን የተቀደሰ ሕይወት እንደምንኖር ሦስት ምክንያቶችን ይሰጠናል፦

## 1. እግዚአብሔር አብ ስለሚወደን (1ኛ ዮሐ. 3፡1–3)

እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ልዩ ነው። ቁጥር 1፥ «እነሆ፥ እግዚአብሔር ከዚህ ዓለም ፍቅር እንዴት የተለየ ፍቅር እንደሰጠን እዩ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። እግዚአብሔር *ጠላቶቹ* ሳለን ነበር እኛን በመውደድ ልጁን ለእኛ እንዲሞት የላከው።

ጠቅላላው ድንቅና የደኅንነት ዕቅድ የሚጀምረው በእግዚአብሔር ፍቅር ነው።

በቁጥር 1፥ «የእግዚአብሔር ልጆች» የሚለው የምንሸከመው የክብር ስም ብቻ ሳይሆን፥ *እውነታ ነው!* እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን! ይሁንና፥ ዓለም ይህንን አስደሳች ግንኙነት ትረዳዋለች ብለን አንጠብቅም፤ ምክንያቱም ራሱን እግዚአብሔርንም እንኳ አትረዳውምና። የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ መጠራቱን ሙሉ ለሙሉ ተረድቶ ሊያደንቅ የሚችለው በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሰው ብቻ ነው።

ቁጥር 1 *ምን እንደሆንን* ሲናገር፥ ቁጥር 2 *ምን እንደምንሆን* ይናገራል። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ክርስቶስ ለቤተ *ክርስቲያኑ* የሚመለስበት ጊዜ ነው። ይህ በ2፡28 ለተቀደሰ አኗኗር እንደ *ማነቃቂያ* የተገለጸ ሲሆን፥ በዚህም ስፍራ ተደግሞ እናገኘዋለን።

እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር በዳግም ልደት የሚያበቃ አይደለም። ይልቁንም፥ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ የሚቀጥልና ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚያደርሰን ነው። ጌታችን በሚገለጽበት ጊዜ እውነተኞች አማኞች ሁሉ እርሱን ያዩና ይመስሉት ዘንድ ይለወጣሉ (ፊልጵ. 3፡20–21)። ይህ ማለት ለመንግሥተ ሰማይ የሚስማማ አዲስና የከበረ አካል ይኖራቸዋል ማለት ነው።

ይሁንና፥ ሐዋርያው በዚህ አላበቃም! የዛሬው እኛነታችንና ወደፊት የሚገለጠው እኛነታችን *ምን እንደሆነ* ገልጾአል። አሁን በ1ኛ ዮሐንስ 3፡3 *ምን መሆን እንደሚገባን* ይነግረናል። በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት እይታ ሕይወታችንን ማንጻት አለብን።

ይህ ሁሉ የቀረበው ስለ አብ ፍቅር እኛን ለማስታወስ ነው። የእግዚአብሔር ልጆች የሆንነው አብ ስለ ወደደንና ልጁ ስለእኛ ይሞት ዘንድ ስለ ላከው ነው። እግዚአብሔር ስለሚወድደን አንድ ቀን ከእርሱ ጋር እንድንኖር ይፈልጋል። ስለሆነም፥ ከመነሻው እስከ መድረሻው

ደኅንነት የእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫ ነው። የዳንነው በእግዚአብሔር «ጸጋ» ቢሆንም (ኤፌ.። 2፡8–9፤ ቲቶ 2፡11–15)፥ ለደኅንነታችን የሚያስፈልገው የጸጋ ስጦታ የመነጨው ከእግዚአብሔር ፍቅር ነው። ስለሆነም፥ የአብን ፍቅር ስለ ተቀበልን በኃጢአት የመኖር ፍላጎት የለንም።

ኃጢአት የሚሠራ የማያምን ሰው በፈጣሪው ላይ የሚያምፅ ፍጡር ነው። ኃጢአት የሚሠራ ክርስቲያን ግን በአባቱ ላይ የሚያምፅ ልጅ ነው። ስለሆነም፥ የማያምነው ከሕግ ላይ ኃጢአትን ሲያደርግ የሚያምነው በፍቅር ላይ ኃጢአትን ያደርጋል።

ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ተደጋግሞ የተገለጸውን «እግዚአብሔርን መፍራት» የሚል ትርጉም ያስታውሰናል። ይህ ሐረግ የእግዚአብሔር ልጆች በሽብር ድባብ እንደሚኖሩ አያመለክትም፤ «እግዚአብሔር የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና» (2ኛ ጢሞ. 1፡7)። ይልቁንም፥ የእግዚአብሔር ልጆች አባታቸውን እንደሚያከብሩትና ሆን ብለው ትእዛዙን እንደማይተላለፉ ወይም ሊያበሳጩት እንደማይሞክሩ ያመለክታል።

አፍላ ዕድሜ ላይ ያሉ ወጣቶች የሚገኙበት ቡድን ፓርቲ አድርጎ እየተዝናና ሳለ፥ አንድ ሰው የተሻለ ጊዜ ለማሳለፍ ወደ አንድ ምግብ ቤት እንዲሄዱ ሓሳብ አቀረበ።

በዚህ ጊዜ ጃን ለወንድ ጓደኛዋ፥ «ወላጆቼ ያንን ስፍራ ስለማይወዱት ወደ ቤቴ ብትወስደኝ እመርጣለሁ» አለችው።

ከልጃገረዶቹ አንዱም፥ «አባትሽ እንዳይጎዱሽ ፈርተሽ ነው?» ስትል ምፀት የተቀላቀለበት ጥያቄ አቀረበችላት።

ጃንም፥ «የለም... የፈራሁት አባቴ ይጎዳኛል ብዬ ሳይሆን እኔ እንዳልጎዳው ነው» ስትል መለሰች።

ይህች ልጅ የእግዚአብሔርን ፍቅር የተቀበለ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ በዚያ ፍቅር ላይ ሊያምፅ እንደማይፈልግ የሚያስረዳውን መመሪያ ተረድታለች ማለት ነው።

## 2. እግዚአብሔር ወልድ ስለ እኛ ስለ ሞተ (1ኛ ዮሐ. 3፡4–8)

በዚህ ስፍራ ዮሐንስ *ከወደፊቱ* የክርስቶስ መገለጥ (ቁጥር 2) ወደ *አለፈው* መገለጡ (ቁጥር 5) ይመለሳል። ዮሐንስ ኢየሱስ ለምን እንደሞተ ሁለት ምክንያቶችን ይሰጣል። ይኸውም ሀ) ኃጢአታችንን ለማስወገድ (ቁጥር 4–6) እና ለ) የዲያብሎስን *ሥራ* ለማፍረስ ነው (ቁጥር 7–8)። የእግዚአብሔር ልጅ በኃጢአት የሚቀጥል ከሆነ

ድርጊቱ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያደረገለትን ውለታ እንዳልተረዳና ለዚሁም አመስጋኝ ልብ እንደሌለው ያስረዳል።

*ሀ. ክርስቶስ ኃጢአታችንን ለማስወገድ ተገለጠ (3፡4-6)።*

በመጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት አያሌ ድንጋጌዎች አሉት፤ «ከእምነትም ያልሆነ ሁሉ ኃጢአት ነው» (ሮሜ 14፡23)። «የስንፍና ሐሳብ ኃጢአት ነው» (ምሳ. 24፡9)። «እንግዲህ መልካም ነገር ማድረግን እያወቀ የማያደርግ ሰው፥ አለማድረጉ ኃጢአት ይሆንበታል» (ያዕ. 4፡17-ከ1980 ዓ.ም. እትም)። «ክፉ *ሥራ* ሁሉ ኃጢአት ነው» (1ኛ ዮሐ. 5፡17- ከ1980 ዓ.ም. እትም)። ይሁንና የዮሐንስ መልእክት ኃጢአትን እንደ *ዓመፅ* የሚደነግግ ነው (3፡4)። ኃጢአትን እንደ *ርኩሰት* ይመለከተዋል (1፡9-2፡2)፤ በዚህ ስፍራ ግን እንደ *ዓመፅ* ይገልጸዋል።

በዚህ ስፍራ አጽንኦት የተሰጠው በኃጢአቶች (ብዙ ቁጥር) ላይ ሳይሆን፥ በኃጢአት (ነጠላ ቁጥር) ላይ ነው፤ «*ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ...*» ኃጢአቶች ፍሬዎች ሲሆኑ፥ *ሥሩ* ግን *ኃጢአት* ነው።

እግዚአብሔርን ፍቅር ነው ማለት ለቤተሰቡ *ሥርዓት*ና ደንብ የለውም ማለት አይደለም። «ትእዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን» (2፡3)። «ትእዛዙን የምንጠብቅና በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን የምናደርግ ስለ ሆንን የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን» (3፡22)። «እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃለን» (5፡2)።

የእግዚአብሔር ልጆች በብሉይ ኪዳን ሕግ በባርነት አይገዙም፤ ለምን ቢባል ክርስቶስ ነፃ ስላወጣንና ነጻነትን ስለ ሰጠን ነው (ገላ. 5፡1-6)። ይህም ሲባል የእግዚአብሔር ልጆች *ሥርዓተ*-አልባና ዓመፀኞች ይሆናሉ ማለት አይደለም። ከእግዚአብሔር ሕግ ውጭ አይደሉም፤ ይልቁንም ከክርስቶስ ሕግ በታች ናቸው (1ኛ ቆሮ. 9፡21)።

በመሠረቱ፥ ኃጢአት የፈቃድ ጉዳይ ነው። ለእኛ የራሳችንን ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ማስቀደም ዓመፅ ሲሆን ዓመፁ ደግሞ የኃጢአት *ሥር* ነው። ይህም ኃጢአት በዓመፀኛ ባሕርይ ውስጥ ራሱን ስለሚገልጽ ብቻ ሳይሆን፥ የኃጢአት ዓይነተኛ ባሕርይ ዓመፀኛነት (*ሥርዓተ*-አልበኝነት) ስለሆነ ነው። ውጫዊ ተግባሩ ምንም ይሁን ምን የኃጢአተኛ ሰው ውስጣዊ አዝማሚያ የዓመፅ ነው።

ትንሿ ጁዲ ከአባቷ ጋር በመኪና ውስጥ ተቀምጣ አብረው ይጓዙ ነበር። ከዚያም ፊተኛው ወንበር ላይ ወጥታ ለመቆም ወሰነች። አባቷ እንድትቀመጥና ከወንበሩ ጋር የተያያዘውን ቀበቶ እንድታጠልቅ

አዘዛት፤ እርሷ ግን እምቢ አለች። ለሁለተኛ ጊዜ ቢነግራትም አልሰማችውም።

*«አሁኑኑ ባትቀመጪ ከመንገዱ ጥግ አወርድሽና እጠፈጥፍሻለሁ»* ሲል አባት በመጨረሻ ተቆጣት፤ በዚህ ጊዜ ትንሺ ልጅ ታዘዘች። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ግን ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ፥ «አባባ፥ እስከ አሁን በሆዴ ውስጥ እየቆምሁ ነኝ» አለች።

*ሥርዓተ-*አልበኝነት! *ዓመፀኝነት!* ምንም እንኳ ከወደ ውጭ የሚያስገድድ ኃይል ቢኖርም፥ አሁንም ከወደ ውስጥ ዓመፀኝነት ነበር፤ ይህም አመለካከት የኃጢአት ዓይነተኛ ባሕርይ ነው።

*ዳሩ* ግን አንድ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ በኋላ፥ ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን *ዳግም* ከተወለደ በኋላ የዓመፀኝነትን ተግባር ሊፈጽም አይችልም። ለዚህም ዓይነተኛው ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ኃጢአት መሆኑና በእርሱ መኖር ማለት ደግሞ ኃጢአት ከሌለው ጋር መተባበር ስለሆነ ነው። ከዚህም በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው *ኃጢአታችንን ለማስወገድ* ነው! የክርስቶስን ማንነት ካወቅንና ከሞቱ በረከት ከተካፈልን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከቶውንም ቸል አንለውም። ክርስቲያን የሆነ ሰው ሆን ብሎ ኃጢአት ማድረግ ሲቀጥል፥ ጠቅላላውን የመስቀል ላይ *ሥራ* ከዱል ማለት ነው። ጳውሎስ እንዲህ ዓይነቶችን ሰዎች «የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች» ብሎ ከሚጠራባቸው ምክንያቶች አንዱ ይኼው ነው (*ፊልጵ.* 3፡18-19)።

«በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም» (1ኛ ዮሐ. 3፡6)። «መኖር» ዮሐንስ አዘውትሮ ከሚጠቀምባቸው *ቃላት* አንዱ ነው። በክርስቶስ *«መኖር»* ማለት ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ እንዲሁም በእኛና በእርሱ መካከል ምንም ዓይነት ግርዶሽ እንዳይፈጠር ማድረግ ማለት ነው። *ልጅነት* (ከእግዚአብሔር መወለድ) ከክርስቶስ ጋር ወዳለው «ጥምረት» *ሲያመጣን፥ «ኅብረት»* ደግሞ ከክርስቶስ ጋር *«አንድነት»* እንዲኖረን *ያደርጋል። ቃሉን* ሆን ብለን እንዳንተላለፍ የሚጠብቀን ከክርስቶስ ጋር አንድነት ማድረጉ (በእርሱ መኖሩ) ነው።

ሆን ብሎ በዘልማድ ኃጢአት የሚያደርግ ሰው ክርስቶስን እንደማያውቅና በእርሱ ሊኖር እንደማይችል ያረጋግጣል።

*ምንም* እንኳ ከኃጢአት *መዳናችን* ድንቅ ቢሆንም፥ የክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት ያስገኘው ይህንኑ ብቻ አይደለም። ክርስቶስ በሞቱ በሕይወታችን ውስጥ የነበረውን የኃጢአት *መመሪያ* አስወግዶአል። የሮሜ 6-8 ጭብጥ ይኸው ከክርስቶስ ጋር በሞቱና

በትንሣኤው መተባበር ነው። ክርስቶስ ለእኔ መሞቱ ብቻ ሳይሆን እኔም ከክርስቶስ ጋር ሞቼአለሁ! ስለሆነም አሁን ራሴን ለእርሱ አሳልፌ ልሰጥ እችላለሁ፤ ኃጢአት በእኔ ላይ ሊገዛ አይችልም።

*ለ. ክርስቶስ የተገለጠው የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ ነው (1ኛ ዮሐ. 3፡7-8)።*

በዚህ ስፍራ የሚገኘው እውነታ ግልጽ ነው፤ አንድ ሰው እግዚአብሔርን ቢያውቅ ይታዘዘዋል፤ የዲያብሎስ ከሆነ ግን ለዲያብሎስ ይታዘዛል።

ዮሐንስ የአካላዊ ዲያብሎስን እውነታ ይቀበላል። ይህ ጠላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስሞች ይጠራል፤ ሰይጣን (ጠላት)፥ ዲያብሎስ (ከሳሽ)፥ አብዶን ወይም አጶልዮን (አጥፊው)፥ የዚህ ዓለም ገዥ፥ የተጣለው ዘንዶ፥ ወዘተ... በየትኛውም ስም ብትጠራው ዋነኛ ሥራው ክርስቶስንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ መቃወም እንደሆነ ግን አትዘንጋ።

በዚህ ስፍራ ንጽጽር የተደረገው ኃጢአት ባላደረገው ክርስቶስ (ቁጥር 5) እና ከኃጢአት በቀር ሌላ ተግባር በማያውቀው ዲያብሎስ መካከል ነው።

የሰይጣን ምንጩ ምሥጢራዊ ነው። አያሌ ምሁራን በአንድ ወቅት እግዚአብሔር በመላእክትና በምድር ላይ የሾመውና ከሊቀ መላእክት አንዱ እንደነበረ፥ በኋላም በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ ምክንያት እንደተጣለ ያምናሉ (ኢሳ. 14፡9-17፤ ሕዝ. 28፡ 12-14)።

ሰይጣን ፍጡር በመሆኑ እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ አይደለም። *በተፈጠረ ጊዜ* ዓመፀኛ አልነበረም። የአሁን ባሕርዩ የቀድሞ ዓመፀኝነቱ ውጤቱ ነው። ሰይጣን እንደ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ፥ ሁሉን አዋቂ፥ ወይም በሁሉም ስፍራ መገኘት የሚችል አይደለም። ይህም ሆኖ፥ አጋንንት በሚባሉና በአንድ ጊዜ በብዙ ስፍራዎች ተግባሩን እንዲያከናውን በሚረዱት የፍጡራን መናፍስት ሠራዊት ይታገዛል (ኤፌ. 6፡10-12)።

ሰይጣን ዓመፀኛ ሲሆን፥ ክርስቶስ ታዛዥ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ክርስቶስ እስከ ሞት ለዚያውም እስከ መስቀል ሞት ድረስ የታዘዘ ነበር (ፊልጵ. 2፡8)። ክርስቶስ አምላክ ሲሆን ባሪያ ለመሆን ፈቃደኛ ነበር። ሰይጣን ግን ባሪያ ሲሆን አምላክ ለመሆን ፈለገ። ከተግባሩ ጅማሬ ጀምሮ ሰይጣን ኃጢአተኛ የነበረ ሲሆን፥ ክርስቶስ የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ ተገለጠ።

«ማፍረስ» (1ኛ ዮሐ. 3፥8) የሚለው «ማውደምን» አያመለክትም። ሰይጣን ዛሬ ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል። «ማፍረስ» በዚህ ስፍራ «ማዳከም፥ ኃይሉን መንጠቅ» ማለት ነው። ሰይጣን አልጠፋም፤ ዳሩ ግን ኃይሉ የተቀነሰበት ሲሆን፥ መሣሪያዎቹም እንደሚገባ እንዳይሠሩ ተበላሽተዋል። ምንም እንኳ ገና ኃያል ጠላት ቢሆን፥ ለእግዚአብሔር ኃይል ብቁ ተወዳዳሪ አይደለም።

ኢየሱስ ይህንን ዓለም አያሌ ጠቃሚና ውድ ዕቃዎችን ከያዘ ቤተ መንግሥት ጋር ያወዳድረዋል። ይህም ስፍራ የሚጠበቀው በጠንካራ ዘብ ነው (ሉቃስ 11፥14–23)። ጠንካራው ሰይጣን ሲሆን «ንብረቱ» ደግሞ ከደኅንነት ርቀው የጠፉ ወንዶችና ሴቶች ናቸው። «ንብረቱን» ለማስለቀቅ ብቸኛው መንገድ ጠንካራውን ጠላት ማሰር ሲሆን፥ ኢየሱስም በመስቀል ላይ ያደረገው ይህንኑ ነው። ኢየሱስ ወደ ምድር በመምጣት የሰይጣንን «ቤተ መንግሥት» ወርሯል። በመስቀል ላይ ሲሞት ደግሞ የሰይጣንን ኃይል በመስበር ንብረቱን ማርኮአል። ከደኅንነት ርቆ የነበረ አንድ ኃጢአተኛ ወደ ክርስቶስ በተመለሰ ጊዜ ሁሉ፥ የሰይጣን «ምርኮኞች» ቁጥር ይቀንስበታል።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተፈጸመ ከብዙ ወራት በኋላ፥ የጃፓን ወታደሮች በዋሻዎችና በፓስፊክ ደሴቶች ውስጥ ተደብቀው ተገኝተዋል። እነዚህ ሰዎች ጦርነቱ እንደተፈጸመ ሳያውቁ በፍርሃት ተሸብበው ይኖሩ ነበር። መዋጋቱ አስፈላጊ እንዳልሆነ ከተረዱ በኋላ እጃቸውን ሰጡ።

ክርስቲያኖች ሰይጣን የተሸነፈ ጠላት በመሆኑ እውነታ ሊያርፉ ይችሉ ይሆናል። ምናልባት አልፎ አልፎ ጥቂት ጦርነቶችን ሊያሸንፍ ቢችልም፥ *ድሉን ግን አጥቷል!* የፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት ሲሆን፥ ቅጣቱ እስኪፈጸምበት ድረስ ግን ጥቂት ጊዜ አለው። ክርስቶስን የሚያውቅና ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱ ከኃጢአት ባርነት ነፃ የወጣ ሰው ለሰይጣን የመታዘዝና እንደ ዓመፀኛ የመኖር ፍላጎት አይኖረውም።

«ልጆች ሆይ፥ ማንም አያስታችሁ!» አስመሳይ ክርስቲያኖች አንድ ሰው ከዳነ በኋላ በኃጢአቱ ሊቀጥል እንደሚችል በመግለጽ እውነተኛ አማኞችን ለማሳመን ይጥሩ ነበር። ዮሐንስ ክርስቲያኖች በኃጢአት ሊወድቁ እንደሚችሉ ባይክድም፥ ክርስቲያኖች *በኃጢአት መቀጠል እንደሌለባቸው ያምናል።* ስለሆነም፥ ሆን ብሎ በሚሠራው ኃጢአት *ደስ የሚሰኝና* የሕሊና ወቀሳ ወይም የእግዚአብሔር ቅጣት የማይደርስበት ሰው በትክክል ከእግዚአብሔር መወለዱን ለማረጋገጥ ራሱን ቢመረምር መልካም ነው።

## 3. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በእኛ ይኖራል (1ኛ ዮሐ. 3፡9–10)

«ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም!»

ለምን? ምክንያቱም በውስጡ አዲስ ባሕርይ ስላለውና ያ አዲስ ባሕርይ ኃጢአትን ሊለማመድ ስለማይችል ነው። ዮሐንስ ይህንን አዲስ ባሕርይ የእግዚአብሔር «ዘር» ሲል ይጠራዋል።

አንድ ሰው ክርስቶስን እንደ አዳኙ አድርጎ ሲቀበል በሕይወቱ ከፍተኛ መንፈሳዊ ለውጦች ይካሄዳሉ። በእግዚአብሔር ፊት አዲስ ማንነት ተሰጥቶት እንደ ጻድቅ ተቀባይነት ያገኛል። ይህም አዲስ «ጽድቅ» የተባለ ሲሆን ከቶውንም የማይለወጥና የማይጠፋ ነው።

ከዚህም በላይ ለአዲስ ክርስቲያን አዲስ ማዕረግ ይሰጠዋል፤ ይኸውም ለእግዚአብሔር ክብር ይኖር ዘንድ ለዓላማዎቹ ይለያል። ይህም አዲስ ማዕረግ «ቅድስና» ይባላል። ቅድስና ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያድግ ነው። አንዳንድ ጊዜ ይበልጥ ወደ ክርስቶስ በመቅረብ በበለጠ ዝግጁነት እንታዘዛለን።

ይህም ሆኖ፥ በአዲስ አማኝ ሕይወት እጅግ አስደናቂው ለውጥ «ዳግም ልደት» የምንለው ሳይሆን አይቀርም። በዚህም አማኙ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ «ዳግም ይወለዳል።»

ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት አዲስ *አቋም ማግኘት* ሲሆን፥ ቅድስና ደግሞ ለእግዚአብሔር *መለየት* ነው፤ ዳግም ልደት አዲሱን ባሕርይ ያውም የእግዚአብሔርን *ባሕርይ* መቀበል ነው (ከ2ኛ ጴጥሮስ 1፡4 ጋር አመሳክር)።

ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት ለመግባት ብቸኛው መንገድ ክርስቶስን አምኖ ይህንን አዲስ ልደት ማግኘት ነው። «ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል» (1ኛ ዮሐ. 5፡1)።

*ሥጋዊ* ሕይወት *ሥጋዊውን* ሕይወት ብቻ ሲያስገኝ፥ መንፈሳዊ ሕይወት የሚመጣው ከመንፈሳዊ ሕይወት ነው። «ከ*ሥጋ* የተወለደ *ሥጋ* ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው» (ዮሐ. 3፡6)። ክርስቲያኖች ዳግመኛ የተወለዱት «ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ» (1ኛ ጴጥ. 1፡23)። የክርስቲያን «ከመንፈሳዊ ወላጆች» የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ናቸው። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም ኃጢአተኛውን ስለ ኃጢአቱ ይወቅስና አዳኙን ይገልጥለታል።

የዳንነው በእምነት ነው (ኤፌ. 2:8)፤ «እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሮሜ 10:17)። በአዲስ ልደት ተአምር መንፈስ ቅዱስ አዲስን ሕይወት ያውም የእግዚአብሔርን ሕይወት ለሚያምነው ኃጢአተኛ ያጎናጽፋል፤ ከዚህም የተነሣ ግለሰቡ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ይወለዳል።

በሥጋ የተወለዱ ልጆች የወላጆቻቸውን ባሕርይ እንደሚይዙ ሁሉ የእግዚአብሔርም መንፈሳዊ ልጆች የእርሱን ባሕርይ ይይዛሉ። በውስጣቸው መለኮታዊ «ዘር» አለ። ስለሆነም፥ ክርስቲያን ከሥጋዊ ልደቱ አሮጌ ባሕርይ፥ ከመንፈሳዊ ልደቱ አዲስ ባሕርይ አለው። አዲስ ኪዳን እነዚህን ሁለት ባሕርያት በማነጻጸር በተለያዩ ስሞች ይጠራቸዋል።

| አሮጌ ባሕርይ | አዲሱ ባሕርይ |
|---|---|
| «አሮጌው ሰዋችን» | «አዲሱ ሰው» |
| (ሮሜ 6:6) | (ቆላ. 3:10) |
| «ሥጋ» | «መንፈስ» |
| (ገላ. 5:24) | (ገላ. 5:17) |
| «የሚጠፋው ዘር» | «የእግዚአብሔር ዘር» |
| (1ኛ ጴጥ. 1:23) | (1ኛ ዮሐ. 3:9) |

አሮጌው ባሕርይ ኃጢአትን ሲያመርት፥ አዲሱ ባሕርይ ግን ወደ ተቀደሰ ሕይወት ይመራል። ስለሆነም፥ አንድ ክርስቲያን ኃላፊነቱ ከአዲሱ ባሕርዩ አኳያ መኖር እንጂ አሮጌውን ባሕርይ እንዲያንፀባርቅ አይጠበቅበትም።

ይህንን አሳብ ለማብራራት የሚረዳው አንዱ መንገድ «የውጭው ሰው» እና « የውስጡን ሰው» ማነጻጸር ነው (2ኛ ቆሮ. 4:6)። ሥጋዊው ሰው ምግብ እንደሚፈልግ ሁሉ፥ የውስጡም ሰው ማለትም መንፈሳዊ ሰው ምግብ ይፈልጋል። «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» (ማቴ. 4:4)። ክርስቲያን በየዕለቱ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ጥሞና የማይወስድ ከሆነ ውስጣዊ ሰውነቱ ኃይልን ያጣል።

አዲሱን ባሕርይ በእግዚአብሔር ቃል የሚመገብ ክርስቲያን ፈሪሃ-እግዚአብሔር የሰፈነበትን ሕይወት ለመኖር የሚያስችል ኃይል ይኖረዋል። «የሥጋችሁን ፍላጎት ለማርካት አታስቡ» (ሮሜ 13፥14 ከ1980 ዓ.ም. እትም)።

ሥጋዊ ሰውነት ንጽሕናን እንደሚፈልግ ሁሉ፥ ውስጣዊውም ሰው ንጽሕናን ይፈልጋል። በየጊዜው እጆቻችንንና ፊታችንን እንታጠባለን። እንደዚሁም አማኝ ወደ እግዚአብሔር ቃል መስተዋት በመመልከት (ያዕ. 1፥22-25) ራሱን መመርመር ይገባዋል። ኃጢአቶቹንም ተናዝዞ የእግዚአብሔርን ይቅርታ መቀበል አለበት (1ኛ ዮሐ. 1፥9)። ይህ ካልሆነ ውስጣዊው ሰው ይቆሽሻል፤ ይህም ቆሻሻ ለ«መንፈሳዊ በሽታ» ያጋልጣል።

ኃጢአትን አለመናዘዝ መጽሐፍ ቅዱስ «ከዳተኛነት» ወደ ኋላ መመለስ ብሎ ለሚጠራው ነገር የመጀመሪያው እርምጃ ነው፤ ይህም ከዳተኛነት ከክርስቶስ ጋር በቅርብ ከመጓዝ ቀስ በቀስ የምንኖርበትን ዓለም ወደ መምሰሉ የምናዘግምበት ነው።

«ከዳተኛነታችሁን እፈውሳለሁ» የሚለው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል (ኤር. 3፥22) ከዳተኛነት ሥጋዊ በሽታን እንደሚመስል ያሳያል። መጀመሪያ ታማሚው በማያውቀው መንገድ ሰውነቱ በበሽታው ተሐዋስያን (ጀርሞች) ይወረራል። ከዚያም በሽታው ይከተልና ቀስ በቀስ መጠቃቱ ይመጣል፤ ቀጥሎም ጉልበት እየደከመ፥ የመመገብና ዕለታዊ እንቅስቃሴዎችን የመወጣት ዓቅም እየቀነሰ ይሄድና በመጨረሻም ውድቀት ይከተላል!

መንፈሳዊ ውድቀትም እንዲሁ ነው። መጀመሪያ ኃጢአት ይወረናል። እኛም መዋጋት ሲኖርብን እጃችንን እንሰጠዋለን (ከያዕቆብ 1፥14 ጋር አመሳክር)፤ በዚህም ጊዜ በሽታው ይጀምራል። ቀስ በቀስም ማሽቆልቆሉ ይከተላል። ይህም ሲሆን ለመንፈሳዊ ነገሮች የነበረንን ፍላጎት በማጣት ስልቹዎችና ብስጩዎች እንሆናለን፤ በመጨረሻም ለውድቀት እንዳረጋለን።

ለዚህ ብቸኛው መፍትሔ ኃጢአታችንን በመናዘዝና በመተው ለመንጻትና ለመፈወስ ወደ ክርስቶስ መመለስ ነው።

ውስጣዊው ሰው ምግብንና መንጻትን ብቻ ሳይሆን፥ ልምምድንም ይፈልጋል። «ለመንፈሳዊ ነገርም ራስህን አለማምድ» (1ኛ ጢሞ. 4፥7-ከ1980 ዓ.ም. እትም)። ስፖርታዊ ልምምድ የማያደርግና ዝም ብሎ የሚመገብ ሰው ከመጠን በላይ ይወፍራል፤ ተገቢውን ምግብ

ሳያገኝ ስፖርታዊ ልምምድ የሚያደርግ ደግሞ ራሱን ለአደጋ ያጋልጣል። በሁለቱም መካከል ተገቢ ሚዛናዊነት ሊኖር ይገባል።

ለአማኝ «መንፈሳዊ ልምምድ» ስለ ክርስቶስ ለሌሎች መመስከርን፥ በክርስቶስ ስም ሰናይ ምግባር መከወንንና ሌሎች አማኞችን ለማነጽ እገዛ ማድረግን ያካትታል። እያንዳንዱ ክርስቲያን ለቤተ ክርስቲያን በጎነት ሊያውለው የሚገባው ቢያንስ አንድ መንፈሳዊ ስጦታ አለው (1ኛ ቆሮ. 12፡1–11)። «የተለያዩትን የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታዎች በታማኝነት በማስተዳደር ከእናንተ እያንዳንዱ በተሰጠው የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል» (1ኛ ጴጥ. 4፡10– ከ1980 እትም)።

ለዚህ የፈተናና የኃጢአት ጠቅላላ ሂደት የተሰጠውን ግልጽ ማብራሪያ ቀጥለህ ተመልከት፡–

«ማንም ሲፈተን፥ በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች» (ያዕ. 1፡13–15)።

ፈተና መሠረታዊ የተፈጥሮ ፍላጎቶቻችንን ይማርካል። እነዚህ ፍላጎቶች ክፉ አይደሉም፤ ነገር ግን በክፉ መንገድ እንድናሟላቸው በር ይከፍትልናል። መራብ ኃጢአት አይደለም፤ ዳሩ ግን ረሃብን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ማስታገሥ ኃጢአት ነው። ሰይጣን ለኢየሱስ ያቀረበው የመጀመሪያ ፈተና ይኼ ነበር (ማቴ. 4፡1–4)።

«መሳብ» እና «መታለል» የሚሉ ሁለት ቃላት (ያዕ. 1፡14) ከአደን ወይም ከዓሣ ማጥመድ ጋር ይዛመዳሉ፤ ይኸውም ከወጥመዱ ወይም ከዓሣ መንጠቆው ውስጥ የሚጨመረውን የመሳቢያ ምግብ የሚያመለክቱ በመሆናቸው ነው። እንስሳው (ወይም ዓሣው) ይህ የማቅረቢያ ምግብ በተቀመጠበት ወጥመድ አካባቢ ሲያልፍ ተፈጥሮአዊ ፍላጎቱ ወደዚያው ይስበዋል። ምግቡንም ለመብላት ሲሞክር ለወጥመዱ፥ ዓሣም ከሆነ ለመንጠቆው ይደረጋል። የዚህም ፍጻሜ በሞት ይደመደማል።

ሰይጣን ወጥመዶቹን ለአሮጌው ባሕርይ ማለትም ለሥጋ ምቾት በሚጥም መልኩ ያዘጋጃል። ይሁንና፥ ለመማረክ የተዘጋጀው ማባበያ በክርስቲያን ውስጥ ለሚገኘው አዲሱ መለኮታዊ ባሕርይ የሚጣፍጥ አይሆንም። አማኙ ለአሮጌው ባሕርዩ ራሱን ከሰጠ ለመማረኪያው በመጎምጀት ኃጢአትን ይፈጽማል። ይሁንና፥ የአዲስ ባሕርይን ዝንባሌዎች ቢከተል መሳቢያውን ትቶ እግዚአብሔርን ይታዘዛል። «ነገር

ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ» (ገላ. 5፡16)።

ለኃጢአት ራስን መስጠት «የዲያብሎስ ልጆች» የመለያ ምልክት ነው (1ኛ ዮሐ. 3፡10)። በቃላቸው አንድ ነገር ሲናገሩ በኑሮአቸው የተገላቢጦሹን ያሳያሉ። ሰይጣን ውሸተኛና የውሸት አባትም ነው (ዮሐ. 8፡44)፤ ልጆቹም ደግሞ ልክ እንደ አባታቸው ናቸው። «(እግዚአብሔርን) አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው። እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም» (1ኛ ዮሐ. 2፡4)። አንድ ሰው ክርስቲያን ሊሆንና ኃጢአት በመሥራት ሊቀጥል እንደሚችል አድርገው እንዲያስቡ በማሳመን የዲያብሎስ ልጆች የእግዚአብሔር ልጆችን ሊያስቱአቸው ይሞክራሉ። «ልጆች ሆይ፥ ማንም አያስታችሁ፤ እርሱ (እግዚአብሔር) ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው» (3፡7)።

በዮሐንስ ዘመን የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች [ እንደ ዛሬዎቹ «መንፈስ ነን» ባዮች] ኃጢአት የሚተገበረው በሰውነት ላይ ስለሆነና ሰውነት የሚያደርገው ተግባር በምንም ዓይነት መንፈስን ስለማይጎዳ፥ ክርስቲያን ስለ ኃጢአት መጨነቅ እንደሌለበት ያስተምሩ ነበር። እንዲያውም አንዳንዶች ሰውነት ኃጢአተኛ ስለሆነ፥ ኃጢአት መሥራት የሰውነት ተለምዶአዊ ተግባር ነው እስከ ማለት ደርሰው ነበር።

አዲስ ኪዳን ስለ ኃጢአት የሚሰጠውን እንዲህ ዓይነት የሞኝነት ገለፃ ያጋልጣል።

ቀድሞ ነገር «አሮጌው ባሕርይ» ሰውነት አይደለም። ሰውነት በራሱ አሮጌው የኃጢአት ባሕርይም ሆነ አዲሱ መለኮታዊ ባሕርይ ሊጠቀሙበት የሚችሉት ገለልተኛ ነገር ነው። «እንግዲህ ለምኞቱ እንዳትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፤ ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ» (ሮሜ 6፡12–13)።

የእግዚአብሔር ልጅ የአሮጌውን ተፈጥሮ ፍላጎቶች የሚያሸንፈው እንዴት ነው? በእያንዳንዱ ዕለት ሰውነቱን እንደ ሕያው መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በማቅረብ መጀመር አለበት (ሮሜ 12፡1)። የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና በማጥናት አዲሱን ባሕርይ ሊመግብ ይገባዋል። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላውና ክርስቶስን ለማገልገልና ለማስከበርም የሚያስችለውን ኃይል እንዲሰጠው መጠየቅ አለበት።

ክርስቲያን የቀን ውሎውን ሲያሳልፍ በውስጣዊ ሰውነቱ በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ አለበት። ፈተናዎች ሲጠጉት ድልን ለመቀዳጀት ወዲያው ወደ ክርስቶስ መመለስ አለበት።

ወደ ክርስቶስ ከተመለሰ ከልቡ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ከኃጢአት ይጠብቀዋል። «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» [መዝ(119)፡11]። በኃጢአት *ከወደቀ* ግን ወዲያውኑ ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር በመናዘዝ ይቅርታ ማግኘት አለበት። ይሁንና፥ *ኃጢአት መሥራት አስፈላጊው* አይደለም። ሰውነቱን በውስጡ ላለው መንፈስ ቅዱስ በመስጠት ፈታኙን ለማሸነፍ የሚያስፈልገውን ኃይል ያገኛል።

መልካሙ ልምድ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል መያዙ ነው፤ «ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል« (1ኛ ቆሮ. 10፡13)።

አንድ የሰንበት ትምህርት ቤት መምህር በታዳጊዎች ለተገነባው የተማሪዎች ቡድን፥ በክርስቲያን ውስጥ ስለሚገኙ ሁለት ባሕርያት ማለትም ስለ አሮጌውና አዲሱ ባሕርያት እያብራራ ነበር።

«አሮጌው ባሕርያችን ከአዳም የተላለፈልን ሲሆን፥ አዲሱ በሕርያችን ደግሞ የኋለኛው አዳም ተብሎ ከተጠራው ከክርስቶስ የተሰጠን ነው» ሲል ገለጸ። በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡45 የተጻፈውንም ለክፍሉ ተማሪዎች አነበበ፤ «እንዲሁ ደግሞ፡- ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ።»

ከታዳጊዎቹም አንዱ፥ «ይህ ከሆነ፥ በእኔ ውስጥ ሁለት ‹አዳሞች› አሉ ማለት ነው» ሲል ተናገረ።

«ልክ ብለሃል! የዚህ እውነታ ተግባራዊ እሴት ምንድን ነው?» ሲል ጠየቀ መምህሩ።

ክፍሉ ለአፍታ ጸጥ ብሎ እንደቆየ ከወደ ጥግ አንዲት እጅ ብቅ አለች።

«ይህ የሁለት አዳሞች አሳብ ፈተናን ስለመጋፈጥ ትልቅ ትምህርት ይሰጠኛል» አለ እጁን ያወጣው ተማሪ። ቀጥሎም፥ «ፈተና በሩን ሲያንኳኳ የመጀመሪያው አዳም ምላሽ እንዲሰጥ ከላክሁት በኃጢአት መውደቅ ነው። የኋለኛውን አዳም ከላክሁ ግን ድሉን አገኛለሁ» አለ።

እውነተኛ አማኝ ኃጢአትን ሥራዬ ብሎ አይለማመድም፤ አስመሳይ አማኝ ግን በውስጡ የእግዚአብሔር አዲስ ባሕርይ ስለሌለው ኃጢአትን ከመለማመድ የተሻለ ተግባር ሊከውን አይችልም። በተጨማሪም፥ እውነተኛው አማኝ ሌሎች ክርስቲያኖችን ይወዳል፤ ይህም በ1ኛ ዮሐንስ 3፡11–24 በዝርዝር ተገልጾአል።

ይሁንና፥ እነዚህ ቃላት የተጻፉት እኔና አንተ የሌሎች ሰዎችን ሕይወት እንድንመረምር አይደለም። ይልቁንም፥ እነዚህ ቃላት በእስትንፋሰ – እግዚአብሔር የተላለፉልን ራሳችንን እንመረምር ዘንድ ነው። እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር ፊት በታማኝነት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልንመልስ ይገባናል።

1. በልቤ ውስጥ መለኮታዊ ባሕርይ አለ ወይስ ክርስቲያን ነኝ ብዬ እያስመሰልሁ ነው?
2. ይህንን መለኮታዊ ባሕርይ በዕለታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና በጸሎት አሳድገዋለሁ?
3. ማንኛውም ንስሐ ያልገባሁበት ኃጢአት ውስጠኛ ሰውነቴን አርክሶታል? ተናዝዤ ልተወው ፈቃደኛ ነኝ?
4. አሮጌው ባሕርይ አሳቤንና ፍላጎቴን እንዲቆጣጠር እፈቅዳለሁ፥ ወይስ የሚገዛኝ መለኮታዊው ባሕርይ ነው?
5. ፈተና ሲመጣ አብሬው እጫወታለሁ፥ ወይስ ከእርሱ እሸሻለሁ? ወዲያው በውስጤ ላለው መለኮታዊ ባሕርይ ራሴን እሰጣለሁ?

እውነተኛ የሆነ ሕይወት በእግዚአብሔር ፊት ስለ እነዚህ ዋንኛ ጉዳዮችም እውነተኛ ነው።

# ማፍቀር ወይስ መሞት?

## 1ኛ ዮሐንስ 3፡11-24

የዮሐንስ መልእክት በተደጋጋሚ ወደ ሦስቱ ተመሳሳይ ርእሰ-ጉዳዮች (ፍቅር፥ መታዘዝ፥ እውነት) ስለሚመለስ፥ አልፈው ወደ ሄዱት ስፍራ በሌላ አቅጣጫ መልሶ ከሚያመጣ የሕንፃ ደረጃ ጋር የሚነፃፀር ነው። ምንም እንኳ እነዚህ ጭብጦች በተደጋጋሚ ቢታዩም፥ አሳቡ ባዶ ድግግሞሽ አይደለም። ወደ ርእሰ-ጉዳዩ በተመለስን ጊዜ ሁሉ፥ አሳቡ ከሌላ እይታ አንጻር የሚቀርብልን ሲሆን ይበልጥ ወደ ጠለቀ መረዳት እናመራለን።

ቀደም ብለን ለሌሎች አማኞች፥ ማለትም ለወንድሞች ስለሚኖረን ፍቅር የተማርን ቢሆንም(2፡7-11)፥ በምዕራፍ ሁለት አጽንኦት የተሰጠው *ለኅብረት* ነው። «በብርሃን የሚመላለስ» አማኝ ይህንኑ እውነት የሚያሳየው ወንድሞችን በመውደድ ነው። በዚህኛው ክፍል ግን አጽንኦት የተሰጠው ከሌሎች አማኞች ጋር በሚኖረን *ግንኙነት* ላይ ነው።

ክርስቲያኖች ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለዱና ይህም ሁሉንም በክርስቶስ ወንድማማቾች እና እህትማማቾች ስለሚያደርጋቸው፥ እርስ በርሳቸው ይዋደዳሉ።

መታዘዝና ፍቅር የልጅነትና የወንድምነት መረጃዎች ናቸው። ቀደም ብለን እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ጽድቅን እንደሚያደርግ የተመለከትን ሲሆን (3፡1-10)፥ አሁን ደግሞ በወንድሞች መካከል ስለሚኖር ፍቅር እንነጋገራለን (ቁ. 11-24)። ይህ እውነት መጀመሪያ የተገለጸው በአሉታዊ መልኩ ነው፤ «ጽድቅን የሚያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም» (ቁ. 10)።

ከዚህ በፊት በተመለከትነውና አሁን በቀረበልን የወንድማማች ፍቅር መካከል አስደንጋጭ ልዩነት እንዳለ ልናጤን ይገባል። ስለ ኅብረት በሚናገረው ክፍል ውስጥ (2፡7-11) ወንድሞችን መውደድ የብርሃንና የጨለማ ጉዳይ እንደሆነ ተነግሮናል። ስለ እምነታችን ምንም ያህል ብናወራ ወንድሞችን እስካልወደድን ድረስ በብርሃን ልንመላለስ አንችልም። ዳሩ ግን በዚህ ስለ ወንድማማቾች በቀረበው ክፍል (3፡11-24) መልእክቱ ይበልጥ ጠለቅ ብሎ ይሄዳል። በዚህም ወንድሞችን መውደድ *የሕይወትና የሞት ጉዳይ* እንደሆነ ተነግሮናል። «ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል» (ቁ. 14)።

ስለዚህ የወንድማማች ፍቅር ስንነጋገር፥ አንድ ሰው ሊኖርባቸው የሚችላቸው አራት «የግንኙነት ደረጃዎች» አሉ፤ እነዚህም፥ ግድያ (ቁ. 11–12)፥ ጥላቻ (ቁ. 13–15)፥ ግዴለሽነት (ቁ. 16–17) እና ክርስቲያናዊ ርኅራኄ ናቸው (ቁ. 18–24)።

የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ፍጹም የክርስቲያን ባሕርያት አይደሉም፤ ሦስተኛው ከክርስቲያን ባሕርይ ያነሰ ሲሆን፥ ለእውነተኛ የክርስትና ፍቅር የሚስማማው የመጨረሻው ብቻ ነው።

## 1. ግድያ (1ኛ ዮሐ. 3፡11–12)

በመሠረቱ ግድያ አንድ ሰው ከሌላው ጋር የሚኖረው ግንኙነት እጅግ ዝቅተኛው መለኪያ ሲሆን፥ ይህ ራሱ ሰይጣን የሚኖርበት ደረጃ ነው። ዲያብሎስ ከውድቀቱ ጅማሬ ጀምሮ ነፍሰ–ገዳይ ነበር (ዮሐ. 8፡44)፤ ክርስቲያኖች ግን ገና ከመጀመሪያው ልምዳቸው የሰሙት ነገር ቢኖር «እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ» የተነገራቸውን መልእክት ነው። ዮሐንስ በ«ጅማሬዎች» ላይ አጽንኦት በማድረግ፥ «ወደ መጀመሪያው ተመለሱ» ይላል። መንፈሳዊ ገጠመኞችን የጀመረው ከአብ ከሆነ፥ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባል። ከሰይጣን ከጀመረ ግን ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው። «እናንተስ ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ጸንቶ ይኑር» (1ኛ ዮሐ. 2፡24)።

ቃየን የጥላቻ ሕይወት ምሳሌ ሲሆን፥ ዘገባውን ከዘፍጥረት 4፡1–16 እናገኛለን። ወንድማማች የነበሩት ቃየንና አቤል አንድ አባትና እናት እንደነበሩአቸው፥ ሁለቱም ለእግዚአብሔር መሥዋዕታቸውን እንዳቀረቡ መመልከቱ መልካም ነው። ቃየን ያቀረበው እንደ ከሃዲ ሳይሆን እንደ አምላኪ ነበር። ይሁንና፥ ቁም ነገሩ እዚህ ላይ ነው፤ ይኸውም የዲያብሎስ ልጆች እውነተኛ አማኞች መስለው ሊቀርቡ ይችላሉ። እንደ ቃየን ሃይማኖታዊ ስብሰባዎች ሊካፈሉና መሥዋዕታቸውንም ሊያቀርቡ ይችላሉ። ይህም ሆኖ፥ እነዚህ ተግባራት በራሳቸው የአንድን ሰው ከእግዚአብሔር መወለድ አያረጋግጡም። እውነተኛው ፈተና ለወንድሞች በሚኖረው ፍቅር ነው– ቃየንም የወደቀው እዚህ ጋ ሲደርስ ነበር።

እያንዳንዱ ሰው ሥጋዊም ሆነ «መንፈሳዊ የዘር ሐረግ» አለው፤ የቃየን «መንፈሳዊ አባት» ዲያብሎስ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ይህ ማለት ግን ቃየን በቀጥታ የተረገዘውና የተወለደው ከሰይጣን ነው ማለት አይደለም። ይልቁንም የቃየን ተግባራትና አመለካከቶች ከሰይጣን የመነጩ ናቸው ማለት ነው። ቃየን እንደ ሰይጣን ሁሉ ነፍሰ–ገዳይና ውሸታም ነበር (ዮሐ. 8፡44)። የገዛ ወንድሙን ገድሎ ሲያበቃ ስለ ድርጊቱ የውሸት ምክንያቱ አቅርቧል። «እግዚአብሔርም ቃየንን

አለው፦ ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? እርሱም አለ፦ አላውቅም» (ዘፍ. 4:9)።

ከዚህ በተቃራኒ፥ እግዚአብሔር ፍቅር (1ኛ ዮሐ. 4:8) እና እውነትም ነው (5:6፤ ዮሐ. 14:6)፤ ስለሆነም፥ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ፍቅርንና እውነትን ይለማመዳሉ።

በቃየን መሥዋዕትና በአቤል መሥዋዕት መካከል የነበረው ልዩነት «እምነት» ነበር (ዕብ. 11:4)፤ እምነት ደግሞ እግዚአብሔር በሰጠው ግንኙነት ላይ የሚመሠረት ነው (ሮሜ 10:17)። እግዚአብሔር እንዴት ሊመለክ እንደሚገባ ግልጽ ትእዛዛትን የሰጠ ይመስላል። ቃየን ግን የእግዚአብሔርን ቃል ትቶ በራሱ መንገድ ለማምለክ ወሰነ። ይህም ከሰይጣን ጋር የነበረውን ግንኙነት ያሳያል፤ ምክንያቱም ሰይጣን ሁልጊዜም ሰዎችን ከተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ ለመመለስ ስለሚፈልግ «በውኑ እግዚአብሔር አዝዞአልን?» (ዘፍ. 3:1) የሚለው የሰይጣን ቃል ለቃየን ወላጆችና ከዚያም በኋላ ለነበሩት የሰው ልጆች ሁሉ የመከራ ጅማሬ ነበር።

ጌታ የአቤልን መሥዋዕት ተቀብሎ የቃየንን የጠላበት ውጫዊ ምልክት አልተገለጸም። ምናልባትም የአቤልን የእንስሳና የደም መሥዋዕት ትበላ ዘንድ ከሰማይ እሳት አውርዶ ይሆናል። ውጤቶቹ ግን በግልጽ ተቀምጠውልናል፤ ይኸውም፥ አቤል ከመሠውያው አካባቢ የተመለሰው በልቡ የእግዚአብሔርን የተቀባይነት ምስክር ይዞ ሲሆን፥ ቃየን ግን ተቆጥቶና ተበሳጭቶ መሄዱ ነበር (4:4–6)። እግዚአብሔር ኃጢአት በደጁ ላይ እንደ አደገኛ አውሬ እያደባች መሆኗን በመግለጽ ቃየንን አስጠንቀቀው (ቁ. 7)፤ በዚህም ላይ፥ ቃየን እግዚአብሔርን ቢታዘዝ እንደ አቤል ሰላምን አግኝቶ እንደሚደሰት ቃል ገባለት።

ቃየን የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ እንደመስማት ለሰይጣን ድምፅ ጆሮውን በማዋሱ፥ የገዛ ወንድሙን ለመግደል አሤረ። ቅንዓቱ ወደ ጥላቻና ቁጣ ተለወጠ። የራሱን ክፋትና የወንድሙን ጻድቅነት ልቡ ያውቀው ነበር። ስለሆነም፥ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ንስሐ መግባት ሲኖርበት ወንድሙን ለማጥፋት ወሰነ።

ከምእተ–ዓመታት በኋላ ፈሪሳውያንም በኢየሱስ ላይ ተመሳሳይ በደል ፈጽመዋል (ማር. 15:9–10)፤ ኢየሱስም የዲያብሎስ ልጆች ሲል ጠርቶአቸዋል (ዮሐ. 8:44)።

የቃየን አመለካከት የዛሬውን ዓለም አመለካከት ይወክላል (1ኛ ዮሐ. 3:13)። ዓለም ክርስቶስን የሚጠላው ቃየን አቤልን በጠላበት ምክንያት ነው (ዮሐ. 15:18–25)፤ ይኸውም፥ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት

በማጋለጥ ትክክለኛ ባሕርዩን ስለሚያሳይ ነው። ልክ እንደ ቃየን፥ ዓለም ከእውነታ ጋር ፊት ለፊት ስትጋፈጥ ማድረግ የምትችለው ከሁለቱ ውሳኔዎች አንዱን ብቻ ነው፤ ይኸውም፥ ንስሐ ገብቶ መለወጥ ወይም ያጋለጣትን ማጥፋት ነው።

ሰይጣን «የዚህ ዓለም አለቃ» ስለሆነ (ዮሐ. 14፡30)፥ በነፍስ ግድያና በውሸት አማካኝነት ይቆጣጠረዋል። በዚህ የሰይጣን የአኗኗር ደረጃ መመላለሱ ምንኛ የከፋ ነገር ነው!

አንድ አዳኝ ዝናብ ሲመጣበት በዋሻ ውስጥ ተጠለለ። የልብሱን ርጥበት ትንሽ ካደረቀ በኋላም፥ ጊዜያዊ መጠለያውን በሚገባ ለማየት ፈልጎ ባትሪውን አበራ። በዚህም ጊዜ ዋሻዪቱን ከሸረሪቶች፥ ከእንሽላሊቶችና ከእባቦች ጋር እየተጋራት እንዳለ ሲያውቅ ምን እንደሚሰማው መገመት አያዳግትም! ከመቅጽበት ሮጦ ወጣ።

ያልዳነው ዓለም ዓይኑን ገልጦ ሊመለከት ቢችል፥ በዚያ በጥንቱ እባብ ሰይጣንና ጠቅላላ የአጋንንት ሠራዊት ተከብቦ በዝቅተኛ የግድያና የውሸት ደረጃ እንደሚኖር ይገነዘብ ነበር። እንደ ቃየን፥ የዓለም ሕዝቦች እውነተኛውን ባሕርያቸውን በሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ለመሸፈን ይጥራሉ፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ቃል ላይ እምነት የላቸውም። በዚህ ደረጃ መኖራቸውን የሚቀጥሉ ሰዎች በመጨረሻው ለዘላለም ከእግዚአብሔር ተለይተው ወደሚሠቃዩበት የውጭ ጨለማ ከሰይጣን ጋር ይጣላሉ።

## 2. ጥላቻ (1ኛ ዮሐ. 3፡13-15)

ምናልባትም በዚህ ጊዜ፥ «እኔ ግን ማንንም አልገደልሁም!» ብለህ እያሰብህ ይሆናል። ለዚህ አሳብህ እግዚአብሔር፥ «ልክ ነህ፤ ይሁንና፥ ለክርስቲያን ጥላቻም ከነፍስ ግድያ እኩል እንደሆነ ልብ በል» ሲል ይመልሳል (ቁ. 15ን ከማቴ. 5፡22 ጋር አመሳክር)። በደረጃ አንድና ደረጃ ሁለት መካከል የሚታይ ልዩነት ቢኖር ውጫዊ ሕይወት የመንጠቅ ተግባር ብቻ ነው! ውስጣዊው ፍላጎት ግን ያው ነው።

የእንስሳትን ፓርክ ለመጎብኘት የሄደው ሰውዬ ከአናብስት ቤት ጠባቂ ጋር ይነጋገር ነበር።

«በቤቴ ድመት አለችኝ። ያንተም አናብስት ልክ እንደ እኔዋ ድመት ናቸው የሚሆኑት። ሰላማዊ እንቅልፍ ሲተኙ እያቸው! እናም እነዚያን ውብ ፍጡሮች በሽቦ አጥር መከለሉ የሚያሳዝን ተግባር ይመስላል» ሲል ጎብኚው ተናገረ።

ጠባቂውም እየሳቀ፥ «ወዳጄ፥ እነዚህ አናብስት ያንተን ድመት መስለው ይታዩ ይሆናል፤ ባሕርያቸው ግን ሙሉ ለሙሉ የተለየ ነው። በልባቸው ውስጥ የመግደል ጥማት አለ። ይልቁንም የሸበ አጥሮቹ ዙሪያ ስላለህ ደስ ልትሰኝ ይገባል» ሲል መለሰለት።

አንዳንድ ሰዎች አንዱንም ሰው እንኳ ያልገደሉበት ብቸኛው ምክንያት እስራትን በመፍራት፥ ሃፍረትን በመሸሽ፥ የሕግ ቅጣትን በማሰብና ምናልባትም ሊከተል የሚችለውን የሞት ፍርድ በማሰላሰል ነው። ይሁንና፥ «በነጻነት ሕግ» እንዳኛለን (ያዕ. 2:12)። ጥያቄው እንግዲህ፥ «ምን *አድርገሃል?*» የሚል ሳይሆን፥ «ምን *ልታደርግ ፈልገህ ነበር?* እንደ ልብህ የማድረግ ነጻነት ቢኖርህ ኖሮ ምን *ታደርግ* ነበር?» የሚል ነው። ኢየሱስ ጥላቻን ከግድያ (ማቴ. 5:21–26)፥ ምኞትን ከዝሙት (ቁ. 27–30) ጋር እኩል የሚያደርገው ለዚህ ነው።

ይህ ማለት ግን በልብ ውስጥ ያለ ጥላቻ ከግድያ ጋር ተመሳሳይ መጠን ያለው አደጋ ወይም እኩል በደለኛነት ያስከትላል ማለት አይደለም። ጎረቤትህ ከምትገድለው ይልቅ ብትጠላው ይመርጣል! በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ግን ጥላቻ ከግድያ ጋር እኩል የሥነ–ምግባር ደረጃ አለው፤ ጥላቻ ልጓም ካልተደረገበት ወደ ግድያ ይመራል። ክርስቲያን ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገረ ሲሆን (ዮሐ. 5:24)፥ የዚህም ማረጋገጫው ወንድሞችን መውደዱ ነው። የዓለም ሥርዓት አካል በነበረ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሰዎች ሲጠላ ቢቆይም፥ አሁን ግን የእግዚአብሔር በመሆኑ ይወዳቸዋል።

በአማኝ ሕይወት ውስጥ ስለሚገኝ የልምድ ኃጢአት እንደሚናገሩት ሁሉ፥ (1፥5–2፥6) እነዚህም ጥቅሶች (1ኛ ዮሐ. 3:14–15) ስለተወሰነ የሕይወት ፍሬ ይገልጻሉ፤ ይኸውም፥ ምንም እንኳ በአጋጣሚ ከወንድሙ ጋር ሊጣላ ቢችልም (ማቴ. 5:22–24)፥ አማኝ ወንድሞችን በመውደድ ልምምድ ውስጥ ነው። በአጋጣሚ የሚከሰት ጥል መመሪያውን አይሽረውም። አብረውት ከሚያመልኩ ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት የሌለው አማኝ ጎስቋላ ሰው ስለሆነ፥ የጥል ገጠመኞች ይህንኑ ያረጋግጡለታል።

ሌላም እውነት አለ፦ ነፍሰ–ገዳዮች ሊድኑ እንደማይችሉ አልተጠቀሰም። ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱ በእስጢፋኖስ መወገር ላይ እገዛ ያደረገ ሲሆን (የሐዋ. 7:57–60)፥ የእርሱ ድምፅ ንጹኃን ሰዎችን ለመግደል እንደረዳ አምኖአል (1ኛ ጢሞ. 1:12–15፤ የሐዋ. 26:9–11)። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ጳውሎስን አድኖታል።

እዚህ ላይ ቁም ነገሩ ነፍሰ–ገዳይ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል ወይ? የሚል ሳይሆን፥ አንድ ሰው የነፍሰ–ገዳይነት ተግባሩን እንደቀጠለ ሆኖ

ክርስቲያን ሊሆን ይችላል ወይ? የሚል ነው። መልሱ አይሆንም ነው። «ነፍሰ-ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ» (1ኛ ዮሐ. 3፡15)። ነፍሰ ገዳዩ በአንድ ወቅት የዘላለም ሕይወት ኖሮት አሁን ማጣቱ አይደለም፤ ከቶውንም የዘላለም ሕይወት አልነበረውም።

እስካሁን አንዱንም ሰው ያለመግደልህ እውነታ እንድትታበይ ሊያደርግህ ወይም በራስ ብቃት ሊያስመካህ አይገባም። በልብህ ውስጥ ጥላቻ ተፈጥሮ አያውቅምን?

ጥላቻ ከማንም በላይ የሚጎዳው የጠላውን ነው (ማቴ. 5፡21-26)። አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ዘመን ቁጣ የተቆጣውን ሰው በፍርድ ችሎት ያቆም ነበር። ወንድምን «የማትረባ» ብሎ መሳደብ በታላቁ የአይሁድ ሸንጎ ፊት ሲያቀርበው፥ «ደደብ» ማለቱ የሲኦልን የዘላለም ፍርድ ያስከትላል። ንስሐ ገብተው ያልተዉት ጥላቻ ወደ መንፈሳዊና ስሜታዊ ወኅኒ ቤት ይከታል! (ቁ. 25)።

ለጥላቻ መድኃኒቱ ፍቅር ነው። «መጣላትና መጠላላት» ያልዳነው ሰው ተለምዶአዊ ሕይወት ነው (ቲቶ 3፡3)። ዳሩ ግን የጥላቻ ልብ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሲከፈት አፍቃሪ ልብ ይሆናል። ከዚያም በጥላቻ አማካኝነት ሌሎችን «ለመግደል» ከመፈለግ ይልቅ ሊወዳቸውና የዘላለምን ሕይወት ሊያካፍላቸው ይሻል።

ወንጌላዊው ጆን ዌስሊ በመንገድ ላይ በሌሊት ሲሄድ ሳለ አንድ ሰውዬ ገንዘቡን ዘረፈው። ዌስሊ ለዚህ ሰው፥ «ይህንን ክፉ መንገድ ለቅቀህ ለእግዚአብሔር ለመኖር የምትፈልግበት ዕለት ከመጣ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነጻ አስታውስ» ብሎታል።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ዝግጅት አልቆ ሲወጣ አንድ ሰው ወደ ዌስሊ መጣ። ሰውዬውም፥ «ታስታውሰኛለህ?» ሲል ጠየቀው። ከዚያም፥ «አንድ ምሽት አስቁሜ ስዘርፍህ ሳለ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነጻ ነግረኸኝ ነበር። እኔም በክርስቶስ በማመኔ ሕይወቴን ለውጦልኛል» ሲል ታሪኩን አጫወተው።

## 3. ግድየለሽነት (1ኛ ዮሐ. 3፡16-17)

የክርስትና ፍቅር መለኪያው በሌሎች ላይ *ክፉ* አለመሥራት ብቻ ሳይሆን፥ *መልካም* ማድረግም ጭምር ነው። የክርስትና ፍቅር አሉታዊም አዎንታዊም ገጽታዎች አሉት። «ክፉ ማድረግን ተዉ፥ መልካም መሥራትን ተማሩ» (ኢሳ. 1፡16-17)።

ቃየን ለውሸተኛ ፍቅር ጥሩ ምሳሌ ሲሆን፥ ክርስቶስ ለእውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር ምሳሌ ነው። እውነትን እናደርግ ዘንድ ኢየሱስ ሕይወቱን ስለ እኛ ሰጥቶአል። እያንዳንዱ ክርስቲያን ዮሐንስ 3፡16ን ያውቀዋል፤ ግን ለ1ኛ ዮሐንስ 3፡16 አትኩሮታችንን የምንሰጥ ስንቶቻችን ነን? የዮሐንስ 3፡16ን በረከት መቀበሉ ግሩም ነው፤ እንዲሁም 1ኛ ዮሐንስ 3፡16ን በመታዘዙ የተቀበልነውን በረከት ለሌሎች *ማጋራቱ* የበለጠ ግሩም ነው፤ ይኸውም ክርስቶስ ስለ እኛ ነፍሱን እንደ ሰጠ እኛም ስለ ሌሎች ነፍሳችንን ልንሰጥ እንደሚገባን ነው።

የክርስትና ፍቅር *መሥዋዕትነትን*ና አገልግሎትን ያካትታል። ክርስቶስ ስለ ፍቅሩ *መናገር* ብቻ ሳይሆን፥ የፍቅሩን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ሞቷል (ሮሜ 5፡6–10)። ኢየሱስ በፈቃዱ ነፍሱን *ሰጠ* እንጂ እንደ *ሰማዕታት* አልተገደለም (ዮሐ. 10፡11–18፤ 15፡13)። *«ራስን ማዳን»* የሥጋዊ ሕይወት ቀዳሚ ሕግ ሲሆን፥ *«ራስን መሠዋት»* የመንፈሳዊ ሕይወት ቀዳሚ ሕግ ነው።

እግዚአብሔር ግን ሕይወታችንን እንድንሰጥ አይጠይቀንም። የሚጠይቀን በችግር ላይ ያለውን ወንድም እንድንረዳ ብቻ ነው። ዮሐንስ በ1ኛ ዮሐንስ 3፡16 «ወንድሞች» ከማለት በቁጥር 17 «ወንድሙ» ወደ ማለቱ በጥበብ ይዛወራል።

«ወንድሞችን ስለ መውደድ» እያወሩ ግን አንዱን አማኝ ለመርዳት አለመፈለግ ቀላል ነው። ይሁንና፥ የክርስትና ፍቅር ግላዊና የሚሠራ ነው።

ኢየሱስ በመልካሙ የሰማርያ ሰው ምሳሌ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክትም ይህ ነው (ሉቃ. 10፡25–37)። ሕግ አዋቂው ስለ ረቂቅ ርእሰ–ጉዳይ ለመነጋገር ፈልጎ፥ «ባልንጀራዬ ማን ነው?» ሲል ጠየቀ። ኢየሱስ ግን *አጽንኦቱን በችግር ላይ ወዳለው አንድ ሰው* በማተኮር፥ ጥያቄውን «ለማን ባልንጀራ ልሆንለት እችላለሁ?» ወደሚል መንፈስ ቀየረው።

ሁለት ጓደኛሞች የወንጌል ስርጭትን በተመለከተ የተዘጋጀውን ስብሰባ እየተካፈሉ ነበር። ከስብሰባዎቹ በአንዱ ሌሪ ፒተር የተባለ ጓደኛውን ያማዋል። በኋላም ለተሰብሳቢዎቹ በተዘጋጀው ምግብ ላይ ሲያገኘው፥ «በአሥር ሰዓቱ ስብሰባ ላይ አልነበርህም። በጣም ጠቃሚ ስብሰባ ነበር! የት ነበርህ?» ሲል ይጠይቀዋል።

ፒተርም፥ «ከበሩ ጥግ የሆቴሉ ውስጥ ሠራተኛ ለሆነ ልጅ ስለ ክርስቶስ እየተናገርሁ ነበርና፥ በክርስቶስ ሊያምን ችሏል!» ሲል መለሰለት።

ስብሰባዎችን መካፈል ስሕተት ባይሆንም፥ ጠቅለል ባሉ ጉዳዮች ላይ እየተነጋገሩ አንድን ግለሰብና ችግሮቹን መዘንጋቱ ቀላል ነው። የክርስትና ፍቅር መለኪያው ጠቅላላውን ቤተ ክርስቲያን እንደሚወዱ ጮክ ብሎ በመናገር የሚደመደም ሳይሆን በችግር ውስጥ ያለውን ወንድም ሌላው ሰው ሳያውቅ መርዳት ነው። ስለሆነም፥ ወንድማችንን የማንረዳ ከሆነ ለወንድሞቻችን ነፍሳችንን ለመስጠት አንችልም።

አንድ ሰው ኃጢአት ለመሥራት የግድ ነፍስ ማጥፋት የለበትም፤ ጥላቻም ራሱ በልብ ሰውን መግደል ነው። እንዲሁም ኃጢአተኛ ለመሆን ሰው ወንድሙን መጥላት አያስፈልገውም፥ ስለ ችግሮቹ ቸልተኛ ወይም ግድየለሽ መሆኑ እንኳ ይበቃዋል። ቁሳዊ ሀብት ያለውና የወንድሙን ችግሮች ሊያቃልል የሚችል አማኝ ይህንኑ ማድረግ አለበት። በወንድም ላይ «የልብን በር መዝጋት» የግድያ ዓይነት ተግባር ነው።

ወንድሜን ለመርዳት ስነሣ ሦስት ሁኔታዎችን ማሟላት አለብኝ። መጀመሪያ፥ ችግሩን ለማቃለል የሚያስችል መንገድ ሊኖረኝ ይገባል። ሁለተኛ፥ የችግሩን መኖር ማወቅ አለብኝ። ሦስተኛ፥ ያለኝን ለማካፈል በቂ ፍቅር ሊኖረኝ ይገባል።

ለመርዳት ዓቅሙ የማይፈቅድለት ወይም የወንድሙን ችግር የማያውቅ አማኝ አልተኮነነም። የተኮነነው በድሀ ወንድሙ ላይ ልቡን የሚያደነድን አማኝ ነው። ክርስቲያኖች በሥራ ሊተጉ ይገባቸዋል፤ ምክንያቱም የተቸገረውን ለመርዳት እንዲችሉ ነው (ኤፌ. 4:28)።

በዚህ አያሌ ማኅበራዊ ድርጅቶች ባሉበት ዘመን፥ ለክርስቲያኖች ግዴታዎቻቸውን መዘንጋቱ ቀላል ነው። «እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ» (ገላ. 6:10)።

ይህ «መልካም ማድረግ» በገንዘብ ወይም በቁሳቁስ ደረጃ ብቻ የሚገለጽ መሆን የለበትም። የግል አገልግሎትንና ራስን ለሌሎች መስጠትን ሊያካትት ይገባል። በአብያተ ክርስቲያናታችን ፍቅርን ያጡና ለጓደኝነት እጆቻቸውን የሚዘረጉ ሰዎች ሞልተዋል።

በምስክርነት ስብሰባ ላይ አንዲት ወጣት የልጆች እናት ለግል የጽሞና ተግባር ምንም ጊዜ እንዳልነበራት ሳትደብቅ ተናግራ ነበር።

አያሌ ትናንሽ ልጆች ስለነበሩአትና ለእነዚህም ልጆች እንክብካቤ ማድረግ ስለነበረባት፥ ሰዓቶቹ በጥድፊያ ያልፉባት ነበር።

በሌላ ቀን ሁለት የቤተ ክርስቲያን ሴቶች ከቤትዋ በር ላይ ሲታዩ ምን ያህል እንደተደነቀች ልትገምት ትችላለህ።

«እኛ የመጣነው ልንረዳሽ ነው። አንቺ ወደ መኝታ ክፍልሽ ግቢና የጽሞና ጊዜሽን ጀምሪ» አሉአት። የዚህ ዓይነቱ እገዛ ለተከታታይ ጊዜያት ከቀጠለ በኋላ ወጣቷ እናት የራሷን የጽሞና ተግባር ልታከናውን በመቻሏ ዕለታዊ ተግባሯን በሚገባ ልትወጣ ችላለች።

የእግዚአብሔርን ፍቅር አግኝተን በልባችን ለመደሰት ከፈለግን፥ እስከ *መሥዋዕትነትም* ድረስ ቢሆን ሌሎችን መውደድ አለብን። ለወንድም ችግር ግድየለሽ መሆን ማለት ይበልጥ ከሚያስፈልገን ነገር ማለትም በልባችን ሊኖር ከሚገባው የእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችንን ማቀብ ማለት ነው። ጥያቄውም የማፍቀር ወይም የመሞት ጉዳይ ይሆናል!

## 4. የክርስትና ፍቅር (1ኛ ዮሐ. 3፡18–24)

እውነተኛ የክርስትና ፍቅር ማለት በተግባርና በእውነት መውደድ ነው። የተግባር ተቃራኒ ንግግር ሲሆን፥ የእውነት ተቃራኒ ደግሞ አንደበት ነው። በንግግር ብቻ የሆነን ፍቅር እንዲህ አስቀምጦታል። «ለምሣሌ የሚለብሱትና የሚመገቡት የሌላቸው ወንድሞችና እህቶች ቢኖሩ እናንተ ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሳትሰጡአቸው ‹በሰላም ሂዱ! ይሙቃችሁ! ጥገቡ!› ብትሉአቸው ምን ይጠቅማቸዋል?» (ያዕ. 2፡15–16 – ከ1980 ዓ.ም. እትም)

«በቃል» መውደድ ማለት ስለሚያስፈልገው ነገር ከማውራት አያልፍም። «በተግባር» መውደድ ግን የሚያስፈልገውን ለመስጠት መጣርን ይጨምራል። ስለ ወንድማችን ችግር ብንወያይ አልፎም ብንጸልይ ድርሻችንን ተወጣን ማለት አይደለም። እውነተኛው ፍቅር ከንግግርም ያልፋል። የመሥዋዕትነት ሥራንም ይጠይቃል።

«በእውነት መውደድ» ማለት አንድን ሰው ከአንደበት ብቻ ሳይሆን በሚገባ ከልብ መውደድ ማለት ነው። ስለሆነም፥ ሰዎች በእውነተኛ ፍቅር ሲሳቡ፥ «አርተፊሻል» ባሕርይ ግን ይገፈትራቸዋል። ኃጢአተኞች ወደ ኢየሱስ ከመጡባቸው ምክንያቶች አንዱ ከእውነተኛ ልብ እንደሚወዳቸው እርግጠኞች መሆናቸው ነበር።

«ግን ለአማኝ የዚህ ዓይነቱን ፍቅር መከተል ከፍተኛ ዋጋ *አይጠይቀውም?»*

አዎን፥ ይጠይቃል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ከፍሎአል። ይሁንና፥ የዚህ ፍቅር ውጤቶች ሆነው የሚመጡልህ ግሩም ጠቀሜታዎች ከምትከፍለው መሥዋዕትነት የላቀ ካሳ ያተርፉልሃል። እንደ እውነቱ ከሆነ አንተ ሌሎችን የምትወደው በምላሹ አንድ ነገር ለማግኘት አይደለም፤ ዳሩ ግን «ስጡ ይሰጣችሁማል» (ሉቃ. 6:38) የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ ለፍቅርም ሆነ ለገንዘብ ይሠራል።

ዮሐንስ በክርስትና ፍቅር ለሚኖር አማኝ የሚመጡለትን ሦስት መልካም በረከቶች ይጠቅሳል፦

*1. ዋስትና (1ኛ ዮሐ. 3:19-20)።*

አንድ አማኝ ከሌሎች ጋር ያለው ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ላለው ግንኙነት ተጽዕኖ ያደርጋል። ከወንድሙ ጋር ያልተስማማ ሰው መሥዋዕቱን በመሠዊያው ላይ ከማቅረቡ በፊት ጉዳዩን ማስተካከል አለበት (ማቴ. 5:23-24ን ተመልከት)። ፍቅርን የሚከተል ክርስቲያን ለእግዚአብሔር እውነት ባለው ግንዛቤ በማደግ፥ በእግዚአብሔር ፊት ልቡን በመተማመን (ድፍረት) ሞልቶ የደስታ ሕይወት ይመራል።

«የሚኮንነው ልብ» የአማኙን ሰላም የሚነጥቀው ነው። ይህም «የሚወቅስ ሕሊና» በሚለው ሐረግ ሊገለጽ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ልባችን በስሕተት ይከስሰናል፤ ይህም «የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል?» እንደተባለው ነው (ኤር. 17:9)። ለዚህ ጥያቄ የሚኖረን መልስ *«እግዚአብሔር* ልብን ያውቃል!» የሚል ነው። ራሳቸውን በውሸት የከሰሱ ወይም ከሚገባው በላይ በራሳቸው ላይ የጨከኑ /የከበዱ/ ክርስቲያኖች አሉ፤ እግዚአብሔር ግን ከቶውንም የዚህ ዓይነት ስሕተት አይፈጽምም። በፍቅር የሚኖር ክርስቲያን ለእግዚአብሔር የተከፈተ ልብ ስላለው እግዚአብሔር በስሕተት እንደማይፈርድ ያውቃል። «እግዚአብሔር ፍቅር *ነው።»*

ምናልባትም ዮሐንስ ለዚህ ጠቃሚ መመሪያ ማብራሪያ የሚሆኑ ሁለት ገጠመኞችን ከኢየሱስ የምድር ላይ አገልግሎት ሊያስታውስ ይችል ነበር። ኢየሱስ ቢታንያን በጎበኘ ጊዜ በማርታና በማርያም ቤት ነበር ያረፈው (ሉቃ. 10:38-42)። ማርታ ምግብ ለማዘጋጀት ደፋ ቀና ስትል፥ ማርያም ግን ከእግሩ ሥር ተቀምጣ ትምህርቱን ታዳምጥ ነበር። በዚህም ጊዜ ማርታ ማርያምንና ኢየሱስን ብትወቅሳቸውም፥ ኢየሱስ ግን የማርያምን ልብ ያውቅ ስለነበረ ተከራከረላት።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ጌታውን ከካደ በኋላ አምርሮ ሲያነባ፥ ስለ ኃጢአቱ በጸጸትና በንስሐ እንደተሞላ ጥርጥር የለውም። ጌታ ግን

ጴጥሮስ ንስሐ እንደገባ ያውቅ ነበርና፥ ከትንሣኤው በኋላ ለተጣዳፊው ዓሣ አጥማጅ የይቅርታ ዋስትና የሚሰጥ ልዩ መልእክት ላከለት (ማር. 16፡7)። ምናልባትም የጴጥሮስ ልብ ጌታን ሦስት ጊዜ እንደካደ ስለሚያውቅ ኮንኖት ይሆናል፤ ይሁንና፥ እግዚአብሔር ከልቡ በላይ ነበር። ስለሆነም፥ ኢየሱስ ሁሉንም ነገር እያወቀ የሚያስፈልገውን ዋስትና ሰጠው።

ዲያብሎስ እንዳይከስህና ድፍረትህን እንዳይቀማህ ተጠንቀቅ (ራእይ 12፡10)። አንድ ጊዜ ኃጢአትህን ተናዝዘህ ይቅርታ ካገኘህ በኋላ ይከስህ ዘንድ ዕድል አትስጠው። የጴጥሮስ ክርስቶስን የመካድ ኃጢአት ይቅር ስለተባለለትና ስለተዘነጋ፥ አይሁዶችን ሊጋፈጥና «እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ካዳችሁ!» ብሎ ለመናገር ችሎአል (የሐዋ. 3፡14)።

ማንኛውም ክርስቲያን ኃጢአትን በዋዛ ሊመለከት አይገባም፤ ዳሩ ግን የትኛውም ክርስቲያን ከእግዚአብሔር በላይ በራሱ ላይ ሊጠጥር አይገባም። አንዳንድ ሰዎች የተጧዘዘ የራስ-ምርመራና ራስን የመኮነን ዘመቻ ያካሂዳሉ፤ ይህም መንፈሳዊነት አይደለም። ለወንድሞች እውነተኛ ፍቅር ካለህ፥ ልብህ በእግዚአብሔር ፊት ቀጥተኛ ሆኖአል፤ ይህም በልብህ ውስጥ ተመሣሣይ የልማድ ኃጢአት ቢኖር ኖሮ መንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በሕይወትህ አይገልጽም ነበር። ይህም በመሆኑ፥ መንፈስ ቅዱስን ስታሳዝን የእግዚአብሔር ፍቅር እንዳይቀርብህ ታደርገዋለህ (ኤፌ. 4፡30-5፡2)።

*2. የጸሎት መልስ (1ኛ ዮሐ. 3፡21-22)።*

ለወንድሞች የሚኖርህ ፍቅር ከእግዚአብሔር ጋር ላለህ ግንኙነት አስተማማኝ መሠረት ሲጥል፥ ይህም በበኩሉ ለምትፈልገው ነገር እግዚአብሔርን የመጠየቅ ድፍረት ይሰጥሃል። እንዲያም ሆኖ ወንድሞችን በመውደድ ለጸሎትህ መልስ ታገኛለህ ማለት አይደለም። ይልቁንም፥ ለወንድሞች የሚኖርህ ፍቅር እግዚአብሔር ጸሎትህን ሊመልስ በሚችልበት የፈቃዱ አቅጣጫ እንዳለህ ያረጋግጣል። «ትእዛዙን የምንጠብቅና በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን የምናደርግ ስለሆንን የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን» (ቁ. 22)። ፍቅር የእግዚአብሔር ሕግ ፍጻሜ ስለሆነ (ሮሜ 13፡8-10)፥ ወንድሞችን ስትወድ ትእዛዛቱን ስለምትጠብቅ፥ እርሱም ጥያቄዎችህን ለመመለስ ይችላል።

አማኝ ከወንድሞች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ከጸሎት ሕይወቱ ሊገነጠል አይችልም። ለምሳሌ፥ ባሎችና ሚስቶች የእግዚአብሔርን ቃል የማይታዘዙ ከሆነ ጸሎታቸው ይከለከላል(1ኛ ጴጥ. 3፡7)።

አንድ ወንጌላዊ ስለ ክርስቲያን ቤተሰብ ስብከት አቅርቦ ነበርና፥ ስብሰባው ሲያበቃ አንድ አባት ወደ ወንጌላዊው መጡ። «ለዓመታት ስለ ዓመፀኛው ልጄ እጸልይ ነበር፤ ይሁንና፥ እግዚአብሔር ጸሎቴን አልመለሰልኝም» ሲሉ አማረሩ።

ወንጌላዊውም፥ «በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር» የሚለውን የመዝሙር (66)፥18 ጥቅስ አነበበላቸው።

ከዚያም፥ «ለራስዎና ለእግዚአብሔር እውነተኛ ሁኑ፤ በእርስዎና በሌላ ክርስቲያን መካከል ሊስተካከል የሚገባው ነገር አለ?» ሲል ጠየቃቸው።

እኚህ አባት ጥቂት ካንገራገሩ በኋላ፥ «አዎ፥ መች ነገር ይጠፋል? በዚህ ቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው ላይ ቂም ይዤአለሁ» አሉት።

«እንግዲያው ይሂዱና ጉዳዩን ያስተካክሉ» ሲል መከራቸው፤ ሰውዬውም ካስቀየማቸው ወንድም ጋር ይቅር ተባብለው ሊጸልዩ ቻሉ። አባትም ከሰውዬው ጋር የነበራቸውን ጉዳይ ከመጨረሳቸው በፊት ዓመፀኛው ልጃቸው ወደ ጌታ ሲመለስ ተመለከቱ።

በመሠረቱ፥ እነዚህ ጥቅሶች ለጸሎት መልስ የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ ባያስቀምጡልንም *የታዛዥነትን* አስፈላጊነት ያጎላሉ። ለጸሎት መመለስ አንዱ ታላቅ ምሥጢር ታዛዥነት ሲሆን የታዛዥነት ምሥጢር ደግሞ ፍቅር ነው። «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» (ዮሐ. 14፥15)። «በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል። ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ» (ዮሐ. 15፥7፥ 10)።

በመሠረቱ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በፍቅር መንፈስ ሳይሆን በፍርሃት ወይም በባርነት መንፈስ መጠበቅ ይቻላል። በጠፋው ልጅ ታሪክ ውስጥ የተመለከተው የታላቁ ልጅ ኃጢአት ይህ ነበር (ሉቃ. 15፥24–32)። አንድ አማኝ የአብን ትእዛዛት የሚጠብቀው ይህንኑ ማድረግ ስለሚያስደስተው ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚኖር ክርስቲያን እግዚአብሔር ልጁን የሚያስደስትበትን መንገድ እንደሚያገኝ ይገነዘባልና። «በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፥ የልብህን መሻት ይሰጥሃል» [መዝ. (37)፥4]። *ደስታችን* በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ የተመሠረተ ሲሆን፥ *መሻታችንም* እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናል።

### *3. መኖር (1ኛ ዮሐ. 3፡23-24)።*

አንድ ጸሐፊ ኢየሱስን ታላቂቱ ትእዛዝ የትኛዪቱ እንደሆነች እንዲነግረው በጠየቀ ጊዜ፥ «እግዚአብሔር አምላክህን ውደድ» ሲል መልሶለታል። ቀጥሎም ሁለተኛዪቱን ትእዛዝ አከለለት፤ «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» (ማቴ. 23፡34-40)። በተጨማሪም፥ ሰውንና እግዚአብሔርን የምታካትት *አንዲት ትእዛዝ* ሰጥቷል፤ «በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ፥ ትእዛዝንም እንደ ሰጠን እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ» (1ኛ ዮሐ. 3፡23)። በእግዚአብሔር ማመንና ሰዎችን መውደድ የክርስቲያንን ግዴታዎች ያጠቃልላሉ። ክርስትና «በፍቅር የሚሠራ እምነት» ነው። (ገላ. 5፡6)።

ለእግዚአብሔር የሚኖረን እምነትና ለሰው የሚኖረን ፍቅር የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ይሁንና፥ በእምነት ማለትም በትክክለኛ አስተምህሮ ላይ እያተኮሩ ፍቅርን ችላ ማለት ቀላል ነው። በሌላ በኩል፥ ዶክትሪን አስፈላጊ እንዳልሆነና ዋናው ኃላፊነታችን መዋደድ እንደሆነ የሚናገሩ ሰዎች አሉ። *ዶክትሪንና ፍቅር ሁለቱም አስፈላጊዎች ናቸው።* አንድ ሰው በእምነት ሲጸድቅ፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በልቡ ውስጥ እንደሚፈስ ማወቅ አለበት (ሮሜ 5፡1-5)።

በእግዚአብሔር ላይ ድፍረት እንዲኖረውና የጸሎት መልስ እንዲሰጠው ለሚፈልግ አማኝ «በክርስቶስ *መኖር*» ዋንኛው ነገር ነው። ኢየሱስ በሰገነቱ ላይ ለደቀ መዛሙርቱ ባቀረበው መልእክት ስለ «መኖር» አብራርቶላቸዋል (ዮሐ. 15፡1-14)። በዚህም መልእክቱ ተከታዮቹን ከወይን ቅርንጫፎች ጋር አወዳድሮአል። ቅርንጫፍ የጉልበቱ ምንጭ የሆነውን ምግብና ውኃ ከወይኑ የሚስብ ከሆነ ፍሬ ያፈራል። ዳሩ ግን ራሱን ከወይኑ ከገነጠለ ጠውልጎ ይደርቃል።

በዚህ ስፍራ ኢየሱስ የተናገረው ስለ ፍሬ ማፍራት እንጂ ስለ ደኅንነት አይደለም። አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ በሚያምንበት ወቅት ወዲያው ከክርስቶስ ጋር *ጥምረት* ይፈጥራል፤ ይሁንና፥ *በአንድነቱ መኖር* የማያቋርጥ ኃላፊነቱ ነው። *መኖር* ቃሉን በመታዘዛችንና በንጽሕና በመኖራችን ላይ ይመሠረታል (ቁ. 3፡10)።

አስቀድመን እንደተመለከትነው፥ አንድ አማኝ በፍቅር በሚመላለስበት ጊዜ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ቀና ስለሚሆንለት ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ አንድነት ይኖረዋል። «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን» (ዮሐ. 14፡23)።

በ1ኛ ዮሐንስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በስም የተጠቀሰው በ3፡24 ላይ ነው። ዮሐንስ ቀደም ሲል በ2፡20 ከቅዱሱ ጋር አስተዋውቆናል፤ በዚህም ስፍራ አጽንኦት ያደረገው በመንፈስ ቅዱስ ቅባትና በማስተማር አገልግሎት ላይ ነው። (ይህም ከዮሐንስ 14፡26 እና 16፡13-14 አሳብ ጋር አብሮ ይሄዳል።) በተጨማሪም *መንፈስ ቅዱስ የሚኖር መንፈስ ነው*። (1ኛ ዮሐ. 3፡24፤ 4፡13)። አንድ አማኝ እግዚአብሔርን ሲታዘዝና ወንድሞችን ሲወድ፥ በውስጡ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ሰላምንና ድፍረትን ይሰጠዋል። ምንም በውስጡ ለዘላለም ቢኖርም እንኳ (ዮሐ. 14፡16)፥ መንፈስ ቅዱስ በሚያዝንበት ጊዜ በረከቶቹን ያቀባል።

እንዲሁም፥ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑት *ምስክርነት የሚሰጥ ወይም የሚያረጋግጥ መንፈስ ነው* (1ኛ ዮሐ. 4፡1-6)። አማኝ በክርስቶስ የሚኖር ከሆነ፥ መንፈስ ቅዱስ ምሪት በመስጠት ወደ ጥፋት ከሚወስደው የውሸት መንፈስ ያስጠነቅቀዋል።

ከዚህም በላይ መንፈስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና አገልግሎት *ይመሰክራል* (1ኛ ዮሐ. 5፡6-8)። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት በሮሜ 8፡14-16 ተጠቅሶአል።

አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱ አማኙ የፍቅር ሕይወት ውስጥ ተካትቶአል። እግዚአብሔር አብ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ሲያዝን እግዚአብሔር ወልድ ሕይወቱን በመስቀል ላይ ስለ እኛ ሰጥቶአል፤ እንዲሁም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሚያስፈልገንን ፍቅር ለመስጠት በውስጣችን ይኖራል (ሮሜ 5፡5)። በፍቅር መኖር ማለት በእግዚአብሔር መኖር ሲሆን፥ በእግዚአብሔር መኖርም በፍቅር መኖር ነው። የክርስትና ፍቅር ስንፈልግ ብቻ «የምንፈጥረው» ሳይሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በልባችን የፈሰሰ ነው፤ ይህም በክርስቶስ ስንኖር የማያቋርጥ የሕይወት ልምምዳችን ይሆናል።

አንድ ሰው ሊኖርባቸው የሚችላቸው አራት ደረጃዎች አሉ። በመሆኑም፥ እጅግ ዝቅተኛውን የሰይጣንን ደረጃ ሊመርጥና ግድያን ሊፈጽም ይችላል። የነፍሰ-ገዳዮችም «ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው» (ራእይ 21፡8)።

ወይም አንድ ሰው ቀጣዩን የጥላቻ ደረጃ ሊመርጥ ይችላል። ይሁንና፥ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ጥላቻም እንደ ነፍስ ግድያ ነው። በጥላቻ የሚኖር ሰው ሌላውን ሳይሆን ቀስ በቀስ ራሱን ገዝግዞ ይገድላል! የሥነ-ልቡና ጠበብት ከፋትና ጥላቻ ጠቅላላዎቹን አካላዊና ስሜታዊ ቀውሶች እንደሚያስከትሉ በመግለጽ ያስጠነቅቁናል።

እንዲያውም አንድ የሙያው ጠቢብ የመጽሐፉን ርእስ *«አፍቅር ወይም ሞት!»* ሲል ሰይሞአል።

እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ጭራሽ ክርስቲያን የማይፈጽማቸው ድርጊቶች በመሆናቸው፥ ሦስተኛው የግድ የለሽነት ደረጃ ከእነርሱ ይሻላል። በልቡ የማያቋርጥ ጥላቻ ያለበት ወይም የመግደል ሱስ ያለበት ሰው ከቶውንም ከእግዚአብሔር እንዳልተወለደ ያረጋግጣል። ይሁንና ክርስቲያን ሆኖ ለሌሎች ችግር ጆሮ ዳባ ልበስ ማለት ይቻላል።

ሰውን የሚገድል ሰው እንደ ቃየን ሁሉ *የሰይጣን ንብረት ነው።* ሌላውን የሚጠላው ደግሞ በሰይጣን ቁጥጥር ሥር የሚማቅቅ *የዓለም ንብረት ነው* (1ኛ ዮሐ. 3፥13)። ይሁንና፥ ግድ የለሽ የሆነው ክርስቲያን የሰይጣንን ዓላማዎች ለሚያገለግለው *ሥጋ* ይኖራል።

ልንኖርበት የሚገባን ብቸኛው አስደሳችና ቅዱስ መንገድ እጅግ ከፍተኛው የክርስትና ፍቅር ደረጃ ነው። ይህ የደስታና የነጻነት ጸሎት መልስ የሚያገኝበት ሕይወት ነው። ይህ ከሕይወት ችግሮች ባሻገር ድፍረትንና ብርታትን የሚሰጥ ሕይወት ነው።

የኒውዮርኩ ዶክተር ሬኔ ስፒዝ ፍቅርና ቸልተኝነት በልጆች ላይ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ ለማወቅ ጥናት አድርገው ነበር። የጥናት ውጤታቸው እንደሚያስረዳው፥ ችላ ተብለው የተተዉና ያልተወደዱ ልጆች ዕድገታቸው ዘገምተኛ ሲሆን አንዳንዶቹም ሞተዋል። ይህም በአካላዊ ገጽታውም ቢሆን ፍቅር ዋንኛው የዕድገትና የሕይወት ዋስትና እንደሆነ ያስረዳል።

በመንፈሳዊ በኩል ደግሞ ከዚህ የጠለቀ ነው።

እንዲያውም፥ ጉዳዩ የማፍቀር ወይም የመሞት ምርጫ ነው!

# – 8 –

# የጠለቀ ፍቅር

## 1ኛ ዮሐንስ 4፡7–16

የፍቅርን ጉዳይ ለሦስተኛ ጊዜ ማንሣታችን ነው።

እንዲህ ሲባል ግን ዮሐንስ አሳቡ ስለተሟጠጠበት አስቀድሞ የጻፈውን እየደጋገመ ነው ማለት አይደለም። ይልቁንም፥ ዮሐንስን በእስትንፋሰ–መለኮት ያንቀሳቀሰው መንፈስ ቅዱስ ርእሰ–ጉዳዩን ወደ ጠለቀ ደረጃ በመውሰድ ዳግም እየገለጸው ነው ማለት ነው።

*መጀመሪያ፥* ለወንድሞች የሚኖር ፍቅር *ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖር ኅብረት* ማረጋገጫ ሆኖ ቀርቧል (2፡7–11)፤ ከዚያም *የልጅነት* ማረጋገጫ ሆኖ ቀርቧል (3፡10–14)። በቀደመው ምንባብ ለወንድሞች የሚኖር ፍቅር የጨለማ ወይም የብርሃን ጉዳይ ነበር፤ ቀጥሎ ደግሞ የሕይወትና የሞት ጉዳይ ሆኖ ተገልጾአል።

በ4፡7–16 ግን ወደ ጉዳዩ ጥልቅ ክፍል እንደርሳለን። በዚህ ስፍራ ፍቅር እውነተኛ የሆነው ሕይወት አስፈላጊ አካል የሆነበትን *ምክንያት* እንረዳለን። «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» ስለሚል ፍቅር የኅብረታችንና የልጅነታችን ትክክለኛ መመዘኛ ነው። ፍቅር የእግዚአብሔር ዓይነተኛ ህላዌና ባሕርይ አካል ነው። በመሆኑም፥ በክርስቶስ በማመን ከእግዚአብሔር ጋር ወደ አለው አንድነት ከመጣን፥ ባሕርዩን እንናገራለን። ባሕርዩ ደግሞ ፍቅር ስለሆነ፥ ፍቅር የመንፈሳዊ ሕይወታችን እውነተኛነት መፈተኛ ሆኖ ያገለግላል።

አንድ መርከበኛ የሚሄድበትን አቅጣጫ ለመወሰን የሚታገዘው በአቅጣጫ ጠቋሚ (ኮምፓስ) ነው። *ለምን* ኮምፓስን መጠቀም አስፈለገው? ምክንያቱም ኮምፓስ አቅጣጫ ስለሚያሳየው ነው። ኮምፓስ ወደ ሰሜን የሚያመለክተው *ለምንድን ነው?* ይህ የሆነው ኮምፓስ የምድሪቱ ላይኛው ጫፍ አካል ለሆነው የስበት አካባቢ (ማግኔቲክ ፊልድ) ምላሽ እንዲሰጥ ሆኖ ስለ ተሠራ ነው። በመሆኑም፥ ኮምፓስ ለምድር ባሕርይ ምላሽ ይሰጣል ማለት ነው።

የክርስትና ፍቅርም እንዲሁ ነው። የእግዚአብሔር ባሕርይ ፍቅር ነው። ስለሆነም፥ እግዚአብሔርን የሚያውቅና ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰው ለእግዚአብሔር ባሕርይ ምላሽ ይሰጣል። ኮምፓስ በባሕርዩ ወደ ሰሜን እንደሚያመለክት ሁሉ፥ አማኝም በባሕርዩ ፍቅርን ይፈጽማል፤ ምክንያቱም ፍቅር የእግዚአብሔር ባሕርይ ነውና። ይህ ፍቅር በግድ የሚሰጥ ሳይሆን፥ ተፈጥሮአዊ ምላሽ ነው። አንድ አማኝ ለሌሎች

ወንድሞች የሚኖረው ፍቅር የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና ኅብረትም እንዳለው ያረጋግጣል።

ዮሐንስ በዚህ ክፍል እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ሦስት ጊዜያት ደጋግሞ ያበረታታናል (ቁ. 7፡11፥12)። እነዚህንም ምክሮች የሚያጠናክርልን ስለ እግዚአብሔር ሦስት መሠረታዊ እውነቶች በመግለጽ ነው።

## 1. እግዚአብሔር ምን እንደሆነ፤ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» (1ኛ ዮሐ. 4፡7–8)

በዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ከሚናገሩ አገላለጾች ይህ ሦስተኛው ነው፤ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው» (1ኛ ዮሐ. 4፡24)፤ «እግዚአብሔር ብርሃን ነው» (1ኛ ዮሐ. 1፡5)፤ እና «እግዚአብሔር ፍቅር ነው»። ከእነዚህ መካከል የትኛውም አገላለጽ የእግዚአብሔር *ሙሉ* መገለጥ ስላልሆነ መከፋፈሉ ትክክል አይደለም።

*እግዚአብሔር በራሱ መንፈስ ነው፤* እርሱ ሥጋና ደም አይደለም። በእርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ የከበረ አካል አለው፤ እኛም ደግሞ አንድ ቀን የእርሱን የሚመስል አካል እንለብሳለን፤ በመሆኑም፥እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ፥ እርሱ እንደ ፍጥረታቱ በጊዜና በቦታ የተገደበ አይደለም።

*እግዚአብሔር ብርሃን ነው።* ይህ ቅዱስ ባሕርዩን ያመለክታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብርሃን የቅድስና ምልክት ሲሆን ጨለማ የኃጢአት ምልክት ነው (1፡5–10፤ ዮሐ. 3፡18–21)። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ኃጢአት ሊያደርግ አይችልም። እኛም በእርሱ ቤተሰብ ውስጥ ስለተወለድን፥ ቅዱስ ባሕርዩን ተቀብለናል (2ኛ ጴጥ. 1፡4፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡14–16)።

*እግዚአብሔር ፍቅር ነው።* ይህ ማለት ግን «ፍቅር እግዚአብሔር ነው» ማለት *አይደለም።* ስለዚህም፥ ሁለት ሰዎች እርስ በርሳቸው ይዋደዳሉ ማለት ፍቅራቸው የግድ ቅዱስ ነው ማለት አይደለም። ስለሆነም፥ «ፍቅር እግዚአብሔርን አይገልጸውም፤ እግዚአብሔር ግን ፍቅርን ይገልጸዋል» መባሉ ትክክል ነው። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ብርሃንም ነው፤ ይህም በመሆኑ ፍቅሩ ቅዱስ ፍቅር ከመሆኑም በላይ፥ ቅድስናውም በፍቅር ተገልጾአል። እግዚአብሔር *የሚያደርገው* ነገር ሁሉ የእግዚአብሔርን *ማንነት* ይገልጻል። ፍርዶቹም እንኳ የሚከናወኑት በፍቅርና በምሕረት ነው (ሰቆቃ. 3፡22–23)።

በዘመናዊው ማኅበረሰብ ዘንድ በአብዛኛው «ፍቅር» ተብሎ የሚጠራው ነገር ቅዱስና መንፈሳዊ ከሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር ጋር

በምንም አይመሳሰልም ወይም አይገናኝም። ይህም ሆኖ፥ በአሜሪካ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው!» የሚለው ዓርማ ብዙ ፌስቲቫሎች በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ተሰቅሎ ይታያል፤ ይህም በተለይ ወጣቶች የልባቸውን በሚሠሩባቸው ስፍራዎች ሳይቀር የተቀመጠ ነው፤ «ፍቅር» ተብሎ በመጠራቱ አጉራዘለልነት ክብር ያገኘ ይመስል።

የክርስትና ፍቅር የተለየ ዓይነት ፍቅር ነው። 1ኛ ዮሐንስ 4:10 «እውነተኛ ፍቅር የታየው በዚህ መንገድ ነው» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። የውሸትም ፍቅር አለ፤ እግዚአብሔር የዚህ ዓይነቱን ፍቅር ይጠላዋል። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነና እግዚአብሔር ብርሃን ስለሆነ፥ ከእግዚአብሔር ዓይነተኛ ባሕርይ የበቀለ ፍቅር መንፈሳዊና ቅዱስ መሆን አለበት። ይህም እውነተኛ ፍቅር በተሰጠን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከልባችን የፈሰሰ ነው (ሮሜ 5:5)።

ስለሆነም፥ ፍቅር የእውነተኛ ክርስቲያናዊ እምነት ተገቢ መፈተኛ ነው። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነና እኛም ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት እንዳለን ስለተናገርን፥ በአኗኗራችን የግድ ፍቅሩን ማሳየት አለብን። የእግዚአብሔር ልጅ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ፥ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ ይጋራል። እግዚአብሔርም ፍቅር ስለሆነ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ሊዋደዱ ይገባል። ይህም የማፍረሻ ምላሽ የማይገኝለት እውነተኛ ብያኔ ነው።

ከእግዚአብሔር ተወልደናል፤ ይህም ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም እናውቀዋለን። በመጽሐፍ ቅዱስ፥ ማወቅ የሚለው ቃል ከምሁራዊ ግንዛቤ ወይም መረዳት የጠለቀ ፍች አለው። ለምሳሌ፥ የባልና ሚስት የቅርብ ጥምረት የተገለጸው «ማወቅ» በሚል አንቀጽ ነው (ዘፍ. 4:1)። በመሆኑም፥ እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር የጠለቀ ግንኙነት ማድረግ ማለት ነው፤ ሕይወቱን መጋራትና በፍቅሩ መርካት። ይህም ሐቆችን የመገንዘብ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፥ እውነትን መቀበልም ነው (1ኛ ዮሐ. 2:3-5)።

«ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም» የሚለውን አሳብ በዚህ ግንዛቤ ብርሃን ልንረዳው ይገባል (4:8)። ብዙ የማያምኑ ሰዎች ቤተሰቦቻቸውን እንደሚወዱና አንዳንዴም ለእነርሱ ሲሉ ራሳቸውን አሳልፈው እንደሚሰጡ ግልጽ ነው። ከእነዚህም ሰዎች ብዙዎቹ ስለ እግዚአብሔር የተወሰነ ምሁራዊ ወይም አእምሮአዊ እውቀት እንዳላቸው እሙን ነው። እንግዲህ የጎደላቸው ምን ይሆን? የሚጎድላቸው *ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት* ማድረጉ ነው። ቁጥር ስምንትን አብራርተን ስንገልጸው እንዲህ ይነበባል፦ «የዚህ ዓይነት መለኮታዊ ፍቅር የሌለው ሰው እግዚአብሔርን በግሉና

በሕይወት ልምምዱ ወደ ማወቁ ደረጃ አልደረሰም። የሚያውቀው በአእምሮው ብቻ እንጂ ከልቡ ላይ ጠብ ያለ ነገር የለውም።»

*የእግዚአብሔር ምንነት የእኛንም ምንነት ይወስነዋል።* «እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና» (ቁ. 17)። የክርስቲያኖች እርስ በርስ *መዋደድ* ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዳላቸውና የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው፤ *እግዚአብሔርን እንደሚያውቁም* እንዲሁ ያረጋግጣል። ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖራቸው ኀጠመኝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚደረግ አይደለም። ይልቁንም ዕለት በዕለት እርሱን ይበልጥ እያወቁ የመሄድ ሁኔታ ነው። ስለሆነም እውነተኛ ሥነ-መለኮት ከሕይወት ጋር የማይገናኝ ደረቅ ዶክትሪን ሳይሆን፥ ክርስቶስን እንመስል ዘንድ የሚረዳን አስደሳች የዕለት ተዕለት ልምምድ ነው።

ከፍተኛ መጠን ያለው ጨረር አመንጪ (ሬድዮአክቲቭ) ንጥረ-ነገር ከሆስፒታል ተሰርቆ ነበርና፥ የሆስፒታሉ አስተዳዳሪ ለፖሊሱ እንዲህ አሉት፦ «እባክህ ለሌባው ሞትን ተሸክሞ እንዳለ አስጠንቅቀው፤ ማንም ሰው ጨረር አመንጪዎችን ደብቆ ሊያቆይ አይችልም። ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ነገር ነው።»

እግዚአብሔርን እንደሚያውቅና ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዳለው የሚመሰክር ሰው በግል ደረጃ ከዚሁ ግንኙነት አኳያ ዕድገት ሊያሣይ ይገባል። በመሆኑም ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ምንነት ሊረዳና ከዚያውም ምንነት አኳያ ራሱን ሊቀርጽ ይገባል፤ እግዚአብሔር በባሕርዩ ፍቅር ነው። ይህንን አሳብ ለማፋለስ መሞከር ማለት እግዚአብሔርን እንደማያውቁ መግለጽ ነው!

## 2. እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ፤ «ልጁን ላከ» (1ኛ ዮሐ. 4፡9-11)

እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ በቃላት ብቻ ሳይሆን በተግባርም ፍቅሩን መግለጽ ነበረበት። እውነተኛ ፍቅር ውስንና እንቅስቃሴ አልባ አይደለም። ስለሆነም፥ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ፍቅሩን በብዙ መንገዶች ገልጾአል። ፍጥረትን ሁሉ ያቀናጀው የሰዎችን ፍላጎቶች እንዲያሟሉ አድርጎ ነው። የሰው ኃጢአት ፍጥረትን ለባርነት እስካስገዛበት ጊዜ ድረስ፥ ሰው እግዚአብሔርን የሚወድበትና የሚያገለግልበት ፍጹም ቤት በምድር ላይ ነበረው።

እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ባደረጋቸው ግንኙነቶች ፍቅሩን ገልጾአል። «እግዚአብሔር የወደዳችሁና የመረጣችሁ ከአሕዛብ ሁሉ በቁጥር ስለበዛችሁ አይደለም፤ እናንተ ከአሕዛብ ሁሉ በቁጥር

ጥቂቶች ነበራችሁና፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ስለወደዳችሁ... በጽኑ እጅ አወጣችሁ» (ዘዳ. 7፡7–8)።

ከሁሉም የሚልቀው የእግዚአብሔር የፍቅሩ መግለጫ የልጁ ሞት ነው። «ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል (ሮሜ 5፡8)።

በ1ኛ ዮሐንስ 4፡9 «ተገለጠ» የሚለው ቃል «በግልጽ መታየትንና በይፋ መታወቅን» ያሳያል። ይህ ከ «መደበቅ» እና «ምሥጢር ከማድረግ» የሚቃረን ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከሥርዓታዊ ተግባራትና እንቅስቃሴዎች በስተኋላ በነበሩ ጥላዎች ተደብቆ ነበር (ዕብ. 10፡1)፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ግን «ሕይወት ተገለጠ» (1ኛ ዮሐ. 1፡2)። ኢየሱስም፥ «እኔን ያየ አብን አየ» ብሏል (ዮሐ. 14፡9)።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠው ለምን ነበር? «እርሱም ኃጢአትን ሊያስወግድ እንደተገለጠ ታውቃላችሁ» (1ኛ ዮሐ. 3፡5)። «ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» (ቁ. 8)። ለመሆኑ ኢየሱስ ኃጢአታችንን ያስወገደበትና የዲያብሎስን ሥራ ያፈረሰበት ስፍራ የትኛው ነበር? *መስቀሉ ነበር!* እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን ልጁን እንደ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ፍቅሩን የገለጸው በመስቀሉ ላይ ነበር።

በመልእክቶች ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር አንድ (አንድያ) ልጅ ተብሎ የተጠራው በዚህ ስፍራ ብቻ ነው። ይህ ስም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥም ተጠቅሶአል (1፡14)። ይህም «ከዓይነቱ ብቸኛና ልዩ» የሚል ፍች ይሰጣል። እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም *መላኩ* ለኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት አንዱ መረጃ ነው። ሕፃናት ከሌላው ስፍራ ወደ ዓለም አይላኩም፤ በዓለም ውስጥ *ይወለዳሉ* እንጂ! ኢየሱስ እንደ ፍጹም ሰው በዚህች ዓለም ቢወለድም፥ እንደ ዘላለማዊ ልጅ ግን ወደ ዓለም ተልኮአል።

ይህም ሆኖ፥ ክርስቶስ ወደ ዓለም እንዲላክና በመስቀል ላይ እንዲሞት ያደረገው ሰው ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር አይደለም። ይልቁንም እግዚአብሔር ለሰው ካለው ፍቅር የተነሣ ነው። ይህ ዓለም ለእግዚአብሔር ፍቅር የለውም።

ለክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት ሁለት ዓላማዎች ተሰጥተዋል፤ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ (1ኛ ዮሐ. 4፡9) እና ስለ ኃጢአታችን ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ (ቁ. 10)። ሞቱ የታቀደ ጉዳይ እንጂ በአጋጣሚ የተከሰተ ነገር አይደለም። የሞተውም እንደ ብርቱ ድል ነሺ እንጂ እንደ ደካማ ሰማዕት አይደለም።

ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው «በእርሱ በኩል» (ቁ. 9)፥ «ለእርሱ» (2ኛ ቆሮ. 5፡15) እና «ከእርሱ ጋር» (1ኛ ተሰ. 5፡9–10) በሕይወት እንኖር ዘንድ ነው። ኃጢአተኛ «በበደሉና በኃጢአቱ» ምክንያት የሞተ በመሆኑ፥ በብርቱ የሚያስፈልገው ሕይወት ነው (ኤፌ. 2፡1)። እኛ በሕይወት እንኖር ዘንድ ክርስቶስ ለመሞት መገደዱ አደናጋሪ ነገር ነው! ይሁንና፥ የሞቱን ምሥጢር ልንረዳ ባንችልም አንድ ነገር እናውቃለን። እርሱ የሞተው ስለ እኛ ነው (ገላ. 2፡20)።

የክርስቶስ ሞት «ማስተሰሪያ» ተብሎ ተገልጾአል። ዮሐንስ ይህንኑ ቃል ቀደም ብሎ ስለ ተጠቀመ፥ በዝርዝር ማጥናቱ አስፈላጊ አይሆንም (1ኛ ዮሐ. 2፡2)። ማስተሰረይ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ወይም ቁጣውን ለማርገብ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብን የሚያመለክት እንዳልሆነ መረዳት አለብን። ይልቁንም፥ ማስተሰረይ ሰዎች ይቅርታን ለማግኘት ይችሉ ዘንድ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ነው። «እግዚአብሔር ብርሃን» ስለሆነ ቅዱስ ሕጉን መጠበቅ አለበት። በሌላ በኩል «እግዚአብሔር ፍቅር» ስለሆነ፥ ኃጢአተኞችን ይቅር ብሎ ለማዳን ይፈልጋል። እንግዲህ፥ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ይቅር ሊልና በቅዱስ ባሕርዩ ሊኖር የሚችለው እንዴት ነው? ለዚህ ጥያቄ መልሱ መስቀሉ ነው። በመስቀሉ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአትን ቅጣት ተሸክሞ የቅዱስ ሕጉን ጻድቅ ጥያቄዎች አሟላ። በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር በመስቀሉ ፍቅሩን በመግለጽ ሰዎች በእምነት እንዲድኑ ያደርጋል።

በዚህ ላይ ትኩረት የተደረገው በክርስቶስ ልደት ላይ ሳይሆን *በሞቱ* ላይ እንደሆነ ልብ ማለቱ አስፈላጊ ነው። የኢየሱስ «*ሥጋ መሆን*» (ዮሐ. 1፡14) ያለጥርጥር የእግዚአብሔር ጸጋና ፍቅር መረጃ ነው፤ ዳሩ ግን «ኃጢአት የመሆኑ» (2ኛ ቆሮ. 5፡21) እውነታ *በአጽንኦት* ቀርቦልናል። እናም የክርስቶስ ምሳሌነት፥ የክርስቶስ ትምህርቶች፥ ጠቅላላው የክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት እውነተኛ ትርጉሙንና ፍጻሜውን የሚያገኘው በመስቀሉ ነው።

አማኞች ለሁለተኛ ጊዜ «እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ» ተመክረዋል። (1ኛ ዮሐ. 4፡11)። ይህ ምክር ሊፈጸም የሚገባው ትእዛዝ ሲሆን (ቁ. 7)፥ *መሠረቱም* የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። እንደምናውቀው እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ እኛም እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባል። ይሁንና፥ እርስ በርስ ስለመዋደድ የተገለጸው ምክር የቀረበው እንደ ዕድልም እንደ ኃላፊነትም ነው፤ «እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል» (ቁ. 11)። በእርግጥ እኛ የዳንነው ክርስቶስን *በመውደድ* ሳይሆን በክርስቶስ *በማመን* ነው (ዮሐ. 3፡16)። ዳሩ ግን በመስቀል

ላይ ያደረገልንን ሥራ ከተረዳን በኋላ የምንለማመደው ምላሻችን እርሱን መውደድና እርስ በርሳችንም መዋደድ ሊሆን ይገባል።

ክርስቲያኖች በፍቅር ግንዛቤአቸው ያድጉ ዘንድ ያስፈልጋቸዋል። ከኃላፊነት ስሜት ተነሣሥቶ እርስ በርስ መዋደድ መልካም ቢሆንም፥ (ከግዴታ ይልቅ) በአስመስጋኝነት መንፈስ መዋደዱ የተሻለ ነው።

ኢየሱስ የቅዱስ ቁርባንን ሥርዓት ከመሠረተባቸው ምክንያቶች አንዱ ይኸ ሳይሆን አይቀርም። እንጀራውን ስንቆርስና ጽዋውንም አብረን ስንካፈል ሞቱን እናስታውሳለን። ሞታቸው እንዲታወስ የሚፈልጉ ሰዎች የሚኖሩ አይመስልም። እንዲያውም፥ እኛ የምንፈልገው የወዳጆቻችንን ሕይወት ለማስታወስና የሞታቸውን አሳዛኝነት ለመዘንጋት ነው። ክርስቶስ ግን እንዲህ አይደለም። እርሱ ሞቱን እንድናስታውስ *ያዝዘናል*፤ «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉ!»

ስለሆነም፥ የጌታችንን ሞት ልናስታውስ የሚገባን በመንፈሳዊ መንገድ እንጂ በስሜታዊ አስተሳሰብ ብቻ አይደለም። አንድ ሰው ስሜትን «ኃላፊነት የማይሰማው ባዶ አሳብ» ሲል ተርጉሞታል። በመሆኑም፥ በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ አገልግሎት ላይ ስሜታዊ መጣበብ ሊታይብንና ከዚያ ስንወጣ ያንኑ የሽንፈት ሕይወታችንን ልንቀጥል እንችላለን። እውነተኛ መንፈሳዊ ልምምድ ሁለንተናን የሚያካትት ነው። *አእምሮ* መንፈሳዊ እውነትን ሊረዳ፥ *ልብ* ሊያፈቅረውና ሊያደንቀው፥ *ፈቃድ* ደግሞ ከዚያው አኳያ ተግባሩን ሊወጣ ይገባል። ወደ መስቀሉ ፍች ይበልጥ እየጠለቅን በሄድን መጠን፥ ለክርስቶስ የሚኖረን ፍቅርና እርስ በርሳችን የሚኖረን ተግባራዊ መተሳሰብ የበለጠ ያድጋል።

እስካሁን እግዚአብሔር ማን እንደሆነና ምንስ እንዳደረገ ተመልክተናል፤ ይሁንና፥ ሦስተኛው መሠረታዊ እውነት ወደ ክርስትና ፍቅር ፍችና ጥቅም አጥልቆ ያስገባናል።

## 3. እግዚአብሔር አሁን የሚያደርገው፤ «እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል» (1ኛ ዮሐ. 4፡12-16)

በዚህ ስፍራ ዮሐንስ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» ስለሚለው መሠረታዊ እውነት ሲናገር የቆየውን መከለሱ ጠቃሚ ነው!

ይህ እውነት በቃሉ ውስጥ የተገለጠልን ሲሆን፥ ክርስቶስ ስለ እኛ በሞተበት መስቀል ላይም ተገልጦአል። «እግዚአብሔር ፍቅር ነው!» የሚለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ ዶክትሪን ብቻ ሳይሆን፥

በኅልኅታ በግልጽ የታየ ዘላለማዊ እውነታም ነው። እግዚአብሔር አንድ ነገር ለእኛ መናገር ብቻ ሳይሆን፥ አንድ ነገር ለእኛ አድርጎአል።

ይህ ሁሉ ግን ለሦስተኛው ታላቅ እውነታ ማለትም እግዚአብሔር *በውስጣችን ለሚሠራው* ነገር ለማዘጋጀት ነው! እኛ መጽሐፍ የምናነብ ተማሪዎች ወይም በጥልቀት የሚንቀሳቀሰውን አጋጣሚ የምንመለከት ታዛቢዎች ሳንሆን፥ የእግዚአብሔርን ታላቅ ፍቅር በሚያሳየው ተውኔት ውስጥ *ተሳታፊዎች ነን!*

የአንድ ኮሌጅ የተውኔት ክፍል ገንዘብ ለመቆጠብ ሲል የአንድን ተውኔት ጥቂት ትዕይንቶች ብቻ በመግዛት በተለያዩ ትናንሽ ክፍሎች አዋቀረ። የተውኔቱ ዳይሬክተርም ለእያንዳንዱ ተዋናይ የሚደርሰውን ክፍል ሰጡና ልምምዱን አስመሩ።

ይሁንና፥ ምንም ነገር በትክክል ሊሠራ አልቻለም። ስለሆነም፥ ለአንድ ሰዓት ያህል ጠቃሚ ምልክቶች ጠፍተውና ቅደም ተከተሉ ተዛብቶ ከቆየ በኋላ፥ ተዋንያኑ ልምምዳቸውን አቆሙ።

በዚህ ጊዜ ዳይሬክተሩ ተዋንያኑ ሁሉ ከመድረኩ ላይ እንዲቀመጡ አድርገው፥ «አሁን ጠቅላላውን ተውኔት ላነብላችሁ ስለሆነ አንዳችሁም ትንፍሽ እንዳትሉ!» ሲሉ ተናገሩ። ጠቅላላውን የተውኔት ጽሑፍ አንብበው ሲጨርሱ፥ ከተዋንያኑ አንዱ፥

«ይኸው ነበር ለካ!» ሲል ተናገረ።

በዚህ ዓይነት፥ ጠቅላላውን ታሪክ ከተረዱ በኋላ ትዕይንቶቻቸውን አንድ ላይ አድርገው የተሳካ ልምምድ ሊያካሂዱ ቻሉ።

ከቁጥር 12-16 ያለውን ስታነብ፥ «ይኸው ነው ለካ!» የሚል ስሜት ያድርብሃል፤ ይህም የሚሆነው በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የደኅንነትን ዕቅድ ሲወጥን በአእምሮው የያዘውን ቁም ነገር ስለምንረዳ ነው።

በቀዳሚነት የእግዚአብሔር ፍላጎት *በእኛ ውስጥ መኖር* ነው። እንደሚወደን *በመናገር* ወይም *በማሳየት* ብቻ አልረካም።

በመጽሐፍ ቅድስ ውስጥ የተመዘገቡትን የእግዚአብሔርን የማደሪያ ስፍራዎች መመልከቱ አስገራሚ ነው! በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግላዊና ቀጥተኛ ግንኙነት ያደርግ ነበር (ዘፍ. 3፥8)፤ ኃጢአት ግን ያንን ግንኙነት አበላሸው። ስለሆነም፥ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ከእርሱ ጋር ወዳለው ኅብረት ይመጡ ዘንድ ኃጢአቶቻቸውን ለመሸፈን የእንስሳትን ደም ለማፍሰስ ተገደደ።

በኦሪት ዘፍጥረት ከሚገኙ ቁልፍ ቃላት አንዱ *«መመላለስ»* ወይም «አካሄድ» የሚለው ነው። እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ሲመላለስ ሰዎች ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ይመላለሱ ነበር። ሄኖክ (ዘፍ. 5:22)፥ ኖኅ (6:9)፥ አብርሃም (17:1፤ 24:40) ከእግዚአብሔር ጋር ተመላልሰዋል።

ይሁንና፥ በኦሪት ዘጸአት ውስጥ የሚገኙ ክስተቶች በተመዘገቡበት ወቅት ለውጥ ተደረገ፤ ይኸውም እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር *መመላለስ* ብቻ ሳይሆን፥ ከእነርሱ ጋር *መኖሩ* ወይም *ማደሩ* ነው። እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠው ትእዛዝ፥ «በመካከላቸው አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ» የሚል ነበር (ዘጸ. 25:8)። ከእነዚህም መቅደሶች የመጀመሪያው የመገናኛው ድንኳን ነው። ሙሴ ይህንን ድንኳን ባስመረቀ ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር ወርዶ በድንኳኑ ውስጥ ገባ (40:33–35)።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በሠፈሩ ውስጥ ቢያድርም በእያንዳንዱ እስራኤላዊ አካል ውስጥ *አላደረም* ነበር።

የሚያሳዝነው ግን በሕዝቡ ኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር ክብር መነሣቱ ነው (1ኛ ሳሙ. 4:21)። ይህም ሆኖ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ስፍራው ለመመለስ ሳሙኤልንና ዳዊትን የተጠቀመ ሲሆን፥ ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ማለፍያ ሕንፃ ሠርቶለታል። ይህም መቅደስ በተመረቀ ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር እንደገና በምድሪቱ ሊኖር መጣ (1ኛ ነገ. 8:11–12)።

ይሁንና፥ ታሪክ የቀድሞ ክስተቱን በመድገሙ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ሕግጋት ተላልፈው ወደ ምርኮ ተወሰዱ። ማራኪውም መቅደስ ወደመ። ከምርኮ ነቢያት አንዱ የነበረው ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ክብር ከመቅደሱ ተነሥቶ ሲሄድ አየ (ሕዝ. 8:4፤ 9:3፤ 10:4፤ 11:22–23)።

ክብሩ ዳግም ተመለሰ ይሆን? አዎን፥ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ተመልሶአል። «ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ» (ዮሐ. 1:14)። የእግዚአብሔር ክብር በኢየሱስ ክርስቶስ አካል በምድር ላይ አደረ፤ አካሉ የእግዚአብሔር መቅደስ ነበረና (ዮሐ. 2:18–22)። ዳሩ ግን ኃጢአተኞች አካሉን በመስቀል ላይ ቸነከሩት። «የክብርን ጌታ» ሰቀሉት (1ኛ ቆሮ. 2:8)። ይህ ሁሉ የአስደናቂው የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል ሲሆን፥ ክርስቶስም ከሞት ተነሥቶ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ *በሰዎች ውስጥ ይኖር ዘንድ መንፈሱን* ላከው።

አሁን የእግዚአብሔር ክብር በእግዚአብሔር ልጆች ውስጥ ይኖራል። «ወይስ *ሥጋችሁ* ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም» (1ኛ ቆሮ. 6፡19)። እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ባልፈለጉ ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር ከመገናኛው ድንኳንና ከመቅደሱ የተለየ ሲሆን፥ ኢየሱስ ግን መንፈስ ቅዱስ *ለዘላለም* ከእኛ ጋር እንደሚኖር ቃል ገብቷል (ዮሐ. 14፡16)።

ከዚህ ዳራ በመነሣት የ1ኛ ዮሐንስ 4፡12–16ን መልእክት በተሻለ ሁኔታ ልንረዳ እንችላለን። እግዚአብሔር የማይታይ አምላክ በመሆኑ (1ኛ ጢሞ. 1፡17)፥ *ማንም* ሰው በተፈጥሮአዊ ባሕርዩ ሊያየው አይችልም። ኢየሱስ «የማይታየው አምላክ ምሳሌ» ነው (ቆላ. 1፡15)። ኢየሱስ የሰውን *ሥጋ* በመልበስ እግዚአብሔርን ሊገልጥልን ችሏል። አሁን ግን ኢየሱስ በምድር ላይ አይደለም ያለው። እንግዲህ እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች የሚገልጸው እንዴት ነው?

ራሱን የሚገልጸው በልጆቹ ሕይወት በኩል ነው። ሰዎች እግዚአብሔርን ለማየት ባይችሉም *እኛን ለማየት ይችላሉ።* ስለሆነም፥ እኛ በክርስቶስ ብንኖር እርስ በርሳችን እንዋደዳለን፤ ይህም የእርስ በርሳችን ፍቅር ለጎስቋላው ዓለም የእግዚአብሔርን ፍቅር ይገልጻል። በመሆኑም፥ የእግዚአብሔር ፍቅር *መጀመሪያ* በእኛ መካከል ይተገበርና ቀጥሎም *በእኛ በኩል* ይገለጻል።

ይህች *«መኖር»* የተባለችው ትንሽ ቃል በ1ኛ ዮሐንስ 4፡12–16 ውስጥ ስምንት ጊዜያት ተጠቅሳለች። ይህችም ቃል ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለንን ግላዊ ኅብረት ታመለክታለች። በክርስቶስ መኖር ማለት ኃጢአት በመካከል ሰርጎ እንዳይገባ ከእርሱ ጋር በመንፈሳዊ አንድነት መቀጠል ማለት ነው። «ከእግዚአብሔር ስለተወለድን» ከክርስቶስ ጋር *አንድነት* አለን፤ ይሁንና፥ ከእርሱ ጋር *ኅብረት* የሚኖረን እርሱን ስናምንና ትእዛዛቱን ስንጠብቅ ብቻ ነው። ታማኝ ባልና ሚስት በብዙ ኪሎ ሜትሮች በሚቆጠር ርቀት ግርዶሽ ተለያይተው ሳለ እንኳ «በፍቅር እንደሚኖሩ» ሁሉ አማኝም በእግዚአብሔር ፍቅር ይኖራል። ይህም መኖር እውን ሊሆን የቻለው መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ በመኖሩ ነው (4፡13)።

እስኪ እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ ሲኖር የሚሆነውን አስደናቂ ሁኔታና ዕድል በምናብህ አስተውል። የእግዚአብሔር ህልውና በዚያ ሕንፃ ውስጥ ስለነበር፥ የብሉይ ኪዳኑ እስራኤላዊ የመገናኛውን ድንኳን ወይም ቤተ መቅደሱን በአድናቆት ይመለከተው ነበር።

እግዚአብሔር በክብር ዙፋኑን ወደ ሞላበት ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት የሚደፍር ሰው አልነበረም! እኛ ግን *በውስጣችን* የእግዚአብሔር መንፈስ *ይኖርብናል!* እኛም በዚህ ፍቅር በመኖር እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ሲኖር የሚሆነውን ነገር እንለማመዳለን። «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን፤ በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን» (ዮሐ. 14:23)

«እግዚአብሔር ፍቅር ነው» ተብሎ በቃሉ *የታወጀ* ሲሆን፥ በመስቀሉ *ማረጋገጫ* ተሰጥቶታል። በዚህ ስፍራ ግን አንድ የጠለቀ ነገር አለ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ፍቅር በአማኙ ውስጥ *ፍጹም* እንደተደረገ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም የተደረገው ለመላእክት ሳይሆን በጸጋው ለዳኑ ኃጢአተኞች መሆኑ አስደናቂ ነው። አሁን እኛ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሚያድርባቸው የመገናኛ ድንኳኖችና ቤተ መቅደሶች ነን። ስለሆነም፥ እግዚአብሔር ፍቅሩን በእርሱ በኩል ይገልጣል።

ታዋቂው የብሪታኒያ ሰባኪ ዶ/ር ጂ. ካምፕቤል ሞርጋን በኋላ ወደ ወንጌሉ አገልጋይነት የመጡ አምስት ልጆች ነበሩአቸው። አንድ ቀን ወደ ቤታቸው የመጣ እንግዳ አንድ የግል ጥያቄ ሊጠይቃቸው ደፈረ። ጥያቄውም፥ «ከእናንተ ከስድስታችሁ እጅግ የላቀው ሰባኪ ማን ነው?» የሚል ነበር።

ሁላቸውም በአንድ ላይ «እናታችን!» ሲሉ መለሱ።

በመሠረቱ ሚስዝ ሞርጋን በቤተ ክርስቲያን የስብከት አገልግሎት ሰጥተው አያውቁም፤ ዳሩ ግን ሕይወታቸው ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ዘላቂ ስብከት ነበር። በእግዚአብሔር ፍቅር የሚኖር ክርስቲያን ሕይወት በዓለም ውስጥ ለእግዚአብሔር ጠንካራ ምስክርነት ነው። ሰዎች እግዚአብሔርን ሊያዩት ባይችሉም፥ ፍቅሩ እኛን ለእርዳታና ለቸርነት ተግባራት ሲያነሣሣ ሊመለከቱ ይችላሉ።

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ሦስት የተለያዩ ዓይነት ምስክርነቶች ተመልክተዋል፤ እነዚህም፥ (1) *አማኙ* ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚሰጠው ምስክርነት (1ኛ ዮሐ. 4:15)፤ (2) መንፈስ ቅዱስ በአማኙ *ውስጥ* ሆኖ የሚሰጠው ምስክርነት (ቁ. 13)፤ እና (3) እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነና ልጁ ስለ ዓለሙ እንዲሞት እንደላከው በአማኙ *በኩል* የሚሰጥ ምስክርነት ናቸው (ቁ. 14)።

እነዚህ ምስክርነቶች ሊነጣጠሉ አይችሉም። ዓለም የእግዚአብሔር ፍቅር በልጆቹ ሕይወት ሲሠራ እስካልተመለከተች ድረስ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንደሚወድ ልታምን አትችልም።

አንዲት የደኅንነት ሠራዊት አባል በመንገድ ዳር የምትኖር ድሀ ሴት አገኘችና ለዕርዳታ ወደ ጸሎት ቤታቸው እንድትመጣ ጋበዘቻት፤ ሴቲቱ ግን እምቢ አለች። የደኅንነት ሠራዊት አባሏ፥ «እባክሽ ስለምንወድሽ ልንረዳሽ እንፈልጋለን። እግዚአብሔር ይወድሻል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አንቺ ሞቶአል» እያለች የማረጋገጫ ቃላት ትደረድር ገባች። ሴቲቱ ግን ጨርሶ አልተነቃነቀችም።

ከዚያም መለኮታዊ ግፊት እንደተሰጣት ሁሉ ወጣቷ የደኅንነት ሠራዊት አባል ወደ ሴቲቱ ተጠጋችና አቅፋ ሳመቻት። በዚህም ጊዜ ሴቲቱ የእንባ ዘለላዎችን እያዘራች እንደ ሕፃን ልጅ ተመርታ ወደ ጸሎት ቤቱ ተጓዘች፤ በመጨረሻም በዚሁ ስፍራ ክርስቶስን ለማመን በቃች።

በኋላም ይህች ሴት፥ «እግዚአብሔር እንደሚወደኝ *ነግረሽኝ* ነበር፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር እንደሚወደኝ *ባሳየሽኝ* ጊዜ ነበር ደኅንነትን ለማግኘት የፈለግሁት» ብላለች።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሕይወቱን በመስጠት አረጋግጦታል እንጂ፥ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ሰብኮ ብቻ አላበቃም ነበር። ተከታዮቹም ይህንኑ ምሳሌ እንዲከተሉ ይፈልጋል። በክርስቶስ ብንኖር በፍቅሩ ደግሞ እንኖራለን። በፍቅሩም ብንኖር ፍቅሩን ለሌሎች ማካፈል አለብን። ስለሆነም፥ ይህንን ፍቅር ለሌሎች በምናካፍልበት ጊዜ ሁሉ በክርስቶስ እንደምንኖር ልባችን ያረጋግጥልናል። በሌላ አገላለጽ በክርስቲያኑ ውስጣዊ ሕይወትና ውጫዊ ሕይወት መካከል ልዩነት የለም ማለት ነው።

በእግዚአብሔር ፍቅር መኖር በአማኝ ሕይወት ሁለት ድንቅ መንፈሳዊ ውጤቶችን ያመጣል፤ ይኸውም፥ አማኙ 1) በእውቀት እና 2) በእምነት እንዲያድግ መርዳቱ ነው (ቁ. 16)። እግዚአብሔርን ይበልጥ በወደድን መጠን የእግዚአብሔርን ፍቅር ይበልጥ እንረዳለን። ፍቅሩን ይበልጥ ስንረዳ፥ እርሱን ለማመን ይበልጥ ይመቸናል። ከአንድ ሰው ጋር የቀረበ ግንኙነት ሲኖርህና ከልብህ ስትወደው በዚህ ሰው ለመተማመን አትቸገርም።

የሰላምታ ቃላት የተጻፉባቸው ካርዶች ወደሚሸጡበት መደብር የመጣ አንድ ሰው የትኛውን እንደሚመርጥ ተቸግሮ ነበር። ስለዚህ ሻጭዋ ትረዳው እንደሆነ ከጠየቀ በኋላ የሚከተለውን ተናገረ፡—

«ይኼ አርባኛው ዓመት የጋብቻ በዓላችን በመሆኑ እኔ ለመናገር የምፈልገውን የሚገልጽ ካርድ ለማግኘት አልቻልሁም። አየሽ፥ ከአርባ ዓመታት በፊት ለእኔ ካርድ መርጦ ማንሣቱ ቀላል ነገር ነበረ፤

ምክንያቱም ያኔ ፍቅር ምን እንደሆነ የማውቅ ይመስለኝ ነበር። አሁን ግን እኔና ባለቤቴ በጣም ስለምንዋደድ ይህንኑ ፍቅር የሚገልጽልኝ ካርድ አጣሁ።»

እያደገ የሚሄድ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውም ልምምድ እንዲሁ ነው። በክርስቶስ ሲኖርና ከእርሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ ጊዜ ሲወስድ፥ እግዚአብሔርን በይበልጥ ይወደዋል። በተጨማሪም፥ ለሌሎች ክርስቲያኖች፥ ላልዳኑትና ለጠላቶቹም ሳይቀር የሚኖረው ፍቅር ያድጋል። የአብን ፍቅር ለሌሎች ሲያካፍል፥ እርሱም ለራሱ የአብን ፍቅር በበለጠ ይለማመዳል። በዚህም የአብን ፍቅር በተሻለ ሁኔታ እየተረዳ ይመጣል።

በዚህ ጊዜ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» የሚለው ቃል መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ብቻ ሆኖ አይቀርም። ይልቁንም አማኙ ከእግዚአብሔርና አብሮት ከሚኖር ሰው ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት መሠረት ይሆናል። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ እኛም ልናፈቅረው እንችላለን። ፍቅሩም *ያለፈ ታሪክ* ሳይሆን የአሁኑ *እውነታ* ነው። ስለሆነም፥ «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው ቃል እንደ *ትእዛዝ* ይጀምርና (ቁ. 7) በኋላ *መልካም ዕድል* ወደ *መሆን* ያድጋል (ቁ. 11)። ይሁንና፥ አሳቡ ከትእዛዝ ወይም ከዕድል የላቀ ነው። በተጨማሪም፥ በክርስቶስ የመኖራችን አስደሳች *ውጤትና መረጃም* ነው (ቁ. 12)። በመሆኑም፥ እርስ በርስ *መዋደድ* ልናደርግ *የሚገባን* ሳይሆን፥ ልናደርግ *የምንፈልገው* ነገር ነው።

ከዚህ *መሠረታዊ* እውነታ አንዳንድ ተግባራዊ ተዛምዶዎች ሊወጡ ይችላሉ፦

*በመጀመሪያ*፥ የእግዚአብሔርን ፍቅር በተሻለ *ሁኔታ* ስናውቅ እንደ ክርስቲያን ለመኖር የበለጠ ይቀልለናል። የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ብቻውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ግላዊ ልምምድ ሊተካው አይችልም። እንዲያውም፥ ካልተጠነቀቅንበት ይህ አካሄድ አደገኛ ነገር ሊሆን ይችላል።

ሔለን ከወጣቶች የተሐድሶ ፕሮግራም ስትመለስ እጅግ እንደተደሰተች ፊቷ ላይ የሚውረገረገው ፈገግታዊ ጸዳል ይመሰክር ነበር።

ለእህቷ ለጆይስ ስትናገርም፥ «እንዴት የግል የጽሞና ጊዜ እንደምናካሂድ የሚያስተምሩ አስደናቂ የስብሰባ ፕሮግራሞች ነበሩን። እናም በየዕለቱ የጽሞና ጊዜ እንዲኖረኝ ዐቅጃለሁ» ስትል ገለጸች።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ጆይስ ቤቱን እያጸዳዳች ሳለች፥ ሔለን፥ «ያን ሁሉ ድምፅ ማሰማት ይገባሽ ነበር? የጽሞና ጊዜዬን ተግባራዊ ለማድረግ እየሞከርኩ እንዳለሁ አታውቂም?» ስትል ጮኸችባት። ይህም የቃላት ውርጅብኝ የበፋን በኃይል መበርገድ ተከትሎ የመጣ ነበር።

ሔለን የግል የጽሞና ተግባራት በራሳቸው ፍጻሜዎች እንዳልሆኑ መማር ነበረባት። እግዚአብሔርን እንድንወድና እርስ በርሳችን እንድንዋደድ እስካልረዱን ውጤታቸው እምብዛም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫ ነው፤ በመሆኑም፥ ፍቅሩን ይበልጥ በተረዳን መጠን እርሱን ለመታዘዝና ሌሎችን ለማፍቀር ይመቸናል።

ሁለተኛው ነገር ያልዳኑትን ሰዎች እስካልወደድን ድረስ፥ ለእነርሱ የምናቀርበው የቃል ምስክርነት ጥቅም እንደማይኖረው ነው። የወንጌሉ መልእክት የፍቅር መልእክት ነው። ይህ ፍቅር በኢየሱስ ክርስቶስ ታውጆአል፤ ታይቶአልም። በመሆኑም፥ ሌሎችን የምንማርክበት ብቸኛው ስኬታማ መንገድ ወንጌሉን ማወጅና በኑሮአችንም ማሳየት ነው። ዛሬ የሚበዛው «ምስክርነት» የአፍ ምስክርነት ብቻ ነው። ሰዎች የፍቅር መግለጫ ያስፈልጋቸዋል።

እግዚአብሔር ዓለም ክርስቲያኖችን እንዲጠላ የሚፈቅድበት አንደኛው ምክንያት፥ ክርስቲያኖች ለዓለም ጥላቻ ፍቅርን ይመልሱ ዘንድ ነው። «ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። እኔ ግን እላችኋለሁ... ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥... ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ» የሚረግሙአችሁንም መርቁ» (ማቴ. 5፡11፥44)

በአንድ የሰንበት ትምህርት ፍጻሜ ላይ ወይዘሮ ባርተን፥ «ውድ መጋቢ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ባልንጀሮቻችሁን [ጎረቤቶቻችሁን] ውደዱ ይላል፤ ዳሩ ግን የእኔን ጎረቤቶች ሊወድ የሚችል ሰው ስለመኖሩ እጠራጠራለሁ። ጥሩ ወዳጅ ለመሆን የሞከርሁ ብሆንም ምንም ውጤት አላገኘሁም» አሉ።

መጋቢውም፥ «ምናልባትም ጥሩ ወዳጅ መሆን ለእነርሱ እውነተኛ መፍትሔ ላይሆን ይችላል። ይህም የሚሆነው፥ በተሳሳተ አመለካከት ለሰዎች መልካም መሆን ስለሚቻል ነው» ሲሉ አብራሩ።

«እንዳይቃወሙኝ በገንዘብ ለመደለል እንደመሞከር ማለትም ነው?»

«አዎን፥ እንደዚያ ዓይነት ነገር እግዚአብሔር ለጎረቤቶችዎም እውነተኛ ፍቅር እንዲሰጥዎ እኔና እርስዎ መጸለይ አለብን። በክርስትና መንገድ የሚወዱአቸው ከሆነ፥ በእነርሱ ላይ ምንም ጉዳት ሊያደርሱ አይችሉም» ሲል መለሰላቸው።

ምንም እንኳ ጊዜው ጥቂት ሳምንታት ቢወስድም፥ ወይዘሮ ባርተን ለጎረቤቶቻቸው ባላቸው ፍቅር ከማደጋቸውም በላይ፥ የራሳቸውም መንፈሳዊ ሕይወት እየተለወጠ ሲመጣ ተመለከቱ።

በዚህም ጊዜ ለአንድ የጸሎት ቡድን ሲናገሩ፥ «ምንም እንኳ ጎረቤቶቼ ሁሉንም ነገር ባይለውጡም፥ ለእነርሱ ያለኝ አመለካከት በትክክል ተለውጧል። ከዚህ በፊት የእነርሱን ድጋፍ ለማግኘት በመሻት አንዳንድ መልካም ነገሮችን አደርግላቸው ነበር። አሁን ግን ነገሮችን የማደርግላቸው ለኢየሱስ ክርስቶስ ብዬ ነው – እርሱ ሞቶላቸዋል – ይህም ከፍተኛ ለውጥ ያደርጋል!» ብለዋል።

ዮሐንስ በዚህኛው የደብዳቤው አንቀጽ ወደ ክርስትና ፍቅር ዋንኛ መሠረት አምጥቶናል። ይህም ሆኖ፥ ገና የሚያስተምረን ቁም ነገር አለው። በቀጣዩ ክፍል፥ ለእግዚአብሔር ስለሚኖረን ግላዊ ፍቅር በመግለጽ፥ እግዚአብሔር ያንን ፍቅር እንዴት በእኛ ውስጥ ፍጹም እንደሚያደርገው ያብራራል።

እነዚህ የክርስትና ፍቅር ሁለት ገጽታዎች እርስ በርሳቸው አይነጣጠሉም። እነርሱም እግዚአብሔርን የምንወድ ከሆነ እርስ በርሳችን እንዋደዳለን፤ እርስ በርሳችን የምንዋደድ ከሆነ፥ ለእግዚአብሔር በሚኖረን ፍቅር እናድጋለን።

እንዲሁም፥ «እግዚአብሔር ፍቅር» ስለሆነ፥ ሁለቱም አሳቦች እውነት ናቸው።

# ውደድ፥ አክብር፥ ታዘዝ

## 1ኛ ዮሐንስ 4፡17–5፡5

በቅርቡ የሚጋቡት ሁለት እጮኛሞች ስለ ሠርጋቸው አፈጻጸም ከመጋቢው ጋር ሲነጋገሩ ወንድየው በንዴት ጦፈ።

ወጣቱ፥ «የጋብቻን ቃል ኪዳን ቅጂ ማየት እፈልጋለሁ» በማለቱ መጋቢው የፍላጎቱን አሟላለት። በጥንቃቄ አንብቦ ከመለሰ በኋላም፥ «ይኼ አይሆንም፥ በዚህ ውስጥ እርሷ እኔን ስለመታዘዟ የተጠቀሰ ነገር የለም!» ሲል ተናገረ።

እጮኛው ፈገግ ብላ እጁን ያዘችና፥ «የእኔ ውድ፥ *መታዘዝ* የሚለው ቃል በመጽሐፉ ውስጥ የግድ መጻፍ የለበትም። ቀደም ብሎ በልቤ ውስጥ በፍቅር ተጽፎአል» አለችው።

በዚህኛው የ1ኛ ዮሐንስ መልእክት ክፍል የተገለጸው እውነት ይኼ ነው። እስካሁን ድረስ አጽንኦት የተሰጠው አማኞች *እርስ በርሳቸው* በመዋደዳቸው ላይ ነበር፤ አሁን ግን ይበልጥ ወደ ጠለቀና ይበልጥ አስፈላጊ ወደ ሆነ ርእሰ-ጉዳይ እንገባለን፤ ይህም አማኞች *ለአብ* የሚኖራቸው ፍቅር ነው። ሰማያዊ አባታችንን እስካልወደድን ድረስ ባልንጀራችንን ወይም ወንድማችንን ልንወድ አንችልም። *መጀመሪያ* በሙሉ ልባችን እግዚአብሔርን መውደድ አለብን፤ ከዚያ በኋላ ባልንጀራችንን እንደ ራሳችን እንወደዋለን።

በዚህ ክፍል ቁልፍ ቃል *«ፍጹም»* የሚለው ነው። እግዚአብሔር እኛ ለእርሱ የሚኖረንን ፍቅርና እርሱ ለእኛ የሚኖረውን ፍቅር በእኛ ውስጥ ፍጹም ሊያደርግ ይፈልጋል። *ፍጹምነት* የተባለው ቃል *የብስለትንና የምሉዕነትን* አሳብ ይይዛል። አማኝ በጸጋና በእውቀት ብቻ ሳይሆን (2ኛ ጴጥ. 3፡18)፥ ለአብ በሚኖረውም ፍቅር ጭምር ማደግ አለበት።

እግዚአብሔር ምን ያህል ይወድደናል? መልሱ ልጁ ስለ እኛ እንዲሞት ለመላክ የሚችለውን ያህል ነው። (ዮሐ. 3፡16)። ልጆቹን የሚወደው *ክርስቶስን በሚወድበት ልክ ነው* (17፡23)። ኢየሱስም አብ ወልድን የወደደበት ፍቅር በልጆቹ ዘንድ እንዲሆን መፈለጉን ይነግረናል (ቁ. 26)።

በሌላ አገላለጽ፥ የክርስትና ሕይወት በእግዚአብሔር ፍቅር የማደግ *ዕለታዊ ልምምድ* መሆን አለበት ማለት ነው። ይህም አማኙ በፍቅር

ሲያድግ በጠለቀ መንገድ ለማያዊ አባቱን እያወቀ መምጣቱን ያካትታል።

የክርስትና ሕይወትን በመከፋፈል ከሙሉ ገጽታው ይልቅ በአንዳንድ ክፍልፋዮች ላይ ማተኮሩ ቀላል ነው። በዚህም ምናልባት አንደኛው ቡድን በ«ቅድስና» ላይ በማተኮር አባላቱ በኃጢአት ላይ ድልን እንዲቀዳጁ ይገፋፋ ይሆናል። ሌላው ደግሞ ምስክርነት ወይም «ከዓለም በመለየት» ላይ ያጠብቅ ይሆናል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እነዚህ አጽንኦቶች እያንዳንዳቸው ከሌላ አቅጣጫ የሚገኙ ፍሬዎች ናቸው፤ ይኸውም አማኙ ለአብ የሚኖረው ፍቅር ውጤቶች መሆናቸው ነው። እናም፥ ዛሬ በእግዚአብሔር ሕዝብ መሀል እንደ አጠቃላይ ጉድለት የሚንጸባረቀው ጉዳይ ክርስቲያናዊ ፍቅር ነው።

አማኝ ለአብ ያለው ፍቅር ፍጹም እየሆነ እንዳለ እንዴት ሊያውቅ ይችላል? ይህ የ1ኛ ዮሐንስ አንቀጽ አራት መረጃዎችን ይጠቁማል።

## 1. ድፍረት (1ኛ ዮሐ. 4:17–19)

በዚህ ስፍራ ዮሐንስ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ያልተጠቀማቸውን ሁለት ቃላት ይጠቅሳል፤ እነዚህም፥ *ፍርሃትና ቅጣት (ሥቃይ)* ናቸው። ይህም ደግሞ *ለአማኞች* የተጻፈ ነው። ክርስቲያኖች በፍርሃትና በሥቃይ ሊኖሩ ይችላሉ? አዎን፤ የሚያሳዝነው አያሌ አማኞች ዕለት በዕለት በፍርሃትና በሥቃይ መኖራቸው ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ በእግዚአብሔር ፍቅር አለማደጋቸው ነው።

*«ድፍረት»* የሚለው ቃል *«መተማመን»* ወይም *«የንግግር ነጻነት»* ተብሎ ሊፈታ ይችላል። ቅጥ ያጣ ድፍረትንና ኃፍረተ–ቢስነትን ግን አያመለክትም። ፍጹም ፍቅርን የሚለማመድ አማኝ በእግዚአብሔር ባለው መተማመን ያድጋል። ለእግዚአብሔር የሚኖረው የአክብሮት ፍርሃት እንጂ የቅጣት ፍርሃት አይደለም። አማኝ አባቱን የሚያከብር ልጅ እንጂ በዳኛው ፊት የሚንቀጠቀጥ እስረኛ አይደለም።

በሥነ–ልቡና መጻሕፍት ውስጥ ልዩ ልዩ ዓይነት ፍርሃቶች ተጠቅሰዋል፤ ለምሳሌ ከፍተኛ ቦታዎችን፥ ውኃን፥ ወዘተ… ስለመፍራት የተዘረዘሩ አሳቦች አሉ። ዮሐንስ የሚጽፈው ግን «ፍርድን ስለ መፍራት» ነው። ዮሐንስ ቀደም ብሎ ስለዚህ የጠበቀ እውነት የገለጸ ሲሆን (2:28)፥ አሁንም በድጋሚ ያነሣዋል።

ሰዎች የሚፈሩ ከሆነ የሚፈሩት ስለሚረብሻቸው ያለፈ ትውስታ፥ ወይም ስለሚያሳዝናቸው የአሁን ገጠመኝ፥ ወይም ወደፊት ይደርስብናል ብለው ስለሚያስቡት ክስተት ነው። ምናልባት የሦስቱ ፍርሃቶች ጥምረት ይንጣቸው ይሆናል። በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን

ሰው የእግዚአብሔርን ፍቅር ስለተለማመደና ይህም ፍቅር በሕይወቱ ዕለት በዕለት ፍጹም እየሆነ ስለሚሄድ ስላለፈው፥ አሁን ስላለውና ወደፊትም ስለሚመጣው ነገር ሊፈራ አይገባም።

«ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደተመደበባቸው» (ዕብ. 9:27) ቢታወቅም፥ ክርስቲያን ግን ወደፊት ስለሚመጣው ፍርድ አይፈራም፤ ይህም የሆነው እርሱ ሊቀበል የሚገባውን ፍርድ ክርስቶስ ተቀብሎ በመስቀል ላይ ስለተሠቃየለት ነው። «እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም» (ዮሐ. 5:24)። «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» (ሮሜ 8:1)። ለክርስቲያን ፍርድ ወደፊት የሚመጣ ክስተት ሳይሆን *ያለፈ ታሪክ ነው።* ኃጢአቶቹ ቀደም ብለው በመስቀሉ ላይ ፍርዳቸውን የተቀበሉ ሲሆን፥ ከእንግዲህ በእርሱ ላይ እንደገና ከሳሾች ሆነው አይቀርቡም።

የድፍረታችን ምሥጢሩ፥ «እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም» መሆናችን ነው (1ኛ ዮሐ. 4:17)። እርሱ በሚመለስበት ጊዜ እርሱን እንድንመስል እናውቃለን (3:1-2)፤ ይሁንና ይህ ዓረፍተ-ነገር በቀዳሚነት የሚያመለክተው አማኞች የሚቀበሉአቸውን የከበሩ አካላት ነው (ፊልጵ. 3:20-21)። *ሰፍራችንን በተመለከተ* አሁኑኑ «እርሱ እንዳለ» (እንደ እርሱው) ነን። እንደ አካሉ ክፍሎች ከክርስቶስ ጋር በቅርብ የተቆራኘን በመሆናችን፥ በዚህ ዓለም ሳለን ሁኔታችን በሰማይ እንደከበረው ስፍራው ነው።

ይህም ማለት አብ ከእኛ ጋር የሚዛመደው ልክ ከውድ ልጁ ጋር በሚዛመድበት መልኩ ነው ማለት ነው። እንግዲህ፥ ምን ብለን ልንፈራ እንችላለን?

ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ በኃጢአታችን ላይ የፍርድ ብያኔ ስለ ተሰጠ፥ *ስለ ወደፊቱም* መፍራት የለብንም። «እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና።» አብ በልጁ ላይ ስለፈረደ ዳግም በኃጢአታችን ላይ አይፈርድም።

*ስላለፈውም* ቢሆን መፍራት የለብንም፤ «እርሱ አስቀድሞ ወድዶናልና።» ከመጀመሪያው ጀምሮ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ግንኙነት የፍቅር ግንኙነት ነበር። ይህም እኛ እርሱን እንደወደድነው ሳይሆን፥ ዳሩ ግን እርሱ እኛን እንደወደደን ነው (1ኛ ዮሐ. 4:10)። «ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን» (ሮሜ 5:10)። እግዚአብሔር

ከቤተሰቡ ውጭ ሆነን በማንታዘዘው ጊዜ ከወደደን፥ አሁን ልጆቹ ከሆንን በኋላ ምን ያህል የበለጠ ይወድደን ይሆን?

«ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ስለሚጥል» (1ኛ ዮሐ. 4፡18)፥ *ስለ አሁኑም መፍራት የለብንም።* በእግዚአብሔር ፍቅር እያደግን ስንሄድ፥ ወደፊት ምን እንደሚሠራ በማሰብ መስጋታችን ይቀራል።

ተገቢ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ቢኖርም እንኳ፥ ይህ ግን ሥቃይን የሚያስከትል ዓይነት አይደለም። «አባ አባት ብለን የምንጮኸበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና» (ሮሜ 8፡15)። «እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና» (2ኛ ጢሞ. 1፡7)።

ፍርሃት በመሠረቱ የሥቃይ ጅማሬ ነው። ከፊታችን ስለሚጠብቀን ነገር ስናስብ ራሳችንን እናሠቃያለን። ብዙ ሰዎች ወደ ጥርስ ሐኪም ዘንድ ለመሄድ ሲያስቡ ይሠቃያሉ። እንግዲህ አንድ ያልዳነ ሰው የፍርድን ዕለት ሲያስብ ምን ያህል እንደሚሠቃይ አስብ። ክርስቲያን ግን በፍርድ ዕለት ድፍረት ስላለው፥ ዛሬ ሕይወትን ሲጋፈጥ ድፍረት ሊኖረው ይችላል! ይህም የሚሆነው ዛሬ ወደ ፊት ከሚመጣው የፍርድ ዕለት አሠቃቂነት ጋር ሊወዳደር የሚችል የሕይወት ገጠመኝ ስለማይኖር ነው።

እግዚአብሔር ልጆቹ በፍቅርና በመተማመን ድባብ እንጂ በፍርሃትና በሥቃይ እንዲኖሩ አይፈልግም። በእግዚአብሔር ፍቅር ወደ ፍጹምነት እየተጓዝን ስላለን ሕይወትን ወይም ሞትን መፍራት አያስፈልገንም። «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን? በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥ ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ» (ሮሜ 8፡35፥ 37-39)።

አስተውል! *በፍጥረት ሁሉ አሁንም ሆነ ወደፊት ምንም ነገር* በእኛና በእግዚአብሔር ፍቅር መካከል ጣልቃ ሊገባ አይችልም!

በሕይወታችን የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም የሚሆነው አያሌ ደረጃዎችን እያለፈ ነው። ከደኅንነት ርቀን በጠፋን ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ምንም ነገር ሳናውቅ በፍርሃት እንኖር ነበር።

በክርስቶስ ካመንን በኋላ በልባችን ውስጥ የፍርሃትና የፍቅር አደናጋሪ ውህደት ተፈጠረ። ዳሩ ግን ከአብ ጋር ባለን ኅብረት እያደግን ስንሄድ ቀስ በቀስ ፍርሃት እየጠፋ ሄዶ ልባችን በፍቅሩ ብቻ ሊዋጥ ቻለ። ስለሆነም፥ የበሰለው ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፍቅር ሲያርፍ፥ ያልበሰለ ክርስቲያን ግን በፍቅርና በፍርሃት መካከል ይዋዥቃል።

ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር እያደገ መሆኑን ከሚያሳዩን የመጀመሪያ መረጃዎች አንዱ በእግዚአብሔር ህልውና ላይ የሚኖረን መተማመን እያደገ መምጣቱ ነው። ይህም ሆኖ፥ መተማመን ብቻውን የሚቆም ነገር ሳይሆን ሁልጊዜ ወደ ሌሎች የሥነ-ምግባር ውጤቶች የሚመራ ነው።

## 2. ታማኝነት (1ኛ ዮሐ. 4፡20-21)

«ማንም... እያለ...» የሚለው ቃል ለሰባተኛ ጊዜ መጠቀሱ ነው። ይህንን ጠቃሚ ሐረግ ብዙ ጊዜ የተመለከትን ሲሆን፥ በእያንዳንዱ ጊዜም ቀጣዩን ነገር እናውቅ ነበር፤ ይኸውም በማስመሰል ላይ የሚሰነዘር ማስጠንቀቂያ ነው።

ብዙውን ጊዜ ፍርሃትና ማስመሰል አብረው ይሄዳሉ። እንዲያውም፥ አብረው የተወለዱት የመጀመሪያው ወንድና የመጀመሪያዋ ሴት ኃጢአት ባደረጉ ጊዜ ነበር። አዳምና ሔዋን በደላቸውን ካወቁ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ከእግዚአብሔር ሊደበቁና ዕራቁትነታቸውን ሊሸፍኑ ሞከሩ። ይሁንና፥ ሽፍንፍናቸውም ሆነ ማመኻኛቸው ሁሉንም ከሚያይ የእግዚአብሔር ዓይን ሊጋርዳቸው አልቻለም። ስለሆነም፥ አዳም በመጨረሻ፥ «በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለሆንሁ ፈራሁ» ሲል እውነቱን ለማውጣት ተገደደ (ዘፍ. 3፡10)።

ዳሩ ግን ልባችን በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት ሲኖረው ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰዎች ማስመሰሉ አስፈላጊ አይሆንም። በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት የሌለው አማኝ በእግዚአብሔር ሕዝብም ዘንድ ድፍረት አይኖረውም። ፍርሃት ከሚፈጥረው ሥቃይ ውስጥ፥ «ሌሎች ሰዎች ምን ያህል ስለ እኔ ያውቃሉ?» የሚለው የማያቋርጥ ጭንቀት ይገኝበታል። ይሁንና፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት ሲኖረን ይህ ፍርሃት ስፍራ ይለቅና ሰዎችንም ሆነ እግዚአብሔርን ያለፍርሃት እንጋፈጣቸዋለን።

አንድ ጎብኚ፥ «በቤተ ክርስቲያናችሁ ምን ያህል አባላት አሉ?» ሲል መጋቢውን ጠየቀው።

መጋቢውም፥ «ወደ አንድ ሺህ አካባቢ» ሲል መለሰለት።

ጎብኚውም «ይህ ሁሉንም ሰው ለማስደሰት ለሚደረገው ጥረት ብዙ ነው» ሲል አስተያየቱን ሰጠ።

መጋቢውም ፈገግ ብሎ፥ «ላረጋግጥልህ የምፈልገው ነገር ቢኖር፥ ወዳጄ፥ አባሎቼን ሁሉ ወይም ከመካከላቸው አንዳንዶቹን እንኳ ለማስደሰት እንደማልሞክር ነው። እኔ ለማስደሰት የምፈልገው አንዱ አካል ያውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ነው። ከእርሱ ጋር ያለኝ ግንኙነት ትክክል ከሆነ በእኔና በሕዝቡ መካከል የሚኖረው ግንኙነት ትክክል ይሆናል» ሲል ገለጸለት።

ለእግዚአብሔር ባለው ፍቅር ያላደገ «ጥሬ» ክርስቲያን «በመንፈሳዊነቱ» ሌሎችን ማስደሰት እንዳለበት ሊያስብ ይችላል። ይህ ስሕተት ግን በውሸት አዘቅት ውስጥ ይከትተዋል! በተግባር የማያውለውን ነገር እየተናገረ ከመሆኑም በላይ ሕይወትን እንደ መኖር የትወና ጥበብ እየከወነ ነው ማለት ነው።

ምናልባትም የዚህ ኃጢአት ከሁሉም የተለየ ምሳሌ የታየው በሐናንያና ሰጲራ ተግባር ውስጥ ይሆናል (የሐዋ. 5)። መሬታቸውን ሸጡና ከገንዘቡ *የተወሰነ መጠን* ለጌታ አመጡ፤ ይሁንና፥ ገንዘቡን *ሁሉ* እንዳመጡ ተናገሩ። የነዚህ ባለትዳሮች ኃጢአት *ገንዘቡን* ከእግዚአብሔር መውሰዳቸው አይደለም፤ ምክንያቱም ጴጥሮስ ገንዘቡ የራሳቸው እንደነበር ገልጾአልና (ቁ. 4)። ኃጢአታቸው ግብዝነት ነበር። ሰዎች ከእውነተኛው ልግስናቸውና መንፈሳዊነታቸው በላይ እንዲመለከቱአቸው ለማድረግ ይሞክሩ ነበር።

ማስመሰል ከትናንሽ ልጆች ተወዳጅ ተግባራት አንዱ ቢሆንም፥ በአዋቂዎች ግን ከቶውንም የብስለት ምልክት አይደለም። አዋቂዎች ክርስቶስ ለምን ዓላማ እንደፈጠራቸው በመገንዘብ ራሳቸውን *ሊያውቁና ራሳቸውን ሊሆኑ* ይገባል። ሕይወታቸው በታማኝነት ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል።

መንፈሳዊ ታማኝነት ይህንኑ ለሚለማመድ ሰው ሰላምንና ኃይልን ይሰጣል። የዚህ ዓይነቱ ሰው የተናገራቸውን ውሸቶች መዝግቦ ማቆየት የለበትም፤ ጉልበቱንም የሚጠቀመው ውሸቶቹን ለመሸፋፈን አይደለም። ከአብ ጋር በግልጽ ታማኝነት ስለሚኖር፥ ከሌሎች ሰዎችም ጋር በታማኝነት ሊኖር ይችላል። ፍቅርና እውነት አብረው ይሄዳሉ። እግዚአብሔር እንደሚወድደውና ከጥፋቶቹ ሁሉ ጋር እንደሚቀበለው ስለሚያውቅ፥ ሌሎችን ለማስደሰት አይጥርም፤ እግዚአብሔርን ይወድዳል፤ ከዚህም የተነሣ ሌሎች ክርስቲያኖችን ይወድዳል።

የጄሪ የትምህርት ውጤት ከተለመደው የወረደ ሲሆን፥ ከዚህም በላይ የጤንነቱ ጉዳይ አሳሳቢ ይመስል ነበር። በመሆኑም አዲሱ የክፍል ጓደኛው ሁኔታው ስላሳሰበው ለግቢው የሥነ-ልቡና አዋቂ እንዲናገር ገፋፋው።

ጄሪም «የራሴው ሁኔታ አደናግሮኛል። ባለፈው ዓመት ትምህርቱ ይቀለኝ የነበረ ሲሆን፥ በዚህ ዓመት ግን ጦርነት የመዋጋት ያህል ሆኖብኛል» ሲል ለሥነ-ልቡና ጠቢቡ ገለጸለት።

«አዲሱ የክፍል ጓደኛህ ችግር አይፈጥርብህም አይደል?» ሲል ጠየቀው አዋቂው።

ጄሪ ቀጥተኛ መልስ ባለመስጠቱ አማካሪው ፍንጭ አገኘ።

«ጄሪ፥ የምታተኩረው ሕይወትህን እንደ ጥሩ ተማሪ በመኖሩ ላይ ነው ወይስ አዲሱን የክፍል ጓደኛህን በችሎታዎችህ በማስደሰቱ ላይ ነው?»

ጄሪ በእፎይታ ከተነፈሰ በኋላ፥ «አዎ፥ እንደዚያ ይመስለኛል። በማስመሰል ኑሮ በጣም ስለዛልሁ ለመቀጠል የሚበቃ ዓቅም አልነበረኝም» ሲል መለሰ።

በእግዚአብሔር ዘንድ የሚኖረን ድፍረትና ከሌሎችም የምናተርፈው ታማኝነት ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ወደ ፍጹምነት እያደገ መሄዱን የሚያሳዩን ሁለት መለያዎች ናቸው።

## 3. በደስታ መታዘዝ (1ኛ ዮሐ. 5፡1–3)

*መታዘዝ* ብቻ ሳይሆን *በደስታ መታዘዙ* አስፈላጊ ነው! «ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም» (ቁ. 3)።

ከሰው በቀር በፍጥረት ዓለም ውስጥ የሚገኝ ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ይታዘዛል። «እሳትና በረዶ አመዳይና ውርጭ፥ ቃሉን የሚያደርግ ዐውሎ ነፋስም» (መዝ. 148፡8)። በትንቢተ ዮናስ ነፋሳትና ማዕበል፥ ዓሦችም ሳይቀሩ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እየፈጸሙ፥ ነቢዩ ዮናስ ግን በአለመታዘዙ ሲጸና እንመለከታለን። ተክሏና ትንሿ ትል እንኳ እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ፈጽመዋል። ነቢዩ ግን ልቡን በማደንደን የራሱን መንገድ ፈልጎአል።

ለእግዚአብሔር ፈቃድ አለመታዘዝ አሳዛኝ ነገር ሲሆን፥ በኀዘን ወይም በግድ መታዘዝም እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር ትእዛዛቱን እንድንተላለፍ አይፈልግም፤ እንዲሁም ደግሞ ከፍርሃት ወይም ከግዴታ የተነሣ እንድንታዘዘውም አይፈልግም። ጳውሎስ *ስለ መስጠት*

የጻፈው አሳብ *በአኗኗራችንም* ላይ ይሠራል፤ «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፥ በኃዘን ወይም በግድ አይደለም» (2ኛ ቆሮ. 9፡7)።

*በደስታ የመታዘዝ ምሥጢሩ ምንድን ነው? ምሥጢሩ መታዘዝ* ቤተሰባዊ ጉዳይ እንደሆነ መገንዘቡ ነው። እኛ አፍቃሪውን አባት የምናገለግል ስንሆን በክርስቶስ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የሆኑትን ወገኖች እየረዳን ነው። ከእግዚአብሔር ስለተወለድን እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ልጆች እንወዳለን። ይህንንም ፍቅር በተግባር የምናሳየው የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመጠበቅ ነው።

አንዲት ሴት ከደረሰቻቸው ግጥሞች ጥቂቱን እንደምትሸጥለት ተስፋ በማድረግ ወደ አንድ የጋዜጣ አዘጋጅ ቢሮ ሄደች።

አዘጋጁም፥ «ግጥሞችሽ ስለ ምን ርእሰ-ጉዳይ የሚያወሩ ናቸው?» ሲል ጠየቃት።

«ስለ ፍቅር!» ስትል በአጽንኦት ገለጸችለት ገጣሚዋ።

አዘጋጁም ከወንበሩ ላይ ተመቻችቶ ከተቀመጠ በኋላ፥ «መልካም፥ እስኪ አንብቢልኝ። ዓለሙ በርግጥ ገና ተጨማሪ ፍቅር ሊያሻው ይችላል!» አለ።

ገጣሚዋ ያነበበችለት ግጥም በተራ ስሜታዊ ነገሮች የተሞላ በመሆኑ አዘጋጁ እስከትጨርስ ለመታገሥ አልቻለም።

ስለሆነም፥ «እባክሽ የእኔ እመቤት፤ ፍቅር ምን እንደሆነ የምታውቂ አይመስለኝም! ፍቅር የጨረቃ ብርሃንና ጽጌሬዳ አይደለም። ፍቅር በበሽተኛ አልጋ ዳር ሌሊቱን ሁሉ ተቀምጦ ማደር ወይም ልጆች አዲስ ጫማ እንዲቀይሩ ተጨማሪ ሰዓታት መሥራት ነው። ስለሆነም ዓለም የሚፈልገው ያንችን አዲስ ቅኔያዊ ፍቅር ሳይሆን፥ ጥሩ የሆነ እውነተኛ *ተግባራዊ* ፍቅር ነው» ሲል መለሰላት።

ዲ.ኤል. ሙዲ ብዙ ጊዜ፥ «እያንዳንዱ መጽሐፍ ቅዱስ በጫማ ቆዳ መጠረዝ አለበት» ይሉ ነበር። ፍቅራችንን ለእግዚአብሔር የምናሳየው በባዶ ቃላት ሳይሆን በፈቃደኝነት የተፈጸሙት ድርጊቶች መሆን አለበት። እኛ አንድን ጌታ የምንታዘዝ ባሪያዎች ሳንሆን፥ አባታችንን የምንታዘዝ ልጆች ነን። ኃጢአታችንም ቢሆን የቤተሰብ ጉዳይ ነው።

በሳል ፍቅር ከሚመዘንባቸው መንገዶች አንዱ ለመጽሐፍ ቅዱስ ባለን የግል አመለካከት ነው፤ ይህም የሚሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሕይወታችን ተገልጦ ስለምናገኝ ነው። ደኅንነትን ያላገኘ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን እንደማይረዱት መጽሐፍ

የሚቆጥረው በአብዛኛው መንፈሳዊ መልእክቱ ስለማይገባው ነው (1ኛ ቆሮ. 2፡14)። ያልበሰለ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስን ትእዛዛት እንደ ከባድ ሸክም ይቆጥራቸዋል። የዚህ ዓይነቱ ሰው ለመታዘዝ እየተማረ ሳለ፥ «ለምን ይህንን ማድረግ አስፈለገኝ» ወይም «እንዲህ ባደርግ አይሻልም ኖሯል?» ሲል እንደሚጠይቅ ትንሽ ልጅ ነው።

የእግዚአብሔርን ፍጹም ፍቅር እየተለማመደ ያለ አማኝ ግን በእግዚአብሔር ቃል ደስ ሲሰኝና ከልቡ ሲወደው ይገኛል። መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነበው እንደ መማሪያ መጽሐፍ ሳይሆን፥ እንደ ፍቅር ደብዳቤ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ከሁሉም በላይ ረዥሙ ምዕራፍ መዝሙር (119) ሲሆን፥ ጭብጡም የእግዚአብሔር ቃል ነው። ከሁለት ቁጥሮች (ቁ. 122 እና 132 በቀር) ሌሎቹ ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ «ሕግ»፥ «ደንቦች» ወይም «ትእዛዛት»፥ ወዘተ... ይጠቅሳሉ። የሚያስገርመው ግን መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ቃል መውደዱና ስለዚህም ለእኛ ስለ ቃሉ ለመናገር መደሰቱ ነው! «አቤቱ፥ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ!» (ቁ. 97)። ሕጉ ደስታንና ተድላን ይሰጠዋል (ቁ. 14፥ 16፥ 24፥ 162)። ለአፉ ማር ነው (ቁ. 103)። እንዲያውም፥ የእግዚአብሔርን ሕግ ለዝማሬ ይጠቀምበታል፤ «በእንግድነቴ አገር ሥርዓትህ መዝሙር ሆነችኝ» (ቁ. 54)።

*ሥርዓት (ሕግ) ወደ ዝማሬ* ሲለወጥ ይታይህ! እንበልና የአንድ አገር ሙዚቀኞች የትራፊክ ሥርዓትን ደንቦች በመዝሙር ቢያቀርቡት ምን ይሰማሃል? ብዙዎቻችን ሕግጋት የአስደሳች ዝማሬ ምንጭ ይሆናሉ ብለን አንገምትም፤ መዝሙረኛው ግን የእግዚአብሔርን ሕግ የተመለከተው የአስደሳች ዝማሬ ምንጭ አድርጎ ነው። እግዚአብሔርን ስለወደደው ሕጉንም ወደደው። ለእርሱ የእግዚአብሔር ትእዛዛት አስቸጋሪዎችና ከባዶች አልነበሩም። አባቱን የሚወድ ልጅ ትእዛዛቱን በደስታ እንደሚቀበል ሁሉ፥ ፍጹም ፍቅር ያለው ክርስቲያንም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በደስታ ይፈጽማል።

አሁን በዕለታዊ ሕይወታችን ስለሚሆነው «በሳል ፍቅር» ልንከልስና ተግባራዊ ፍችውንም ልንመለከት እንችላለን። ለአብ ያለን ፍቅር እየበሰለ ሲሄድ፥ በእርሱ ዘንድ ድፍረት ስላለን ከእንግዲህ ስለ ፈቃዱ በማመንታት አንፈራም። በተጨማሪም ለሌሎች ሰዎች ታማኞች ስለምንሆን፥ ተቀባይነት እናጣለን ብለን መፍራታችን ይቀራል። ለእግዚአብሔር ቃልም አዲስ አመለካከት ይኖረናል፤ ይኸውም፥ የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫ እንደሆነና

ይህንኑም በመታዘዝ ደስ እንደምንሰኝ ነው። በመሆኑም፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት፥ ለሌሎች ታማኝነትና በደስታ መታዘዝ የፍጹም ፍቅር መለያዎችና ደስታ ለሰፈነበት የክርስትና ሕይወት ወሳኝ ጥንተ–ነገሮች ናቸው።

በተጨማሪም፥ ኃጢአት እንዴት ይህንን ሁሉ እንደሚያበላሽ ልንመለከት እንችላለን። እግዚአብሔርን ሳንታዘዝ ስንቀር በእርሱ ዘንድ የነበረንን ድፍረት እናጣለን። በዚህም ጊዜ ኃጢአታችንን ወዲያውኑ ተናዝዘን ይቅርታውን ካልተቀበልን (1ኛ ዮሐ. 1:9) ለመሸፋፈን ስንል ማስመሰልን እንጀምራለን። አለመታዘዝ ወደ አለመታመን የሚመራን ሲሆን፥ ሁለቱም ልባችንን ከእግዚአብሔር ቃል ይመልሱታል። የአባታችንን ፈቃድ እናገኝ ዘንድ ቃሉን በደስታ እንደ ማንበብ ችላ ልንለው ወይም በሥርዓታዊ መንገድ ልናነበው እንጀምራለን።

ሰው በራሱ መንገድ እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚሞክርበት ሃይማኖታዊ ሸክም ከባድና አስቸጋሪ ነው (ማቴ. 23:4)፤ ክርስቶስ የሚያስቀምጥብን ቀንበር ግን ከቶውንም ከባድ አይደለም (ማቴ. 11:28–30)። ፍቅር ሸክሞችን ያቀልላቸዋል። ያዕቆብ የወደዳትን ሴት ለማግኘት የግድ ለሰባት ዓመታት ማገልገል ነበረበት፤ ይሁንና፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው «እርስዋንም ይወድዳት ስለ ነበረ በእርሱ ዘንድ እንደ ጥቂት ቀን ሆነለት» (ዘፍ. 29:20)። ፍጹም ፍቅር በደስታ መታዘዝን ያስከትላል።

## 4. ድል ወይም ማሸነፍ (1ኛ ዮሐ. 5:4–5)

የግሪኩ ዓለም ሴት የድል አምላክ ኒኬ ትባል ነበር፤ ይህም የታላቋ አሜሪካ የአየር ለአየር ሚሳይል ስያሜ ሆኗል። የዚህም ስያሜ ትርጉም ድል የሚል ነው። ለመሆኑ ድል እየበሰለ ከሚሄድ ፍቅር ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

ክርስቲያኖች በእውነተኛ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ በመሆናቸው፥ ለአስቸጋሪ መሰናክሎች ይጋለጣሉ። ስለሆነም፥ እግዚአብሔርን መታዘዙ ቀላል አይደለም። ከዓለም ጋር መተባበሩ፥ እግዚአብሔርን አለመታዘዝና እንደፈለግን መኖር ቀላል ነው።

ክርስቲያን ግን «ከእግዚአብሔር ተወልዶአል።» ይህም ማለት በውስጡ መለኮታዊ ባሕርይ ስላለው፥ ይኸው መለኮታዊ ባሕርይ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሊተላለፍ አይችልም ማለት ነው። «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና» (ቁ. 4)። የሚቆጣጠረን አሮጌው ባሕርይ ከሆነ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት

እንተላለፋለን፤ ዳሩ ግን አዲሱ ባሕርይ የሚቆጣጠረን ከሆነ እግዚአብሔርን እንታዘዛለን። ዓለም አሮጌውን ባሕርይ በመማረክ (2፥15−17)፥ የእግዚአብሔር ትእዛዛት ከባዶች እንደሆኑ ለማሳየት ትሞክራለች።

*ማሸነፋችን የእምነት ውጤት በመሆኑ፥* በፍቅር ስናድግ በእምነትም እናድጋለን። አንድን ሰው ይበልጥ ስትወደው ለማመንም ያንኑ ያህል ይቀልሃል። ስለሆነም፥ ፍቅርና እምነት ጎን ለጎን እየበሰሉ ስለሚሄዱ፥ ለክርስቶስ ያለን ፍቅር ይበልጥ ፍጹም ሲሆን በክርስቶስ ላይ ያለንም እምነት ያንኑ ያህል ፍጹም ይሆናል።

*«ማሸነፍ»* የሚለው ቃል ዮሐንስ የሚወደው ቃል ነው፤ ይህንንም ቃል በ2፥13−14 ዲያብሎስን ከማሸነፍ ጋር አያይዞ ይጠቅሰዋል። በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ደግሞ አማኞችንና የሚቀበሉአቸውን በረከቶች ለመግለጽ ሰባት ጊዜያት ጠቅሶታል (2፥7፥11፥17፥ 26፤ 3፥5፥ 12፥21)። *አሸናፊ* የሚለውን ቃል የሚጠቀመው የተወሰኑ አማኞችን መደብ ለመግለጽ አይደለም፤ ለእውነተኛ ክርስቲያን ሁሉ እንደሚገባ እንጂ። ይህም የሆነው ከእንግዲህ ከእግዚአብሔር በመወለዳችን ምክንያት አሸናፊዎች ስለሆንን ነው።

በታላቁ እስክንድር የጦር ሠራዊት ውስጥ አንድ ሰነፍ ወታደር እንደነበር የሚያወሳ ታሪክ አለ። ይህ ሰነፍ ወታደር ወደፊት መገስገስ ሲኖርበት ወደ ኋላ ይንፉዋቀቅ ነበር።

እናም ታላቁ ጄኔራል ወደ እርሱ ቀርቦ፥ «ስምህ ማን ነው?» ሲል ጠየቀው።

ሰውዬውም፥ «ጌታዬ፥ ስሜ እስክንድር ነው» ሲል መለሰለት።

ጄኔራል ፊት ለፊት ተመልክቶት ሲያበቃ፥ «ውድ ወታደር፥ ብድግ በልና በርትተህ ተዋጋ − አለበለዚያ ግን ስምህን ቀይር!» አለው።

*የእኛስ ስም ማን ነው?* «የእግዚአብሔር ልጆች − ከእግዚአብሔር ዳግም የተወለድን።» ታላቁ እስክንድር ስሙ የጀግንነት ተምሳሌት እንዲሆን ፈልጎአል፤ የእኛም ስም የድል ዋስትናን ይዞአል። ከእግዚአብሔር መወለድ ማለት የእግዚአብሔርን ድል መጋራት ማለት ነው።

ይህ የእምነት አሸናፊነት ነው፤ ግን የትኛው እምነት? ከተባለም ይህ እምነት የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ዓለምን የሚያሸንፈው «ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚያምን» ሰው ነው (1ኛ ዮሐ. 5፥5)። ድሉን የሚሰጠን በራሳችን ላይ

ሳይሆን በክርስቶስ ላይ የሚኖረን እምነት ነው። «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ» (ዮሐ. 16:33)።

ከክርስቶስ ጋር መተባበሩ በዮሐንስ መልእክት ውስጥ ብዙ ጊዜ ያነበብነውን «እርሱ እንዳለ» ያስታውሰናል። «እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና» (4:17)። «እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ልንመላለስ ይገባል» (1:7)። በእርሱ እንኖራለን የምንል ከሆነ ባሕርያችንም እርሱን ሊመስል ይገባል (2:6)። እርሱ በሰማይ እንደሆነ ልጆቹ በምድር ሊሆኑ ይገባል። ለእኛም የሚያስፈልገን ይህንን ድንቅ ስፍራ *በእምነት መያዝና* በዚሁ *መሠረት ተግባራዊ ክንዋኔዎችን መፈጸሙ* ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሞት እኛም ከእርሱ ጋር ሞተናል። ጳውሎስ፥ «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ» ብሏል (ገላ. 2:20)። ክርስቶስ በተቀበረ ጊዜ ከእርሱ ጋር ተቀብረናል። ሲነሣ ደግሞ ከእርሱ ጋር አብረን ተነሥተናል። «እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን» (ሮሜ 6:4)።

ክርስቶስ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ እኛም ከእርሱ ጋር ስላረግን አሁን በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አለን (ኤፌ. 2:6)። ሲመለስም የክብሩ ተካፋዮች እንሆናለን። «ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ» (ቆላ. 3:4)።

እነዚህ ሁሉ ጥቅሶች በክርስቶስ ያለንን መንፈሳዊ ስፍራ ይገልጻሉ። ይህን ስፍራ በእምነት ስንይዝ የድሉ ተካፋዮች እንሆናለን። እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት ሲያስነሣው፥ «ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና... ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው... ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት» (ኤፌ. 1:20–22)። ይህም ማለት በተዋረድ ሲታይ የእግዚአብሔር ልጅ ሁሉ ከጠላቶቹ ሁሉ በላይ ልቆ ይቀመጣል ማለት ነው።

አንድ ሰው የሚቀመጥበት ስፍራ ምን ያህል ሥልጣን ሊኖረው እንደሚችል ይወስናል። በዋና ሥራ አስኪያጅ ወንበር ላይ የሚቀመጥ ሰው የተወሰነ ሥልጣን አለው። በምክትል ፕሬዚዳንቱ ወንበር ላይ የሚቀመጥ ሰው ከዚህኛው የበለጠ ሥልጣን አለው። ዳሩ ግን *«ፕሬዚዳንት»* የሚለው ጽሑፍ ከሰፈረበት ጠረጴዛ በስተጀርባ

የተቀመጠው ሰው ከሁሉም የላቀ ሥልጣን ይኖረዋል። ይህ ሰው በፋብሪካው አካባቢ ወይም በቢሮው ውስጥ ቢሆን ከመቀመጫው የተነሣ አክብሮትንና ታዛዥነትን ያተርፋል። ሥልጣኑ የሚወሰነው በስፍራው እንጂ በግላዊ አቀራረቡ ወይም በስሜቱ አይደለም።

የእግዚአብሔር ልጅም እንዲሁ ነው፤ ሥልጣኑ የሚወሰነው በክርስቶስ ባለው ስፍራ ነው። በክርስቶስ ባመነ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከክርስቶስ ጋር በመተባበር የአካሉ ክፍል ሆኗል (1ኛ ቆሮ. 12፡12-13)። አሮጌ ሕይወቱ ተቀብሮ ለአዲስ የክብር ሕይወት ተነሥቷል። ስለሆነም፥ በክርስቶስ በአጽናፈ-ዓለሙ ዙፋን ላይ በመቀመጥ ላይ ይገኛል።

አንድ በአገሪቱ ውስጥ በተካሄደው የእርስ በርስ ውጊያ ላይ የተሳተፈ የቀድሞ ወታደር የሚበላውንና የሚያድርበትን ስፍራ እየለመነና ሁልጊዜም «ሚስተር ሊንኮልን» ስለተባለ ወዳጁ እያወራ ከቦታ ቦታ ይንከራተት ነበር። ከደረሰበት የአእምሮ ጉዳት የተነሣም በአንድ ቦታ ረግቶ ለመሥራት አይችልም ነበር። ነገር ግን ለመጓዝ እስከቻለ ድረስ፥ ስለ ወዳጁ ለመናገር ይችል ነበር።

አንድ ቀን ግን ይህን አሳቡን ያልተቀበለ አንድ ተጠራጣሪ፥ «አንተ ሚስተር ሊንኮልንን አውቃለሁ ትላለህ። እኔ ግን እኝህን ሰው ስለማወቅህ እርግጠኛ አይደለሁምና ማረጋገጫ ስጠኝ» አለው።

ሽማግሌውም፥ «ምን ገዶኝ፥ ላረጋግጥ እችላለሁ። እንዲያውም፥ ሚስተር ሊንኮልን ራሳቸው ፊርማቸውን አሳርፈው የሰጡኝ ወረቀት በእጄ ይገኛል» ሲል መለሰለት።

ከዚያም ካረጀችው የወረቀት መያዣ በርሳው ውስጥ የነተበ ወረቀት አወጣና ለሰውዬው አሳየው።

ማንበብ ባለመቻሉ ይቅርታ ጠይቆት፥ «ዳሩ ግን ይህ የሚስተር ሊንኮልን ፊርማ እንደሆነ አውቃለሁ» አለው።

በዚህ ጊዜ ካነበቡት ተመልካቾች አንዱ «በዚህ ጽሑፍ የተሰጠውን ነገር ታውቃለህ? በፕሬዚዳንት ሊንኮልን ፊርማ የጸደቀና በመደበኛነት የሚከፈል ከፍተኛ የመንግሥት የጡረታ ቃል ተገብቶልሃል። ከእንግዲህ እንደ ድሀ ለማኝ ከቦታ ቦታ መዘዋወር የለብህም! ሚስተር ሊንኮልን ባለጸጋ አድርገውሃል!» አለው።

የዮሐንስ አሳብ አፍታተን ስናስቀምጥ፥ «ኢየሱስ ክርስቶስ አሸናፊዎች ስላደረጋችሁ፥ እናንተ ክርስቲያኖች በሽንፈት መመላለስ የለባችሁም! ጠላታችሁን ሁሉ ስላሸነፈላችሁ ድሉን ትጋራላችሁ። አሁን እንግዲህ *በእምነት* ድሉን ጨብጡ» የሚል ይሆናል።

በመሠረቱ ቁልፉ *እምነት* ነው፤ ይህ ሁልጊዜም እግዚአብሔር ለድል የሚጠቀምበት ቁልፍ ነው። በዕብራውያን ምዕራፍ 11 የተጠቀሱት ታላላቅ ወንዶችና ሴቶች ድሎቻቸውን የተቀዳጁት «በእምነት» ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል አምነው በዚያው ላይ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ፥ እርሱም እምነታቸውን በማክበር ድልን ሰጣቸው። እምነት ማለት እግዚአብሔር *የተናገረው እውነት እንደሆነ መቀበል* ብቻ አይደለም፤ እውነተኛ እምነት እግዚአብሔር የሚናገረው እውነት ስለሆነ በዚያው ላይ *ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ* ነው። አንድ ሰው እንደተናገረው፥ እምነት ማለት መረጃ ሳይኖር ማመን ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የሚያስከትለውን ውጤት ሳያስቡ መታዘዝ ነው ብሏል።

ድል-ነሺ እምነት የበሳል ፍቅር ውጤት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን የበለጠ ባወቅንና በወደድን መጠን፥ ከሕይወት ጉድለቶችና ውጊያዎች ሁሉ ጋር እርሱን መታመኑ የበለጠ ይቀልለናል። ስለሆነም ይህ እየበሰለ የሚሄድ ፍቅር የዕለታዊ ሕይወታችን መደበኛና ተግባራዊ ጉዳይ መሆኑ አስፈላጊ ነው።

ክርስቲያን የዚህ ዓይነቱን ፍቅርና ከእርሱም የሚፈልቁትን በረከቶች የሚለማመደው እንዴት ነው?

በቀዳሚነት፥ የዚህ ዓይነቱን ፍቅር ኮትኩቶ ማሳደግ ያሻል። ይህ በአወጣ ያውጣው የተጀመረ ወዳጅነት የሚያመጣው ውጤት አይደለም፤ ከቀደመው ጥናታችን እንደተረዳነው አማኝ ወደ ኋላ የሚመለሰው ደረጃ በደረጃ ነው፦

1. ከዓለም ጋር ወዳጅነት ይጀምራል (ያዕ. 4፡4)።

2. በዓለም እድፍ ይበላሻል (ያዕ. 1፡27)።

3. ዓለምን ይወዳል (1ኛ ዮሐ. 2፡15-17)።

4. ዓለምን ይመስላል (ሮሜ 12፡2)።

በተመሳሳይ ሁኔታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የሚኖረን ግንኙነት የሚያድገውም ደረጃ በደረጃ ነው፦

1. ከክርስቶስ ጋር ያለንን ግንኙነት ኮትኩተን ማሳደግ አለብን። አብርሃም ራሱን ከዓለም ለይቶ እግዚአብሔር የነገረውን ስለ ፈጸመ «የእግዚአብሔር ወዳጅ» ነበር (ያዕ. 2:23)። ምንም እንኳ ሕይወቱ ፍጹም ባይሆንም፥ በኃጢአት በሚወድቅበት ጊዜ ኃጢአቱን ተናዝዞ ወደ እግዚአብሔር ይመለስ ነበር።

2. ይህ ወዳጅነት ሕይወታችንን መለወጥ ይጀምራል። ቃሉን ስናነብና ስንጸልይ፥ ብሎም ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ኅብረት ስናደርግ፥ ክርስቲያናዊ ጸጋ በሕይወታችን ውስጥ መታየት ይጀምራል። በዚህም ጊዜ አሳባችን ከበፊቱ እየጠራ፥ ውይይታችን ይበልጥ ትርጉም እያገኘ እና መሻታችንም እየተሟላ የሚሄድ ይሆናል። ይሁንና፥ ይህ በዝግታ የሚከናወን ሂደት እንጂ ከመቅጽበት የምንለወጥበት አይሆንም።

3. ከክርስቶስ ጋር ያለን ወዳጅነትና እርሱን እየመሰልን መምጣታችን ለክርስቶስ ጥልቅ ፍቅር እንዲኖረን ያደርጋል። በሰው ደረጃ እንኳ ቢሆን ወዳጅነት ብዙውን ጊዜ ወደ ፍቅር ይመራል፤ በመለኮታዊ ደረጃም ከክርስቶስ ጋር የሚኖር ወዳጅነት ወደ በለጠ ፍቅር ሊመራ ይገባል። «እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን» (1ኛ ዮሐ. 4:19)። የእግዚአብሔር ቃል ፍቅሩን ይገልጽልናል፤ በውስጣችን የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ይህንኑ ፍቅር ይበልጥ ግልጽ ያደርግልናል። በተጨማሪም፥ ይኸው ፍቅር በታዛዥነት አማካኝነት በየዕለቱ በሕይወታችን ተግባራዊ ይሆናል። ክርስትና ዘላቂ ፍቅር መስጠት፥ ክርስቶስን ለማስደሰትና ፈቃዱን ለማድረግ የሚኖረን ጥልቅ መሻት እንጂ አላፊ ስሜት አይደለም።

4. ይበልጥ ባወቅነው መጠን ይበልጥ እንወደዋለን፤ ይበልጥ ስንወደው ደግሞ ይበልጥ እርሱን እንመስላለን፤ የልጁን መልክ እንመስል ዘንድ እንለወጣለን (ሮሜ. 8:29)። በርግጥ ፊት ለፊት እስክናየው ድረስ ሙሉ ለሙሉ ክርስቶስን አንመስልም (1ኛ ዮሐ. 3:1–3)፤ ዳሩ ግን አሁን ሂደቱን እንጀምራለን።

ይህ ምንኛ አስደሳች የአኗኗር መንገድ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ፍጹም ሲሆን፥ በእርሱ ዘንድ ድፍረት ስለሚኖረን በፍርሃት አንኖርም። ፍርሃት ስለተወገደም ግብዝነቱ ቀርቶ በታማኝነትና በግልጽነት ልንመላለስ እንችላለን። እንግዲህ ፍርሃት ስፍራ ስለለቀቀ ለትእዛዛቱ የሚኖረን ታዛዥነት የሚመነጨው ከፍቅር እንጂ ከፍርሃት አይሆንም። ትእዛዛቱም ከባዶች እንዳልሆኑ እንረዳለን። በመጨረሻም፥ በዚህ የፍቅር ድባብ ውስጥ በመኖር ዓለምን ድል በሚነሣ እምነት ልንጋፈጥና ከመሸነፍ ፈንታ ልናሸንፍ እንችላለን።

የምንጀምርበት ስፍራ ከፍተኛ የድፍረት ልምምድ የሚታይበት አይሆንም። ይልቁንም የጅማሬው ስፍራ ዝግ ያለ የግል የጸሎት ስፍራ ነው። ጴጥሮስ ሕይወቱን ስለ ኢየሱስ ለመስጠት ቢፈልግም፥ በጸሎት እንዲያግዝ በተጠየቀ ጊዜ ግን ተኛ (ሉቃስ 22፡31-33፥ 39-46)። ቃሉን በማንበብ፥ በዚያው ላይ በማሰላሰልና ክርስቶስን በጸሎትና በምስጋና በማምለክ ቀኑን የሚጀምር አማኝ ይህንኑ ፍቅር ይለማመዳል።

ገና ከጅማሬው እርሱም ሆነ ሌሎች ያውቁታል። ሕይወቱም በድፍረት፥ በታማኝነት፥ ደስታ በሞላበት ታዛዥነትና በድል ተለይቶ ይታወቃል።

# በእርግጠኛነት የምታውቀው ነገር ምንድን ነው?

## 1ኛ ዮሐንስ 5፡6–21

በ1789 ቤንጃሚን ፍራንክሊን፥ «ከሞትና ከቀረጦች በቀር ስለመኖሩ እርግጠኛ የምንሆንበት ነገር የለም» ሲሉ ጽፈዋል። በመሠረቱ፥ እንደ ፍራንክሊን ያለ አዋቂ ሰው ሌሎችም እርግጠኛ የምንሆንባቸው ነገሮች እንዳሉ ያውቅ ነበር። ክርስቲያን ደግሞ ብዙ እርግጠኛ የምንሆንባቸው ነገሮች እንዳሉ ያውቃል። ስለ መንፈሳዊ እውነት ክርስቲያኖች *«እኛ እናውቃለን!»* ለማለት አይፈሩምና። እንዲያውም፥ በዚህች አጭር የዮሐንስ መልእክት ውስጥ ብቻ *«ማወቅ»* የሚለው ቃል 39 ጊዜያት ተጠቅሶአል፤ ከእነዚህም 39 ጊዜያት ስምንቱ የሚገኙት በዚህ የመዝጊያ ምዕራፍ ውስጥ ነው።

ሰው አንድን ነገር በእርግጠኛነት ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉት ስላለው፥ ምትሐታዊ ኃይሎችን እስከማማከር እንኳ አይመለስም። ከቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ ጋር እራት ይበላ የነበረ አንድ ነጋዴ፥ «በዚያ በመንገዱ ጥግ ያሉትን ቢሮዎች ታያለህ? በዚህች ከተማ ከሚገኙት ታላላቅ ነጋዴዎች ብዙዎቹ በነዚያ ቢሮዎች ውስጥ ተቀምጠዋል። ብዙዎች ከአንዲት ዕድል ተንባይ ጋር ለመገናኘት እዚህ ይመጡ ነበር። አሁን ሴቲቱ እዚህ የለችም፤ ከጥቂት ዓመታት በፊት ግን ሰዎች ከእርሷ ጋር ለመነጋገር ወረፋ እየጠበቁ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ይሰጡአት ነበር» አለው።

እውነተኛ የሆነ ሕይወት በኢየሱስ ክርስቶስ በሚገኙ መለኮታዊ እርግጠኝነቶች ላይ የተመሠረተ ነው። ዓለም ክርስቲያኑ ኩራተኛና ግትር እንደሆነ በመግለጽ ይወቅሰው ይሆናል፤ ይህ ግን «አውቃለሁ!» ከማለት አያግደውም። በነዚህ የዮሐንስ መልእክት የማጠቃለያ ክፍሎች ውስጥ ሕይወታችንን በድፍረት ልንመሠርት የምንችልባቸውን አምስት የክርስትና ማረጋገጫዎች ወይም ዋስትናዎች እናገኛለን።

### 1. ኢየሱስ አምላክ ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡6–10)

በ5፡1–5 አጽንኦት የተሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስን በማመኑ ላይ ነው። በክርስቶስ የሚያምን ሰው ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ ዓለምን ለማሸነፍ ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ማመኑ ለክርስቲያናዊ ሕይወት መሠረታዊ ጉዳይ ነው።

ይሁንና፥ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ እንዴት እናውቃለን? በምድር ላይ በነበረ ጊዜ አንዳንዶች ውሸተኛና አታላይ እንደሆነ

ይናገሩ ነበር (ማቴ. 27፡63)። ሌሎች ደግሞ ሃይማኖታዊ አክራሪ፥ እብድ፥ ወይም እውነተኛ የሆነ አገር ወዳድና ዳሩ ግን በሚያሳዝን ሁኔታ ለስሕተት የተዳረገ ሰው አድርገው ይቆጥሩት ነበር። ዮሐንስ የሚጽፍላቸው ሰዎችም በዘመኑ ይነፍስ ለነበረው ወሬ ተጋልጠው ነበር፤ ይህም ወሬ ኢየሱስ ሰው ብቻ እንደነበረና በተጠመቀ ጊዜ «መሢሑ» እንደመጣበት የሚገልጽ ነበር። በመስቀል ላይ ኢየሱስ «አምላኬ፥ አምላኬ፥ ስለምን ተውኸኝ?» ሲል መሢሕነትን ስለተወ እንደ ማንኛውም ሰው ሞተ።

የዮሐንስ መልእክት ይህንን የሐሰት ትምህርት ፉርሽ ያደርገዋል። ስለሆነም፥ የኢየሱስን አምላክነት ለማረጋገጥ ሦስት ሁነኛ ምስክሮችን ያቀርባል።

*የመጀመሪያው ምስክር- ውኃው።* ኢየሱስ የመጣው «በውኃና በደም» ነው። ውኃው በዮርዳኖስ ወንዝ የተፈጸመውን የእርሱን ጥምቀት ያመለክታል፤ በዚህም ጊዜ አብ ከሰማይ ድምፅ አሰምቶ፥ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሏል (ማቴ. 3፡13-17)። በተመሳሳይ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ወርዶ በእርሱ ላይ አርፎአል። ይህ በአገልግሎቱ *መጀመሪያ* አብ ስለ ልጁ የሰጠው ምስክርነት ነበር።

*ሁለተኛው ምስክር- ደሙ።* ኢየሱስ የሚሞትበት ጊዜ እየቀረበ ሲመጣ አብ ተጨማሪ ምስክርነት ሰጥቷል። ከሰማይ ድምፅ አሰምቶ፥ «[ስሜን] አከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ» ሲል ለኢየሱስ ተናገረ (ዮሐ. 12፡28)። እንዲሁም፥ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በነበረ ጊዜ አብ በተአምራዊ ኃይል መስክሮአል፤ ይህም መለኮታዊ ጽልመት፥ የምድር መንቀጥቀጥ እና የመቅደስ መጋረጃ መቀደድ የሚገኙበት ክስተት ነበር (ማቴ. 27፡45፥ 50-53)። ስለሆነም፥ በአካባቢው የነበረው የመቶ አለቃ፥ «ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ» ብሎ መጮኹ የሚያስደንቅ አይሆንም (ማቴ. 27፡54)።

ኢየሱስ «መሢሕነቱን» በጥምቀቱ ተቀብሎ በመስቀል ላይ አላጣውም። በሁለቱም አጋጣሚዎች አብ የልጁን አምላክነት መስክሮአል።

*ሦስተኛው ምስክር-መንፈሱ።* መንፈስ ቅዱስ የተሰጠው ለክርስቶስ እንዲመሰክር ነበር (ዮሐ. 15፡26፤ 16፡14)። መንፈስ ቅዱስ እውነት ስለሆነ፥ ምስክርነቱን ልናምን እንችላለን። እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትም ሆነ ሞት ላይ አልነበርንም፤ መንፈስ ቅዱስ ግን እዚያ ነበረ። ክርስቶስ በምድር ላይ ሲያገለግል በነበረ ጊዜ አብሮ የነበረውና ዛሬም እዚህ በትጋት የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ስለሆነም

የአብ ምስክርነት ያለፈ ታሪክ ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ግን የአሁን ልምምድ ነው። የመጀመሪያው ውጫዊ ሲሆን፥ ሁለተኛው ውስጣዊ ነው–ሁለቱም ደግሞ በአንድ ይስማማሉ።

መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ልብ ውስጥ የሚመላለሰው እንዴት ነው? «አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል» (ሮሜ 8፡15–16)። የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት የክርስቶስ መሆናችንን ለውስጣችን በመናገር መተማመኛ የሚያስጨብጠን መንገድ እንጂ፥ እኛው ለራሳችን «የምንፈጥረው» ጉዳይ አይደለም፤ ይህ ግን እግዚአብሔር የሚሰጠን መተማመኛ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በተጨማሪም በቃሉ አማካኝነት ይመሰክርልናል። የእግዚአብሔርን ቃል በምናነብበት ጊዜ ለእኛ በመናገር ያስተምረናል። ይህ የሚሠራው ለአማኝ ብቻ እንጂ ላልዳኑት ጭምር አይደለም (1ኛ ቆሮ. 2፡4)።

በክርስቲያኑ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ስላለ ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር ተስማምቶ ይኖራል። ይህም መንፈስ ቅዱስ የሚመሰክርበት ሌላው መንገድ ነው።

አንድ ጉዳይ እንዲጸና ከተፈለገ ከሕግ አኳያ ሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች ያስፈልጋሉ (ዘዳ. 19፡15)። አብ በጥምቀቱና በመስቀሉ ላይ መስክሮለታል፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ አሁን በአማኙ ውስጥ ሆኖ ይመሰክራል፤ መንፈስ ቅዱስ፥ ውኃውና ደሙ የኢየሱስን አምላክነት በምስክርነት ያጸናሉ።

የሰዎችን ምስክርነት እየተቀበልን የእግዚአብሔርን ምስክርነት ችላ የምንለው ለምን ይሆን?

ብዙውን ጊዜ ሰዎች «እምነት ሊኖረኝ ቢችል እወድ ነበር!» ይላሉ። ይሁንና፥ ሁሉም ሰው የሚኖረው በእምነት ነው! ቀኑን ሁሉ አንድ ሰው ሌላውን ሲያምን ይውላል። ሰዎች ሐኪሙን፥ መድኃኒት ቀማሚውንና ሻጩን (ፋርማሲስት)፥ በሆቴል ምግብ አብሳዩን፥ እንዲሁም በመንገድ ላይ በሌላ መስመር እያሽከረከረ የሚሄደውን ሰው ሳይቀር ያምናሉ። ሰዎችን ለማመን ከቻልን እግዚአብሔርን ለማመን የማንችለው ለምንድን ነው? እርሱን አለማመን ደግሞ ቃሎቹን ውሸተኛ ማድረግ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው። ይህም የመጀመሪያው የክርስቲያን እርግጠኛነት ሲሆን፥ ለማንኛውም ሌላ ነገር መሠረት ነው።

## 2. አማኞች የዘላለም ሕይወት አላቸው (1ኛ ዮሐ. 5፡11-13)

በ5፡6-10 ውስጥ ቁልፍ ቃል *«ምስክር»* ነው። እግዚአብሔር ለልጁ ምስክርነት ሰጥቷል፤ በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር ለልጆቹ ማለትም ለግለሰብ አማኞችም ምስክርነት ሰጥቷል። የዘላለም ሕይወት እንዳለን *እናውቃለን!* ይህንንም የምናውቀው በውስጣችን ካለው ከመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ብቻ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ቃል ምስክርነት ጭምር ነው። «የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ» (ቁጥር 13)።

የዘላለም ሕይወት ስጦታ እንጂ የእኛ የሥራ ውጤት አይደለም (ኤፌ. 2፡8-9፤ ዮሐ. 10፡27-29)። ይህ ስጦታ ደግሞ አካል ነው- እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የዘላለምን ሕይወት የምናገኘው *ከክርስቶስ* ብቻ ሳይሆን *በክርስቶስ* ነው። «ልጁ ያለው ሕይወት አለው» (ቁጥር 12)። ይህም ተራ ሳይሆን እውነተኛ ሕይወት ነው (1ኛ ጢሞ. 6፡19)።

ይህንንም ስጦታ የምንቀበለው በእምነት ነው። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጣቸው በቃሉ ገልጾአል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር መዝገብ እውነት መሆኑን ያረጋግጣሉ። ይህንን አለማመን እግዚአብሔርን ውሸተኛ ማድረግ ነው። እግዚአብሔርንም እንደ ውሸተኛ ከቆጠርነው እርግጠኛ የሚሆን ነገር አናገኝም።

እግዚአብሔር ልጆቹ የእርሱ መሆናቸውን እንዲያውቁ ይፈልጋል። ዮሐንስ በወንጌሉ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ሊያረጋግጥልን በእስትንፋሱ- እግዚአብሔር ተነሣሥቶ ነበር (ዮሐ. 20፡31)። ይህንንም መልእክት የጻፈው የእግዚአብሔር ልጅ መሆናችንን እንድናረጋግጥ ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡13)።

ስለሆነም፥ እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ልጆች ባሕርያት መከለሱ ጠቃሚ ነው።

- «ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደ ተወለደ እወቁ» (2፡29)።
- «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም» (3፡9)።
- «እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን» (3፡14)።

• ወዳጆች ሆይ፥ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ፥ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ፥ እርስ በርሳችን እንዋደድ» (4፡7)

• «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና» (5፡4)።

እነዚህ «የልደት ምልክቶች» በሕይወትህ ውስጥ ካሉ በድፍረት የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ ልታውቅ ትችላለህ።

ሰውን የማደንዘዝ ዓቅም ያለውን የክሎሮፎርም ንጥረ ነገር ተመራምረው ያገኙት ሰር ጄምስ ሲምፕሰን ለሞት በሚያጣጥሩበት ወቅት አንድ ጓደኛቸው፥ «ሰር፥ [ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት] የእርስዎ ግምት ምንድን ነው?» በማለት ጠይቀዋቸው ነበር።

ሲምፕሰንም፥ «ግምት! እኔ የምገምተው ነገር የለኝም፤ «ያመንሁትን አውቃለሁና፥ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ» (2ኛ ጢሞ. 1፡12)» ብለዋል።

## 3. እግዚአብሔር ጸሎትን ይመልሳል (1ኛ ዮሐ. 5፡14–15)

የኢየሱስን አምላክነትና እኛም የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ማወቁ አንድ ነገር ነው፤ ለመሆኑ የዕለታዊ ሕይወት ጉድለቶችና ችግሮችስ ጉዳይ ምን ይሆናል? ኢየሱስ እዚህ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ ሰዎችን ይረዳ ነበር፤ አሁንስ ይረዳቸዋል? ምድራዊ አባቶች ለልጆቻቸው እንክብካቤ ያደርጋሉ፤ ሰማያዊ አባትስ ልጆቹ ሲጠሩት ምላሽ ይሰጣል?

ክርስቲያኖች ስለ ፍርድ ድፍረት እንዳላቸው ሁሉ በጸሎትም ድፍረት አላቸው (2፡28፤ 4፡17)። አስቀድመን እንዳየነው ድፍረት የሚለው ቃል የንግግርን ነጻነት የሚገልጽ ነው። ስለሆነም፥ በነጻነት ወደ አባታችን ልንመጣና ጉድለቶቻችንን ልንነግረው እንችላለን።

በርግጥ ልንፈጽማቸው የሚገቡ ቅድመ-ሁኔታዎችም አሉ።

በመጀመሪያ፥ የማይኮንነን ልብ ሊኖረን ይገባል (3፡21–22)። ንስሐ ያልገባንበት ኃጢአት ለጸሎት ምላሽ ከፍተኛ መሰናክል ይፈጥራል [መዝ. (66)፡18]። በክርስቲያን ባልና በሚስቱ መካከል የሚኖሩ አለመግባባቶች ጸሎታቸውን ሊከለክሉ እንደሚችሉ መገንዘብ ተገቢ ነው (1ኛ ጴጥ. 3፡1–7)። በእኛና በሌላ ክርስቲያን መካከል አንድ የተበላሸ ነገር ካለ ልናስተካክለው ይገባል (ማቴ. 5፡23–25)። እንዲሁም፥ አንድ አማኝ በታዛዥነትና በፍቅር በክርስቶስ ካልኖረ ጸሎቱ አይመለስለትም (1ኛ ዮሐ. 15፡7)።

ሁለተኛ፥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ አኳያ መጸለይ አለብን። «ፈቃድህ ይሁን (ማቴ. 6፡10)። ሮበርት ላው፥ «ጸሎት የሰውን ፈቃድ በሰማይ ለመፈጸም ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ለመፈጸም ታላቅ መሣሪያ ነው» ሲሉ ጽፈዋል። ለጸሎት በሚሰጠው ምላሽ በሺህ የሚቆጠሩትን ወላጅ አልባ ልጆች ለመመገብ የቻሉት ጆርጅ ሙለር፥ «ጸሎት የእግዚአብሔርን እምቢታ ማሸነፍ አይደለም። ይልቁንም፥ የእግዚአብሔርን ፈቃደኝነት መጠቀም ነው» ብለዋል።

በጉዳዩ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ባለማወቃችን ምክንያት፥ «የእኔ ሳይሆን ያንተ ፈቃድ ይፈጸም» ብለን ልንጸልይ የምንችልባቸው ጊዜያት አሉ። ብዙውን ጊዜ ግን ቃሉን በማንበብ፥ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ በመስማት (ሮሜ 8፡26–27) እና በዙሪያችን የሚገኙትን ሁኔታዎች በመገምገም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልናውቅ እንችላለን። አንድ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመጠየቅ የሚኖረን እምነት ራሱ ሊሰጠን እንደሚፈልግ የሚያረጋግጥልን ነው (ዕብ. 11፡1)።

በጸሎት ልንቀበላቸው የምንችላቸው አያሌ የተስፋ ቃሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። እግዚአብሔር ስግብግብነታችንን ሳይሆን፥ ጉድለታችንን ለማሟላት ቃል ገብቶአል (ፊልጵ. 4፡19)! ፈቃዱን እያደረግን አንዳች ነገር ብናጣ በራሱ መንገድና በራሱ ጊዜ ይሰጠናል።

«ግን አንድን ነገር ማግኘት ለእኔ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ለምን መጸለይ አስፈለገኝ?» እንል ይሆናል። ይህ የሆነው እግዚአብሔር ልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙ የሚፈልግበት መንገድ ስለሆነ ነው። እናም እግዚአብሔር ፍጻሜውን ብቻ ሳይሆን ወደ ፍጻሜ የሚያደርሰውን መንገድ ማለትም ጸሎት ጭምር እንዳዘጋጀ እንመለከታለን። ስለዚህም ጉዳይ የበለጠ ባሰብህ ቁጥር አስደናቂነቱን የበለጠ ትረዳለህ። እንደ እውነቱ ከሆነ ጸሎት የመንፈሳዊ ሕይወት የሙቀት መለኪያ (ቴርሞ ሜትር) ነው። እግዚአብሔር ጉድለቴን እንዲሞላ የምጠብቅ ከሆንሁ ከእርሱ ጋር የቀረበ አካሄድ እንዲኖረኝ ወስኖአል።

ዮሐንስ «እንደተቀበልን እናውቃለን» (1ኛ ዮሐ. 5፡15) አለ እንጂ፥ «ወደፊት እንደምንቀበል እናውቃለን» አላለም። በግሪኩ የዚህ አንቀጽ የጊዜ አመልካች የአሁን ጊዜ ጠቋሚ ነው። ለጸሎታችን ቅጽበታዊ ምላሽ ላንመለከት ብንችልም፥ ዳሩ ግን እግዚአብሔር እንደመለሰልን የሚያረጋግጥ ውስጣዊ መተማመኛ አለን። ይህ መተማመኛ ወይም እምነት የማይታዩ ነገሮች መረጃ ነው (ዕብ. 11፡1)። ይህም እግዚአብሔር እንደ ሰማና እንደ መለሰ የሚመሰክርልን ነው።

አየርን መተንፈስ ለሥጋዊ ሰው እንደሆነ ሁሉ ጸሎትም ለመንፈሳዊ ሰው እንዲሁ ነው። ባንጸልይ እንታክታለን (ሉቃስ 18፡1)። ጸሎት የከንፈር መነባንብ ብቻ ሳይሆን፥ የልብ መሻትም ነው። «ሳታቋርጡ ጸልዩ» (1ኛ ተሰ. 5፡17) ሲባል ክርስቲያን ሁልጊዜም ጸሎት ያነበንባል ማለት አይደለም። ጌታ የሚሰማን ለብዙ ቃላችን አይደለም (ማቴ. 6–7) ስለሆነም፥ «ሳታቋርጡ ጸልዩ» የሚለው የልብን ዝንባሌና የአፍን ቃላት የሚያመለክት ነው። ልቡ በክርስቶስ ላይ ያረፈለትና ሊያስከብረውም የሚጥር ሰው ሳያውቅም እንኳ ባለማቋረጥ እየጸለየ ነው።

ታዋቂው ሰባኪ ቻርልስ ስፐርጀን በነገው ዕለት በሚሰብኩት ምንባብ ላይ ተግተው ሲሠሩ ቢያመሹም ሊጨርሱ አልቻሉም ነበርና ባለቤታቸው ቀጣዩን ምክር ለገሱአቸው። «አሁን ወደ መኝታ ክፍልህ ገብተህ ተኛ። ጠዋት በማለዳ እቀሰቅስህና ስብከትህን አዘጋጅተህ ትጨርሳለህ።»

ስፐርጀን የባለቤታቸውን ምክር ሰምተው አሸለቡና ሲያስጨንቃቸው የዋለውን ስብከት ማዝነብ ያዙ! ባለቤታቸውም የስፐርጀንን የእንቅልፍ ልብ ስብከት ጽፈው በበነጋው ሰጧቸው።

«ይገርማል! ይህንኑ ነበር ለማለት የፈለግሁት!» አሉ የተደነቁት ሰባኪ። መልእክቱ በልባቸው ውስጥ ነበር፤ የተፈለገው ያንን ነገር መግለጽ ብቻ ነው። ጸሎትም እንዲሁ ነው፤ በክርስቶስ የምንኖር ከሆነ ድምፃችንን ብናሰማም ባናሰማም የልባችን መሻቶች በእግዚአብሔር ይደመጣሉ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾችና የዓለም ታሪክ ገጾች ጸሎት ምላሽ ባገኙት ዘገባ የተሞሉ ናቸው። ጸሎት መንፈሳዊ ራስን የማደንዘዝ ጥበብ አይደለም። እንዲሁም ጸሎት ጥሩ ስሜት እንዲሰማንም አይደለም። የምንጸልየው እግዚአብሔር ስላዘዘንና ጸሎት አማኙ እግዚአብሔር ሊሰጠው የሚፈልገውን ነገር ለመቀበል እንዲችል ከእግዚአብሔር የተወሰነ መንገድ በመሆኑ ነው። ጸሎት ክርስቲያኑን በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የሚያኖረው ሲሆን፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መኖሩ ደግሞ ክርስቲያኑን በበረከትና በአገልግሎት ስፍራ ያስቀምጠዋል። በመሆኑም፥ እኛ ለልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን ለመስጠት ወደሚወድ ባለጸጋ አባት የምንቀርብ ልጆች ነን እንጂ ለማኞች አይደለንም።

ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ ቢሆንም፥ በጸሎት ላይ ተደገፎ ነበር። እኛ ልናደርግ እንደሚገባን ኢየሱስ በአብ ላይ ተደግፎ በምድር ላይ ኖረ። ምንም እንኳ ብዙዎችን ለመፈወስ ሲል አምሽቶ ቢተኛም፥

ለመጸለይ ሲል ማልዶ ይነሣ ነበር (ማር. 1:35)። አንዳንዴም ሌሊቱን ሁሉ በጸሎት ያሳልፍ ነበር (ሉቃስ 6:12)። በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ «ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር» ጸሎትን አቀረበ (ዕብ. 5:7)። በመስቀሉ ላይ ሳለ ሦስት ጊዜ ጸልዮአል። ኃጢአት ለሌለው የእግዚአብሔር ልጅ ጸሎት ካስፈለገው፥ ለእኛስ ምን ያህል አብልጦ ያስፈልገን ይሆን?

ስለ ጸሎት እጅግ አስፈላጊው ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በአንድ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ ጊዜ ልንወስድ ይገባል፤ በተለይም ከጊዜው ሁኔታችን ጋር የሚዛመዱትን የተስፋ ቃሎችና መመሪያዎች በመመርመር ይህንኑ ልናደርግ ይገባል። አንዴ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካወቅን ዘንዳ በመተማመን ልንጸልይና መልሱን እንዲገልጽልን ልንጠባበቅ እንችላለን።

## 4. ክርስቲያኖች ኃጢአትን በማድረግ አይቀጥሉም (1ኛ ዮሐ. 5:16–19)

«ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንዳያደርግ... እናውቃለን» (ቁጥር 18)። «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም» (3:9)። በዚህ ስፍራ የተመለከተው በአጋጣሚ የሚፈጸም ኃጢአት ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ሥራዬ ተብሎ የሚፈጸምን የልምድ ኃጢአት ነው። አማኝ አዲስ ባሕርይ («የእግዚአብሔር ዘር» 3:9) ስላለው፥ አዳዲስ መሻቶችና ፍላጎቶች አሉት፤ ይህም በመሆኑ፥ በኃጢአት ደስ አይለውም።

ሦስቱ የክርስቲያን ጠላቶች ማለትም ዓለም፥ ሥጋና ዲያብሎስ ሁልጊዜም ወደ ኃጢአት ሊመሩት ይሻሉ።

ዓለም «በክፉ» (5:19) ማለትም የዚህ ዓለም አምላክ (2ኛ ቆሮ. 4:3–4) እና የዚህ ዓለም አለቃ (ዮሐ. 14:30) በሆነው በሰይጣን ተይዛለች። ይህም በማይታዘዙ ልጆች ውስጥ የሚሠራው መንፈስ ነው (ኤፌ. 2:2)፥

ሰይጣን አማኙን ወደ ኃጢአት የሚመሩ አያሌ መሣሪያዎች አሉት። ለሔዋን እንዳደረገው ውሸትን ይናገራል (2ኛ ቆሮ. 11:1–3፤ ዘፍ. 3)፤ ሰዎችም የእርሱን ውሸት ሲያምኑ የእግዚአብሔርን እውነት ከመታዘዝ ይመለሳሉ። እንዲሁም፥ በኢዮብና በጳውሎስ ላይ እንዳደረገው አካላዊ ሥቃይ ሊያመጣ ይችላል (2ኛ ቆሮ. 12:7–9)። ሰይጣን ዳዊትን ለማሳሳት የተጠቀመው መሣሪያ ትዕቢትን ነበር፤ በዚህም ዳዊት ሕዝቡን እንዲቆጥር አነሣስቶ እግዚአብሔርን እንዲበድል አድርጓል (1ኛ ዜና 21)። ሰይጣን እንደሚያታልል እባብ (ራእይ 12:9) እና

እንደሚውጥ አንበሳ ነው (1ኛ ጴጥ. 5፡8—9)። እናም ሰይጣን አስፈሪ ጠላት ነው።

ከዚያም አብሮን የተወለደንና አብሮን የሚኖር አሮጌው ባሕርይ የሥጋ ችግር አለ። በውስጣችን አዲስ ባሕርይ (መለኮታዊ ዘር— (1ኛ ዮሐ. 3፡9) እንዳለ እውነት ቢሆንም፥ ሁልጊዜም ለአዲሱ ባሕርያችን አንገዛም።

ሦስተኛዋ ጠላታችን ዓለም ነች (2፡15፥ 17)። ለሥጋ ምኞት፥ ለዓይን አምሮትና ለሕይወት ትምክህት መገዛቱ ቀላል ነው። በአካባቢያችን ያለው ድባብ ለእግዚአብሔር ንጹሕ አእምሮና እውነተኛ ልብ እንዳይኖረን ይዋጋናል።

እንግዲያስ፥ አማኝ ኃጢአትን ከማድረግ የሚቆጠበው እንዴት ነው?

ምዕራፍ 5 ቁጥር 18 መልሱን ይሰጠናል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ አማኙን ስለሚጠብቀው ጠላት እጁን ሊያሳርፍበት አይችልም። «የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ይጠብቀዋል፤ ሰይጣንም አይነካውም» (ከ1980 እትም)። የእንግሊዝኛው «አተራይዝድ ቨርዥን» እና የ1954 ዓ.ም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትሞች አማኝ ራሱን ከኃጢአት እንደሚጠብቅ ቢያመለክቱም፥ የጥቅሱ ሐሳብ ግን እንዲህ አይደለም። በርግጥ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ራሱን መጠበቅ አለበት (ይሁዳ 21)፤ ዳሩ ግን ክርስቲያን ሰይጣንን ለማሸነፍ በራሱ ላይ መደገፍ የለበትም።

ጴጥሮስ ከሰይጣን ጋር ያሳለፈው ገጠመኝ ይህንኑ እውነት ለመረዳት ይጠቅመናል።

ኢየሱስ፥ «ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና» ብሏል (ሉቃስ 22፡31—32)።

ቀድሞ ነገር ሰይጣን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ማንኛውንም አማኝ አይነካም። ሰይጣን ደቀ መዛሙርቱን ሁሉ ለማበጠር ሲፈልግ ኢየሱስ ፈቃድ ሰጠው። ይሁንና፥ ኢየሱስ በተለይ ለጴጥሮስ ጸለየ፤ ጸሎቱም ምላሽ አገኘ። ምንም እንኳ ብርታት ቢያጣም የጴጥሮስ እምነት ሙሉ ለሙሉ አልጠፋም ነበር። እናም በኋላ ወደ እምነቱ ተመልሶ ታላቅና ውጤታማ ነፍሳት ማራኪ ሆኗል።

ሰይጣን በሚያጠቃን ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ፈቃድ እንደሰጠው እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ከዓቅማችን በላይ እንድንፈተን ስለማይፈቅድ (1ኛ ቆሮ. 10፡13) ለሰይጣን ፈቃድ ከሰጠ ለእኛ ደግሞ የምናሸንፍበትን ኃይል ይሰጠናል።

ከ«መንፈሳዊ ብርቱዎች» መለያ ፀባይ አንዱ ክፉውን የማሸነፍ ችሎታቸው ነው (1ኛ ዮሐ. 2:13-14)። ምሥጢራቸው ምን ይሆን? «የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ይኖራል» (2:14)። ከእግዚአብሔር ዕቃ ጦር ውስጥ አንዱ የመንፈስ ሰይፍ ነው (ኤፌ. 6:17)፤ ይህም ሰይፍ ሰይጣንን ያሸንፋል።

አንድ አማኝ ኃጢአት በሚሠራበት ጊዜ ኃጢአቱን ተናዝዞ ይቅርታ ሊያገኝ ይችላል (1ኛ ዮሐ. 1:9)። ይሁንና፥ ኃጢአት ዓመፅ ስለሆነ፥ አማኝ ከኃጢአት ጋር ለመጫወት ሊደፍር አይገባም። ስለሆነም፥ በኃጢአት ሕይወት የሚገፋ ሰው የሰይጣን መሆኑን ያረጋግጣል (3:7-10)። በተጨማሪም፥ ኃጢአት ወደ ሥጋዊ ሞት ሊመራ እንደሚችል እግዚአብሔር ያስጠነቅቃል!

«ርኩሰት ሁሉ ኃጢአት ነው!» ይህም ሆኖ፥ አንዳንድ ኃጢአት ከሌላው የከፋ ነው። ኃጢአት ሁሉ ለእግዚአብሔር አስጸያፊ ስለሆነ፥ ለአማኙም አስጸያፊ ሊሆን ይገባል፤ አንዳንድ ኃጢአት ግን የሞትን ቅጣት የሚያስከትል ነው። ዮሐንስ በኃጢአት ምክንያት ሕይወቱን ስላጣው ወንድም (ወይም አማኝ) ገልጾአል (5:16-17)።

መጽሐፍ ቅዱስ በኃጢአታቸው ምክንያት ስለሞቱት ሰዎች ጠቅሶአል። የካህኑ አሮን ልጆች የነበሩት ናዳብና አብዩድ ሆን ብለው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለጣሱ ሞተዋል (ዘሌ. 10: 1-7)። ቆሬና ቤተሰቡ እግዚአብሔርን በመቃወማቸው ሞተዋል (ዘኁ. 16)። አካን በኢያሪኮ በኢያሱ አማካኝነት የተላለፈለትን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስላልሰማ በድንጋይ ተወግሮ ሞቷል (ኢያሱ 6-7)። ዖዛ የተባለ ሰው የቃል ኪዳኑን ታቦት በመንካቱ ከእግዚአብሔር በወረደ መቅሰፍት ሞቷል (2ኛ ሳሙ. 6)።

ምናልባትም፥ «እነዚያ የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎች ናቸው! ዮሐንስ የሚጽፈው ከጸጋ በታች ለሚኖሩ የአዲስ ኪዳን አማኞች ነው» ብሎ የሚከራከር ሰው ሊኖር ይችላል።

ብዙ ከተሰጠው ብዙ ይጠየቃል። የዛሬው አማኝ ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳን የበለጠ እግዚአብሔርን የመታዘዝ ኃላፊነት አለበት። እኛ የተሟላ መጽሐፍ ቅዱስ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ሙሉ መገለጥና እግዚአብሔርን እንታዘዝ ዘንድ ለመርዳት ከውስጣችን የሚኖር መንፈስ ቅዱስ አለን። ከዚህም በላይ፥ በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው ምክንያት ሰዎች ሕይወታቸውን ያጡባቸው አጋጣሚዎች አሉ።

ሐናንያና ሰጲራ ስለ ስጦታቸው ለእግዚአብሔር በመዋሸታቸው ሞተዋል (የሐዋ. 5:1–11)። በጌታ እራት ላይ ባሳዩአቸው ጉድለቶች አንዳንድ አማኞች በቆሮንቶስ ሞተዋል (1ኛ ቆሮ. 11:30)። እንዲሁም 1ኛ ቆሮንቶስ 5:1–5 አንድ በደለኛ ሰው ኃጢአቱን ባይናዘዝ ኖሮ ይሞት እንደነበረ ገልጾአል (2ኛ ቆሮ. 2:6–8)።

አንድ አማኝ በኃጢአቱ ላይ የማይፈርድና ኃጢአቱን የማይናዘዝ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ሊቀጣው ይገደዳል። ይህ ሂደት *ራሱን ለአብ የማያስገዛ ሰው በሕይወት እንደማይኖር* በሚገልጸው የዕብራውያን 12:1–13 ክፍል ውስጥ ተገልጾአል (ቁጥር 9)። በሌላ አባባል፥ *መጀመሪያ* እግዚአብሔር ዓመፀኞች ልጆቹን ይቀጣቸዋል፤ በዚህ የማይበገሩና ለፈቃዱ የማይገዙ ከሆነም አለመታዘዛቸው ሌሎችን ወደ ጥፋት እንዳይመራና ለስሙም ሌላ ውርደት እንዳያስከትል ከዓለም ያስወግዳቸዋል።

«ለሞት የሚያበቃ *ኃጢአት*» አንድ *የተወሰነ* ኃጢአት አይደለም። ይልቁንም፥ ይህ ወደ ሞት የሚመራ የኃጢአት *ዓይነት* ነው። የናዳብንና አብዩድን ሁኔታ በተመለከተ ይህ ወደ ሞት የመራቸው ኃጢአት የካህኑን ሥልጣን በመያዝና ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባት የፈጸሙት ትዕቢት ነበር። አካንን በተመለከተ ምኞት ነበር። ሐናንያና ሰጲራ የግብዝነትና መንፈስ ቅዱስን የመዋሸት ኃጢአት ፈጽመዋል።

ክርስቲያን አንድ ወንድሙን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ሊጸልይለት ይገባል (1ኛ ዮሐ. 5:16)። ይኸውም ኃጢአቱን ተናዝዞ ከአብ ጋር ወዳለ ኅብረት እንዲመለስ ነው። ሲጸልይ ሳለ ግን የሚጸልየው በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እንደሆነ ካልተሰማው (በቁጥር 14–15 እንደ ታዘዘው)፥ ለዚያ ወንድም መጸለይ የለበትም። «እንግዲህም አልሰማህምና ስለዚህ ሕዝብ አትጸልይ ስለ እነርሱም ልመናና ጸሎት አታድርግ፤ አትማልድላቸው» (ኤር. 7:16)።

ያዕቆብ 5:14–20 በመጠኑ ከ1ኛ ዮሐንስ 5:16–17 ጋር ይመሳሰላል። ያዕቆብ ምናልባትም በኃጢአቱ ምክንያት ስለ ታመመ አማኝ ይገልጻል። ይህ አማኝ ሽማግሌዎች ይጸልዩለት ዘንድ እንዲጠራ ተጠይቆአል። የእምነት ጸሎት የሚፈውሰው ሲሆን፥ ኃጢአት ሠርቶ ከሆነም ይሰረይለታል። «የእምነት ጸሎት» በ1ኛ ዮሐንስ 5:14–15 እንደተጠቀሰው፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የሚደረግ ጸሎት ነው። ይህም «በመንፈስ መጸለይ» ነው (ይሁዳ 20)።

ክርስቲያኖች ሆን ብለው ኃጢአት አይሠሩም። ከውስጣቸው መለኮታዊ ባሕርይ አላቸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጠብቃቸው ሲሆን፥ የእግዚአብሔርን ቅጣት አይፈልጉም።

## 5. የክርስትና ሕይወት እውነተኛው ሕይወት ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡20–21)

ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ ነው። እኛም እውነት የሆነውን እርሱን እናውቀዋለን፤ እውነት በሆነው *በእርሱ* እንኖራለን። «እውነተኛ ነገር» አለን!

«እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፤ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው» (ቁጥር 20)። *«እውነታ»* የዮሐንስ መልእክት ሁሉ ዋና ጭብጥ ሲሆን፥ አሁንም በድጋሚ ቀርቦልናል።

ምናልባትም ዮሐንስ የሚጽፈው ጣዖትን በማምለክ በታወቀችው በኤፌሶን ለሚኖሩ አማኞች ሳይሆን አይቀርም። ከጥንቱ ዓለም ሰባት አስደናቂ ነገሮች አንዱ የነበረው የዳያና መቅደስ በኤፌሶን የሚገኝ ሲሆን፥ ጣዖታትን መሥራትና መሸጥ ከሕዝብ ዋንኛ ሥራዎች አንዱ ነበር (የሐዋ. 19፡21–41)። ስለሆነም፥ በዚያ የነበሩ አማኞች በጣዖት አምልኮ ተከብበው ስለነበር ሕዝቡን የመመሳሰል ከፍተኛ ውጥረት ነበረባቸው።

ዳሩ ግን «ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደሆነ ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን» (1ኛ ቆሮ. 8፡4)። ስለሆነም ጣዖት እውነተኛ ህላዌ የለውም። ስለ ጣዖት አሳዛኙ ነገር የሞተ ምስል እውነተኛ ባለመሆኑ ለሚያመልከው ሰው የሚፈይደው ነገር አለመኖሩ ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ዕብራውያን ጸሐፊዎች ጣዖትን «ባዶዎች፥ ከንቱ ነገሮች፥ ትነቶች፥ ምናምንቴዎች» ሲሉ ጠርተዋቸዋል። ጣዖት ለእውነተኛ ነገር ወኪልነት የሚሠራ እርባና ቢስ መተኪያ ነው።

መዝሙረ ዳዊት የጣዖትን አስቀያሚ ገጽታዎች ይዘግባል [መዝ. (115)፥ 1–8፤ (135)፥15–18]። ጣዖት ዓይን፥ ጆሮ፥ አፍ፥ አፍንጫ፥ እጅ፥ እግር፥ ስላሉት ለሰዎች እይታ እውነተኛ ይመስላል፤ ይሁንና፥ እነዚህ ሁሉ የእውነተኛ ነገር እርባና ቢስ ቅጂዎች ናቸው። ዓይኖቹ ስውር፥ ጆሮዎቹ ደንቆሮ፥ አፉ ዲዳ፥ እጆቹና እግሮቹ ሽባ ናቸው። የሚያሳዝነው ደግሞ «የሚሠሩአቸውም የሚታመኑባቸውም ሁሉ» እንደእነዚህ ጣዖታት» መሆናቸው ነው [መዝ. (115)፥8]። ማንም ቢሆን የሚያመልከውን እየመሰለ መምጣቱ አይቀርም!

የእውነተኛ ሕይወት ምሥጢሩ ይኼ ነው። እውነተኛውን አምላክ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላገኘን፥ ከእውነታ ጋር ግንኙነት አለን። ኅብረታችን እውነተኛ ከሆነ አምላክ ጋር ነው። አስቀድመን

እንደተመለከትነው፥ «እውነተኛ» የሚለው ቃል «ከቅጂ በተቃራኒ ዋንኛ ምንጭ፥ ከማስመሰል በተቃራኒ ትክክለኛ» የሚል ፍች አለው። ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ብርሃን (ዮሐ. 1:9)፥ እውነተኛ እንጀራ (6:32)፥ እውነተኛ የወይን ግንድ (15:1) እና ራሱም እውነት ነው (14:6)። እርሱ ብቻ ዋንኛ ምንጭ (ኦሪጅናል) ሲሆን፥ ሌላው ሁሉ ቅጂ ነው። እርሱ ብቻ ትክክለኛ ሲሆን፥ ሌላው ሁሉ በማስመሰል ጥበብ የተሠራ ነው።

ክርስቲያኖች የሚኖሩት በእውነታ ድባብ ውስጥ ሲሆን ብዙዎቹ ያልዳኑ ሰዎች በግብዝነትና በማስመሰል ይኖራሉ። ክርስቲያኖች እውነቱን ከውሸት ነጥለው የሚያውቁበት መንፈሳዊ የመለየት ጥበብ የተሰጣቸው ሲሆን፥ ያልዳኑት ግን ይህ ግንዛቤ የላቸውም። ክርስቲያኖች የሚመርጡት ከመልካምና ከክፉ ብቻ ሳይሆን ከሐሰትና ከእውነትም ነው። ጣዖት ባዶ የሆነውን ይወክላል፤ ለጣዖታት የሚኖርም ሰው ራሱ ውሸትና ባዶ ይሆናል።

ዛሬ ጥቂት ሰዎች ከእንጨትና ብረት ለተሠሩ ጣዖታት ይሰግዳሉ። ይህም ሆኖ፥ ሌሎች ጣዖታት ቀልባቸውንና ፍቅራቸውን ይወስዳሉ። ለምሳሌ፥ *መመኘት* አምልኮተ–ጣዖት ነው (ቆላ. 3:5)። አንድ ሰው አረማውያን የሚባሉት አስቀያሚ ጣዖታቸውን በሚያመልኩበት የተነቃቃ ስሜት የባንክ ቤት ደብተሩን ወይም የገንዘብና የመረጃ ቦርሳውን ሊያመልክ ይችላል። «ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፥ እርሱንም ብቻ አምልክ» (ማቴ. 4:10)። *የምናገለግለው የምናመልከውን ነው!* ስለሆነም፥ ሕይወታችንን የሚቆጣጠረውና ቀልባችንን የሚያሳጣው ነገር አምላካችን ነው።

ይህም እግዚአብሔር ለምን ከአምልኮተ ጣዖት እንድንታቀብ እንደሚያስጠነቅቀን ያስረዳል። አምልኮተ–ጣዖት ትእዛዙን በመጣስ ብቻ ሳይሆን (ዘጸ. 20:1–6)፥ ሰይጣን እኛን የሚቆጣጠርበት ስውር መንገድ ነው። በሕይወታችን ውስጥ «ነገሮች» የእግዚአብሔርን ስፍራ ሲወስዱ፥ የአምልኮተ–ጣዖት ሰለባዎች ሆነናል ማለት ነው። ይህም ሲሆን *ከእውነተኛው ይልቅ ለቅጂው* እየኖርን ነው ለማለት ይቻላል።

ለዓለማዊ ሰው የክርስትና ሕይወት ቅጂ ሲሆን፥ ዓለማዊ ሕይወት እውነተኛ ነው። ይህም የሆነው የዓለም ሰው የሚኖረው በሚያየውና በሚዳስሰው (ነገሮች) እንጂ፥ እግዚአብሔር በቃሉ በሚናገረው ባለመሆኑ ነው። ጣዖት ጊዜያዊ *ነገር* ሲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ዘላለማዊ አምላክ ነው። *«የሚታየው የጊዜው ነውና የማይታየው ግን የዘላለም ነው»* (2ኛ ቆሮ. 4:18)።

ክርስቲያን እንደ ሙሴ የማይታየውን በማየት ይታገሣል (ዕብ. 11:27)። እምነት የማይታዩትን ነገሮች የሚያሳየን ነው (ዕብ. 11:1)።

ኖኅ የጎርፍ አደጋ አይቶ ባያውቅም፥ በእምነት ይህ አደጋ እንደሚመጣ «አይቶ» እግዚአብሔር ያዘዘውን ነገር አደረገ። አብርሃም በእምነት ስማያዊቱን ከተማና አገር አይቶ፥ እግዚአብሔርን ለመከተልና የራሱን ምድራዊ ቤት ለመተው ፈቀደ። በዕብራውያን 11 የተጠቀሱት የእምነት ጀግኖች ሁሉ የፈጸሙትን ተግባር ያከናወኑት የማይታየውን በእምነት ስላዩት ነበር። በሌላ አባባል፥ ከእውነታ ጋር ተራክበ ነበራቸው።

ዓለም ስለ አብርሆቱ በመናገር ቢመካም፥ ክርስቲያን ግን *በብርሃን* ይመላለሳል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ብርሃን ነውና። ዓለም ስለ ፍቅር ያወራል፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ፍቅር በመሆኑ ክርስቲያን ያገኘውን እውነተኛ ፍቅር ብዙም አያውቀውም። ዓለም ጥበብንና ትምህርቱን ቢያውጅም፥ ክርስቲያን ግን «መንፈስ ቅዱስ እውነት ስለሆነ» በእውነት ይኖራል። እግዚአብሔር ብርሃን፥ ፍቅርና እውነት ነው— እነዚህም በአንድነት *እውነተኛ* የሆነውን ሕይወት ይመሠርታሉ።

ይሁንና፥ «አንድ ሰው ታማኝ እስከሆነ ድረስ የሚያምነው ነገር ለውጥ አያመጣም» የሚል ሰው ሊኖር ይችላል።

ይህ የተለመደ ማመኻኛ እምብዛም ማፍረሻ የሚያሻው አይደለም። አንድ የመድኃኒት ቀማሚና ሻጭ፥ የቀዶ ሕክምና ባለሙያ፥ ወይም የመድኃኒት ጠቢብ የሚያምነው ነገር ለውጥ ያመጣ ይሆን? ይህ በጣም ታላቅ ለውጥ ያስከትላል!

ለምስኪኑ ጂም ብራውን አልቅሱ፤

ከዛሬ ወዲያ የለም እርሱ።

ውኃ * ነው ብሎ የወሰደው፤

ከቶ አሲድ ** ኖሮ ገደለው።

ክርስቲያን ከጣዖታት ሕያውንና እውነተኛውን አምላክ ወደ ማገልገሉ ተመልሶአል (1ኛ ተሰ. 1፡9)። ጣዖታት ሙት ሲሆኑ፥ ክርስቶስ ግን ሕያው አምላክ ነው። ጣዖታት ውሸት ሲሆኑ፥ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ ነው። የእውነተኛ ሕይወት ምሥጢር ይህ ነው!

ስለሆነም «ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ» የሚለው የዮሐንስ ምክር፥ «ቅጂና አርቲፊሻል ከሆነው ተጠብቃችሁ **እውነተኛ ሁኑ!**» ተብሎ ሊብራራ ይችላል።

* ውኃ = ($H_2O$)

** ዲኚ (ሰልፈሪክ አሲድ) = ($H_2SO_4$)

## እስካሁን ድረስ ወደ አማርኛ ተተርጉመውና ታትመው በስርጭት ላይ ያሉ በዋረን ዌርዝቢ የተጻፉ የ«ሁን» ተከታታይ መጻሕፍት።

1. ለጌታ የተገዛህ ሁን (የማቴዎስ ወንጌል)
2. ርኅሩኅ ሁን (ሉቃስ 1–13)
3. የበረታህ ሁን (ሉቃስ 14–24)
4. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመላለስ (የሐዋርያት ሥራ1–12)
5. ደፍረህ መስክር (የሐዋርያት ሥራ 13–28)
6. ተጽናና (2ኛ ቆሮንቶስ)
7. አርነት መውጣት (ገላትያ)
8. ደስተኛ ሁን (ፊልጵስዩስ)
9. ፍጹም ሁን (ቆላስይስ)
10. ለምጽአቱ ተዘጋጅ (1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ)
11. ታማኝ ሁን (1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፥ ቲቶ፥ ፊልሞና)
12. በብስለት ማደግ (የያዕቆብ መልእክት)
13. ንቃ! (2ኛ ጴጥሮስ፥ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ፥ ይሁዳ)
14. እውነተኛ ሁን (1ኛ ዮሐንስ)
15. ድል አድራጊ ሁን (ራእይ)

# እንዴት እግዚአብሔር የሚፈልግህን ዓይነት ሰው እንደምትሆን

- አኗኗርህ ከምትናገረው የበለጠ ኃይለ-ቃል ስላለው
- ግብዝነትና ከዓለም ጋር ድብብቆሽ መጫወቱ አንተንና በአካባቢህ ያሉትን ስለሚጎዳ
- ሰዎች «የሚወድቁባቸው» አያሌ ስሜቶች ፍቅር ስላልሆኑ
- እውነተኛ እምነት በተፈተነ እውነት ላይ መደገፍ ስላለበት

በመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት ላይ የተመሠረተና እንዴት እግዚአብሔር እንደሚፈልግህ ዓይነት ሰው ሆነህ እንደምትኖር የሚያሳይህ መጽሐፍ ቀርቦልሃል።

# እውነተኛ ሁን

ዶክተር ዋረን ደብልዩ. ዌርዝቢ ከሁሉም በላይ የሚታወቁት በደራሲነታቸው፥ በመጋቢነታቸውና በሬድዮ መምህርነታቸው ነው። ለብዙ ዓመታት የሺካጎው የሙዲ መታሰቢያ ቤት ክርስቲያን መጋቢ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፥ በቅርቡ ደግሞ «ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስ» ለተባለው ፕሮግራም ዋና መምህር ሆነው ሠርተዋል። እነዚህን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማብራሪያዎች ጨምሮ፥ ከ100 በላይ መጻሕፍት ጽፈው ለኅትመት አብቅተዋል።

Bible Based Books
SIM Publishing

**BE REAL**

**Printed by SIM Press**